

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

[illegible]

Finfinne Printing & Publishing S.C.

Price Birr 50 birr USD $15 Euro €14

# የዘረኝነት አውራቂስ

2ኛ ዕትም
ተሻሽሎ የቀረበ




ባይሣ ገመቹ

# የዘረኝነት አውራቂስ

ባይሣ ገመቹ

አዲስ አበባ

ሚያዚያ 2011 ዓ.ም

# የዘረኝነት አውራቂስ


የቅጂ መብት - ባይሣ ገመቹ © 2011 ዓ.ም

Copyright © 2019 by Bayissa Gamachu

መብቱ በህግ የተጠበቀ ነው፡፡

ይህንን መጽሐፍ ለንግድ ወይም ትርፍ ለሚያስገኝ ሥራ በሙሉም ሆነ በከፊል አባዝቶ መጠቀም አይፈቀድም፡፡ ሆኖም በደራሲው ፈቃድ ለአገልግሎት መጠቀም ይቻላል፡፡


የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት በ1954 ዓ.ም. በኢትዮጵያ መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ከታተመውየአማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ ወይም በ1993 ዓ.ም በኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ከታተመው አዲሱ መደበኛ ትርጉም ነው፡፡


አንደኛ እትም - 2007 ዓ.ም
First Edition - 2015
ሁለተኛ እትም - 2008 ዓ.ም
Second Edition - 2016
ሦስተኛ እትም - 2011 ዓ.ም
Third Edition - 2019



አስተያየት ቢኖርዎት፡ Tele: +251 924 11 03 23
E-mail: bayissagam@gmail.com

# ማውጫ


አስተያየቶች......................................................................... i
አበርክቶት........................................................................ iii
ምስጋና............................................................................ iv
መቅድም.............................................................................v
መግቢያ............................................................................vii

ምዕራፍ 1፡ ዘረኝነት ምንድነው?.............................................1

1.1. ባይሣ ደፋሩ! ..........................................................1
➢ የሴራው ጥንስስ...............................................3
➢ በረከቱ መርገም ሆኖብንይሆን?.................................4
1.2. የዘረኝነት ትርጉም...................................................6
➢ ብሔርተኛ የሆነ ብሔር አለ?......................................11
1.3. የዘረኝነት ምክንያቶች..............................................12
➢ የዘረኝነት አይነቶች..................................................15
1.4. የዘረኝነት መገለጫዎች..............................................15
1.4.1. በማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች...................16
1.4.2. በፖለቲካው ምህዳር......................................19
1.4.3. በኃይማኖት ተቋማት.......................................21

ምዕራፍ 2፡ በጥላቻ እና ዘረኝነት እየታመሡች ያለች ዓለም...........24

2.1. ተግባርን ሸጣ መርህን ብቻ ታቅፋ የምትኖረው ዓለማችን.24
2.2. የአመጽ እና የጦርነት አውድማ......................................26
ሀ. የአቤል ደም...................................................27
ለ. የኖህ ዘመን...................................................27
ሐ. የአብረሃም ጥሪ ዋነኛ ዓላማ.................................28
መ. የድህረ አብርሃም ውጥንቅጦች...............................30
2.3. የዓለማችን ትልቁ ኪሳራ..............................................31
2.3.1. የጸረ-ሴማዊያን ትግል (Anti-semetism)................31
2.3.2. የሻርፒቫይል የዘር ማጥፋት ዘመቻ........................32
2.3.3. የሁቱ እና ቱትሲ ጦርነት...................................33
2.3.4. ስረብረኒካ.....................................................34
2.3.5. የአሜሪካ የውስጥ ትኩሳት..................................35

2.3.6. የጀርመን አይሁዳዊያን ሰቆቃ……………………..36
➢ ሰውን ገድለን ማንን እናተርፍ ይሆን……………………38
2.4. የጥቁር ህዝብ ቀንበር…………………………………………40
2.4.1. የባሪያ ንግድ……………………………………………41
2.4.2. የቅኝ አገዛዝ ጠባሳ……………………………......42
2.4.3. ፌደራሊዝም በአፍሪካ……………………………43
2.4.4. አፍሪካ በመጽሐፍ ቅዱስ መነጽር………….……….44

ምዕራፍ 3፡ በኢትዮጵያ ላይ የወደቀው ጽልመት……………………46

3.1. ለመሆኑ ኢትዮጵያ የማን ናት?…………………..……47
➢ ያለፉት አባቶች/መሪዎች/ተጽኖ……………………….47
➢ ምሳሌ የሆኑን መሪዎች ነበሩን?……………….…......48
3.2. የኢትዮጵያ ብሔሮች ንክሻ!..........................................50
3.3. የትግል አቅጣጫችን…………………………………..52
➢አመጽንና ሰላማዊ ተቃውሞን እንለይ……………….........53
3.4. ልማት! ልማት! ልማት!.........................................…………57
➢ በእጃችን ላይ ያለው ወርቃማው ዕድል………………..…59

ምዕራፍ 4፡ የዘረኝነት አስከፊ አደጋዎች……………………………61

4.1. በግለሰቦች ህይወት ላይ……………………………….61
4.2. በቤተክርስቲያን ላይ የሚያመጣው እክል…………………64
4.3. በአገራችን ሁለንተናዊ እድገት ላይ……………………72

ምዕራፍ 5፡ የቤተ-ክርስቲያን አደራና ኃላፊነት…………………..…73

5.1 የአንድነታችን ሚስጥር……………………..……………75
➢ ኢየሱስ - ከወገኖቹ በላይ የሆነ ተልዕኮ……………79
➢ ጳውሎስ - ለጥሪው የኖረ ጀግና!...............................79
5.2. የቤተክርስቲያን ቅንብር መጠበቅ……………………….80
5.3. እያሉ ያለ መኖር……………………………………..82
➢ ያሉ ሰዎች አሉ?……………………………………82
➢ የዘረ-መል (DNA) ምርመራ ይደረግ…………………….83
5.4. አንገብጋቢ ጥሪ ወደ እውነተኛ ህብረት……………...……84
➢ የቤተክርስቲያን ሰቆቃ………………………………85
➢ ይቆረጥ!.........................................................................87

➢ ቤተ-ክርስቲያን የባህልና የቋንቋ ማስፋፊያ ስፍራ አይደለችም.......................................................89
5.5. ሌሎች ብሔሮችን የመውደድ ግዴታ አለብን..............91
5.6. አሁንም ተስፋ አለ.......................................92
➢ እውነተኛ ለውጥ ከቤት ውስጥ...........................93
➢ አምባሳደሩ ዜግነታቸውን ቀየሩ................................95
➢ አንድነት የቤተ-ክርስቲያን ኃይል ነው!.......................96
➢ የፍትህ መልዕክት ከቤተ-ክርስቲያን መነሳት አለበት......96

ምዕራፍ 6፡ የመፍትሔ አቅጣጫዎች......................................99

6.1. ድል ነሺ ማንነት.............................................99
➢ ወዳጆቼ ሆይ እንነሳ!.............................................101
6.2. የግል ውሳኔ...................................................102
➢ የ “ማ” መርሆች..................................................102
6.3. የቤተ-ክርስቲያን ኃላፊነት....................................105
➢ አንድነትን በተመለከተ ወጥ አስተምህሮ ማዘጋጀት......105
➢ የተሻለ አማራጭ ይዞ መቅረብ ይኖርብናል...............107
➢ የግል ፍላጎታችንን ሰውተን ለኅብረት እንኑር.............108
➢ የኤሳው የይቅታ ልብና የዮሴፍ የምህረት ጉዞ............110
6.4. እንደ ማኅበረሰብ ማድረግ የሚገባን.........................113
➢ በቁጭት እንነሳ.................................................113
➢ በንስሃና በእርቅ እንጀምር...................................114
➢ ቫይረሱን ለመግታት በጀት ይመደብ.......................115
➢ ታሪክን በአግባቡ መያዝ.......................................116
➢ ቋንቋን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መጠቀም...................117
➢ ኩሬውን ማድረቅ ይሻላል....................................117
➢ የንግድ መርህን እንከተል.....................................118
➢ ሙዙን እንብላዉ.................................................118
➢ መልካም ባህሎቻችንን ብንጋራስ..........................119
➢ የአባ ዶዮ ወርቃማ ምክር ....................................121
6.5. የፍቅር አብዮት ይቀጣጠል!...................................123
ከልብ የሆነ መልዕክት ለውድ ወዳጄ!..................................126
ዋቢ መጽሐፍት..........................................................128

# አስተያየቶች

የለህም ብለን ብንክደው ከየመንደራችን ያልጠፋ፣ አንድነታችንን እየፈጀ ያለ ድምጽ አልባ መሳሪያ የሆነው ዘረኝነት እያደረሰ ላለው ጉዳት መግለጫ እንዲሆን “አውራቂስ” የሚል ተገቢ ቅጽል ሥም ተሰጥቶት በወንድማችን ባይሣ በልበ ሙሉነት በዚህ መጽሐፍ መነሳቱ ይበል የሚያሰኝ ነው፡፡ “አውራቂስ” ስያሜ የተወሰደው እነ ጳውሎስ ወደ ሮም በሚሄዱበት ጊዜ ከገጠማቸው ማዕበል ሲሆን ንፋሱ የወንጌል ተልዕኮ የተሰጠውን ሐዋሪያ፣ እስረኞች፣ ነጋዴዎች እና የተለያዩ ኃላፊነቶች ያላቸውን ተሳፋሪዎች እንዳናወጣቸው ሁሉ ሰላማዊ ኑሮውን የሚመራን ዜጋ፣ በቅንነት ከሁሉ ሰው ጋር በሰላም ለመኖር የሚታትሩትን፣ ለልማት ቀና ደፋ የሚሉትን ሠራተኞች እንዲሁም ክርስቶስ ልዩ ተልዕኮ ሰጥቷት በምድር ላይ ያለችውን የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ሳይቀር እየናጠ መሆኑ አሳሳቢ ወቅት ላይ መሆናችንን የሚጠቁም ነው፡፡ ስለሆነም አንባቢያን ፈርጀ ብዙ ፋይዳ ያለውን ይህንን መጽሐፍ በማንበብ አመለካከታቸውን እንዲፈትሹበትና ተግባራዊ እርምጃ እንዲወስዱ በትህትና ለማሳሰብ እወዳለሁ፡፡

አለሙ ዘገዬ<br>
በዘወርድ ፎር ዘዎርልድ ኢትዮጵያ<br>
የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ፕሮጀክት አስተባባሪ

የተያያዝንበት፤ የተጋመድንበት የሕብረታችን ምሰሶ ክርስቶስ ሆኖ ሳለ አሁን ባለንበት ዘመን የአንድነታችን ማዕከል እስኪሆን ድረስ ዘረኝነት እያጠቃን ይገኛል፡፡ አንዳንዶች ዘረኝነት የለም ብለው ለመሸፋፈን ቢሞክሩም ባይሣ ግን ዘረኝነት መኖሩን ከነምክንያቱ እና መገለጫው ጭምር ያሳየናል፡፡ ለብዙዎች አይነኬ የሆነውን ይህንን ርዕሰ ጉዳይ ወንድማችን ስለደፈረው ተባረክ እያልኩ ወደፊት በዳበረ መልኩ በሌላ ሁነኛ ርዕስ እንደሚመጣ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

ምንያህል ጋተው<br>
የልጆች ልማት ፕሮጀክት ዳይሬክተር

ዘረኝነት ከማንነት ጋር አብሮ የሚኖር የአዳማዊ አስተሳሰብ መገለጫ እና የኃጢያት ውጤት የሆነ ክፉ መርዝ ነው፡፡ ማጥፋት የሚቻለው አዲስ ማንነት በሆነዉ የአእምሮ መታደስ ብቻ ነው፡፡ ከዚህ ድንቅ መጽሐፍ ይህንን ሃሳብ መረዳት ችያለሁ፡፡ ባይሣ ጌታ አብዝቶ ይባርክህ!

ኢዮብ አድነው
የትግራይ ክልል ቃለ ሕይወት ቤተ-ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ

የዘር ጉዳይ ጆሮና ትንፋሽን የሚያቆም ርዕስ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ ስለ ዘር ማሰብ ኃጢያት ባይሆንም፣ ዘረኝነት ግን ከጽድቅ ጎራ ሊያሰልፈው የሚያበቃ ፍሬ የለውም፡፡ ዘረኝነት “ወገኔ” ከሚሰኝ ክፍል ፈቀቅ ብሎ የቆመውን ሁሉ ከባላናጣና ከወደረኛ ጎራ ፈርጆ የመጥላት፣ የማግለል፣ የመዝለፍ፣ የማዋረድ፣ የማጥላላትና ሌሎችን እኩይ ድርጊቶችንም የማሸከም “አስተሳሰብንም” አንግቦ ነው የሚጓዘው፡፡
እንደ ዘረኝነት ሰብአዊ ክብርን ትብያ ያላበሰና ዓለምን ያመሰ “አስተሳሰብ” ይኖራል ብሎ መገመት ሲበዛ ይከብዳል፡፡ ሰው የመሆን ክብር መስመሩን ያለፈ ጊዜ የማንነት መለክያ ይናዳል፣ እናም በዚህ የተወናከረ መስፈርት ማህበራዊ እርከኖች፣ ኢኮኖሚያዊ ግንኙነቶች፣ ፖለቲካዊ መስተጋብሮችና ኃይማኖታዊ ፈለጎች የታሹ እንደሆነ፣ የሰው ልጅ ሰው ከመሆን ወድቆ ንረት አሊያም ድባቴ ባጠቃው ዘረኝነት ውስጥ ይሰጥማል፡፡ እንግዲህ የዘረኝነት ፈረስ ይህን መነሻ አድርጎ ትውልድን እንዳይበላ፣ ግብሯን ከክርስቶስ ትምህርት ጋር ያስታረቀች ቤተክርስቲያን ኢፍትሐዊነትን፣ በደልን ጭቆናን፣ አድልዎን በማነወር የክህነት አገልግሎቷን አብዝታ ትከውን ዘንድ ያስፈልጋታል፡፡ የክህነት አገልግሎቷም እግዚአብሔር ጻድቅ መሆኑን ትውልድ ሊመለከተው በሚችል የብርሃን ማማ ላይ ማኖርም ግድ ይላታል፡፡ አማኞቿም ከዚህ የተለየ ተግባር አይጠበቅባቸውም፣ ባይሣም ከዚህ የወጣ መልዕክት የለውም፡፡

ፍቅረየሱስ ሁንዴሣ
የብርሃን መጽሔት ዋና አዘጋጅ

# አበርክቶት

ይህች መጽሐፍ ከክርስቶስ ዳግም መወለድ የዘላለም ሕይወት የሚገኝበት ብቸኛው መንገድ መሆኑን ተረድተው፣ ከዘረኝነት በላይ የሆነ ተልዕኮ አንግበው፣ በጥላቻ እና በመከፋፈል እየታመሰች ባለች ዓለም ውስጥ የፍቅርን አብዮት ለማቀጣጠል ለተዘጋጁ የዚህ ዘመን አገልጋዮች ትሁንልኝ፡፡

# ምስጋና

ለጌታ የሚመጥን ምስጋና የለኝም አይኖረኝምም፡፡ ሁሉ ከእርሱ በእርሱ ለእርሱ ነውና፡፡ ስሙ ይክበርልኝ! ይህች መጽሐፍ እውን እንድትሆን በሕይወቴ ላይ በጎ ተጽዕኖ ያኖሩ ወዳጆቼ ሁሉም ልዩ ምስጋና አላቸው፡፡ ያለ እነርሱ አሁን ያለኝን ማንነት አይኖረኝም ነበርና፡፡ በተለይ ብዙ ችግሮች እያሉብኝ ከእነዚያ ይልቅ በጥቂት መልካም ነገሬ ላይ በማትኮር የዛሬ ሰው እንድሆን የለፉብኝን ወንድሞቼን ዮሴፍ ፊንታው፣ ምንያህል ጋተው እና መኮንን ምህረቱን ተባረኩ እላለሁ፡፡ የአገልግሎትን ክቡርነት እና ለጥሪ የመኖርን ዋጋ ያስተማረኝን፣ ከጊዜያዊ ጥቅም ይልቅ በወደፊቱ ብድራቴ ላይ እንዳተኩር የረዳኝን በሥጋ ታላቅ ወንድሜ በመንፈስ ደግሞ አባቴ የሆነውን ፓስተር ኤጀርሣ ገመቹን ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡

በገንዘብና በብዙ አቅጣጫ የረዳችኝን እህቴን ፋኖስ ገመቹ እና ባለቤቷ መሳይ አበራን፣ ለምለም ይፍሩ፣ ቢሹ ተድላ፣ ጋሼ ተካልኝ ጋቸና በለጠ ዋቅቤካ፣ኢንጂነር በቀለ ደበለ፣ ንጉሤ አሰፋን ተባረኩ እላለሁ፡፡ ፀጋአብ ተመስገን፣ ሚክያስ አዳነና ኢዮብ ሙሉጌታ በዚህ ሥራና በአገልግሎተ ሁሉ ቀኝ እጄ ናቸውና ምስጋናዬን ይኸው፡፡

የሀሳብ ፍሰቱን የጠበቀ እንዲሆን የለፉ፣ የጎደለውን በመሙላት፣ የተጣመመውን በማቅናት ከብዙ ስህተት የታደጉኝ እና አባታዊ ምክራቸዉን ውድ ጊዜያቸውን ሰውተው በትህትና የመከሩኝን ጋሼ ንጉሤ ቡልቻን ከልብ በሆነ አክብሮት ላመሰግናቸው እወዳለሁ፡፡ ለዚህ ለሁለተኛው እትም ግብዓት የሚሆኑ ገንቢ አስተያየቶችን የለገሰኝን ጳውሎስ ፍቃዱ እና ጋሽ ፍቅረየሱስ ሁንዴሣን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ ከሥነ-መለኮት አንጻር ተገቢ እርማት የሰጡኝን መምህር ዘለለው አርጋዉን፣ የቃላት ግድፈትን ለማስወገድ የአርትኦት ስራውን በብቃት የተወጡትን ወዳጆቼን መልሕቅ ሠናይን እና ሽመልስ ወ/ማሪያምን ከልብ አመሰግናለሁ፡፡ የውጭ ሽፋን ዲዛይን የሰራችውን ሉሊት አበራን ተባረኪ እላለሁ፡፡

በመጨረሻ ለአለምገና ሙሉ ወንጌል አማኞች ቤተክስቲያን አማኞች፣ ወጣቶች (ኃያላን) በተለይ ለBCMT አባላት (የአሸናፊዎች አምባ) ከልባቸው ፈልቆ ሕይወቴን በየዕለቱ እያራሰ ላለው ፍቅራቸው፣ሁሌ መልካሙንና ደጉን ለሚመኙልኝ፣በደካማ ጎኔ ቆመው ውበትና ሙላት ለሆኑኝ ልዩ ምስጋናና አክብሮት አለኝ፡፡

# መቅድም

ለምድራችን አስፈላጊ ከሆኑ ድምጾች ምናልባትም በደንብ ሊሰሙ ከሚገባቸው ሁሉ ነገሮች ቅድሚያውን ሊያገኝ የሚገባው ድምጽ በዚህች ትንሽ በምትመስል መጽሐፍ ተዘጋጅቶልናል፡፡ ደራሲው ከታሪክ፤ ከህይወት ተሞክሮና ባብላጫው ደግሞ ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነታዎች ነጥቦችን እያነሳ ከአውሎ ንፋሱ እንድንጠነቀቅ፣ የሚነፍሰው የፖለቲካ ነፋስ እንዳይቀብረን ያነቃናል፡፡ ከጎጥ ይልቅ ሀገርን ከጎሳ ይልቅ ህዝብን ከክልል ይልቅ ሀገርን ከደም ይልቅ ማንነትን ከምንም በላይ ደግሞ በክርስቶስ እንዳመነ ሰው የሰውን ልጅ ክቡርነት የሰውን እኩልነት በማያሻማ መልኩ አስቀምጦልናል፡፡ የዘረኝነት አውራቂስ መጨረሻው ጥፋት እና ውድመት እርስ በርስ መበላላት መሆኑን አመላክታናለች፡፡ ለኔ ይህች መጽሐፍ እጅግ የምጠብቀውን ድምጽ ይዛልኛለች፡፡ አልዘገየም ወይ? መጠየቅ ያለበት ጥያቄ ይመስለኛል፡፡ ባይሣ ከእድሜውም ከትውልዱም አንጻር የዘገየ አይመስለኝም፡፡ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ግን እንደ ክርስቶስ ሕያው ቤተክርስቲያንነቷ እጅግ እጅግ ዘግይታለች ብየ አምናለሁ፡፡ መዕበሉ ማናወጥ ከጀመረን ቆይቷል፤ ሰነባብቷል፡፡ ከዚህ የተነሳ አንደንዶችን ሲገለብጥ አንዳንዱን ከስራ ሲያፈናቅል አንዳንዱን ከትዳሩ ሲበትነው ሌላውን ደግሞ ያለ ልኩ ማአረግ አሰጥቶ ያሽልመዋል፣ ዘሩ ነዋ! ይሄ ሁሉ ሲሆን ቤተክርስቲያን የቱ ጋር ናት? በአሳዛኝ ሁኔታ ክርስቶስ የሞተላት ቤተክርስቲያን በማእበሉ እየደፈቀች ትንፋሽ አጥሯት ብቅ ጥልቅ በማለት ላይ ነች:: በአንዳንድ ሁኔታዎች ለማየት እንደሚቻለው ደግሞ የጥፋት ሐዋርያነት ሚና ስትጫወት ትታያለች፡፡ የዛሬ 2000 ዓመት ህዝብ በተከፋፈለበት ባሪያና ጨዋ ግሪክና አይሁድ ወንድና ሴት የሰማይና የምድር ያህል በተራራቀበት ሁኔታ "ሁሉ በክርስቶስ አንድ ነው" ብላ የሰበከች ቤተክርስቲያንን ፈጽሞ አትመስልም:: ልትሆንም አትችልም:: ወይ ተቀይጣለች አልያም በማእበሉ ማንነቷን

አጥታለች፣ አማራጩ ንስሃ ነው! አማራጩ መመለስ ነው! ስለዚህ ይህች መጽሐፍ ለዚህ የተጻፈች ትመስለኛለች፡፡ ከዚህ ባለፈ ግን ለበጎ ነገር ለሃገር ግንባታ ለአብሮ መኖር ሁላችን እንድናስብ እንድንደክም ከዛም ባለፈ መጥፎውን ዘር አመጣጡ ምንም ቢሆን እንድንነቅለው አልያም እንዳይበርዘን ራሳችንን እንድንጠብቅ ታሳስበናለች፡፡ ሁላችንም እንደ አንድ ሀገር ለመኖር ከጠባብነት ልንወጣ ይገባናል፡፡ አንደ ክርስቲያንነታችን ደግሞ ዘረኝነት ውስጥ መዘፈቃችን፣ በእግዚአብሔር ቃል ማመጽ ነው፡፡ የዘረኝነት አውራቂስ መዓበሉን በማጋለጥና በመግለጥ ፈር ቀዳጅ ናት! ባይሣ እግዚአብሔር ይባርክህ!!! ወዳጄ ባይሣ በጊዜው ደርሰህልናል እላለሁ መልካም ንባብ!!! ጌታ ማስተዋልን ለሁላችን ይስጠን!!!

መጋቢ ዮሴፍ ፈንታዉ<br>የእንደዋላይቱ መጽሐፍ ደራሲ

# መግቢያ

አውቀናል ያሉት ያልተረዱት፣ ደርሰንበታል ያሉት ያልተገበሩት፣ የሰበኩልን ሊኖሩበት የተሳናቸው፣ ትኩረት የተነፈገው መስዋዕትነት፣ ቸል የተባለ ጀብድ፣ ለአንድነት የተከፈለ ውድ ዋጋ፣ ለዘመናት በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን የጥልን ግድግዳ ከመሠረቱ የናደ የዓለማችን የምንጊዜም የፍቅር ህያው ታሪክ፣ ከጎልጎታ ሥር የፈለቀ የምህረት ምንጭ፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ የእርቅ ሥራ!

ይህ እውነት በአንደበተ ርቱዎች ቢሰበክም፣ በልሂቃን ተውቦ ቢጻፍም ለመኖር የደፈሩት ግን ኢምንት ሆነው ተገኙ፡፡ አንድነት እና ፍቅር ተመችቷቸው ከሚኖሩበት ከቅዱሳን ህብረት ብርቅዬ የዱር እንስሳት በሰደድ እሳት ከመኖሪያቸዉ እንደሚሰደዱ በተቀጣጠለው ዘረኝነትና መከፋፈል እየሸሹ ይገኛሉ፡፡ ይህ ልብ ሰባሪ ድርጊት የኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን በኃይል እንዳትሮጥ ሽባ ሊያደርጋት የተቃረበ ችግር ሆኗል፡፡ የቤተ-ክርስቲያን ሞቷ የተጠራችበትን ተልዕኮ ጥላ ከዓለም ጋር የተባበረች ቀን ነው፡፡ በሂሳብ ስሌት ስንገልጸው የተጠሩበትን ያለ መኖር እኩል ይሆናል ያለ መጠራት፡፡

እየተደጋገፉ አብረው እንዲኖሩ ከአንድ አባት የተወለዱ ልጆች ሲከፋፈሉ ከዚያም አልፎ ሲተራረዱ እንደ ማየት የወላጅን ልብ የሚያደማ የሐዘን ጦር የለም፡፡ ዛሬም ከጌታ የተወለዱ፣ በፍቅር እና በሕብረት እንዲኖሩ የተጠሩ በዘረኝነት እና በመከፋፈል የክርስቶስን ልብ እያቆሰሉት ይገኛሉ፡፡ ጌታ ልጆቹ ሲፋቀሩ ማየት አምሮት በጦር ሲነፈላለግ መገኘታችን ትልቅ ሃዘኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ማንም መክፈል የማይችለውን የኃጢያት እዳ ከፍሎ የራሱ ያደረገንን ጌታ ማቃለላችን ይሆናል፡፡

ብዙዎች ወደ ቤተ-ክርስቲያን አዳራሽ ደርሰው ከምድራዊው የቅዱሳን ሕብረት ተካፍለው በሰማይ ከተዘጋጀው ከበጉ እራት ሳይkሱ ይቀራሉ፡፡ የትሁቱን ጌታ ፈቃድ መከተል እንደ ኂላ ቀርነት ስለሚያስቡ ረብ የሌለውን ዘረኝነትን ትርፍ ማግበስበሻ መሣሪያ አድርገው ይጠቀማሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች በየዘመናቱ የቅዱሳንን ጉባኤ በማተራመስ ይታወቃሉ፡፡ እነዚህም በኢትዮጵያ እና በኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ነቀርሳ

እየሆኑ፣ ጥላቻን እና መከፋፈልን በየስፍራው እየተከሉ ያሉ ዲያብሎስ በአማኞች መካከል ያሰማራቸው የጥልቁ ሐዋሪያት ናቸው፡፡

በዚህች መጽሐፍ የምድራችን አንገብጋቢ ችግር እና የቤተ-ክርስቲያን ዕድገት ማነቆ እየሆነ የመጣውን ዘረኝነትን በስፋት እና በጥልቀት ለመዳሰስ እንሞክራለን፡፡ የክርስቶስ አካል የሆነችውን ሙሽራይቱን በየዘመናቱ እንደ ወርቅ በሚፈትኗት መከራዎች ውስጥ እያለፈች ስደቶች እየተፈራረቁባት ከውዷ ጋር ወደምትገናኝበት የመጨረሻው ዘመን ላይ ደርሳለች፡፡ የቤተ-ክርስቲያን ታሪክ ምሁራን ቤተ-ክርስቲያን ከውጪና ከውስጥ በሚነሱባት መከራዎች እንደምትፈተን ይስማማሉ፡፡ ባላመኑት ሰዎች ዘንድ ተቀባይትን በማጣት መሰደድ፣ መሰደብ አልፎም መገደል የውጭ ተግዳሮቶች ሲሆኑ፤ ዘረኝነት፣ መከፋፈል፣ ቅድስና ማጣት፣ ጥላቻ እና የመሳሰሉት ደግሞ የአማኞች በደቀ-መዝሙርነት ሕይወት መካን መሆን እና አለማዊ ምኞቶችን ከክርስቶስ ጋር ቀብሮ መስቀሉን ተሸክሞ ባለ መሄድ የሚመጡ ችግሮች ናቸው፡፡ ዋናው ትኩረታችን ግን በዘረኝነት ዙሪያ የሚያጠነጥን እንደ መሆኑ መጠን ልዩ ትኩረት ሰጥተን እንዳስሰዋለን፡፡

በእምነት ያለ ማደጋችን እና በተጠራንበት አንድነት ጸንተን መቆም ያለ መቻላችን ዘረኝነትን እንደ ትልቅ ጉዳይ እንድናስብ አገዘፈብን እንጂ ክርስቶስ ወደ ዓለም የመምጣቱ ትርጉም ለገባው አማኝ እንደ ምናምንቴ ነገር የሚወሰድ ኢምንት ችግር ነበር፡፡ አለማደጋችን እና አለማዊያን መሆናችን ዘረኝነት በቅዱሳን ሕብረት መካከል የማያቀራርብ እሾህ እና ኩርንችት ሆኖ እንዲገለጥ እድል ሰጠው፡፡ እኛም በጊዜ ከመንቀልና ከማቃጠል ይልቅ ተንከባክበን ውሃ አጠጥተን አሳደግነው፡፡ ይህ ዛፍ ዛሬ በቤተ-ክርስቲያን ዉስጥ በብዙዎች ሕይወት ውስጥ ሞትን እያፈራ አንድነትን እያቀጨጨ ተንሰራፍቶ ቆሞአል፡፡ የዚህ መጽሐፍ ፍሬ ሃሳብ እና ጥሪ አንድ ነው፡፡ የግሌም ጩኸት ግልጽ ነው የሩዋንዳ እና ቡሩንዲ አብያተክርስቲያናት ለመጋት የተገደዱትን የሃዘን ጽዋ ከመጨለጣችን በፊት ደቡብ አፍሪካን የናጣት አውሎንፋስ ሳያገኘን በጀርመን የፈሰሰው ደም የእኛ ታሪክ ሆኖ ሳይደገም አረሙን እንንቀል ነው!

ዘረኝነት የብዙ ሰዎችን ነፍስ ከእግዚአብሔር ነጥሎ ወደ ዘላለም ጥፋት እየነዳ ያለ ከባድ ጎርፍ ነው፡፡ ይህ አውራቂስ አልፎ ቤተ-ክርስቲያን ውስጥ ዘልቆ መግባቱ ነገሩን አሳሳቢ እያደረገው ነው፡፡ የዓለምን ቋጠሮ ለመፍታት የተጠራን አማኞች በጓዳችን ውስጥ ያለውን እርም ማስወገድ ያለ መቻላችን በትልቅ ሀፍረትና አቅመ ቢስነት ውስጥ እንደሆንን የሚጠቁም ነው፡፡

የሰይጣን ትልቅ ሥራ ቤተ-ክርስቲያንን በብሔር፣ በዘርና በጎሳ በመከፋፈል በድን የሆነ ተልዕኮ ታቅፋ፣ በሐይማኖታዊ ስርዓት ታጅባ ያለ ተጽዕኖ እና ኃይል እንድትቅበዘበዝ ማድረግ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ቤተ-ክርስቲያን እየታየ ያለው ትዕይትንት ይሄው ነው፡፡ ምክንያቱም ከቤተ-ዕምነት አመራር ጀምሮ እስከ አጥቢያ የአገልግሎት ዘርፍ መሪነት ድረስ መሪዎችን ለመምረጥ መንፈሳዊ ብስለት እና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መስፈርቶች ሳይሆኑ ብሔር እንደ ዋነኛ መመዘኛ እየተወሰደ መሆኑ በብዙ አብያተክርስቲያናት በተጨባጭ እየታየ ነው፡፡

ከዚህ ከዘረኝነት ተጠቃሚው ማን ነው? ብለን ብንጠይቅ እንደየቀመራችን የተለያዩ መልሶችን እናገኝ ይሆናል፡፡ ከእግዚአብሔር ሕያው ቃል አንጻር ስናየው ግን መልሱ አንድ ነው እርሱም ሰይጣን፡፡ በዘፍጥረት ምዕራፍ 3 ሰውን እና እግዚአብሔርን፤ ምዕራፍ 4 ላይ ሰውን እና ሰውን በመለያየት ያገኘውን ውጤት ክርስቶስ ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ አሰራሩን እያዘመነ እየተጠቀመበት ይገኛል፡፡ የዲያብሎስ አገልጋይ የሆኑ ሰዎች አባታቸው የሚያሳያቸውን ስልት በንቃት እየተጠቀሙበት ነው፡፡ በተለይ የተለያዩ ብሔሮችን በማጋጨት በህዝብ መካከል ጦርነትን በመፍጠር የሚፈስን ደም ዕድሜአቸውን ወደ ፊት ለማራዘም እንደ ነዳጅ ለሚጠቀሙ መሪዎች አዋጭ አሰራር ነው፡፡

ዶ/ር ማይልስ ሞንሮ *"በዚህ ምድር ላይ አስቀያሚው ነገር ጥሩ ሰዎች መጥፎ ነገር ሲሰራ እያዩ ዝም ማለታቸው ነው"* ብለዋል፡፡ ጥሩ ሰዎች በእኔ መረዳት በክርስቶስ ዳግም የተወለዱ ናቸው፡፡ የእነርሱ ንግግር የጌታ ሃሳብ ነው ምክንያቱም ጌታን ወክለው እየኖሩ ነውና፡፡

የእኔም ዝምታ መልስ ስለማይሆን ልናገር፡፡ ፕሮፌሰር ኤሊ ዊዝል በሁለተኛዉ የዓለም ጦርነት ጀርመን በአይሁዶች ላይ የወሰደችውን የዘር ማጽዳት ዘመቻ ዓለም ለተወሰነ ጊዜ በዝምታ መቆየቷን በመታዘብ እንዲህ ብለዋል "ዓለም ያውቅ ነበር ሆኖም ዝምታን መርጦ ቆይቷል፡፡ ሰብአዊ ፍጥረታት መከራ እና ውርደት በሚቀበሉበት ቦታም ሆነ ጊዜ ሁሉ ዝም ላለማለት የማልኩት ለዚህ ነው፡፡ አቋም መውሰድ አለብን"[1] ፡፡ የቱጋ ቆሜ መናገር እንዳለብኝ ግን ከሁሉ የከበደኝ ጉዳይ ነው፡፡ ሁሉም የራሱን ጫፍ ይዞ በጦር በሚጠባበቅበት አገር ውስጥ ሚዛናዊ እንደ መሆን ከባድ ነገር የለም፡፡ በወንጌላውያን አማኞች መካከል ግማሾቹ ለዘብተኛ የቀሩት ደግሞ በመንፈስ መነቃቃት ጫፍ ላይ ሆነው በሚዘላለፉበት፣ በፓለቲካው ምህዳር ጽንፈኝነት በገነነበት፣ እንዲሁም የኢትዮጵያ ህዝቦች በራሳቸው ብሔር እና ጎሳ ውስጥ አለማቸውን ፈጥረው የቀሩትን የሌሎች ብሔር ተወላጆችን በአንድ ፕላኔት ውስጥ አብሮ እንደሚኖሩ የአዳም ልጆች ሳይሆን ከሌላ ዓለም የመጣ ሰው በላ አውሬ አድርገው በጠላትነት በሚተያዩበት ሁኔታ ውስጥ ማዕከላዊ ቦታ ላይ ቆሞ ሊበታትነን እየመጣ ያለውን የዘረኝነት አውራቂስ መመከት ፈታኝ ሥራ ነው፡፡

የምናገረውን በቅንነት ይረዱኛል ወይ የሚለው ደግሞ ትልቁ ጭንቀቴ ነው፡፡ ሰዎችን የመናቅ፣ የመጥላት እና በብሔር ምክንያት የመከፋፈልን መብት ከክርስቶስ ጋር ስለ ሰቀልኩት አንድነት እና እውነተኛ ህብረት የናፈቀው ሰው የፍቅር ጥሪ መሆኑን እንድትረዱልኝ እፈልጋለሁ፡፡ ሁሉም ሰው ሀሳቤን በሙሉ ይቀበለዋል የሚል እምነት ባይኖረኝም አንድ ነገር ሳስብ ድፍረት አገኛለሁ፡፡ ይህም የመጽሐፍ ቅዱስን መርህ፣ የነገስታት ንጉስ የሆነዉን የአባቴን ፈቃድ በገባኝ መጠን የማስተላልፍ መሆኔን ሳስብ የልብ የልብ ይሰማኛል፡፡ ዝምታ ትክክለኛ መልስ የሚሆነው ንግግራችን መልካም ውጤት የማያስከትል ሲሆን ብቻ ነው፡፡ የተጠራነው ለመናገር ሆኖ ሳለ መናገር በሚገባን ጉዳይ ላይ ዝም ካልን ያ መንፈሳዊነት ሳይሆን ዳተኝነት እና አድርባይነት ነው፡፡

[1] ኤሊ ዊዝል ሌሊት (ትርጉም በጳዉሎስ ፈቃዱ ) 2006፡ ገጽ 134

የራሳቸውን አስተሳሰብ ተሳፍረው በግላቸው ደሴት ላይ ለመኖር የፈረጠጡትን ሰዎች ማቀራረብ ሆድ እና ጅርባን ለማገናኘት የመሞከር ያህል ከባድ ቢመስልም ሰውን እና እግዚአብሔርን ሰውን እና በሞቱ ከራሱ ጋ ያስታረቀንን የክርስቶስን ሥራ መከተል ብቸኛው ተስፋችን ነው።

ይህች መጽሐፍ የግሌ የውስጤ የትግል ውጤት ነች። በተለይ 1990ዎቹ ሁለተኛ አጋማሽ የሁለተኛ ደረጃ እና የዩኒቨርስቲ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት በቤተ-ክርስቲያን እና በትምህርት ቤት ይታይ የነበረው በብሔር ምክንያት የመከፋፈል አባዜ የጽድቅ ሥራ እስኪመስል ድረስ የተለመደ ተግባር ነበር። በወቅቱ ለተፈጠረብኝ ጥያቄ መልስ ለማግኘት ብዙ ኳተንኩ ትልልቅ ናቸው ብዬ ያሰብኳቸውን ሰዎችም ከመጠየቅ እና ህይወታቸውን ከመከታተል ጀምሮ በጉዳዩ ዙሪያ የተጻፉትን መጽሐፍት መዳሰሱን ተያያዝኩት። ስለሆነም የደረስኩበት እና ጥቂቷን መረዳቴን በዚህ አይነት ማቅረብ ተገቢ ሆኖ ስለታየኝ እነሆኝ።

የመጽሐፉ ርዕስ ሃሳብ የተወሰደው በሐዋ 27፡14 ላይ ከተጠቀሰው "አውራቂስ" ከሚል ቃል ነው። ይህ አውሎንፋስ ደቡባዊ ምስራቅ በመባልም ይታወቃል። እነ ጳውሎስ መልካም ወደብ ከሚባልበት ቦታ ወደ ሮም ጉዞ ለማድረግ በተነሱበት ሰዓት ቁልቁል መጣባቸው። አውራቂሱ የመጀመሪያ ጉዳቱ አቅጣጫን ማስለቀቅ ነበር። ከዚያ በማነገላታት ስላስጨነቃቸዉ ጭነታቸውን መጣል ጀመሩ። በመጨረሻ ለሕይወታቸውም አስጊ በመሆን የመኖር ተስፋቸዉን አጨለመ። ዘረኝነት በእጅጉ ከዚህ ማእበል ጋር ይመሳሰላል። የዘረኝነት አውሎ ንፋስ ያገኘው ሰው ከሕይወት መንገድ ያፈናቅላል በተጨማሪ ያለ ጥርጥር ብዙ ውድ ነገሮችን ያስጥለዋል። ነፍሱ በክፋትና በጥላቻ ስለምትንገላታ በጌታ ላይ ተተክሎ መቆየት ይከብደዋል።

መጽሐፏ በስድስት ምዕራፎች ተከፋፍላለች። የመጀመሪያው ምዕራፍ የዘረኝነትን ምንነት የሚንገነዘቡበት ሲሆን መንስኤዎችን እና መገለጫዎቹንም እናያለን። በሁለተኛው ምዕራፍ ላይ ዘረኝነት የዓለም አቀፍ ችግር መሆኑን በወፍ በረር ካየን በኋላ በተለይ በእርስ በእርስ

ግጭት የምትታወቀዋን አህጉራችንን እንዳስሳለን፡፡ በሦስተኛው ምዕራፍ በአገራችን ላይ ያጠላውን የዘረኝነት ክፉ ድባብ እንቃኛለን፡፡ የዓለምን፣ የአፍሪካን እንዲሁም የአገራችንን ሁኔታ በምንዳስስበት ጊዜ የቤተ-ክርስቲያንን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ ታሪኮችን እና ክስተቶችን የፖለቲካ እና ማህበራዊ ሁኔታዎችን በመጠኑ እንቃኛለን፡፡ በምዕራፍ አራት ዘረኝነት በቤተ-ክርስቲያን እና በአገር ሁለተንተናዊ እድገት ላይ የሚስከትለውን ኪሳራ ከተመለከትን በኂላ በምዕራፍ አምስት ቤተክርስቲያን በዘረኝነት ምክንያት ተልዕኮዋን እንዳትጥል ምን ማድረግ እንደለባት በስፋት ቃኝተን በመጨረሻው ምዕራፍ የመፍትሔ ሃሳቦችን በማስቀመጥ እንደመድማለን፡፡

*መልካም ንባብ!*
*ባይሣ ገመቹ*

# ምዕራፍ  አንድ

## ዘረኝነት ምንድነው?

*"በራሱ ላይ የበታችነትን ስሜት የሚያመጣው ዘረኛ የሆነ ሰው ነው"*
ፍራንዝ ፋኖን

*"ጠማማ ሰው ጥልን ይዘራል ጆሮ ጠቢ ሰው የተማመኑትን ወዳጆች ይለያያል።"* ምሳ 16፡28

### 1.1. ባይሣ ደፋሩ!

ትንሿ እውቀቴንና ያነበበኳትን ነገር ከመናገሬ በፊት ቁጭ ብዬ ማመዛዘን፣ መፈተንና መመርመር እንዳለብኝ አውቃለሁ። የዘመኑ ክፋት ግን ይህንን እድል ነፈገኝ። የተሻሉ ሰዎች ዝምታ፣ ዘረኝነት እየተዛመተ ያለበት ፍጥነት ምላሽ ለመስጠት እንድገደድ አድርገውኛል።

የዚህችን መጽሐፍ የመጀመርያ እትም የጨበጡ ብዙ አንባቢያን "ደፋር ነህ!" የሚል አስተያየት ለገሱኝ። የማይነካውን ነካህ! ብዙ ሰዎች ዝምታን የመረጡበትን ርዕሰ ጉዳይ እንዴት ተላተምክበት?....የሚል አስተያየት ከበርካታ ወገኖች ዘንድ ጎረፈልኝ። ከዚያ ህዝቡ በፍርሃት ጉድጓድ ውስጥ ስለ ሰጠመ ወይስ እኔ እንደሚባለው ደፋር ሆኜ ነው? የሚል ጥያቄ በህሊናዬ ላይ ማንዣበብ ጀመረ። የአንድነትና የፍቅር ጥሪ ማቅረብ ደፋር ካሰኘ ከዚህ የባሰ ግሳጼ ቢቀርብስ ምን ሊባል ነው? መልስ ፍለጋ ዳከርኩኝ። በማህበረሰባችን ውስጥ ቤተክርስቲያንንም ጨምሮ የማስመሰል ዘር ተዘርቶ የግብዝነትን ፍሬ ተንዠርግጎ ያለበት አሳዛኝ ወቅት ላይ መሆናችንን ተረዳሁ። የከፋውን ተግዳሮት ለመጋፈጥ መዘጋጀት እንዳለብኝ ቀልቤ አረጋገጠልኝ።

የተወሰኑ ወዳጆቼ በቅንነት ሊያበረታቱኝ እንደ ተናገሩ እረዳለሁ። በውስጤ ያለችውን ትንሿን ጭላንጭል እፍ ብለው እንዲንቦገቦግ ለማድረግ የልቤን አመድ ሳይጸየፉ በምክርና ተግሳፅ የሚያጸዱ እንቁ የሆኑ ወንድሞችና

እህቶች በዙሪያዬ አሉ። ስለ እነርሱ ጌታን አመሰግናለሁ። በሌላ ጽንፍ ግን ጥላቻን ማትረፍያቸው አድርገው የሚያስቡ እኩይ ሰዎች ንግዳችንን ባትነካብን የሚል አይነት ቀይ መብራት ለማብራት የተጣጣሩም ነበሩ። እነዚህ ሰዎች በፍርሃት ኮሮጆ ውስጥ ቋጥረውኝ አእምሮዬን ልያኮላሹ የሚያሴሩ በተንኮል የተካኑ ስለሆኑ የተቀበልኩት መንፈስ የፍርሃት ሳይሆን የፍቅር እንደሆነ በገሃድ ልነግራቸው እፈልጋለሁ።

ከሞት በላይ የሆነ ተልዕኮ ያነግብን መልዕክተኞች ነን! የአማኝ ሞቱ ነፍሱን ለማሰንበት እውነትን መሸቃቀጥ ሲጀምር እንጂ ነፍስና ስጋው ተለያይተው አስከሬን ተብሎ…"ነፍሴም ወደ አምላኳ ሥጋም ወደ አፈሩ…" በሚል ዝማሬ ታጅቦ ግብአተ መሬቱ የተፈጸመ እለት አይደለም። መሰንበት መኖር የሚመስላቸው ሰዎች በምድር ላይ ለመቆየት ብለው እውነት የሚያስከፍላቸውን ዋጋ ላለ መክፈል ነፍሳቸውን በውሸት ባህር ውስጥ ደብቀው ርካሽ ኑሮ ለመግፋት ይገደዳሉ።

በፖለቲካ ሜዳ ላይ ያለውን ፍልምያ ገጥሜ የጽድቅ ጥቃት ለማድረስ በአእምሮና በትምህርት ለመብሰል ዘመናትን መጠበቅ ቢኖርብኝም ዘረኝነት ወደ ራሴ ሜዳ (ቤተክርስቲያን) ዘልቆ ገብቶ የመሰነጣጠቅን አደጋ እያደረሰብን መሆኑን ስገነዘብ መነሳትና መመከት ከዳተኝነትና ከአድርባነት እንደሚሻል በማሰብ ነው። ምክንያቱም ቤተክርስቲያን ይህንን የቤት ሥራ በብቃት የማትወጣ ከሆነ በየትኛውም ተቋም ላይ እምነት የለኝም። ስለዚህ ነው አልሞት ባይ ተጋዳይ ፍልምያ ውስጥ ለመግባት የወሰንኩት።

የመከፋፈልና የጥላቻ ነጋሪት በሚጎሰምበት ትውልድ ውስጥ በለሆሳስ ድምጽ እንዋደድ ማለት አያዋጣም። አይሰማማ! ካልተደመጥኩ መናገሩ ለምን ያስፈልጋል? የቤተክርስቲያን ድምጽ በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ እምብዛም መሆኑ ብቻ ሳይሆን ባለ መድኃኒቶቹ መታመማቸው አሳሳቢ ወቅት ላይ መሆናችንን ይጠቁሙናል። ሰው ውሻን አላምዶ አብሮት እየኖረ ከሰው ጋር መኖር እንዴት ያቅተዋል? የሚለው የውስጤ ጥያቄ ነው። በድፍረት የተነሳሁት፣ የሚሸነቁጥ ቃላትም የምጠቀመው ለዚህ ነው። አብረን መኖር አንችልም በሚል ድምዳሜ ላይ የደረሰ ትውልድ ካለ

ይህንን አስተሳሰብ ያነገቡትን ሰዎች በክፉ መርዛቸው እንዳለክፉን ተለይተናቸው በሚቀጥለው ያልተበከለ አመለካከት ባላቸው ትውልድ ላይ መስራት ብቸኛው አማራጫችን ነው!! ከተስማማህ አብረን እንነሳ!

## የሴራው ጥንስስ

የጠብ፣የጥላቻ እና የግድያ ዕድሜ የሰው ልጅ በኃጢአት የወደቀበትን ጊዜ ያህል ረጅም ነው። ክቡር የሆነው የሰው ልጅ በዲያብሎስ ተታሎ ከአምላኩ ጋር የተለያየበት እለት የጀመረው አባዜ እስከ ዛሬ ድረስ የዓለማችን ቋሚ ራስ ምታት ሆኖ ቀጥሏል። መወነጃጀል፣ ማሳበብ እና ውሸት የማንነቱ መገለጫዎች ሆኑ። ከወደቀው አሮጌ ማንነት ውስጥ በፍጥነት የበቀለው የጥላቻ ዛፍ አብቦ ፍሬ ለማፍራት ብዙ ህዝብ እና ትውልድን መጠበቅ አላስፈለገውም። ገና በጠዋቱ የዓለማችን አንድ አራተኛ ሰውን በማጥፋት ተገለጠ። ቃየን አቤልን በክፉ ቅናት ተነሳስቶ በግፍ ገደለዉ። ታሪካቸውም ጥላቻ፣ ቅንአት እና የተዛባ አመለካከት መንሰራፋቱን በግልጽ ያሳየናል ።

*“ቃየንም ወንድሙን አቤልን፦ ና ወደ ሜዳ እንሂድ አለው። በሜዳም ሳሉ ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሣበት፥ ገደለውም።”* ዘፍ 4፡8

ሰው ለመጠላላትና ለመጎዳዳት አልተፈጠረም። ቃየን እኔ የተሻልኩ ነኝ እኔ ብቻ ልኑር የሚል ክፉ ጥላቻ ተጠናውቶት ስለ ነበር የገዛ ወንድሙን ለመግደል አልሳሳም። ነፍስ ማጥፋትና መዋሸት የባህርይው መገለጫዎች ሆኑ። መጀመርያ ወንድሙን አባብሎ ከቤት አውጥቶ በጭካኔ ገደለው፣ በመቀጠል እግዚአብሔርን ለማታለል ሞከረ። የተጋነነ እና ጫፍ የደረሰ ራስ ወዳድነት አብሮ ለመኖር ትልቅ እንቅፋት እንደሆኑ ከቃየን ህይወት እናያለን።

*እግዚአብሔርም አለ፦ ሰውን በመልካችን እንደ ምሳሌአችን እንፍጠር የባሕር ዓሦችንና የሰማይ ወፎችን፥ እንስሳትንና ምድርን ሁሉ፥ በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉይግዙ። እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው ወንድና ሴት አድርጎፈጠራቸው።* ዘፍ 1፡26-27

ይህ የመለኮት ባህርይ የፍጥረቱ መደምደሚያ እና ገዢ በሆነው በአዳም ላይ እየተንጸባረቀ እንዲኖር የተቸረው የማንነቱ መሠረት ነበር፡፡ የአዳም እና የመለኮት ግንኙነት እና አብሮነት የተመሠረተው በዚህ መልክ ላይ ነው፡፡ ሰይጣን ይህንን አንድነት ማደፍረስ ቀዳሚ ተግባሩ በማድረግ ያለ የሌለ ኃይሉን እና ክፋቱን በማስተባበር የሸንገላ ዘመቻውን አጧጧፈ፡፡ ከአምላካቸው ጋር የተለያዩትን ሰዎች እርስ በርሳቸው ማለያየትና ማጋጨት ቀላል እንደሆነ በደንብ ገብቶት ነበርና፡፡ ያለ ነቀፋ የነበረው አዳም ከእግዚአብሔር ጋር የፍቅር ጊዜን ባሳለፈበት በኤደን ገነት ውስጥ ከውድቀት በኋላ ድብብቆሽ እና ሽሽትን ተያያዘው፡፡

*"እነርሱም ቀኑ በመሸ ጊዜ የእግዚአብሔርን የአምላክን ድምጽ ከገነት ውስጥ ሲመላለስ ሰሙ አዳምና ሚስቱም ከእግዚአብሔር ከአምላክ ፊት በገነት ዛፎች መካከል ተሸሸጉ፡፡ እግዚአብሔር አምላክም አዳምን ጠርቶ፦ ወዴት ነህ? አለው፡፡"* ዘፍ 3፡8-9

በተንኮል ተጠንስሶ በስኬት የተደመደመው የኤደን ገነት የሰይጣን የመጀመሪያ ሙከራ በዘፍ 4፡6 ላይ የነበረውን የማገዳደል እኩይ ተግባሩን ባሳለፍነው ክፍለ ዘመን ብቻ በጀርመን በትልቅ ጭካኔ ስድስት ሚልዮን አይሁዳዊያንን ሲፈጅ በአህጉራችንም በ1994 እ.ኤ.አ. በሩዋንዳና ቡሩንዲ ወደ አንድ ሚሊዮን የሚጠጉ ሰዎችን ለህልፈተ ህይወት ዳርጓቸዋል፡፡

አሁንም ቢሆን በዓለማችን ላይ በርዝመቱ ተስተካካይ ከሌለው የትዕቢት ተራራ ስር የሚፈልቀው መርዛማው የዘረኝነት ወንዝ በሚልዮኖች የሚቆጠሩ ሰዎችን በደም ጎርፍ እያጥለቀለቀ ያለ ከልካይ በሰባቱም አህጉራት ላይ እየተንፈላሰሰ ይዞራል፡፡ በኤደን ገነቱ ውድቀታችን ያኔ የወጋን የሰይጣን የማታለል ቀስት እስከ ዛሬ የዓለማችንን ህዝብ ወገብ እንዳጎበጠ ይገኛል፡፡

## በረከቱ መርገም ሆኖብን ይሆን ?

*"እግዚአብሔርም ባረካቸው፥ እንዲህም አላቸው፦ ብዙ፥ ተባዙ፥ ምድርንም ሙሉአት፥ ግዙአትም የባሕርን ዓሦችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው፡፡"* ዘፍ 1፡28

ገና አንድ ወንድ እና ሴት በነበሩበት ወቅት ከእግዚአብሔር በቀጥታ የተቀበሉት የመጀመርያ በረከት ብዙ ተባዙ የሚል ነበር፡፡ አሁን አሁን ግን ዓለማችን መብዛትን እንደ መርገም በመቁጠር የሰው ልጅ እንዳይጋባ የተቀደሰውን ጋብቻ በማርከስ፣ ግብረ ሰዶማዊነትን በማበረታታት፣ በትክክለኛው መንገድ የፍጥረትን ህግ ተከትለው የተጋቡት ደግሞ በልጅ እንዳይባረኩ በማህጸን ውስጥ በማጨናገፍ፣ ከዚህም አምልጠው ያደጉትን ደግሞ በጥላቻ እና በክፋት በማስታጠቅ እርስ በርሳቸው እንዲተራረዱ በማድረግ ክፋትን እንደ ዋና ተግባር በመፈጸም ተጠምዳ፤ የአመጽን ባህር በመዋኘት ላይ ትገኛለች፡፡

አዳምና ሔዋን የተቀበሉት የመብዛት በረከት የተፈጥሮን ህግ ተከትሎ የሚካሄድ ሲሆን ግለሰብ፣ ቤተሰብ፣ ጎሳ፣ ነገድ፣ ብሔር፣ ህዝብ እያለ አገርን ይመሰርታል፡፡ በቁጥር መብዛት ብቻ ሳይሆን ተፈጥሮን እንዲጠብቁ እና እንዲንከባከቡ፣ በትጋት እንዲያስተዳድሩ፣ ፍቅር እና እውነትን እንዲያንጸባርቁ በተጨማሪ የተጣለባቸው ኃላፊነቶች ነበሩ፡፡ መብዛት በራሱ ችግር ቢሆን ኖሮ የችግሩ መንስኤ እግዚአብሔር ይሆን ነበር፡፡ ዳሩ ግን መብዛት በራሱ ችግር ሆኖ ሳይሆን ማንኛውንም መልካም ነገር ወደ ጥፋት በመለወጥ የተካነው ሰይጣን ከወደቀው ማንነት ጋር በማበር በረከቱን ለጥፋት አደረጉት እንጂ፡፡

በዚህ ሰበብ በዓለማችን ላይ ካሉት ከሰባት ቢሊዮን ህዝብ ርቀው በአእምሮአችው ውስጥ የተሳለቸውን መንደር እንደ ገነት በማሰብ ከሌሎች ተገንጥለው በጥላቻ በተከበበው ደሴት ላይ የሚኖሩ ጥቂት አይደሉም፡፡ ከዚህች ክልል ወጥተው ከቀሩት ሰዎች ጋር መቀላቀል ከአውሬ ጋር የመኖር ያህል ስለሚከብዳቸው አይሞክሩትም፡፡ ልባቸው በትዕቢት ስለ ተሞላ የሌላ ብሔር አባላትን የሚቀበሉበት ቦታ የላቸውም፡፡ ውስጣቸውም በጥላቻ ስለ ጨለመ ነገሮችን የሚያመዛዝኑበት ስብዕና የላቸውም፡፡

ዘረኝነት እንደ ጉም ዓይናቸውን ስለ ሸፈነው ከራሳቸው ምህዳር ውጪ ነገሮችን መቃኘትም ማመዛዘንም አይችሉም፡፡ ጥላቻ ሲዘራ እንደ መልካም መሬት ሆነው መለያየትን እንደ ምርጥ ዘር በደንብ ያፈራሉ፡፡ እነዚህ ሰዎች የፍቅር አቀንቃኝ ለሆነችው ቤተክርስቲያን ቋሚ እንቅፋት ናቸው፡፡

## 1.2. የዘረኝነት ትርጉም

*"ወንድሙን የሚጠላ ሁሉ ነፍሰ ገዳይ ነው፥ ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ።"* 1ዮሐ 3፡15

የተለያዩ ምሁራን ዘረኝነትን እንደሚከተለው ለመተርጎም ሞክረዋል፡-

- ዘረኝነት ባጭሩ ከቀለም ወይንም ከዘር ልዩነት የተነሳ ራስን ከሌላው የተሻለ አድርጎ መገመትና በሌላው ላይ ገኖ እና ሰልጥኖ መገኘት ነው። ብሔርተኝነት ሲባል ደግሞ ሕዝቦች በብሔር (ወይንም በነገድ፣ በጎሳ፣ በወገን) በመከፋፈል የአንድ ብሔር ሕዝብ ከሁሉ በላይ እንደሆነ በመቁጠር ሌሎችን ለመግዛት መብት አለው የሚል ሥርዓት ነው።[1]
- ባህሩ ዘርጋው በጻፉት መዝገበ ቃላት ዘረኝነት አንድን ብሔር በጥላቻ፣ በጥርጣሬ እና በጠላትነት በትምህርት ያለ እኔ ሀሳቢ የለም ባይነት፣ ሌሎችን በንቀት ዝቅ አድርጎ ማየት፤ የተዛባ ግንኙነት መፍጠር። በማለት ያስቀምጡታል።
- ዶ/ር አኩይልን ታሪሞ ደግሞ ዘረኝነት በአንድ አካባቢ በጋራ የሚኖሩ ሰዎች ተመሳሳይ ቋንቋ፣ ሐይማኖት፣ ባህል፣ ከአንድ ወገን የመጡ ሰዎች የተጠቀሱትን መስፈርቶች ምክንያት በማድረግ ሌሎችን መግፋት ነው ይላሉ።[2]
- የመንደረኝነት መነሻውም መድረሻውም መንደሩ ነው ከመንደሩ የሰፋ፣የላቀ እና የረቀቀ ነገር አይታየውም። መንደረኝነት የሚጀምረው እዚያው በቅርቡ የሚታየውን እና የሚሰማውን መሰረት በማድረግ ነው። ይህ የመንደረኝነት መሰረት ምንድነው? ዘር ነው? ቋንቋ ነው? ሐይማኖት ነው? ባህል ነው? መንደረኝነት ባህል ምንድነው? ብሎ አይጠይቅም መነሻውም መድረሻውም የመንደሩ ቋንቋ፣የመንደሩ ሐይማኖት፣ የመንደሩ ባህል ከሌላው

---

[1] ማርክሲዝም ሌኒንዝም መዝገባ ቃላት፡ አ.አ. ኩራዝ አስታሚ ድርጅት ገጽ 206፤213

[2]. Rev. Dr Aquiline Tarimo, SJEthnicity, Common Good and the Church in Contemporary Africa (25 September 2000)

ሁሉ የተሻለ እና የበለጠ ነው የሚል ጠባብ አስተያየት ነው መነሻውም መድረሻውም ልዩነትን ማጉላት ነው፡፡[3]

ከላይ ያየናቸው ትርጉሞች በአጠቃላይ የግለሰቦች ምልከታ እንጂ ፍፁምና እንከን የለሽ መረዳት አይደሉም፡፡ ስለ ዘረኝነት በከፊል ለመረዳት ይረዱን ይሆናል፡፡ ነገር ግን ሙሉ ስዕል የሚሰጠን መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው፡፡ በተለይ ባሕሩ ዘርጋው በመዝገበ ቃላታቸው ላይ እንደጻፉት ዘረኝነት "ያለ እኔ ሀሳቢ የለም ባይነት፣ ሌሎችን በንቀት ዝቅ አድርጎ ማየት፣ የተዛባ ግንኙነት መፍጠር" እነደ ሆነ ያስቀምጣሉ፡፡ ይህ ትርጉም በከፊል እውነት ቢሆንም ዘረኝነት እበልጣለሁ ከሚል ስህተት እንደሚመጣ ሁሉ አንሳለሁ ከሚል ፍርሃትም ሊመነጭ እንደሚችል ጋሼ ንጉሤ ቡልቻ ሊሰመርበት የሚገባ እውነት እንደ ሆነ ይናገራሉ፡፡[4]

ከላይ ባለው ክፍል ዘረኝነትን ለመተርጎም ሞክረናል፡፡ ይሁንና አንዱ ብሔር ወይንም የተለያዩ ግለሰቦች ሌላውን ለማንቋሸሽና ለማጥላላት የተለያዩ ስያሜዎችን በመለጠፍ ሲቀራቀዙና ሲዘላለፉ በገሃድ እየታየ ነው፡፡ መቼም ስደበኝ ብሎ ጥያቄ የሚያቀርብ ሰው እንደሌለ ሁሉ ልስደብህ ብሎ ፍቃድ የሚጠይቅም እንደማይኖር ግልጽ ነው፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሳያስተውሉ መከፋፈል፣ ጥላቻና ተንኮልን በተሞሉ የምላስ አለንጋ ወደ ወገኖቻቸው ልብ ጉርጆ ድረስ ዘልቀው እየገረፉ እያቆሰሉ ይገኛል፡፡ በየዋህ ልቡ ላይ የጥላቻን ዘር እየዘሩ ውንጀላውን ተያይዘውታል፡፡ ስድብ የዋልጌነት መለኪያ እንጂ እውቀት ማሳያ ሊሆን አይችልም፡፡ በየትኛውም አገር ስድብ ፍቅርን ሲያመጣ አላየንም፡፡ መናቆርም መቀራረብን ሊወልድ አይችልም፡፡ ዘረኝነት የተለያዩ ስያሜዎች ተሰቶት የዜጎቻችንን የወንድማማችን መዓዛ በክፉ ጠረን እየለወጠ ያለ ስሜትን የሚረብሽ መጥፎ ሽታ ነው፡፡ አሁንም ቢሆን አንድ ብሔር ከሚታወቅበት ህጋዊ መጠርያ ሌላ የሚለጠፍበት አላስፈላጊ ስድቦች ጥላቻን ከማባባስ ውጪ ፋይዳ የሌለው መሆኑ ታውቆ ከድርጊቱ መቆጠብ ተገቢ ብቻ ሳይሆን አፋጣኝ ጥሪ ነው፡፡

---

[3]. መስፍን ወልደማርያም (2005)፣ መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ፣ ገጽ 171
[4]. በግል ስናጫወት፡፡

ዘረኝነት ሞት ከነገሰበት አሮጌው ማንነት ሊዋጀን በመጣው በጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ላይ ማፌዝ ነው፡፡ የዘላለምን ሕይወት የምናገኝበት ብቸኛው መንገድ ከጌታ ዳግም መወለድ መሆኑን መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምረናል፡፡ በተለይ እኛ አማኞች ከዚያ ይልቅ የራሳችንን የጥላቻ መንገድ ቀይሰን መፈርጠጣችን በትልቅ መስዋዕትነት የተሰጠንን እንቁ በእርያ ፊት እንደመጣል እና ክርስቶስን ደግመን እንደመስቀል ይቆጠራል፡፡

*"ኢየሱስም መልሶ፦ እውነት እውነት እልሃለሁ፥ ሰው ዳግመኛ ካልተወለደ በቀር የእግዚአብሔርን መንግሥት ሊያይ አይችልም አለው።"* የሐ 3፡3

ጥላቻ ነፍስን የማጥፋት ያህል ዘግናኝ ምግባር ነው፡፡ ዘረኝነት ደግሞ ከጥላቻ የሚመነጭ እኩይ ተግባር ነው፡፡ የዘረኝነትን ምንነት መረዳት ከዚህ ችግር ለመገላገል ወሳኝ እና የመጀመሪያው እርምጃ ነው፡፡ ችግሩንና የሚያስከትለውን ኪሳራ በሚገባ ማስላት ካልቻልን እንደ ስልጣኔና እውቀት እያሰብን ባለማስተዋል በሞት ባሕር ልንሰጥም እንችላለንና ከፍተኛ ጥንቃቄ ያሻናል፡፡

ዘረኝነት በተለያየ ስያሜ ሊጠራ ይችላል፡፡ ብሔርተኝነት፣ ጎሰኝነት፣ መንደርተኝነት፣ ጎጠኝነት፣ ጠባብነት እና የመሳሰሉ ስያሜዎችን ልንሰጠው እንችላለን፡፡ በቃሉ ስያሜ ላይ አምባጓሮ መፍጠር አላማዬ አይደለም፡፡ የእኔ ትኩረት ጥልቅ የሆነ የምርምር ስራ ማቅረብም አይደለም፡፡ መሠረታዊ እና ሊያግባባን የሚችል አጠራር ካገኘን በቂ ነው፡፡ በብዙ ወገኖች ሕይወት ላይ ጥላቻና ዘረኝነት የነገሰው የዘረኝነትን ትርጉም ስለማያውቁት አይደለም፡፡ ማንም ስብእና ያለው ሙሉ ሰው ጥላቻ ኀጢአት መሆኑን ህሊናው ስለሚነግረው በሚገባ ያውቀዋል፡፡ ዋና ትኩረቴ ይህ ችግር ከሥሩ ተነቅሎ እንዲወጣ ሊረዱ የሚችሉ የመፍትሔ ሀሳቦች ማቅረብ ላይ ነው፡፡

ዘረኝነት ከግለሰብ ጀምሮ እስከ አህጉር ተለጥጦ ሊሄድ የሚችል ችግር ስለሆነ ትልቅ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው፡፡ እያንዳንዳችንውስጣችንን ብንፈትሽ ጦርነት ሊኖር ይችላል፡፡

*“ሥጋ በመንፈስ ላይ መንፈስም በሥጋ ላይ ይመኛልና፥ እነዚህም እርስ በርሳቸው ይቀዋወማሉ፤ ስለዚህም የምትወዱትን ልታደርጉ አትችሉም።”* ገላ 5፡17

አንደኛው ማንነታችን ዳግሞ ልደትን ካገኘበት ከጌታ ጋር ሲወግን ሌላኛው ደግሞ ከአዳማዊ ባህርይ ጋር ለመተባበር ሲፈልግ አእምሮአችን የጦር ሜዳ ይሆናል። አንዳንዴ ጥላቻ በፍቅር፣ ቂም እና በቀል በይቅርታ ላይ ሲያይሉብን ይታያል። ይህንን ጦርነት ጄ. አስ. ስዋን የተባሉ ሰው "እኛው ከእኛው ጋር ስንፋለም" ይላሉ። ይህም ፍቅር እና ጥላቻ፣ትህትና እና ትዕቢት፣ራስን መግዛት እና ልቅነት፣ቂም እና ይቅር ማለት በውስጣችን ሊፋተጉ ይችላሉ።

*“ብልቶቻችሁንም የዓመጸ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለኃጢአት አታቅርቡ፥ ነገር ግን ከሙታን ተለይታችሁ በሕይወት እንደምትኖሩ ራሳችሁን ለእግዚአብሔር አቅርቡ፥ ብልቶቻችሁንም የጽድቅ የጦር ዕቃ አድርጋችሁ ለእግዚአብሔር አቅርቡ።”* ሮሜ 6፡13

ይህ ከባድ ትግል ነው። በዚህ ደረጃ በውስጣችን የጀመረው ክፍፍል በክርስቶስ ሃሳብ አሸናፊነት መፍትሄ ካላገኘ ወደ ቤተሰብ ይሸጋገራል። በቤተሰብ መካከል መከፋፈል ሊመጣ ይችላል። ይህም በመልክ፣ በፆታ፣ በጸባይ እና በተለያየ ምክንያት ለቤተሰቦቻችን አባላት ደረጃ መድበን መክፈል እንጀምራለን።

*“ወንድሞቹም አባታቸው ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ እንደሚወደው ባዩ ጊዜ ጠሉት፥ በሰላም ይናገሩትም ዘንድ አልቻሉም።”* ዘፍ 37፡4-8

ባለማስተዋል በቤተሰቦቻችን አባላት መካከል የምናደርገው አድልዎ በቤተሰቡ አንድነት እና የወደፊት ህልውና ላይ ክፉ ድባብ ያጠላል። ከቤተሰብ ደረጃ ሲያልፍ ወደ ቤተ-ዘመድ ይሻገራል። በዘመዶቻችን መካከል ልዩነትን መፍጠር እንጀምራለን። በዚህ ደረጃ ሀይማኖት፣ የኑሮ ደረጃ፣ መቀራረብ እና የመሳሰሉ ነገሮችን እንደ መስፈርት አበጅተን ለጥላቻችን ምክንያቶችን መደርደር እንጀምራለን።

*"አሁንም ልጄ ሆይ ቃሌን ስማ ተነሣና ወደ ካራን ምድር ወደ ወንድሜ ወደ ላባ ሂድ።"* ዘፍ 27፡43

ከዘመድ ቀጥሎ ወደ ጎሳ ይሻገራል። ከአንድ ነገድ በተገኙ የተለያዩ ጎሳዎች መካከል በተለያየ ሰበብ ክፍፍል ሊፈጠር ይችላል። ከጎሳ ቀጥሎ በነገዶች መካከል ልዩነት ይወለዳል። ዘረኝነት ከግለሰብ ጀምሮ እስከ አህጉር ከዚያም በላይ በዚህ አይነት ሊያድግ ይችላል። በብሔር ደረጃ ያለው መከፋፈል በግልጽ የሚታይ ቢሆንም በአንድ ብሔር መካከል በተለያየ ሰበብ የሚፋተጉ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም። ምክንያቱም ዘረኝነት በብሔር ደረጃ የሚገታ ችግር ሳይሆን ከሌላ ሰው አልፎ ከራሳችንም ጋር የሚያጋጨን ከባድ አውራቂስ ነው።

አንድሪው ጀክስ የተባሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር "ሰው ወደ ገሃዱ አለም ለመምጣት በሥጋ መወለድ አለበት እንደዚሁ ወደ መንግስተ ሰማይ ለመግባትና እዚያ ለመኖር ዳግም ከመንፈስ መወለድ ግድ ይለዋል። ክርስቶስ የሚያውቀው ማንነት ከእርሱ የተወለዱትን ብቻ ነው።" ብለዋል።

በሌላ በኩል እንደ እኔ መረዳት ከግለሰብ ጀምሮ እስከ አህጉር ድረስ በተለያየ መንገድ ሰዎችን ከዘራችን/ብሔራችን ውጪ በመሆናቸው ብቻ በመጥላት ውድቀታቸውን ከመመኘት ጀምሮ የሚጠፉበትን መንገድ ማመቻቸት አልፎም ለመግደል የሚደረግ ሙከራን በአጠቃላይ ዘረኝነት ልንለው እንችላለን።

ጽንሰ ሃሳቡ ይህ ሆኖ ሳለ ብሔርተኝነት፣ ጎሰኝነት፣ ጎጠኝነት የሚሉትን ቃላት በተለዋጭነት ለመጠቀም ሞክሬአለሁ።[5]

---

[5] For further illustration the word racism can be referred as: chauvinism, bigotry, intolerance, prejudice, ethnicity, tribalism, individualism, preferential treatment, discrimination, nepotism, xenophobia, bias, favoritism, slavery, ethnic-cleansing etc, such words may help us to understand the concept of racism more.

ዘረኝነት የጥላቻ ውጤት ነው፡፡ ይህ ጥላቻ ደግሞ ከአዳማዊ ባህርይ የሚመጣ ሲሆን በግለሰቦች፣ በጎሳ፣ በነገድ፣ በብሔር፣ በአገር እና በአህጉር ደረጃ ሊገለጥ ይችላል፡፡ ዘረኝነት በአማኞች ዘንድ ሲከሰት ግን የተወለድንበትን አዲስ ዘር ካለማወቅ ወይንም ከማቅለል የሚመጣ ህይወታችንን የሚያጠፋ ትልቅ ድንዛዜ ነው፡፡ አንዳንድ አማኞች ጥላቻ እና ዘረኝነትን እንደ መብት በመውሰድ በትጋት እየተገበሩት ይገኛሉ፡፡ ይህ ደግሞ በኢትየጵያ ወንጌላዊያን አብያተ-ክርስቲያናት ታሪክ ውስጥ ከየትኛውም ጊዜ በላይ ወደ ጨለማ እየተንዝን መሆኑን የሚጠቁም ነው፡፡ ጌታ ወደ ፍቅሩ እና ወደ ማስተዋል ይመልሰን!

## ብሔርተኛ የሆነ ብሔር አለ?

ፍረጃው ተጧጡፎአል፣ እራስን ጻዲቅ አስመስሎ ሌሎችን መኮነን ተበራክቶአል፡፡ አሁን እያናወጠን ላለው አውራቂስ ኃላፊነቱን አንዱ ብሔር በሌላው ላይ ለመጫን ሲታትሩ በገሃድ ይታያል፡፡ አንዳንዶቹ የራሳቸውን ብሔር የአገሪቱ የሰላም አምባሳደር ሌሎችን ደግሞ ጠብ ጫሪ አድርጎ ለመወንጀል ይቃጣቸዋል፡፡ የመጀመሪያ እትም ያዩ ሰዎች በመደነቅ "እንዴት ባይሣ በብሔርተኝነት ጉዳይ ላይ ይጽፋል?" ብለውኛል፡፡ እኔንም ገርሞኛል! ስለ ዘረኝነት ለመጻፍ ማን መሆን ነበረብኝ? እስኪ ንገሩኝ፡፡ ደመላሽ? ኃየሉም? ላምቦሮ? ዘበርጋ?፡፡ የብዙ ሰዎች አእምሮ ሚዛኑን ስቶ አይቻለሁ፡፡ ስለ ዘረኝነት ለመናገር ማንም ምንም መሆን አያስፈልግም ሰው ብቻ መሆኑ በቂ ነው፡፡ ጥቁር ይሁን ነጭ፣ ማንም አንድነትን ቢሰብክልን እንሰማዋለን እንተባበራለንም፡፡

ዘረኞች በየትኛው ብሔር ውስጥ ይኖራሉ ነገር ግን ይህ ብሔር ዘረኛ ነው ማለት ግን ስህተት ብቻ ሳይሆን የዘቀጠ አመለካከትም ነው፡፡ ማንኛውም ሰው ይህ ብሔር ዘረኛ ነው በማለት የሚለፍፍ ከሆነና ፍረጃ ውስጥ ከወደቀ ተናጋሪው እራሱ በጥላቻ ውስጥ ሰጥሞአል ለእኩይ ባሕሪው ምክንያት ፍለጋ እየዳከረ ነው፡፡ አሁንም ፍረጃ የአንድነት ጎዳና ሊሆን አይችልም፡፡ መካሰሱ፣ መመጻደቁም የውድቀት አካኼድ ስለሆኑ ቶሎ መንገዳችንን ማስተካከል አስፈላጊ ጥሪ ነው፡፡

## 1.3. የዘረኝነት ምክንያቶች

*"የሰው መንገድ ሁሉ በዓይኖቹ ፊት ንጹሕ ነው እግዚአብሔር ግን መንፈስን ይመዝናል።"* ምሳ 16፡2

ጋሼ ንጉሤ ቡልቻ ትውልዱ ለመለያየት የፈጠነ መሆኑን በቁጭት ይናገራሉ። "ትውልዱ በጥላቻ፣ በቂም እና በበቀል ደድሯል። ጠብ ለመጫር ፈጣን ነው። የጫረውን ትንሽ እሳት አፋፍሞ ጫካውን ሁሉ የሚበላ ሰደድ ለማድረግ ጊዜ አይወስድበትም። ይህ ትውልድ እርስ በእርሱ የተፈራራ ጥላውን የማያምን ደንባራ ትውልድ ሆነ። ራሱ ከራሱ ጋር ስምረት ስለሌለው ከሌላው ጋር ተጣጥሞ መኖር ርቆታል። የርሕራሄ ሕዋሱ ደነዘ፣ብዙ መራቀቅ የማይጠይቀዉ ሰብዓዊ ሐዘኔታ እንኳ ከሕሊናዉ ተሟጠጠ። እርቅ እና ሰላም የፌዝ ቃላት ሆኑበት። የባልጀራውን ሕይወት እና ኑሮ እንደ አሮጌ እራፊ ብስክስክ አድርጎ ሲጥል በእብድ ፍጥነት እና ጉልበት ነው"[6]

ከየትኛውም ድርጊት በስተጀርባ ስውር ሀሳብ አለ። አድራጊው ወይንም ሌላ ሰው በውል መረዳት የማይችሉት ነገር ግን እግዚአብሔር ብቻ አብጠርጥሮ የሚያውቀው ድብቅ ሃሳቦች በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ ተሰውሯል። ዘረኝነትም ሰዎችን በማግለል፣ በመጥላት ወይንም በመግደል የሚገለጥ ተግባር ቢሆንም መነሻው ግን ከልብ ዝንባሌ ነው። ይህ ጥንስስ በተለያዩ ምክንያቶች የሚፈጠር ሊሆን ይችላል። የተለያዩ ምሁራንና የማህበረሰብ ሳይንስ ተመራማሪዎች የራሳቸውን ግምት ሲያስቀምጡ ይታያሉ። የብዙዎቹ መላምትና ግምት ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ያፈነገጠ ስለሆነ ትክክለኛውን ምክንያት መጠቆም ተስኗቸው ሲንደፋደፉ አይተናል።

ዘረኝነት የሚከሰትበትን ምክንያት ዶ/ር ሣራ ሸወግባን የተባሉ ጸሐፊ እንደሚከተለው ያቀርባሉ፡-

---

[6] ንጉሤ ቡልቻ (2002)፣መስተአየት ገጽ 65

ሀ. Primordialism (ፕሪሞርዲያሊዝም)፡- ፕሪሞርዲያል ማለት ቀድሞ የነበረ፣ የጥንት፣ ተፈጥሮአዊ ማለት ሲሆን ይህንን አመለካከት የሚያራግቡ ሰዎች ዘረኝነት በተፈጥሮ የሚመጣ ሲሆን ይህም አንድ ሰው ለተወለደበት ማህበረሰብ፣ ለሚናገረው ቋንቋ፣ ለተወለደበት ልማዶቹ ልዩ የሆነ ቁርኝት ወይንም ስበት እንዲያድርበት የሚያደርግ አንዳች ገዢ ኃይል ያሸንፈዋል በማለት ይገልጻሉ።

ለ. Instrumental (እንስትሩሜንታል)፡- እንስትሩመንት ማለት አንድን ተግባር ለማከናወን የምንጠቀምበት መሣሪያነው። የዚህ አመለካከት ጽንፍ አቀንቃኞች ዘር አንድን አላማ ለመምታት የሚያገለግል መሣሪያ እንደሆነ ያምናሉ። ዘር በዋናነት የሚዋቀረው ከዘውጉ መካከል ላሉ ልሂቃን ወይንም በተወሰኑ ቡድኖች አማካኝነት ሲሆን ዋናው አላማውም ለፖለቲካ፣ ለሥልጣን፣ ለኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች እና ለመሰል ግቦች ለመጠቀም ነው።[7]

እንደ ዶ/ር ሣራ ገለጻ በመጀመሪያው ሃሳብ ላይ ሰው ዘረኛ ያለ መሆን አይችልም የሚሉ ይመስላሉ። ምክንያቱም ተፈጥሮአዊ ስለሆነ ይህንን ስበት የማያስተናግድ ሰው ስለማይኖር። በተጨማሪ ዘረኝነት የሰው ልጅ አይቀሬ ገጽታ እንደሆነ ያስቀምጣሉ። በሁለተኛው ላይ ግን ጥላቻን በሰው መካከል ሆን ብሎ በመዝራት ከዚያ የሚገኘውን ትርፍ በማግበስበስ የግል ፍላጎትን ለማርካት እንደሚጠቅም ነው። ይህንን አመለካከት ሎሪን ሐኒስበሪ የተባሉ ሰው *"ዘረኝነት መሳሪያ ነዉ። ሌላ ነገር አይደለም"* በማለት ይደግፉታል።

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ በበኩላቸው ዘረኝነት የጠባብነት ውጤት መሆኑን ይናገራሉ። ይህ ጠባብነት የብዙሃኑን ሃሳብና መብት ያለ መቀበል ነው። እሳቸው እንዳስቀመጡት "የትኛውም ብሔርተኝነት የራሱን ብቻ ነው የሚያየው። ማዕከል የሚያደርገውም የራሱን ብቻ ነው። ሌሎች ብሔሮች

7 ማቴቴስ (ጥቅምት 2, 2002) ገጽ 6

ስለ መኖራቸው እና መብትም እንዳላቸው ያለመቀበል ሁኔታ ይታያል። ምክንያቱም ሁሉም የራሱን ጠባብ ምህዳር ብቻ ነው የሚያየው"።[8]

እኔነት ሌላኛው የዘረኝነት አቀጣጣይ ነዳጅ ነው። ይህ እኔነት (lism/egoism) በራስ ላይ ብቻ ያተኮረ ማንኛውንም ነገር ከራሱ ጥቅም እና ጉዳት አኳያ ብቻ የሚመዝን የዘቀጠ አስተሳሰብ ነው።

*"በእነዚህም ልጆች መካከል እኛ ሁላችን ደግሞ፥ የሥጋችንንና የልቡናችንን ፈቃድ እያደረግን፥ በሥጋችን ምኞት በፊት እንኖር ነበርን እንደ ሌሎቹም ደግሞ ከፍጥረታችን የቁጣ ልጆች ነበርን።"* ኤፌ2፡3

ለዘረኝነት መነሻ ይሆናሉ የምንላቸውን ብዙ ምክንያቶች ማስቀመጥ ይቻል ይሆናል። እነዚህ ሁሉ ግን በአንድ ነጥብ ይቋጫሉ። በቃ! የኃጢአት ሁሉ መሠረት ከአዳም የተወረሰው አሮጌ ማንነት (*የሥጋ ሥራ*) ነው። በገላ 5፡19 ላይ የተዘረዘሩት እና የስጋ ስራ የተባሉት ሁሉ የዚህ አሮጌ ማንነት ውጤት ናቸው። ከሁሉ የሚያሳዝነው ግን ከእነዚህ ባህርያት ነጻ ወጥተናል በምንል አማኞች ብሶ መገኘቱ ነው። የክርስቶስ ስለሆንን ዘረኝነት የሚነግስበትን ማንነት መጽሐፍ ቅዱሳችን ሰቅላችሁታል እያለን እኛ ደግሞ አውርደን ከነክርፋቱ ለብሰነዋል።

*"ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔ ምለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።"* ገላ 6፡14

አሁንም የዘረኝነት ጉዳይ በቤተክርስቲያን ውስጥ የተስፋፋበት ምክንያት አሮጌ ማንነታቸውን ከክርስቶስ ጋር መቀበር የተሳናቸው አማኞች መብዛታቸው ነው። ስለዚህ ዘረኝነት ሰው በመንፈሳዊህይወቱ ሲያሽቆለቁል የሚያነሳው ጉዳይ እንጂ የእድገት፣የእውቀት እና የስልጣኔ ምልክት አይደለም ሊሆንም አይችልም።

---

[8] ዳንኤል ተፋራ፣ ዳንዲ የነጋሶ ጊዳዳ መንገድ፣ 2003 ገጽ 298

## የዘረኝነት አይነቶች

ወንድማችን በድሉ ደሳለኝ ማርጋሬትና ኮሊንስን ጠቅሶ ዘረኝነትን በሁለት ቦታ ከፍሎታል፡፡[9]

1. **ግላዊ ዘረኝነት፡** አንድ ግለሰብ አንድ ዘር ከሌላው ዘር የበላይ እንደ ሆነ ያለው እምነት ሲሆን ከተሳሳተ ድምዳሜ የሚመነጭ ወይም ለአንድ ግለሰብ ከዘሩ ጋር በተያያዘ ከሚያንጸባርቅ አሉታዊ ባህርያት የተነሳ የሚፈጠር ጥላቻ ነው፡፡
2. **ተቋማዊ ዘረኝነት፡** ከግላዊ ዘረኝነት በላቀ ሁኔታ የተደራጀ እምነትና ባሕርይ ያለው ሲሆን አንድ ዘር ከባህላዊ ወይንም ሥነ-ህይወታዊ ጠባያት የተነሣ የተጨቆነ፣ የተገዛ እና የተበዘበዘ እንደ ሆነ ያለ እሳቤ ነው፡፡

## 1.4. የዘረኝነት መገለጫዎች

በአንድ ወቅት በአገራችን ባለ የሥነ-መለኮት ትምህርት ቤት ውስጥ አንድ መምህር ተማሪዎቹን ከብሔራቸሁና ከክርስትናችሁ የትኛው ማንነት ነው ለእናንተ በጣም አስፈላጊው? ብሎ ሲጠይቃቸው ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ተማሪዎች ብሔር ብለው እንደመለሱለት ቦብ ኤሪክሰን ይናገራል፡፡[10] የአንድ ነገር ስህተት አደገኛነቱ ተምረናል አውቀናል ከሚሉ ሰዎች መነሳቱ ነው፡፡

የዘረኝነት በሽታ ያጠቃው ሰው የሚታወቅበት ብዙ መገለጫዎች አሉት፡፡ ዘረኝነት የተጠናወተው ሰው ከምንም ነገር በላይ ከራሱ ጋር ሰላም የለውም፡፡ አዕምሮው በበቀል፣ በጥላቻ፣ በንቀት ስለ ተመረዘ የጸጸት እና የፍርሃት ኑሮ ነው የሚገፋው፡፡ ሰዎችን ለመውደድ በቂ ምክንያት

---

[9] . በልሁ ደለለኝ (2002) ጽንፋዊነት፡ አዲስ አበባ

[10] Bob Erikson (1998). The Gospel of Restoration, International Tryck AB, Sweden P. 71

ያጣል። ያለ ቅድመሁኔታ የሆነውን የክርስቶስ ፍቅር ጨርሶ ስለማያውቀው ኑሮው በጥላቻ ጽልመት የተዋጠ ነው።የዘረኝነትን መገለጫ ከግለሰብ ወደ ማህበራዊ ኑሮ አጉልተን ስናይ በሦስት ማዕዘን ማስቀመጥ ይቻላል።




*ሥዕል 1.1 የዘረኝነት መገለጫ መንገዶች*

የትኛውም አገር በእነዚህ ምሰሶዎችላይ ነው ተገንብቶ የሚኖረው። ማህበራዊ፣ኢኮኖሚ፣ፖለቲካዊ እና ኃይማኖታዊ ሁኔታዎች አንድን አገርለመገንባትም ሆነ ለማፍረስ ልንጠቀምባቸው የምንችል መሣሪያዎች ናቸው። ዘረኝነት በእነዚህ አበይት ጉዳዮች ላይ መታየት ከጀመረ ለዚያች አገርወዮላት! እስኪ አንድ በአንድ ለማየት እንሞክር።

## 1. 4.1. ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎች

*"ብርን የሚወድድ ሰው ብርን አይጠግብም ባለጠግነትንም የሚወድድ ትርፉን አይጠግብም ይህም ደግሞ ከንቱ ነው።"* መክ 5፡10

ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ህይወት ለአንድ አገር ህልውና ወሳኝ ጉዳዮች ናቸው። ስለ ኢኮኖሚ እና ቢዝነስ ካሰብን የንግድ ልውውጥ የምናደርገው ከሰዎች ጋር መሆኑ እሙን ነው። የንግድ ማዕከሉ ሰው ነውና። አንድ እቃ ሲፈበረክ የሰውን ፍላጎት መሠረት በማድረግ ነው። የምድራችን የተፈጥሮ ሀብት፣ የአየር ንብረት በተለያዩ ቦታዎች እንዲኖሩ ያደረገው

እግዚአብሔር ነው፡፡ ንግድ ማለት እነዚህን ሀብቶች በብዛት ከሚገኙበት ወደ ሌሉበት ቦታ በማጓጓዝ የሰውን ፍላጎት ለሚሟላት መስራት ነው፡፡ ይህንን እንቅስቃሴ ስንቃኝ በአንድ ቀን በብዙ ቲሪልየን የሚቆጠሩ ዶላሮች፣ በቴራ ባይቶች የሚላኩ መረጃዎች፣ በሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች፣ በብዙ ትሪልዮን የሚቆጠሩ እቃዎች በምንኖርባት ፕላኔት ላይ ይንቀሳቀሳሉ፡፡

የአገራችንንም የንግዱን ሁኔታ እና የማህበረሰቡን አኗኗር ስንቃኝ በዓለም አቀፍ ከሚስተዋለው እውነታ የራቀ አይደለም፡፡ የሉል አቀፋዊነት ተጽዕኖ በእኛ አገርም እየተስተዋለ ነውና፡፡ መጠኑ እና የአሰፋፈሩ ሁኔታ ይለያይ እንጂ የአንድ ብሔር አባል የሌለበት የአገራችን ክፍል አለ ለማለት ያስቸግራል፡፡ ከኢትዮጵያም አልፈው በተለያዩ የዓለም አገራትም ጭምር በመኖር ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ በረከትም መርገምም አይደለም በቃ በምድር ላይ ስንኖር የምናስተናግደው አይቀሬው የህይወት ገጽታ ነው፡፡

ስለ አገራችን የንግድ እንቅስቃሴ ከታሰበ የቢዝነሱ አቀጣጣይ የሆነውን የጉራጌ ማህበረሰብ ማንሳትግድ ይሆናል፡፡ እነዚህ ወገኖች ለሥራ ካላቸው ጥልቅ ፍቅር የተነሳ ያልገቡበት የሥራ ዘርፍ ያልደረሱበትም የኢትዮጵያ ክፍል አለ ለማለት አይቻልም፡፡ ለዚህ ትልቅ ምሳሌነታቸው ሊመሰገኑ ይገባል፡፡ ጉራጌዎች ብቻ ሳይሆኑ ሁሉም ብሔሮች በአገሪቱ ውስጥ ተዘዋውረው ይሰራሉ፡፡ የመኖሪያ አካባቢያቸውንም በመቀየር ከሌላው ማህበረሰብ ጋር ተቀላቅለው ይኖራሉ፡፡

ይህ በኢትዮጵያ ውስጥ የተከሰተ አዲስ ፈጠራ ሳይሆን የሰው ልጅ በዓለም ላይ መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንስቶ የነበረ እውነት ነው፡፡ እግዚአብሔር ምድርን ሙሏት ብሎ ሲባርክ ካላችሁበት ወደ ሌላ ቦታ ተስፋፉና ኑሩ ማለቱ ነው፡፡ የመስፋፋት ሂደት በራሱ ችግር የለውም ነገር ግን ስግብግብነት፣ እኔ ብቻ ልኑር ባይነት፣ ይህ አገር የእኔ ብቻ ነው የሚልአስተሳሰብ በአንዳንድ ሰዎች ላይ ሲከሰቱ ህብረተሰቡ መታወክ ይጀምራል፡፡ የሀብት ሽሚያ ከብሔር አልፎ ወንድማማቾችን የሚያፋጅ ጉዳይ ወደ መሆን ይመጣል፡፡ አንዱ ብሔር በትዕቢት እና በግፍ ሌላውን ብሔር ሲገፋ ከፍተኛ ደም መፋሰስ ሊከሰት ይችላል፡፡

ይህ እንዳይሆን ቀድሞ በአካባቢው ለረዥም አመታት ይኖሩ ከነበሩት እንዲሁም ከሌላም ቦታ ለተለያዩ የሥራ ጉዳዮች ከአዲስ ማህበረሰብ ጋር ተቀላቅለው ለመኖር ከሚመጡት ሰዎች የሚጠበቅባቸው ኃላፊነቶች እና ግዴታዎች አሉ፡፡ ቀድሞ በአንድ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ያቺን አገር እነርሱ እንዳልሰሯት የተፈጥሮ ሀብቷም የእግዚአብሔር እንጂ የእነርሱ እጅ ሥራዎች ያለመሆናቸውን መቀበል አለባቸው፡፡ በተጨማሪ ምድር ለሰው ልጆች በጊዜአዊ መኖሪያነት የተሰጠች እንጂ ዓለም እስካለች ድረስ እንደ ተራሮች ተቸንክረን የምንቀርባት እንዳልሆነ መገንዘብ ግድ ይላል፡፡ ከሁሉ በላይ ደግሞ እኛም እንደ ጣዖት የምንወድሰውን አካባቢ እና እንደ መላዕክት ከምንወዳቸው ሰዎች በተለያየ ምክንያት ተለይተን እንድንሄድ የሚያደርግ አጋጣሚ በህይወታችን ሊከሰት እንደሚችል ማሰብ ተገቢ ነው፡፡

በሌላ በኩል ለተለያዩ ምክንያቶች በተለይ ለንግድ፣ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ መስሪያ ቤቶች ተቀጥረን ለመስራት ወደ ተለያዩ ቦታዎች እንዘዋወራለን፡፡ ይህ ሲሆን ከአዲስ ማህበረሰብ እና አካባቢ ጋር በሰላም ለመኖር የሚጠበቅብን ግዴታዎች አሉ፡፡

ነጋዴዎች ከትውልድ አካባቢያቸው ርቀው ሲሰሩ የማህበረሰቡን ባህልና ቋንቋ ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡ አንዳንድ በችርቻሮ ንግድ የሚተዳደሩ ነጋዴዎች የአካባቢውን አርሶ አደር እና ነዋሪ ሲንቋቸው ይታያሉ፡፡ ያሳደጋቸውን ህዝብ ያተረፉበትን ህብረተሰብ ማክበር ሲገባቸው በተቃራኒው በትዕቢት ሲያንቋሽሿቸው፣ ጭንቅላታቸው ገንዘብን እንጂ የሰውን ልጅ ክቡርነት ማገናዘብ የማይችል ደካማ መሆኑን ያሳያል፡፡

በተለይ በፍጥነት እያደጉ ባሉ ከተሞች አካባቢ የሚታየው ግፍ የትውልዱን ተቻችሎ የመኖር እሴት የሚያደበዝዝ ከመሆኑም በላይ በብሔሮች መካከል ትልቅ ቁርሾ እያስቀመጠ ይገኛል፡፡ ፋብሪካዎች ሲተከሉ በሰላም ለብዙ መቶ አመታት በአካባቢው ላይ ይኖሩ የነበሩትን ገበሬዎች ያለ በቂ ካሣ አፈናቅለው ከፋብሪካው በሚለቀቀው ቆሻሻ አካባቢውን ይመርዛሉ፡፡ ይህ ሳያንስ አዲስ በተቋቋመው ፋብሪካ ውስጥ የመቀጠር እድል እንኳን ይነፈጋሉ፡፡ ከጥበቃ ሰራተኛ እስከ ሥራ

አስኪያጅ ድረስ ከራሳቸው ዘመድ አሊያም ደግሞ ከብሔራቸው መርጠው ይቀጥራሉ፡፡ ለተጎዳው ህዝብ የተለያዩ መሠረተ ልማቶችን በመገንባት አንደ መካስ የሰውን ልጅ ሳይሆን ዝንጀሮን ፈንቅለው ቦታውን የያዙት ይመስል ይኩራራሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ተፈናቃዮች ቂም እና በቀል መጠንሰስ ይጀምራሉ፡፡

ኢፍትሃዊ የሆነ የሀብት ክፍፍል የብሔርን መስመር ተከትሎ የሚሄድ ከሆነ ወደማያባራ የእርስ በርስ ግጭት ያመራል፡፡ በደንብ አስተውሎ ለተመለከተ አንድ ሕንጻ ሲገነባ አገራችን እያደገች ነው የሚለው ሳይሆን የህንጻው ባለቤት ብሔሩ ምንድነው? የሚል ጥያቄ ነው በብዙ ኢትዮጵያዊ አእምሮ ውስጥ የሚመጣው፡፡

ባለሀብት መሆን አስፈላጊ እና ጠቃሚ ለአገርም ለውጥ ወሳኝ ግብዓት ሆኖ ሳለ ኃላፊነቶችን መዘንጋት ሌላውን ከማሳደግ ይልቅ ለመጨቆን የምንጠቀምበት ከሆነ ግን ከበረከቱ ይልቅ የሚያስከትለው መርገም ያመዝናል፡፡

## 1. 4.2. በፖለቲካው ምህዳር

*"ጮማውን ትበላላችሁ ጠጕሩንም ትለብሳላችሁ፥ የወፈሩትን ታርዳላችሁ በጎቹን ግን አታሰማሩም፡፡ የደከመውን አላጸናችሁትም የታመመውንም አላከማችሁትም የተሰበረውንም አልጠገናችሁትም የባዘነውንም አልመለሳችሁትም የጠፋውንም አልፈለጋችሁትም በኃይልና በጭቈናም ገዛችኋቸው፡፡ እረኛንም በማጣት ተበተኑ፥ ለምድርም አራዊት ሁሉ መብል ሆኑ፥ ተበተኑም፡፡"* ሕዝ 34:3-5

ከላይ ያለው ክፍል የእስራኤል መሪዎች ለህዝቡ መማረክ እና መጎሳቆል ዋነኛ ምክንያቶች እንደሆኑ ያሳያል፡፡ መሪዎች በሚገባ ስላልሰበሰቧቸው ህዝቡ ተበተነ፡፡ የአንድ አገር ህዝብ የአንድነት ሚስጥር በአገሪቱ መሪዎች መካከል አውነተኛ አንድነት እና የአገር ፍቅር መኖሩ ላይ ነው፡፡ የዜጎች ሀሳብ የመሪዎች ሀሳብ ነጻብራቅ ስለሆነ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይፈልጋል፡፡ በተለይ ከተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በተዋቀረች እንደ ኢትዮጵያ ባለች አገር ውስጥ ዘረኝነት በቀላሉ ሊቀጣጠል የሚችል

ሰደድ እሳት ነው። በአመራር ላይ ያሉ ሰዎች በዘረኝነት የተመረዙ ከሆነ ይህ የመከፋፈል ሀሳብ በቀላሉ አገሪቱን ሊያጥለቀልቅ ይችላል።

በፖለቲካ ውስጥ ያሉ ሰዎች (በገዢ እና በተቀዋሚ ፓርቲ ውስጥ ያሉ) የዘረኝነት አጀንዳን እንደ ፖለቲካ መሣሪያ ከተጠቀሙበት የተፈረካከሰች አገር እና የተከፋፈለ ልብ ያላቸው ዜጎች ይፈጥራሉ። ሰዎች በአካል ከመለያየታቸው እና ከመበታተናቸው በፊት የሚለያዩት በሀሳብ ነው። በስልጣን ላይ ለመውጣትም ሆነ ለመሰንበት የህዝቡን ልብ መከፋፈል እንደ ስልት የሚጠቀሙ ፖለቲከኞች ከድህነት በላይ ለአገሪቱ ነቀርሳ የሚሆኑት እነርሱ ናቸው። በአገራችን ውስጥ ያሉትን ብሔሮች በእኩልነት የማያከብር እና አገሪቱን ወክሎ ሳለ የራሱን ብሔር ብቻ በልዩ ሁኔታ ለመጥቀም የሚሰራ አመራር አገሪቷን ልትወጣ በማትችልበት አዘቅት ውስጥ ይቀብራታል።

ፖለቲካውን ተቀላቅለው ለአገራቸው የበኩላቸውን አስተጽዎ ለማበርከት አሜሪካ አገር ለረጅም አመታት ከኖሩ በኋላ ወደ ትውልድ ቀያቸው የተመለሱት አቶ ተመስገን ዘውዴ የታዘቡትን እንዲህ ይገልጻሉ "የተለወጠ ነገር ቢኖር 'መጤ' እና 'ተወላጅ' የሚለው መቧደን ብቻ ነው። ሳውላ እና ቢልቂ መሃል የተጠመደ የዘር ፈንጂ ነው" ብለዋል።[11] የፖለቲካ ሰው እንደ መሆናቸው መጠን የአገራችንን ገጽታ ያዩበትን የተላያዩ ርዕሰ ጉዳዮችን በማንሳት ትዝብታቸውን አስቀምጠዋል። በቂ ትንታኔ በሰጡበት በዘረኝነት ጉዳይ ላይ ቀድሞ የነበረው የአንድነት ስሜት ከትውልድ ቀኤያቸው ተነቅሎ በምትኩ ጥላቻ እንደ አድባር ዛፍ ተንዠርግጎ ማየታቸው የልብ ስብራት እንዳስከተለባቸው በቁጭት ይናገራሉ።

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳም በበኩላቸው በፓለቲካ ሰዎች አካባቢ የሚታየው ዘረኝነት የጠባብነት ውጤት እንደሆነ ይገልጻሉ። "የትኛውም ብሔርተኝነት የራሱን ብቻ ነው የሚያየው። ማዕከል የሚያደርገውም የራሱን ብቻ ነው። ሌሎች ብሔሮች ስለመኖራቸው እና መብትም እንዳላቸው ያለ መቀበል ሁኔታ ይታይበታል። ምክንያቱም ሁሉም

---

[11] ዳንኤል ተፈራ.፣ከፓርላማዉ በስተጀርባ 2006፣ ገጽ 99-100

የራሱን ጠባብ ምህዳር ብቻ ነው የሚያየው፡፡"[12] ይህ የራስወዳድነት ባህርይ ከትዕቢት ጋር ተቀላቅሎ በሌሎች የመኖር ህልውና ላይ አደጋ ማምጣት ይጀምራል፡፡

ከላይ ያየናቸው አስተያየቶች በፖለቲከኞች የተሰነዘሩ በመሆናቸው ምናልባት ለሚነዱት የፖለቲካ መኪና እንደ ነዳጅ ሊጠቀሙበት እንደሚችሉ መገመት አያዳግትም፡፡ እኔ ግን እንደ ግብአት የተጠቀምኩት በአገር መሪዎች ደረጃም ዘረኝነት እንደ ዋና መሳሪያ ጥቅም ላይ የሚውል አውዳሚ ባክቴርያ መሆኑን ለማሳየት ብቻ ነው፡፡

እውነት ለመናገር አሁን በአገራችን ውስጥ ያለው ብሔርተኝነት ለአገር እድገት ከድህነት በላይ አስጊ ቸነፈር ሆኗል፡፡ ምክንያቱም አንድነት ቢኖረን ከልብ ከተደጋገፍን እንኳን ለኢትዮጵያዊ ወገኖቻችን ለአፍሪካ የምንበቃ ነን፡፡ አንድ መሪ የፖለቲካውን ስፍራ ከፕሬዝዳንት እስከ ጎጥ ደረጃ ያለውን ሲይዝ ለአገር ይጠቅማል፣ የአመራር ብቃት አለው፣ ለአገር ያስባል ሳይሆን ብሔሩ ምንድን ነው? የሚለው ጥያቄ ይቀድመናል፡፡ እንደዚህ አይነት ጥያቄዎች መነሳት ከጀመሩ ህዝቡ ወደ ማያባራ የእርስ በርስ ግጭት ሊያመራ ይችላል፡፡ የፖለቲካ ምህዳር በዘረኝነት ከተለከፈ ያቺ አገር ከዚያ አገግማ አንድነትን ማምጣት ከካንሰር እንደ መፈወስ ነው፡፡ ዘመናትን ይፈጅባታል፡፡ እግዚአብሔር የአገራችንን ፖለቲካ ከዘረኝነት የጸዳ እንዲያደርግልን ከመጸለይ ጀምሮ በቅንነት እና በእውነት ለህዝቦች አንድነት የበኩላችንን ድርሻ ማበርከት ይኖርብናል፡፡

## 1.4.3. በኃይማኖት ተቋማት

*"እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና፡፡"* ማቴ 7፡12

ከላይ የተጠቀሰው ክፍል ለክርስቲያኖች (ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክ፣ ፕሮቴስታንት) የኢትዮጵያ የኃይማኖቶች ጉባዔ እንደ መሪ ጥቅስ

[12] ዳንኤል ተፈራ.፣ የነጋሶ ጊዳዳ መንገድ - 2003, ገጽ. 298

ወስዶታል፡፡ አላማውም በሁሉም ኃይማኖቶች መካከል ተከባብሮ የመኖር እሴቶች እንዳሉ ለማሳየት እና መቻቻልን ለማበረታታት ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ክርስትና እና እስልምና ከ85% በላይ ተከታዮች ሲኖራቸው የተቀሩት ደግሞ 15% አካባቢ ይሆናሉ፡፡ ምንም እንኳን ኃይማኖት ያዋጣናል የምንለውን አምላክ በገባን መንገድ ማምለክ ቢሆንም አንዳንዴ ከዘር ጋር ይገናኛል፡፡ ወደ ሐረርጌ አካባቢ ስትሄዱ ክርስቲያን ከሆናችሁ አማራ ትባላላችሁ፡፡፡ አንድ ሰው ከሰሜን ነኝ ካለ በቃ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ ነው በማለት እንደመድማለን፡፡

እንደ አማኝ ወደ ክርስቶስ ስንመጣ ሰውን ሁሉ የምንወድበትን የፍቅር ጉልበት ነው የተጎናጸፍነው፡፡ ለሚጠሉን እና ለሚያሳድዱን ሁሉ የምናሳየው ፍቅር ያለ ስስት ወደሚፈልቅበት ምንጭ ማለት ነው፡፡ አንዳንዴ ግን ይምታታብናል፡፡ ለጌታ ያለንን ፍቅር የምንገልጸው ለወንጌል ጸር የሆኑትን በማጥፋት ይመስለናል፡፡ በተለይ ለወንጌል ዝግ የሆኑ ብሔሮች እና ጎሳዎች ከምድረገጽ ሲጠፉ ደስተኛ የሚሆኑ አማኞች አሉ፡፡ ይህ ግን የክርስቶስ ፈቃድም ዕቅድም አይደለም፡፡ እርሱ ለሁሉም የፍቅር አምላክ በማንም ሰው መሞት የማይደሰት ነው፡፡

ከኢየሱስ ያገኘነው ፍቅር ሰይጣን እና የዓለም ስርዓት ብቻ እስኪ ቀሩ ድረስ ሁሉንም የአዳም ልጆች ለማፍቀር የሚያስችለን ኃይል ያለው ነው፡፡ የክርስቶስ ልብ አለን የሚለው ቃል በመድረክ ላይ ህዝብን ለማነቃቃት ብቻ የምንጠቀምበት ቀረርቶ ሳይሆን የሚሳድዱን እና ከብሔራችን ውጪ ያሉትን በመውደድ በተግባር የምናሳይበት መመሪያ ነው፡፡

በተለይ ክርስቲያኖች ውስጥ የዘረኝነት ጉዳይ አሳሳቢ የሚያደርገው ችግሩ አውቀናል ከሚሉ ሰዎች መነሳቱ ነው፡፡ ይህ የስህተት ሰደድ እሳት ብዙ ተላላዎችን የመፍጀት አቅም አለው፡፡ የቤተክርስቲያን መሪዎች እና አገልጋዮች ለስብከት እራሳቸውን ያሰለጠኑ ያህል በማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ለመሳተፍ የፈለጉ አይመስልም፡፡ ምክንያቱም በማህበረሰቡ ውስጥ የሚነሱ የስህተት አስተሳሰብ ወረርሽኞችን ለመቋቋም አቅም ሲያንሳቸው ይስተዋላልና፡፡ በተለይ አንዳንድ ትጋት የሚጎድላቸው አገልጋዮች የእግዚአብሄርን ፈቃድ ከማህበረሰቡ የእለት ተእለት ኑሮ ጋር ማቆራኘት

ሲሳናቸው ቤተክርስቲያን ተጽዕኖ አልባ ትሆናለች፡፡ በዚህ ጊዜ ብርሃንና ጨው መሆናችን እያከተመ ይመጣል፡፡

ቀድሞ ይኖሩበት ከነበረው እምነት ወጥተው ጌታ ኢየሱስን አንተ "ጌታዬ እና መድኃኒቴ" ነህ ብለው ከክርስቲያኑ ማህበረሰብ ጋር የሚቀላለቀሉት ምን መተውና ምን ይዘው መሄድ እንዳለባቸው እንዳንድ ጊዜ ግራ ይጋባሉ፡፡ በተለይ ከክርስቶስ ጋር ያስተዋወቃቸው ሰው ወይንም የደህንነትን ትምህርት የሚያስተምር አገልጋይ ትልቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ አዲስ አማኞች ጌታን ከተቀበሉበት ጊዜ አንስተው አፍ መፍቻ ቋንቋቸውን መተው፣ በባህሎቻቸው መሸማቀቅ፣ ከማህበረሰቡ መገንጠል በተቻለ መጠን ከሌሎች ጋር ተመሳስሎ መኖር በግድ የተጫነባቸው ቀንበር አድርገው ያስባሉ፡፡ ክርስትና በአገራችንም ሆነ በሌሎች የአፍሪካ አገራት ሲመጣ የወንጌል ሰባኪዎቹ የባህልን ጉዳይ ችላ ብለውት ነበር፡፡ የተወሰኑት ሚሽነሪዎች ወደ አፍሪካ ሲመጡ አንዳንድ ባህሎቻችንን ሰይጣናዊ እና የማይጠቅሙ አስመስለው አሳዩን፡፡ የባህልን አያያዝ ካለማወቃቸው የሚሰብኩት ክርስቶስ ከራሳቸው ቋንቋ እና ባህል አንጻር እንድንከተል ጫና አሳደሩብን፡፡ ይህንን ጉዳይ አስመልክቶ ቄስ ጉዲና ቱምሳ እንዲህ በማለት ተናግረው ነበር፡፡ “መዝሙር እና ሌሎች የቤተክርስቲያን ስርዐቶችን ከእኛ ባህል ጋር ለምን አናዋህደውም ቤተክርስቲያን ለምን ኢትዮጵያዊ እንድትሆን አናደርግም? ከዚያ አልፎ ኦሮሞ፣ አማራ፣ ጉራጌ፣… አናደርግም?”[13] ብለዋል፡፡

ወንጌልን ወደ ተለያዩ ብሔሮች ማሰራጨት ያቃተንም ለዚህ ይመስለኛል፡፡ በኦሮሚያ ክልል ውስጥ ክርስትና ወደ 30% ደርሷል፡፡ ሶማሌ ክልል ውስጥ ግን ከ1% በታች ነው፡፡ [14] ለምን? ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም ክርስትናን አውዳዊ አድርገን ከብሔራችን ውጪ ላሉት ዜጎች ማቅረብ ያለመቻል አንዱና ዋነኛ ችግር እንደ ሆነ አስባለሁ፡፡ በቆዩት አብያተ-ክርስቲያናት ውስጥ እንኳን ሳይቀር የዘረኝነት ችግር ዙፋኑን በመቆጣጠር ጌታን ከቤቱ እያራቀ ይገኛል፡፡

---

[13]. ዳንኤል ተፈራ፣ የነጋሶ ጊዳዳ መንገድ 2003 ገጽ 73

[14] .Central Statistical Agency: Census Reports 2007

# ምዕራፍ ሁለት

## በጥላቻ እና ዘረኝነት እየታመሠች ያለች ዓለም

*"ሰላምና ደኅንነት ነው ሲሉ ያን ጊዜ ምጥ እርጉዝን እንደሚይዛት ጥፋት በድንገት ይመጣባቸዋል ከቶም አያመልጡም።"* 1ተሰ 5፡3

### 2.1. ተግባርን ሽጣ መርህን ብቻ ታቅፋ የምትኖረው ዓለማችን

*"ከዓመጻም ብዛት የተነሣ የብዙ ሰዎች ፍቅር ትቀዘቅዛለች።"* ማቴ 24፡12

ዓለማችን ተግባርን መውለድየተሳናቸው መካን መርሆች እና ሕጎችን ታቅፋ የምትቀመጥ ሆናለች። የምታወራው ሰላም፣ መቻቻል እና አንድነት ከወረቀት ወርደው እንዳይተገበሩ ሽባ ሆነዋል። በአንድ እጅዋ ጦር እየሳለች በአደባባይ እና መድረኮች ደግሞ ሰላምን የምታውጅ አታላይ እና ሸንጋይ ናት። መሪዎቿም በውሸት የተካኑ ናቸው። መርህ ብቻውን ምንም ማምጣት እንደማይችል በግልጽ እያየን ነው። ለተፈጻሚነቱ የሚሆን ዝግጅት እና ተአማኒነት ደብዛው እየጠፋ መጥቶአል።

*"ምሳሌውንም ከበለስተማሩ፤ ጫፍዋ ሲለሰልስ ቅጠልዋም ሲያቈጠቍጥ፥ ያን ጊዜ በጋ እንደቀረበ ታውቃላችሁ"* ማቴ 24፡32

ያለንበት ዘመን የመጨረሻው ዘመን መሆኑ ግልጽ ነው። ዓለም በጨለማ ሥራ ተሞልታ ስለታወረች ምን እየተፈጸመ እንደሆነ መገንዘብ ተስኗታል። አልያም የዲያብሎስን ፍቃድ ለመፈጸም ደፋ ቀናማለቱን ተያይዛዋለች። ያሳለፍነው 20ኛው ክፍለ ዘመን አንዳንድ ሰዎች “የደም ክፍለ ዘመን” በማለት ይጠሩታል። ምክንያቱም ሁለት ከባባድ የዓለም ጦርነቶች፣ ቀዝቃዛው ጦርነት፣ የእስራኤል እና የአረብ ውጊያ እና የተለያዩ ዘግናኝ የሆኑ የግድያ ተግባራት ተስተናግደውበታልና ነው። ከየትኛውም ጊዜ በላይ ክቡር የሆነው ሰው በጅምላ ተጨፍጭፎበታል።

*"በሕዝብላይ ሕዝብ መንግሥትም በመንግሥት ላይ ይነሣልና፥ ራብም ቸነፈርም የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ስፍራ ይሆናል።"* ማቴ 24፡7

ይህ ቃል መፈጸም ነበረበት እና ምድራችን ተደጋጋሚ ጦርነቶችን የምታስተናግድ አውድማ ሆናለች፡፡ በአሁኑ ጊዜም የምዕራባውያን እና የአረብ አገራት ፍጥጫ፣ የአሸባሪዎች ስጋት፣ የባህር ላይ ውንብድና፣ የተፈጥሮ አደጋዎች፣ ወረርሽኞች፣ ህገወጥ የጦር መሣሪያ እና የሰዎች ዝውውር፣ የሞራል ውድቀቶች (ግብረሰዶማዊነት፣ ውርጃ፣ልቅ የሆነ የግብረ ሥጋ ግንኙነት) ዓለምን ከምንጊዜውም በላይ በቅድስና ለሚኖሩባት አጸያፊና አዳጋች ስፍራ እያደረጋዳት ነው፡፡

የሰው ልጅ በሰብዓዊ ፍጡርነቱ ክቡር መሆኑን እንዲሁም እኩል እና ሊነጣጠሉ የማይችሉ መብቶች እና ነጻነት ያሉት መሆኑ በዓለም አቀፍ ህጎች ላይ ሰፍሯል፡፡ እነዚህ ደንቦች ቢኖሩም በዘረኝነት ምክንያት በሚፈጠሩ ግጭቶች ግን በብዙ ሚልዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የማያምኑ ሰዎች እንኳን የሰው ዘር መገኛ ከአንድ ወገን መሆኑን ይናገራሉ፡፡ UNESCO በ1951 ባወጣው ደንብ የሰው ልጅ መገኛው አንድ ዘር እርሱም ከሆሞ ሳፒያንስ እንደሆነ አረጋግጧል፡፡ ይህንን ህግ እንዲያወጡ የገፋፋው ምናልባትም እ.ኤ.አ ከ1938 -1945 ጀርመን በአይሁድ እና በሌሎች ላይ የፈጸመችው የዘር ማጥፋት ወንጀል ጫና አሳድሮባቸዋል የሚል የብዙዎች ግምት አለ፡፡ ሳይንሳዊ መረጃ እንደሚያመለክተው እና የተባበሩት መንግስታትም እንዳመነበት ሰው ሁሉ የተገኘውከአንድ ዘር ነው፡፡ በ1965 ይህንን መርህ ይበልጥ ግልጽ በማድረግ በአንቀጽ 6 ላይ በዘር ላይ ተመስርቶ የሚሰራ ማንኛውም አድሎ በድርጊትም ቢሆን በመርህ ደረጃ ስፍራ የሌለው ነገር ነው በማለት ይገልጻል፡፡መጽሐፍ ቅዱስም የሰው ዘር ከአንድ ወገን እንደ ተገኘ በግልጽ ይናገራል፡፡

*“ምናልባትም እየመረመሩ ያገኙት እንደሆነ፥ እግዚአብሔርን ይፈልጉ ዘንድ በምድር ሁሉ ላይ እንዲኖሩ የሰውን ወገኖች ሁሉ ከአንድ ፈጠረ፥ የተወሰኑትንም ዘመኖችና ለሚኖሩበት ስፍራ ዳርቻ መደበላቸው። ቢሆንም ከእያንዳንዳችን የራቀ አይደለም።”* ሐዋ 17፡26-27

በተጨማሪ በዘረኝነት ላይ የተመሠረተ የበላይነት በሳይንሳዊ መንገድ ውሸት፣ በሥነ-ምግባር አቅጣጫ የተወገዘ እንዲሁም በማህበራዊ በኩልም አጥፊ እና ፍትህ የለሽ እንደሆነ አስቀምጧል።

ይህ ድንጋጌ የተባበሩት መንግስታት አባል አገራት በሆኑት ሁሉ ላይ ተግባራዊ መሆን ያለበት ቢሆንም መጠኑ ይለያይ እንጂ በሁሉም የዓላማችን አገራት ላይ ችግሩ እየታየ ነው። ይህ ህግ ከወጣ ሰላሳ አመት እንኳን ሳይሞላ በሩዋንዳ እና ቡሩንዲ ብቻ ከአንድ ሚሊየን ያላነሱ ሰዎች በዘረኝነት ምክንያት ተገድለዋል። ይህ የሚያሳየን የዘረኝነትን ችግር ለመቅረፍ መርህን ብቻ ማስቀመጥ መፍትሄ መሆን እንደማይችል ነው።

*"ሕግ የሌላቸው አሕዛብ ሕግ የሚያዝዘዉን ነገር በተፈጥሮ ሲያደርጉ፣ሕግ ባይኖራቸውም እነርሱ ለራሳቸው ሕግ ናቸው። ህሊናቸው ስለሚመሰክር፣ ሐሳባቸው ስለሚከሳቸው፣ደግሞም ስለሚከላከልላቸው የሕግ ትእዛዝ በልባቸው የተጻፈ መሆኑን ያሳያል።"* ሮሜ 2፡14-15

ሰው በህሊናው ሲፈጠር የተጻፈውን የመለኮት ህግ ሆን ብሎ መጣስ ከቻለ በወረቀት ላይ የሰፈረውን ቢተላለፍ አይደንቅም።

## 2.2. የአመጽ እና ጦርነት አውድማ

*"...ለምድርና ለባሕር ወዮላቸው፥ ዲያብሎስ ጥቂት ዘመን እንዳለው አውቆ በታላቅ ቍጣ ወደ እናንተ ወርዶአልና።"* ራዕ 12፡12

ዓለም ከፍጥረቷ መልካም ነበረች። አሁን ያላትንም ቅርጽ የያዘችውም በእግዚአብሔር መንፈስ ነው። *“እግዚአብሔርም ያደረገውን ሁሉ አየ፥ እነሆም እጅግ መልካም ነበረ።ማታም ሆነጥዋትም ሆነ፥ ስድስተኛ ቀን።"* ዘፍ 1፡31

ይህ ውበቷና ተስማሚነቷ የዘለቀው መሪዋ የነበረው ሰው ከእግዚአብሔር ጋር በጽድቅ እስከ ተጓዘበት ጊዜ ብቻ ነበር። ከውድቀት በኋላ ግን የግፍ ደም የሚፈስባት ቁራ፣እሾህ እና አሜኬላ የበቀለባት የምትዋጋ ሆነች። በየዘመናቱ ሰዎች በግፍ የሚገደሉባት፣ እርኩሰት የሚከናወንባት ደሴት በመሆን ፈጣሪዋን ማሳዘኗን ቀጥላለች። ዲያብሎስ ሃሳቡን በብዙ ረቂቅ

መንገዶች የሚፈጽምባት የጥፋት አውድማምሆናለች። ገና የአቤልን ደም በግፍ የጠጣችው ምድር እስከ ዛሬ ድረስ በዚሁ ቀጥላበታለች።

### ሀ. የአቤል ደም

*"ቃየንም ወንድሙን አቤልን፦ ና ወደ ሜዳ እንሂድ አለው። በሜዳም ሳሉ ቃየን በወንድሙ በአቤል ላይ ተነሣበት፥ ገደለውም።"* ዘፍ 4፡8

በዚህ ምድር ላይ በፍቅር አብረው እንዲኖሩ የተፈጠሩት የሰው ልጆች አንዱ ሌላውን ከምድረ-ገጽ በማጥፋት ተስፋፍቶ የመኖር፣ የበላይ ሆኖ የመግነን አባዜ ከጥዋቱ ተጠናወተው። ገና አራት እያሉ መቻቻል አቃታቸው። ሰፊው ምድር ጠበባቸው። የዋሁእውነተኛ አምላኪ የሆነው አቤል ተገደለ የአቤል ደም በቃየን ላይ ተንከራታችነትን አምጥቶ አለፈ።

*“አሁንም የወንድምህን ደም ከእጅህ ለመቀበል አፍዋን በከፈተች በምድር ላይ አንተ የተረገምህ ነህ።”* ዘፍ 4፡11

### ለ. የኖኅ ዘመን

*"እግዚአብሔርም፦ መንፈሴ በሰው ላይ ለዘላለም አይኖርም፥ እርሱ ሥጋ ነውና ዘመኖቹም መቶ ሀያ ዓመት ይሆናሉ አለ።"* ዘፍ 6፡3

በኖኅ ዘመን በቀጥታ ከዘር ጋር የተገናኘ  አመጽ ተካሄደ። "የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች የሰዎችን ሴቶች ልጆች ውብ ሆነው አዩአቸው፣ ከመካከላቸውም የመረጧቸውን አገቡ" ይለናል ታሪኩ። የእግዚአብሔር ወንዶች ልጆች የተባሉት በአቤል ምትክ የተወለደ የሴት ዝርያዎች ወይንም እግዚአብሔርን የሚፈሩ ዝርያዎች ናቸው ብለው የሚያምኑ የመጽሐፍ ቅዱስ አዋቂዎች አሉ። ለእኔም ይሄው ማብራሪያ ይስማማኛል። በሌላ በኩል የሰዎች ሴቶች ልጆች የሚባሉት ደግሞ የኃጢአትን መንገድ ተከትለው የሚኖሩ ዝርያን ያመለክታል።

*"እግዚአብሔርም የሰው ክፋት በምድር ላይ እንደበዛ፥ የልቡ አሳብ ምኞትም ሁል ጊዜ ፈጽሞ ክፉ እንደ ሆነ አየ። እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ እግዚአብሔርም፦*

*የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ፥ ከሰው እስከ እንስሳ እስከ ተንቀሳቃሽም እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቼአለሁና አለ።"* ዘፍ 6፡5-7

ይህ ቀላል ጉዳይ በአንድ ወቅት ተከስቶ የነበረ ተራ ታሪክ አይደለም። በራሱ አምሳል የሰራውን ሰውን ጨክኖ እንዲያጠፋ ታጋሹ ጌታ በቁጣ እንዲነሳ ያደረገው እጅግ አሳዛኝ ኃጢአት ነው። ለእኔ እንደሚመስለኝ አመጽን እና ጽድቅን ለማጋባት የተደረገ ጥረት ነው። የተፈጸመው ጋብቻ በእግዚአብሔር ዘንድ የተወደደው እና የተጠላውን ነገር አብሮ ለማኖር የተሰራ ሙከራ ነው። ይህ ደግሞ የእግዚአብሔርን መገኘት የሚያርቅ እና ጌታን ከልቡ የሚያሳዝን ክፉ ድርጊት ነው። ከሁሉ በላይ በእግዚአብሔር የጽድቅ እና ቅድስና አቋም ላይ የተደረገ የፌዝ ስራ ነው። ዛሬም ቢሆን ዓለማችን በክፋት እና በጽድቅ መካከል ያለውን ግልጽ ድንበር በማደብዘዝ ላይ ተሰማርታለች። ይህም በምዕራባውያን ዘንድ የተሳካላትን ሰውን ከተፈጠረበት ክብር በማውረድ በእንስሳ መልክ እንዲኖር ህሊናውን ማጨለም ነው።

የኖኅ ዘመን አመጽ ዓለም አቀፋዊ እና ውስብስብ ስለነበር እግዚአብሔር የማጽዳት ዘመቻ አደረገ፡፡ በመሆኑም ከስምንት ሰዎች በስተቀር ሁሉም በጥፋት ውሃ ጠፉ።

*"አንተ ሚስትህንና ልጆችህን የልጆችህንም ሚስቶች ይዘህ ከመርከብ ውጣ።"* ዘፍ 8፡16

## ሐ. የአብርሃም ጥሪ ዋነኛ ዓላማ

*"እግዚአብሔርም አብራምን አለው፦ ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ ታላቅ ሕዝብም አደርጋሃለሁ፣ እባርክሃከለሁ፣ ስምህንም አከብረዋለሁ ለበረከትም ሁን የሚባርኩህንም እባርካለሁ፣ የሚረግሙህንም እረግማለሁ፣ የምድር ነገዶችም ሁሉ በአንተ ይባረካሉ።"* ዘፍ 12፡1-2

ከላይ ባየነው ክፍል የዓለምን ህዝብ እና ታሪክ ለሁለት የከፈለው የአብረሃም ጥሪ ተደረገ። ጥሪው የማዳላትን እቅድ የያዘ ሳይሆን የእግዚአብሔር የትድግና ፕሮጀክት ጅማሬ ነበር። የተበላሸውን ህብረት መልሶ ለማደስ ድልድይ ሲያበጅ የጌታን ርህራሄ የምናይበት ነው። ነገር ግን ብዙ ሰዎች ታላቅ እና ሰፊ የሆነውን የፍቅር ጥሪ የዘነጉበት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ይህ ይመስለኛል። ከአብርሃም የተገኙትን እስራኤላውያንን ከመጥላት አልፈው እግዚአብሔርን በዘፈቀደ የሚሠራ እና የሚያዳላ አምላክ አድርገው የሚያዩ ጥቂቶች አይደሉም። የቸርነቱን በረከት ከመቋደስ ይልቅ እግዚአብሔርን የሚተቹ ደፋሮችም ጥቂት አይደሉም። በተለይ በመካከለኛው ምስራቅ የሚታየው እንደ ኤርታሌ ግለቱን ሳይለቅ ዘመናትን ያስቆጠረው የፖለቲካ ትኩሳት ዋናው ምክንያት ይሄው ነው።

እግዚአብሔር አብርሃምን የጠራው ፍትህን አዛብቶ አንድን ወገን ብቻ የራሱ አድርጎ የቀረውን የዓለም ህዝብ ለማስቀናት እና ለመተው በጭራሽ አይደለም። የዓለም ሁሉ አዳኝ የሆነውን ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ በአብርሃም በኩል በመምጣት ከሞት እንዲታደገን የረዥም ጊዜ እቅድ ይዞ ነው እንጂ። ይህንን ድንቅ ዓላማ የሳቱ ስዎች ከአብራሃም ዘር የተወለደውን የህይወት እንጀራ ከመብላት ይልቅ እስራኤላውያንን መጥላት የሙሉ ጊዜ ስራቸው በማድረግ ከእግዚአብሔር ፍቅር ርቀው በጥላቻ ታስረው ይገኛሉ።

ዛሬ ለሰው ዘር ሁሉ እየተደረገ ያለው የህይወት ጥሪ ያኔ ለአብረሃም ከተደረገለት ጥሪ የተሻለ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። አብርሃም እና ነብያት ኢየሱስን በርቀት አይተው ነው የተሳለሙት፤ ዛሬ ግን እኛ በልባችን ውስጥ እየኖረ ነው። ሙሉ ፍቅር እና የአንድነትን መንፈስ በልባችን አፍስሶ ተዋህደን እንደ ቤተሰቦች እንድንኖር ሊያደርግ አክብሮን መጥቶአል።

ስለ ዘረኝነት ጉዳይ ከተነሳ በአብርሃም ትንሽ ስህተት ምክንያት የጀመረው መከፋፈል በብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ በጉልህ የምናየው እውነት ነው።

ከዚያም አልፎ በአዲስ ኪዳን ውስጥ በግልጽ እየታየ ያለ አሳዛኝ ታሪክ ነው፡፡

## መ. የድህረ አብርሃም ውጥንቅጦች

የአብርሃም ጥሪ በእግዚአብሔር ቸርነት እና ተነሳሽነት የተከናወነ ነበር፡፡ ዓላማውንም ገና የጠራው እለት ግልጽ አደረገለት፡፡ ከእርሱ በሚገኘው ዘር (ኢየሱስ) ዓለምን ማዳን ነው፡፡

*"ለአብርሃምና ለዘሩም የተስፋው ቃል ተነገረ። ስለ ብዙዎች እንደ ሚነገር። ለዘሮቹም አይልም፤ ስለ አንድ እንደሚነገር ግን ለዘርህም ይላል፥ እርሱም ክርስቶስ።"* ገላ 3፡16

ይህ ዘር በይስሐቅ በኩል እንዲሆን የእግዚአብሔር እቅድ ነበር፡፡ የአብርሃም ስህተት እና ያለ መታገስ ግን ችግር ፈጠረ፡፡ አሁንም ቢሆን ከአብርሃም በኋላ ባሉት በእስማኤል እና በይስሐቅ ዘሮች መካከል ያለው ጦርነት እግዚአብሔር አቅዶ ያደረገው ሳይሆን በአብርሃም ስህተት የተከሰቱ ችግሮች ናቸው፡፡

በመቀጠልም እግዚአብሔር ያዕቆብን ይሁዳን እየመረጠ ኢየሱስን ሰጠን፡፡ በአዲስ ኪዳን ዘመን እግዚአብሔር የሚያውቀው ሁለት ዘርን ነው፡፡ የመጀመሪያው በክርስቶስ ለማመን ፈቃደኛ ያልሆኑ እና በእግዚአብሔር ፍርድ ቁጣ ስር ያሉ ሲሆን፡፡ ሁለተኛው ግን ከአብርሃም ስጋ የመጣውን ፍፁም አምላክ እና ፍፁም ሰው የሆነውን ክርስቶስን ያመኑ ከእርሱ ዳግም የተወለዱትን ያካትታል፡፡

ከዘፍጥረት 4 የጀመረው የአቤል እና ቃየን አሳዛኝ ታሪክ በእስማኤል እና ይስሃቅ ዝርያዎች መካከል የነበረው ጦርነት በቅርብ ጊዜ እስከ ተከናወኑት የጀርመኑ ናዚ ፓርቲ፣ ሁቱ እና ቱትሲ አሰቃቂ ግድያዎች መልኩን እየቀያየረ ቀጥሎአል፡፡

ከድሮ ጀምሮ ከፈጣሪው ያፈነገጠው የሰው ልብ ዛሬም ወንድሙን የሚገድልበትን ሰይፍ እየሳለ በአመጻው ገፍቶበታል፡፡ ትዕቢት፣ እኔነት፣ ጥላቻ እና የሥጋ ፍሬ ሁሉ መገለጫው የሆኑት የወደቀው ሰው ማንነት

ከዘመን ዘመን ፈጣሪውን እያሳዘነ የክፋት ጣሪያ በሆነው በዚህ በመጨረሻው ዘመን ላይ ደርሰናል።

አሁን ችግሩን አሳሳቢ ያደረገው አዲስ ዘር የተባሉት ለዓለም ተስፋ የሆኑት አማኞች ለዓለም ብርሃን መሆን ሲገባቸው በዘረኝነት ችግር ውስጥ ተዘፍቀው መገኘታቸው ነው።

## 2.3. የዓለማችን ትልቁ ኪሳራ

*"የሰውን ደም የሚያፈስስ ሁሉ ደሙ ይፈስሳል ሰውን በእግዚአብሔር መልክፈ ጥሮታልና። እናንተም ብዙ፥ ተባዙ በምድር ላይ ተዋለዱ፥ እርቡባትም።"* ዘፍ 9፡6-7

የአሜሪካ አንትሮፖሎጂስት ሩት ቤኒዲክ (1887-1948) "ዘረኝነት በዓለም ላይ ያሉ ሰዎች ሁሉ የተሳተፉበት ነገር ነው። የወደፊት እጣ ፈንታችንም የሚወሰነው ዛሬ በምናደርጋቸው ተግባራት ላይ ነው ይላሉ"። ምድራችን አሰቃቂ እና ዘግናኝ የሚባል የተፈጥሮ አደጋዎችን ስታስተናግድ እግዚአብሔር አንድ ቀንም ተደናግጦ አያውቅም። ሁሉም በቁጥጥሩ ሥር ስለ ሆነ አይገረምም። ልቡን የሚያሳዝነው ነገር ቢኖር ነጻ ፈቃድ ሰጥቶት ከትልቅ ኃላፊነት ጋር በምድር ላይ ያኖረው ሰው ከሃሳቡ አፈንግጦ ያለ ርህራሄ እርስ በርስ ሲገዳደል ማየት ነው።

በምድር ላይ 6 ቀናት ሙሉ የተሰሩ ነገሮች ሁሉ የአንድ ሰው ነፍስን መግዛት አይችሉም። ሰው የዓለማችን ትልቁ ሃብት ነው። ውዱ ነገር አልማዝ ሳይሆን ሰው ነው። በአውሮፓ ከተከሰተው የኢንዱስትሪ አብዮት ወዲህ የሰው ኃይል በተለያዩ የቴክኖሎጂ ውጤቶች እየተተኩ ቢመጡም ሙሉ በሙሉ ሰውን መተካት የሚችል ነገር አልተገኘም። ሰውን የሚተካው ሰው ብቻ ነው።

### 2.3.1. የጸረ-ሴማዊያን ትግል (Anti-Semitism)

የሰው ልጅ ክፍፍል የጀመረው ገና ከዘፍጥረት 11 እና 12 ላይ ሲሆን ጉዳዩም ከኖኅ ከተወለዱት ልጆች ጋር የሚያያዝ ነው።

*"የኖን ልጆች የሴም የካም የያፌት ትውልድ ይህ ነው ከጥፋት ውኃም በኋላ ልጆች ተወለዱላቸው።"* ዘፍ 10፡1

ከብሉይ ኪዳን ሳንወጣ በሴም፣በካም እና በያፌት ዝርያዎች መካከል ጦርነቶች ሲደረጉ ነበር። ነገርግን እግዚአብሔር ለአብርሃም ጥሪ ካደረገለት በኋላ ግልጽ የልዩነት መስመር መታየት ጀመረ። ከአብርሃም በተገኙት በያዕቆብ ነገዶች እና በሌሎች ህዝቦች መካከል ጦርነቶች ሲደረጉ እንደ ነበር ከብሉይ ኪዳን የታሪክ መጽሐፍት መረዳት እንችላለን።

ከኢየሱስ ክርስቶስ ልደት በኋላም ሮማውያን ከ 4ተኛ ምእተ አመት ጀምረው አይሁዶችን የኢየሱስ ክርስቶስ ገዳዮች በማለት ያሳድዷቸዉ ጀመር። በክሩሴድ ጦርነት ጊዜም ብዙ አይሁዶች ተገድለዋል። አይሁድን ከምድረ ገጽ ማጥፋት ላይ ያተኮረውየጸረ-ሴማዊያን ትግል (Anti-Semitism) የሚል እንቅስቃሴ በይፋ የተጀመረው ግን እንደ እ.ኤ.አ.በ1879 ነው። ይህንን ተከትሎ የምስራቅ አውሮፓ አገራት እ.ኤ.አ. በ1881 ፖግራምሰ (pogroms) በሚል መጠርያ የሚታወቅ የጅምላ ጭፍጨፋ ማካሄድ ጀመሩ። በመሆኑም በተለያዩ አገራት በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ አይሁዶች ተገደሉ። እ.ኤ.አ. በ1906 በራሺያ አይሁዳውያን ንብረታቸውን ተቀሙ፣ ከትውልድ ቤታቸው ተፈናቃሉ እንዲሁም በብዛት ተገደሉ። እ.ኤ.አ.ከ1939-1945 በነበረው የዓለም ጦርነት በአውሮፓ ውስጥ ያሉትን አይሁዶች የማስወገድ ዓላማ አንግቦ የተነሳው አዶልፍ ሂትለር ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑትን በመግደል አይሁድ በታሪካቸው አይተው የማያውቁትን መአት አወረደባቸው። እ.ኤ.አ.ከ1945 ጀምሮ ወደ አገራቸው መመለስ የጀመሩት አይሁዳውያን በ1948 በተባበሩት መንግስታት እውቅና የተሰጣትን አገር መሰረቱ። ይህ ግን ለአረቦች የሚዋጥላቸው ስላልሆነ እስከ ዛሬ በንትርክ እና ጦርነት ውስጥ ይገኛሉ።

## 2.3.2. የሻርፒቫይል የዘር ማጥፋት ዘመቻ

በራሳቸዉ ምድር እንደ አንበጣ መንጋ በነጮች ተወረሩ። እንደ ሌሎች አፍሪካውያን ሁሉ በድን በምድር ላይ ሲያይ ተምዘግዝጎ እንደሚወርድ አሞራ ደቡብ አፍሪካ በእንግሊዞች ተወረረች። ለአገዛዝ እንዲያመቻቸውእ.ኤ.አ. በ1948 የአፖርታይድ ስርአትን በመዘርጋት

በጥቁሮች ላይ ዘግናኝ ግፎችን መፈጸም ጀመሩ። እ.ኤ.አ.በ1912 የተመሰረተው የአፍሪካን ናሽናል ኮንግረስ እ.ኤ.አ.በ1959 ከተቋቋመው ፓን-አፍሪካኒስት ኮንግረስ በመጣመር ይህንን ስርአት መጋፈጡን ተያያዙት። ወቅቱ መጋቢት 21/1960 እ.አ.አ ነበር። ፓን-አፍሪካኒስት ኮንግረስ የጭቆና ስርአቱን ለመቃወም ሰላማዊ ሰልፍ በሻርፒቫይል ከተማ እንዲወጡ አስተባበረ። ይህንን ማየት የማይፈልጉት ነጮች ለሰልፉ በወጡት ላይ ተኩስ ከፈቱ። ህጻናት እና ሴቶች ሳይቀር በማምለጥ ላይ እያሉ 69 ሰዎች ተገደሉ፤180 የሚሆኑ ደግሞ ቆሰሉ። ከዘጠኝ ቀናት በኋላ መጋቢት 30/1960 እ.ኤ.አ. 18,000 ጥቁሮች ታፍሰው ወህኒ ቤት ታጎሩ። ከዚያም ለ30 አመታት ያህል የቆየ ትግል ተከናወነ።

## 2.3.3. የሁቱ እና ቱትሲ ጦርነት

ወንጌላዊ ፀጋአብ በቀለ ከአንድ ሩዋንዳዊ ክርስቲያን ጋር ተገናኝተው የተጨዋወቱትን እንዲህ ይገልጻሉ “በምድር ከዘሬ የቀረሁት እኔ ብቻ ነኝ። አባት፣ እናት፣ ወንድም፣ እህት ቀርቶ አንድም ዘመድ አዝማድ በምድር ላይ የለኝም። አባቴ እና እናቴ ቱትሲዎች ስለ ነበሩ በአገሬ በአንድ ህዝብ መካከል በነበረው የብሔር የእርስ በእርስ ጦርነት አንዱ በአንዱ ላይ የበቀል እጁን ባነሳ ጊዜ ወላጆቼ ከሦስት እህቶቼ እና ሁለት ወንድሞቼጋ ከወንጌላውያን ቤተክርስቲያን ወደ አንዱ ሕንፃ ነፍሳቸውን ለማትረፍ ሸሹ። እንደ አጋጣሚ ሆኖ የዚያ ቤተክርስቲያን መጋቢ የሁቱ ብሔር ስለነበር ከወገኖቹ ጋር በማበር ወላጆቼን፣ ወንድሞቼን እና እህቶቼን በአንድነት በቤተክርስቲያን ሕንፃ ውስጥ አርዷቸዋል። እኛ አፍሪካውያን ወንጌልን እንሰብካለን፣ እንዘምራለን፣ እንማራለን እንጂ አልገባንም። ጠባብ ብሔርተኝነትን ሰይጣን ቤተክርስቲያንን እያፈራረሰበት ያለው የዘመኑ አጥፊ መሳሪያ ነው"።[15]

በሩዋንዳ እና ቡሩንዲ ውስጥ በዋናነት ሁቱ እና ቱትሲ የሚባሉ ሁለት ጎሳዎች አሉ። ከቅኝ አገዛዝ በፊት ቱትሲዎች በታንጋኒካ እና ኪቩ ሐይቆች አካባቢ ከብት አርበተዉ፤ ሁቱዎች ደግሞ አርሶ አደሮች በመሆን በሰላም ይኖሩ እንደ ነበር የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ። እነዚህ ጎሳዎች

[15] ፀጋአብ በቀለ (2005)፣ ባለራእይነት ክፍል 2፣ ገጽ 246

ተጋብተው ተዋልደው ከአንድ አካባቢ ወደ ሌላ ቦታ በመዘዋወር ይተዳደሩ ነበር፡፡ በጀርመና እና በቤልጂየም ቅኝ አገዛዝ ስር ሲወድቁ ነገሮች መለዋወጥ ጀመሩ፡፡ ቱትሲዎች ገዢ መሆን አለባቸው በማለት የትምህርት እድሎችን በመስጠት በአስተዳደርም ቢሆን ቀዳሚ ስፍራ በማጎናጸፍ በወንድማማቾች መካከል የልዩነትን እና የጥላቻን መርዝ መርጨት ጀመሩ፡፡ ቱትሲዎች በቁጥር አናሳ ቢሆኑም የበላይነት በመያዝ ከፉኛ መጨቆን ጀመሩ፡፡ ሁቱዎች ሲያምጹባቸው  አ.ኢ.አ በ1972 ቱትሲዎች በጭካኔ 100,000 የሚሆኑትን ሁቱዎች ገደሏቸዉ፡፡ እ.ኤ.አ. በ1988 አሁንም ዘግናኝ እና አስከፊ የሆነ ግጭት በመነሳቱ በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎች ከሁለቱም ጎሳዎች ለህልፈተ ህይወት ተዳረጉ፡፡ ዓለምን አጀብ ያሰኘ እ.ኤ.አ. በ1993  የተቀሰቀሰው ጦርነት ከ1,000,000 በላይ ሰዎች የተገደሉበት የአህጉራችንን አኬልዳማ ያደረጋት ደም መፋሰስ ሆነ፡፡ ዳግም ተወልደናል ያሉት ክርስቲያኖች ሳይቀሩ የተሳተፉበት አሳዛኝ እና አሳፋሪ ተግባር ተፈጸመ፡፡ ምርጫቸው ሳይሆን ከአንዱ ጎሳ መወለዳቸው እንደ ወንጀል ተወስኖባቸው በጭካኔ ብዙ ህጻናት ምንም በማያውቁት ጉዳይ ታርደዋል፡፡ በፍቅር ተስማምተው የተጋቡት ባል እና ሚስት ቃልኪዳናቸውን አፍርሰው በመለያየት ጦር ተማዘዋል፡፡ በህይወት የተረፉት ከሞቱ ባልተናነሰ ሁኔታ ለከፍተኛ ጸጸት እና የስነ-ልቦና ቀውስ ተዳርገዋል፡፡ ዘረኝነትን እንደ መዝራቱ ቀላል አይደለም ሲታጨድ መራራ ነው፡፡

### 2.3.4. ቦስንያ

በ1991 እ.ኤ.አ ዩጎስላቪያ የብሔር መስመርን ተከትላ መሰነጣጠቅ ጀመረች፡፡ በ1992 እ.ኤ.አ የቦስንያ እና ሔርዞጎቪንያ ሪፓፐሊክ ተገንጥለው የራሳቸውን መንግስት አቋቋሙ፡፡ በነጻነታቸው ማግስት ግን በጎሳ ተከፋፍለው መጨፋጨፉን ተያያዙት፡፡ ጦርነትም በቦስኒክስ (የቦስንያ ሙስሊሞች)፣ ክሮኦክስ እና ሰርብስ ብሔሮች መካከል ነበር፡፡ በ1987 እ.ኤ.አ ሚሎሴቪቺ ስልጣን ላይ እንደወጣ ለሰርቦች በማዳላት የአገሪቱ ሕገ መንግስት ለብሔሩ እንዲመች አድርጎ ለወጠው፣ የአገሪቱን መከላከያ 90% ሰርቦች አባላት እንዲሆኑ አድርጎ ገነባ፡፡  ሰርቦች የቦስኒክስ (የቦስንያ ሙስሊሞችን)ና ክሮኦክስ ብሔርን ማጽዳት ጀመሩ፡፡ ለሦስት አመት

በዘለቀው ጦርነትም በአጠቃላይ ከ100,000 ሰዎች በላይ ተግድለውበታል፡፡ ከግድያው በተጨማሪ ከ2 ሚሊዮን በላይ የሚሆኑ ዜጎች ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለስደት ሕይወት ተዳርገዋል፡፡ ጀፍሪ ስሚዝ የሚባል የታሪክ ምሁር እንደ ገለጸው በ1995 እ.ኤ.አ ሰረብረኒካ በምትባል ከተማ ብቻ ከ8,000 በላይ የሚሆኑ ቦስኒክስ ተገድለዋል፡፡ ከሁለተኛ የአለም ጦርነት ወዲህ በአውሮፓ ከተከሰቱት ብሔር ተኮር ጅምላ ጭፍጨፋዎች ቀዳሚውን ስፍራ የሚይዝ ነበር፡፡ በመሆኑም የችግሩ ግዝፈትና ግድያ አስከፊ በመሆኑ ምዕራባዊያን የተኩስ አቁም ስምምነት ለማስተለላፍ ጣልቃ ገብተው ነበር፡፡

## 2.3.5. የአሜሪካ የውስጥ ትኩሳት

የዓለማችን ገናናዋ አገር አሜሪካ ከዘረኝነት በሽታ የጸዳች አይደለችም፡፡ ከ1400-1800 ከአፍሪካ ወደ አሜሪካ የፈለሱት ጥቁሮች ጉዳይ እስከ ዛሬ ራስ ምታት ሆኖባታል፡፡ 12.3 ፐርሰንት የሚሆኑ ጥቁሮች የሚኖሩባት አሜሪካ አሁን ያለው ሁኔታ የተሻለ ቢመስልም ሙሉ በሙሉ ችግር የለባትም ማለት ግን አንችልም፡፡ ከ1775-1783 በነበረዉ የአሜሪካ ሪቮሊዩሽን የባሪያ አስፈላጊነት እየቀነሰ መጣ፡፡ ከ1860 የጸረ-ዘረኝነት ትግል ተጀመረ፡፡ 1865 አብርሀም ሊንከን (1861-1865) የባርያ ንግድ ህገ ወጥ እንደሆነ አበሰሩ፡፡ ይህ ቢሆንም ከደቡብ አሜሪካ የተነሱ ሽብርተኞች ይህንን ሊቀበሉ አልቻሉም ስለዚህ KU KLUX KLAN (KKK)[16] የሚል ቡድን በማቋቋም በጥቁሮች ላይ ግድያዎችን እና የተለያዩ ጭቆናዎችን ሲያደርጉ ቆዩ፡፡ በዚህ ውሳኔ ምክንያት አሜሪካ በሰሜን እና ደቡብ ተከፍላ ከፍተኛ ጦርነት አድርጋለች፡፡ ይህንን ችግር ለመመልከት በ1910 ጥቁሮቹም National Association for the Advancement of Colored

---

[16] Ku Klux Klan: Former Confederate soldiers founded the Ku Klux Klan (KKK) after the American Civil War (1861-1865). The KKK used violence and intimidation to keep blacks segregated and to prevent them from voting and holding office. ከከከ (ኩ ክላክስ ክላን) ማላት ከአሜሪካ ደብባዊ ክልል የተነሱ የጥቁር ሕዝቦችን እኩልነት የሚቃወሙና የነጮች የበላይነትን ለማስጠበቅ የሚዋጉ ብድኖች ናቸው፡፡

People (NAACP) የሚባል ማህበር መስርተው ትግላቸውን ቀጠሉ። ከዚያ የጥቁሮች መብት መከበር ተጀመረ። በዚሁ ሁሉ ሂደት ከአገር መሪዎች እስከ ተራው ህዝብ ድረስ በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ሰዎች ተገድለዋል፣ መብታቸዉ ተረግጧል፣እንደ ሰው ሳይሆን እንደ እንስሳ በመቁጠር እንደ መገልገያነት ተጠቅመውባቸዋል። ይህ ሁሉ የዘረኝነት አስከፊ ገጽታ ነው።

## 2.3.6. የጀርመን አይሁዳውያን ሰቆቃ

*"አንድ ህዝብ፣ አንድ መንግስት፣ አንድ መሪ"* የናዚ መፈክር

የዓለማችን ዘግናኝ ታሪክ የሰው ልጅ በጅምላ የተገደለበት ጠባሳ። ናዚ እ.ኤ.አ. በ1920 የተደራጀ ፓርቲ ሲሆን ብዙ ፕሮግራሞች ቢኖሩትም የአርያንስ ዘሮች የበላይነትን ማረጋገጥ አንዱ ነበር። ዘረኝነት የተጠናወተው የናዚ ፓርቲ የስድስት ሚልዮን አይሁድ ነፍሳትን ብቻ ሳይሆን በሁለተኛ የዓለም ጦርነት ጊዜ ለሞቱት 50 ሚሊዮን ህዝብ እና ለወደመው ንብረት ተጠያቂ ነው። ከ1933 ጀምሮ እ.ኤ.አ. እስከ 1945 ድረስ ከእኔ ውጪ ማንም መኖር የለበትም የሚል አስተሳሰብ የነበረው አዶልፍ ሂትለር ዓለማችንን ለቀውስ ዳርጓት አለፈ። በአውሮፓ ውስጥ ከነበሩት ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት አይሁዳውያን ተገደሉ። ለዚህ ደግሞ አዶልፍ ሂትለር ምክንያት ሲያስቀምጥ "አሁን አይሁዶችን በአንደኛው የዓለም ጦርነት ጊዜ በህዳር 9/1918 ለፈጸሙብን በደል የበቀል ቀን መቷል" በማለት ነው በማጎርያ ካምፖ (Holocaust) የፈጃቸው።

የአለምን ሕዝብ አጀብ ያሰኘ፣ የጥላቻና የግፍ ጥግ የሆነው አዶልፍ ሂትለር በጀርመን ይኖሩ በነበሩት አይሁዳውያን ላይ ፈጸመ። እኔም ከአንድ መጽሐፍ ላይ ያገኙሁትን አሳዛኝ ታሪክ ላካፍላችሁ ወደድኩ። ገና በለጋ ዕድሜያቸው አስከፊ ግፍ ተፈጽሞባቸው የመትረፍ እድል ካገኙት አይሁዶች መካከል በቦስተን ዩኒቨርሲቲ የነገረ-ሰብእ ፕሮፌሰር የሆኑት የ85 ዓመቱ አዛውንት ኤሊ ዊዝል አንዱ ናቸው። በፖላንድ በሚገኘው ኦሽዊትዝ በተባለው የናዚ ማጎሪያ ውስጥ1944 እና 1945 አሳልፈዋል። በመጀመሪያ የራሳቸውን ሰቆቃ ከመናገራቸው በፊት አለቃ ሞሼ ብሎ የሚጠሩት ወዳጃቸው ያጫወታቸውን እንዲህ ያስቀምጣሉ "አንድ ቀን ወደ

ምኩራብ ልገባ ስል አለቃ ሞሼ መግቢያው አካባቢ አግዳሚ ላይ ተቀምጦ አየሁት፡፡ በእሱ እና በባልንጀሮቹ ላይ ምን እንደደረሰባቸው አጫወተኝ፡፡ የተባረሩትን አይሁዶች የያዘው ባቡር የሀንጋሪን ድንበር ተሻግሮ ወደ ፖላንዳውያን ግዛት ክልል ከመግባቱ በጌስታፓ (በጭካኔው የሚታወቅ የናዚ የሚስጥር ፖሊስ) ቁጥጥር ስር ሆኖ ቆመ፡፡ አይሁዶች እንዲወርዱ እና በሚጠብቋቸው የጭነት መኪኖች እንዲወጡ ታዘዙ፡፡ የጭነት መኪኖቹ ወደ አንድ ጫካ አመሩ፡፡ እዚያም እያንዳንዳቸው ከመኪናው እንዲወርዱ ታዘዙ፡፡ ትልልቅ ጉድጓዶችንም እንዲቆፍሩ ተገደዱ፡፡ እነርሱም ስራቸውን ሲጨርሱ የጌስታፓ ሰዎች ስራቸውን ጀመሩ፡፡ እስረኞቻቸው ወደ ጉድጓዱ እንዲቀርቡ በማድረግ ምንም አይነት የኀዘኔታ ስሜት በማይነበብበት መልኩ ተረጋግተው ማጅራታቸው ላይ እየተኮሱ ገደሏቸዉ፡፡ ሕጻናቱ ወደ አየር እየተወረወሩ ለመትረየሶቹ በዒላማነት አገለገሉ፡፡ ይህ ሁሉ የተፈጸመው ኮሎማይ አጠገብ በምትገኘው የጋሊሺያ ጫካ ውስጥ ነው፡፡ ለመሆኑ አለቃ ሞሼ እንዴት አመለጠ? በተአምር፡፡ እግሩ ላይ ቆስሎ ለሞት ተትቶ ነበር፡፡”[17]

እራሳቸው በአረመኔዎቹ የናዚ ወታደሮች ታፍነው ከሚኖሩበት ሲግሄት በብዙ ሺዎች ከሚቆጠሩ አይሁዶች ጋር ወደ ትንሿ ሲኦል (ኦሽዊትዝ) አመሩ፡፡ እዚያ እንደ ደረሱም መጀመሪያ ያዩትን እንዲህ በማለት ይናገራሉ “ከእኛ ብዙም ሳይርቅነበልባል ግዙፍ ነበልባል ከጉድጓዱ እየተወረወረ ይወጣል፡፡ የሆነ ነገር እየተቃጠለ ነው፡፡ አንድ የጭነት መኪና ጠጋ አለና ይዞት የመጣውን ጭነት አራገፈ ትንንሽ ልጆች፡፡ ሕፃናት! አዎን በአይኔ በብረቱ አይቻለሁ… ልጆች ወደ ነበልባል እሳት ሲወረወሩ፡፡ እኛም ወደዚያ ነበር የምናመራው፡፡ ትንሽ አለፍ ስንል ለትልልቅ ሰዎች የተዘጋጀ ሌላ ተለቅ ያለ ጉድጓድ አለ፡፡”[18]

ከአባታቸው ጋር መማከር ጀመሩ…“ ‘አባዬ’ አልኩ፡፡ ይህ እውነት ከሆነ መቆየት አልፈልግም፡፡ በኤሌክትሪክ ወደ ታጠረው እሾኻማ ሽቦ ሮጬ እሄዳለሁ፡፡ በእሳቱ ነበልባል ውስጥ በዝግታ ነድዶ ከመሞት ይሻለኛል፡፡ … ወደ ፊት መጓዛችንን ቀጠልን፡፡ የማያቋርጥ ሙቀት ወደሚነሳበት ወደ

[17] ኤሊ ዊዝል ፣ጳዉሎስ ፈቃዱ (ትርጉም)፡ ሌሊት 2006 ገጽ 24ና 25
[18] Ibd ገጽ 51

እሳቱ ጉድጓድ ይበልጥ እየቀረበን ነው፡፡ ሃያ እርምጃዎች ይቀሩናል፡፡ ራሴን መግደል ካለብኝ ጊዜዉ አሁን ነው፡፡ እኛ ያለንበት ረድፍ ዐሥራ አምስት እርምጃዎች ናቸው የቀሩት፡፡ ጥርሴ ሲንገጫገጭ አባቴ እንዳይሰማ ከንፈሮቼን ነከስኩበት፡፡ ዐሥር እርምጃዎች ብቻ፡፡ ስምንት፡፡ ሰባት፡፡ ልክ እንደ ቀብር ተጓዥ ቀስስተኛ እርምጃ ነው የምንራመደው፤ የራሳችን ቀብር ጉዞ፡፡ አራት ተጨማሪ እርምጃዎች ብቻ፡፡ ሦስት፡፡ ይኸው ጉድጓድ እና ነበልባሉ በጣም ቀርበውናል፡፡ ከሰልፉ መኻል ወጥቼ ራሴን ወደ እሾኻማ ሽቦ ለመወርወር የቀረኝን ዐቅም አሰባሰብኩ፡፡ ከውስጤ ጥልቀት አባቴን መላውን ጽንፈ ዓለም እየተሰናበትኩ ነው ያለ ፈቃዴ በሹክሹክታ 'ይስጋዳል፣ቬይስካዳሽ፣ሽሜይ ራባ...... ስሙ ይባረክ፣ ይቀደስ...' ስል ራሴን አገኘሁት፡፡ ልቤ ሊፈነዳ ደርሷል፡፡ ይኸዉ፤ ከሞት መልአክ ጋር ፊት ለፊት ተጋፍጫለሁ...አይደለም፡፡ ሁለት እርምጃ ለጉድጓዱ ሲቀረን ወደ ግራ ዞረን ወደ አሮጌው አዳራሽ እንድናቀና ታዘዝን፡፡[19]

በተአምር የተረፉት የዛሬውፕሮፌሰር የ1986 ዓ.ም የሰላም ኖቤል ተሸላሚ የሆኑት ኤሊ ዊዝል ትዝታቸውን እንዲህ ይገልጻሉ "...ሕይወቴን ሰባት እጥፍ ወደ ታሸገ ረጅም ሌሊት የለወጡብኝን የካምፑን የመጀመሪያ ሌሊት በጭራሽ መቼም አልረሳውም፡፡ ጸጥ ባለው ሰማይ ሥር ሥጋቸው ወደ ጭስነት ሲለወጥ ያየኋቸውን ሕፃናት ትንንሽ ፊቶች በጭራሽ መቼም አልረሳቸውም፡፡"[20]

## ሰውን ገድለን ምን እናተርፍ ይሆን?

*"ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጐበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው? ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው፡፡ በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት፥"* መዝ 8፡4-6

---

[19] Ibd ገጽ 52-53
[20] Ibd ገጽ 53

እግዚአብሔር ትልቅ ስፍራ የሰጠው እና ያከበረው እንደ ሰው ያለ ፍጥረት የለም። ሰው ክቡር ፍጡር፣ በእግዚአብሔር አምሳል የተሰራ ፣ ጌታ በልቡ ውስጥ የሚያስበው፣ እርሱን ለማዳን ልጁን የላከለት ልዩ ፍጥረት እንደ ሆነ በሚገባ ካልተገነዘብን የተዛባ ህይወት ነው የሚኖረን።

እንግዲህ ሰውን ካጣን ሁሉን ነገር አጥተናል። አዳም የተፈጥሮ ሀብት ሁሉ የእርሱ ቢሆንም ያለ ሰው ህይወቱ ትርጉም የለሽ ነበር። ማናቸውም በምድር ላይ የሚገኙ ሃብቶች ትርጉም የሚኖራቸው ለሰው ልጅ በሚሠጡት ግልጋሎት ነው።

ምድራችን ትልቅ ኪሣራ እያስተናገደች ትገኛለች። ትልቁ ኪሣራ የሚጀምረው በዓለም አቀፍ ደረጃ ገንዘብ የሚዘዋወርባቸው ባንኮች መክሰር ሲጀምሩ ሳይሆን የእግዚአብሔር ስጦታ የሆነው ሰው በአእምሮአችን ውስጥ ዋጋው ሲረክስ ነው። እግዚአብሔር እንደ ትልቅ በረከት የሰጠንን ሰው እንደ ተበላሸ እቃ ስንገፋው የስጦታውን ባለቤት ማቃለላችን ነው። በንግድ ዓለም ላይ ገንዘብ ለመሰብሰብ የሰውን ጉልበት መበዝበዝ የተለመደ ነው።ይህን የሚያደርጉት ሰዎች አእምሮአቸው ጤናማ መሆኑን እጠራጠራለሁ።

ብናተርፍ ብናተርፍ በዚህ ምድር ላይ ሰውን ነው። ገንዘባችን ሰዎችን የማንረዳበት ከሆነ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ የለውም። ለእኛ ለአማኞች ትልቁ ትርፍ ሰውን ማትረፍ ነው።

ከድንቁርናዎች ሁሉ የባሰ ድንቁርና መማር ሳያስፈልግ ሰው ሆኖ የተወለደ ሁሉ በአእምሮው ውስጥ የተጻፈለትን የመለኮት ህግ ሆን ብሎ መተውና ማመጽ ነው።

*"እነርሱም ሕሊናቸው ሲመሰክርላቸው፥ አሳባቸውም እርስበርሳቸው ሲካሰስ ወይም ሲያመካኝ በልባቸው የተጻፈውን የሕግ ሥራ ያሳያሉ።"* ሮሜ 2፡15

ይህ ከፈጣሪ አፈንግጠው የፈበረኩት ከንቱ ፍልስፍና በእግዚአብሔር መልክ የተሰራውን የሰውን ማንነት እና ዋጋ ማወቅ እስኪሳናቸው ድረስ አፍዝዟቸዋል። በዓለማችን ላይ ሰልጥነዋል አውቀዋል ያልናቸው

የኂልዮሽ በመሄድ ከሰው ደረጃ ወርደው የእንስሳትን ኑሮ እየኖሩ ይገኛሉ፡፡

*"እግዚአብሔርን ለማወቅ ባልወደዱት መጠን እግዚአብሔር የማይገባውን ያደርጉ ዘንድ ለማይረባ አእምሮ አሳልፎ ሰጣቸው፤ ዓመጻ ሁሉ፥ ግፍ፥ መመኘት፥ ክፋት ሞላባቸው፤ ቅናትን፥ ነፍስ መግደልን፥ ክርክርን፥ ተንኰልን፥ ክፉ ጠባይን ተሞሉ፤ የሚያሾከሹኩ ፥ሐሜተኞች፥ አምላክን የሚጠሉ፥ የሚያንገላቱ፥ ትዕቢተኞች፥ ትምክህተኞች፥ ክፋትን የሚፈላለጉ፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያስተውሉ፥ ውል የሚያፈርሱ፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ምሕረት ያጡ ናቸው፤ እንደነዚህ ለሚያደርጉት ሞት ይገባቸዋል የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ እያወቁ እነዚህን ከሚያደርጉ ጋር ይስማማሉ እንጂ አድራጊዎች ብቻ አይደሉም፡፡"* ሮሜ 1፡28-32

ሰይጣን በአካል ተገልጦ ካላደረገው በስተቀር የሰው ልጅ ይህንን በሰው ላይ ይፈጽመዋል ወይ? ብለን ብንጠይቅ እስክንጠራጠር ድረስ በጭካኔ የተሞላ የግፍ ግድያዎች ይከናወናሉ፡፡ ይህንን የሚፈጽሙበት ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩም አንዱና ዋነኛው የእኔ ዘር ይበልጣል ስለዚህ ለምን እነካለሁ ከሚል የትዕቢትና እኔነት ስሜት በመነሳት ነው፡፡ ከብሔራቸው ወይንም ዘራቸው ውጪ የሆነ ሰው በእግዚአብሔር አምላክ መፈጠሩን ማሰብ ይሳናቸዋል፡፡

ትልቁ ኪሳራ ሰውን ማጣት ነው፤ ትልቁ ኃጢአት በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን ሰው መግደል ነው፡፡ ትልቁ እግዚአብሔርን የምናቃልልበት መንገድ በራሱ አምሳል የሰራውን ሰውን እንደማይጠቅም በመቁጠር ነው፡፡

## 2.4. የጥቁር ህዝብ ቀንበር

አህጉራችን አፍሪካ የዓለም ማህበረሰብ አባል እንደ መሆኗ መጠን ከዚህ ከዘረኝነት ችግር ውጪ አይደለችም፡፡ በብዙ መንገድ በማደግ ላይ እንደ መሆናችን መጠን ግጭቶች ያለ ማቋረጥ የሚስተናገድባት ሜዳ ነች፡፡ እንዲያውም ከእርስበርስ ጦርነት ነጻ የሆነችበት ጊዜ አለ ለማለት ይከብዳል፡፡ ፕሮፌሰር ሳሙኤል እንደሚሉት “የአፍሪካ አህጉር በኀሳ ግጭት የተሞላች ናት ይህም በሃብት እና በግዛት ላይ ነው፤ ከደቡብ እስከ

ሰሜን ከምስራቅ እስከ ምዕራብ ጦርነት እንደተፋፋመ ነው"[21] ፕሮፌሰሩ አክለው ብዙ ግጭቶች የሚነሱት በአንድ መንግስት ውስጥ በሚኖሩት የተለያዩ ብሔሮች መካከል ነው ይላሉ፡፡

### 2.4.1. የባሪያ ንግድ

ዓለማችን ካስተናገደቻቸው ዘግናኝ ግፎች መካከል አንዱ እና ዋነኛው ሰውን እንደ እቃ መሸጥ እና መግዛቷ ነው፡፡ ልክ እንደ በሬ እና አሞሌ ጨው ክቡር የሆነ ሰው በገብያ ለሽያጭ ሲቀርብ ነበር፡፡ ሰለጠንን ያሉት እነ ፖርቹጋል እና ስፔን ባሪያ ያሉትን ከምዕራብ አፍሪካ ወደ አውሮፓ እና አሜሪካ በገፍ ማጋዝ ጀመሩ፡፡ የሰው ሽያጭ ከድሮም ጀምሮ የነበረ ንግድ ቢሆንም አፍሪካውያን የተሸጡት ግንኢ-ሰብአዊ ተግባራት እየተፈጸመባቸው ነው፡፡

*"ኑ፥ ለእስማኤላውያን እንሽጠው፥ እጃችንን ግን በእርሱ ላይ አንጣል፥ ወንድማችን ሥጋችንም ነውና። ወንድሞቹም የእርሱን ነገር ሰሙት። የምድያም ነጋዶችም አለፉ እነርሱም ዮሴፍን አንሥተው ከጕድጓድ አወጡት ለእስማኤላውያንም ዮሴፍን በሀያ ብር ሸጡት እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብጽ ወሰዱት።"* ዘፍ 37፡27-28

ይህ የባሪያ ንግድ እስከ ዛሬ ድረስ በአውሮፓ አሜሪካ ውስጥ የተዛባ የማህረሰብ ግንኙነት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ በአህጉራችን እ.ኤ.አ. በ1567 የተጀመረው ከአፍሪካ ወደ አሜሪካ እና አውሮፓ ሃገራት ባሪያዎችን የማጓጓዝ ስራ ለ400 አመታት ሲከናወን ቆይቶአል፡፡ ነገር ግን በ1888 ለመጀመሪያ ጊዜ ይህንን ስርዓት ብራዚል አወገዘችው፡፡ የባሪያ ንግድ እና ስርዓት ማቆሟን አሳወቀች፡፡ ይህ ስርዓት እንዲያከትም ትልቁን ሚና የተጫወቱት ባርኮሎም ለስ ካሰስ የተባሉ ካህን ናቸው፡፡ እኚህ ካህን የስፔን እና ፖርቹጋል መንግስት የሰውን የበታችነት እንዲያቆሙ ታግለዋል፡፡

---

[21] . Samuel Waje Kunhiyop. (2008) Africa Christian Ethics Pp 107.

የባሪያ ንግድ አሁን በግልጽ ባይታይም ጠባሳው ግን ከዓለማችን ላይ አልተወገደም አንዳንድ ጊዜ መልኩን ቀይሮ ብቅ ይላል፡፡ አፍሪካ በዚህ አስከፊ ስርዓት ውስጥ ስላለፈች በብዙ መልኩ ተጎድታለች፡፡ ከነገድ፣ ከቋንቋ እና ከብሔር የተዋጀን እኛ አማኞችበምንኖርበት ማህበረሰብ ውስጥ የፈውስ እና የእርቅ ምክንያት ልንሆን ይገባናል፡፡

## 2.4.2. የቅኝ ግዢ ጠባሳ

ዶክተር አኩይልን ታሪሞ የአፍሪካን የዘረኝነት ሁኔታ በሦስት ዋና ዋና ቦታዎች ከፍለው ያስቀምጣሉ፡-

1. **ከቅኝ አገዛዝ በፊት፡-** ከቅኝ አገዛዝ በፊት አፍሪካዊያን ተሰብስበው ገጠራማ በሆነ ቦታ ላይ ሰፍረዉ በሚገርም ሁኔታ በተረጋጋ ሁኔታ እና በሰላም ይኖሩ ነበር፡፡
2. **በቅኝ አገዛዝ ጊዜ፡-** በብሔሮች ከፋፍሎ የመግዛት ግፍ በቅኝ ገዢዎች ተፈጸመባቸው፡፡ በአንዳንድ ቦታ ደግሞ በግዴታ አንድ ላይ እንዲኖሩ ተደረጉ፡፡
3. **ከቅኝ አገዛዝ በኋላ፡-** ኃይለኛ የሆነ ውድድር መከፋፈል በብሔሮች መካከል ታየ፡፡ በተለይበቤተክርስቲያን ውስጥ ሹመቶች በብሔር ላይ ተመስርቶ ሆነ፡፡

እንደ ዶክተር አኩይልን ማብራሪያ የአውሮፓውን ከፋፍሎ የመግዛት ፖሊሲ አሁን ለሚታየው መከፋፈል መሠረት መሆኑን ይናገራሉ፡፡ እነዚህ አውሮፓውያን ሁልጊዜ በወቅቱ የበላይ የሆነውን ገዢ መደብ ለመደገፍ ፈቃዳቸውን ይፈጽሙ ነበር፡፡ ፕሮፌሰር ባህሩ ዘውዴ እንደጻፉት "የኢጣልያ ከፋፍሎ የመግዛት ፖሊሲ ለአገዛዝ እንዲያመቻች ህዝቡን በቋንቋና በብሔር ከፋፍላለች" [22] ይላሉ፡፡ ፕሮፌሰር አሳኖ አለገሙ እንደሚሉት ደግሞ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አውሮፓውያን አፍሪካን ለመቀራመት ሲመጡ የተጠቀሙበት የድንበር ክፍፍል ለግጭት እና ለደም መፋሰስ ምክንያት ሆኗል፡፡

---

[22]. Bahiru Zawde (2001) A History of Modern Ethiopia 1855-1991, AAU Press P.106

በቋንቋ እና በብሔር ላይ የተመሠረተ ክፍፍል እስከ አሁን አህጉሪቱን ሊለቅ አልቻለም። የአውሮፓውን ቅኝ አገዛዝ  በአህጉራችን ላይ ያሳረፈው አሉታዊ ተጽዕኖ ቀላል አይደለም። ተረጋግቶ አብሮ የሚኖረውን የዋህ ህዝብ ከማባላት ጀምሮ ያለ መቀባበልን ዘር ዘርቶብን ሄዷል። ቤተክርስቲያን የማህበረሰብ አካል እንደ መሆኗ መጠን ይህ ጠባሳ በቅዱሳን መካከልም ጭምር እየታየ ነው።

### 2.4.3. ፌደራሊዝም በአፍሪካ

መንግስታት አሰራራቸውን ለማዋቀር ከሦስቱ ስርዓቶች (ዩኒተሪ፣ ኮንፌደሬት እና ፌደራሊዝም) አንዱን ይጠቀማሉ። በዓለማችን በተባበሩት መንግስታት አባል ከሆኑት 192 አገራት 28 የፌደራሊዝምን ስርአት የሚከተሉ ናቸዉ።[23] ወደ አህጉራችን ስንመለስ ፕሮፌሰር አሳኖ አለገሙ፡ "ከ55 የአፍሪካ አገራት በአሁኑ ጊዜ በግልጽ የፌደራሊዝም ስርዓት የሚከተሉ ናይጄሪያ፣ ታንዛንያ፣ ኢትዮጵያ እና ደቡብ አፍሪካ ብቻ ናቸው" ይላሉ[24]። ፌደሬሽን ሁሉም የራሱን ማንነት ሳይጥል በአንድነት ለመኖር ከመፈለግ የመጣ ሥርአት ነው። ሰው በተፈጥሮው ማንነቱን መተው አይፈልግም። ይህ ከማንነት ጋር ተያይዞ የሚነሳ ጉዳይ ትዕቢትን እና እኔ የበላይ ነኝ የሚሉ ስሜቶችን ሊያንጸባርቅ ይችላል። ዶክተር አሰፋ ብዙ አገራት ወደ እርስ በርስ ጦርነት እንዲያመሩ ከሚያደርጓቸው ምክያንያቶች ዋነኛውናአንዱ ቡድን ህብረትን በመፍጠር አንድ እንሁን ሲል ሌላኛው ደግሞ የለም እራሴን በራሴ ማስተዳደር ስለምፈልግ መገንጠል አለብኝ በማለት ሳይስማሙ ሲቀሩ እንደሆነ ይናገራሉ።[25]

የፌደራሊዝም ስርዓት ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ላሉባቸው አገራት አዋጪ የሆነ የአመራር ስልት እንደሆነ ይነገራል። ይህም እያንዳንዱ ብሔር የራሱን ማንነት ሳይለቅ ከሌሎች ጋር በመተባበር እንዲኖር የሚረዳ ስርዓት ነው። ነገር ግን የዓለም የፌደሬሽኖች ፕሬዝደንት "ፌደራሊዝም ለሁሉም ችግሮች መፍትሄ አያመጣም ይላሉ። በተጨማሪ ናይጄሪያ፣

---

[23]. ህብረ ብሔር፣ ህዳር 29 ቀን 2002 ገጽ 62

[24]. Prophessor Asano Alegamu (2000) Federalism and Africa. P 9

[25]. ህብረ ብሔር፣ ህዳር 29 ቀን 2002 ገጽ 63

ደቡብ አፍሪካ እና ኢትዮጵያ በፖለቲካው ውድድር ገኖ የሚታየው አንድ ፓርቲ ብቻ ነው" በማለት ይተቻሉ። ዶክትር አሰፋ የድንበር ጉዳይ የፌደራሊዝም ተግዳሮት እንደሆነ ይናገራሉ።[26] ረዳት ፕሮፌሰር ጸጋዬ ረጋሳ የቋንቋ አጠቃቀም ዙርያ የተዛባ አመለካከት ካለ ያለግጭት መንስኤ ሊሆን እንደሚችል ስጋታቸውን አስቀምጠዋል።[27] ቋንቋ እና ብሔርን መሰረት ያደረገው የአገራችን የፌደራሊዝም ስርአት በብሔሮች መካከል ፍትሃዊ የሆነ የስልጣን ክፍፍል፣የቋንቋ አጠቃቀም እና በድንበር አከባቢ ያሉ ውዝግቦች ጉዳይ በጥልቀት ሊታሰብበት የሚገባ የቤት ስራችን ይመስለኛል።

የፌደራሊዝም መጥፎ ጎን ህዝቦች ስለ አገራዊ ጉዳይ ከማሰብ እና በጋራ ጥቅም ላይ ከማተኮር ይልቅ በብሔራቸው እና በዘራቸው ዙሪያ እንዲያጠነጥኑ ያደርጋል። ፌደራሊዝም ጠቃሚ ቢሆንም በአግባቡ ካልተጠቀምንበት ለእርስ በርስ ጦርነት በር የሚከፍት ስርአት ነው።

### 2.4.4. አፍሪካ በመጽሐፍ ቅዱስ መነጽር

ገና ከዘፍጥረት የተጠቀሰችው አህጉራችን እስከ ዛሬ ድረስ ለክርስትና መስፋፋት ጉልህ ሚና እየተጫወተች ትገኛለች።

*"የሁለተኛውም ወንዝ ስም ግዮን ነው እርሱም የኢትዮጵያን ምድር ሁሉ ይከብባል።" ዘፍ 2፡13*

ከሁሉ በላይ ይህች አህጉር እግዚአብሔር ለብዙ ነገር ተጠቅሞባታል። እስራኤላውያን የተባዙት በአህጉራችን ውስጥ ነበር።

*"የእስራኤልም ልጆች አፈሩ፥ እጅግም በዙ፥ ተባዙም፥ እጅግም ጸኑ ምድሪቱም በእነርሱ ሞላች።"ዘጸ 1፡7*

ኢየሱስም ከሄሮድስ ቁጣ የሸሸው ወዲዚሁ አህጉር ነበር።

[26]. Ibd 65
[27] . Ibd 65

*"እነርሱም ከሄዱ በኋላ እነሆ፥ የጌታ መልአክ በሕልም ለዮሴፍ ታይቶ። ሄሮድስ ሕጻኑን ሊገድለው ይፈልገዋልና ተነሣ፥ ሕጻኑንና እናቱንም ይዘህ ወደ ግብጽ ሽሽ፥ እስክነግርህም ድረስ በዚያ ተቀመጥ አለው።" ማቴ 2፡13*

ኢየሱስ ወደ ጎልጎታ ሲሄድ መስቀሉን የተሸከመው የቀሬና ሰው ነበር። ቀሬና በአሁኗ ሊብያ ውስጥ የምትገኝ ሲሆን በእስልምና ከመጥለቅለቋ በፊት የክርስቲያን አገር ነበረች።

*"ሲወጡም ስምዖን የተባለው የቀሬናን ሰው አገኙ፤ እርሱንም መስቀሉን ይሸከም ዘንድ አስገደዱት።" ማቴ 27፡32*

በበዓለ ሃምሳ ቀን የጴጥሮስን ስብከት ሰምተው ኢየሱሰስ ክርስቶስን የማመን እድል አግኝታ ነበር።

*"በፊርግያ፣ በግብጽ፣ በቀረና አጠገብ ባሉት በሊቢያ አዉራጃዎች የምንኖር..." ሐዋ 2፡10*

የቤተክርስቲያን ትልልቅ አባቶች እነ ቅሌመንጦስ፣ አውግስቲን ከዚሁ አህጉር የተገኙ ነበሩ።

አፍሪካ ከእስያ እና ከአውሮፓ ጋር በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የተጠቀሰች እግዚአብሔር አላማውን ለማከናወን የተጠቀመባት አህጉር ነች። በዚህ በመጨረሻ ሰዓት ለዓለም ሁሉ በረከት የሆኑ የወንጌል አርበኞች ከዚህ አህጉር በመውጣት ላይ ይገኛሉ።

# ምዕራፍ ሦስት

## በኢትዮጵያ ላይ የወደቀው ጽልመት

*"ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች አፍሪካም ትከተላለች"*
ኩዋሜ ኑኩሩማ

### 3.1 . ለመሆኑ ኢትዮጵያ የማን ናት?

ለመሆኑ የምንኖርባት አገር የማን ናት? በዜጎቻችን ውስጥ ስለ አገራዊ ስሜት እና ባለቤትነት የተዛባ አመለካከት ከሰፈነ ሰንበትበት ብሏል። ለዚህም ችግር የታሪክ ምሁራን ብዙ ትንታኔ እንደሚያቀርቡት አይነት የራሴን ግምት አክዬ ለማስቀመጥ አልፈልግም። ነገር ግን ይህ መሠረታዊ ጥያቄ የማያሻማ መልስ ማግኘት ያለበት ጉዳይ ስለሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥቂት ነገር በመጥቀስ መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ተቀራራቢ አቋም እንዲኖረን ለመርዳት ነው።

*"የኖኅ የልጆቹ ነገዶች እንደ ትውልዳቸው በየሕዝባቸው እነዚህ ናቸው። አሕዛብም ከጥፋት ውኃ በኋላ በምድር ላይ ከእነዚህ ተከፋፈሉ።"* ዘፍ 10፡32

በአራራት ተራራ ላይ ካረፈችው መርከብ የወጡ የኖኅ ልጆች ወደ ተለያዩ የዓለም ክፍል በመበታተን የሚኖሩትን የምድራችንን ህዝቦች አፈሩ። በምድር ላይ የሚኖሩ ህዝቦች ሁሉ ከእነዚህ የኖህ ልጆች የተገኙ በመሆናቸው በኢትዮጵያም የሚኖሩ ህዝቦች ከተለየ ፕላኔት የመጡ ሰዎች አይደሉም።

በኢትዮጵያ  ውስጥ የሚገኙ ብሔሮች፣ ጎሳዎች እና ህዝቦች በተለያዩ ጊዜ ፈልሰው የመጡ ናቸው። ስለዚህ ኢትዮጵያ  የአንድ ሰው ወይም የአንድ ብሔር አይደለችም። ነገር ግን ሁሉም ብሔሮች ብሔረሰቦች እና ህዝቦች በጋራ የፈጠሯት አገር ናት።

በዓለማችን ላይ ያሉ ሰዎች በመልካቸው እና ቁመናቸው አማካኝነት በሦስት ቦታዎች ይከፈላሉ፡፡ እነዚህም፡- ካውከሶይድ (ነጭ)፣ ኔግሮይድ (ጥቁር)፣ሞንጎሎይድ (ቢጫ) ህዝብ ናቸው፡፡[28]

ይህ እውነት ሆኖ ሳለ ቁንጽል እና የተዛባ አመለካከት ያላቸው በሌሎች ላይ የበላይነትን ለማግኘት የፈበረኩት ከንቱ ተረት ተረት እና ፍልስፍናዎች በህዝቦቿ መካከል እውነተኛ አንድነት እንዳይፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡

## ያለፉት አባቶች /መሪዎች/ ተጽዕኖ

*"ዓለማችን እየተመራች ያለችው በሞቱ ሰዎች ነው"* ዶ/ር ማይልስ ምንሮ

ማንኛውም ሰው ከሚሞት አካል እና ከማይሞት ሃሳብ ጋር ነው የሚወለደው፡፡ ሰውዬው ከሞተ ከረዥም አመታት በኋላ ሃሳቡ ህያው ሆኖ በሚቀጥለው ትውልድ ውስጥ ይተገበራል፡፡ በሃገራችን ውስጥ የነበሩ አሁን ግን በህይወት የሌሉ መሪዎች ሃሳብ በህይወት በምንኖረው እየተንጸባረቀ ነው፡፡ ከሃሳቡ አመንጪዎች ጋርመቀበር የነበረባቸው ለአገር አንድነት ጠንቅ የሆኑ አመለካከቶች አምልጠው በህያውነታቸው ከቀጠሉ በህብረታችን ላይ ክፉ ጥላ አጥልተው ይኖራሉ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ

---

[28] Early racial classification schemes were based primarily on skin color. For example, many scholars once believed all people could be classified into one of three main races: (1) Caucasoid, or "white"; (2) Negroid, or "black"; and (3) Mongoloid, or "yellow." These races corresponded roughly to the geographic areas of Europe, sub-Saharan Africa, and Asia, respectively. Microsoft ® Encarta ® 2009. © 1993-2008 Microsoft Corporation. All rights reserved.

ለህዝብ አንድነት የተከፈሉ ውድ ዋጋዎች በቀጣዩ ትውልድ ላይ መልካም ተጽዕኖን ያመጣሉ።

እነዚህ ባለፉት ዘመናት የተፈጸሙ ግፍ እና አሳዛኝ ተግባራት በአሁኑ ትውልድ አእምሮ ውስጥ መዘፈቃቸው ህሊናን እረፍት የሚነሳ ነገር ነው። የባለፉት ገዢ መደቦች ሃገሪቱን የመሩባቸው ብልሹ አሰራሮች፣ ዙፋናቸውን ለመጠበቅ ያደረጉት ዘግናኝ ወንጀሎች፣ እንደ ተቀበሩ ፈንጂዎች ባልታሰቡ ጊዜዎች በመንፈንዳት በተለያዩ ስፍራዎች ለግጭት እና ለመለያየት ምክንያት እየሆኑ ነው።

ስለ ተደረጉ ክንውኖች በኢትዮጵያ  ውስጥ የተጻፉ ታሪኮች ቡራቡሬ፣ ወጥነት እና ሚዛናዊነት የጎደለው ስለ መሆኑ ብዙዎች ይስማሙበታል። አንዳንዱን ነጮች የጻፉልን ሌላ ጊዜ ደግሞ የእኛው ምሁራን በቂ ምርምር እና ጥናት ሳያደረጉ በገዢዎች ጫና ስር በመሆን የጻፏቸው ናቸው። አንዳንዴ ደግሞ ሁሉንም የኢትዮጵያ ስፍራ ያዳረሰ ሁሉንም ብሔር እና ህዝብ ያካተተ ስላልሆነ በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት የለውም። ሆን ተብሎ አንድ ብሔር ሌላውን ለመጉዳት እውነትን በማዳፈን የሚሰሩ የፈጠራ ታሪኮች በህዝቦች መካከል ያለመተማመን እንዲሰፍን ያደርጋሉ።

እነዚህ ካለፉት ጊዜያት በተለየ መንገድ ወደዚህ ትውልድ የተሻገሩ መረጃዎች አሁን በምንኖረው ላይ ያላቸው ተጽዕኖ ቀላል አይደሉም። ስለ አንድ ብሔር ክፉ ነገር እየሰማ ያደገ ልጅ ከሌሎች ጋር ተባብሮ የመኖር እድሉ ጠባብ ነው። በቀል እና ጥላቻን ስናስተምር ያሳደግነውን ልጅ ዛሬ ሁሉም ሰው እኩል ነው ብንለው እንዴት ይቀበላል? ስለዚህ ያለፈው ታሪካችን መጥፎ ጠባሳ እያሳደረብን ስለሆነ አእምሮአችንን በሚዛናዊነት እና በመንፈስ ቅዱስ እውቀት ልንጋርደው ይገባናል።

## ምሳሌ የሆኑን መሪዎች ነበሩን?

የባለፈው ታሪካችን የተበላሸ ትውስታ እንዳለበት ሁሉ ደማቅ እና አኩሪ ስራዎች የነበሩበት መሆኑ ግልጽ ነው። ዛሬ ላለንበት ደረጃ ያበቁን ለአገር አንድነት እና እድገት የተሰው አባቶች ነበሩን። በተለይ ሉአላዊነታችንን እና ነጻነታችንን ከወራሪ ኃይል ለመመከት በነገድ እና በጎሳ ሳይነጣጠሉ

አብረው የተዋጉ አርበኞች የምንጊዜም የአገራችን የአንድነት ምልክት ናቸው፡፡ እነዚህን በአንድነት ያሳለፍናቸውን ተጋብተን እና ተዋልደን የኖርንባቸውን ወርቃማ አመታት አመድ ማልበስ ለዘረኝነት መስፋፋት ምክንያት ናቸው፡፡ ኢትዮጵያን የመሩ ነገስታት የሚታወሱባቸው የራሳቸው መጥፎ እና መልካም ምግባሮች አሏቸው፡፡ መጥፎውን ሳይሆን በመልካሙ ላይ ማተኮር ለአገር የሚበጅ ስለሆነ ያንን ማበረታታት ጠቃሚ ነው፡፡

የቀደሙ ነገስታትን ስናስታውሳቸው እንደ ዜጋ አልፎም እንደ ክርስቲያንም ትልቅ ጥንቃቄና ሚዛናዊነት መደረግ አለበት፡፡ ፈርለቀን እንዳንሄድ የሚከተሉትን መርሆች መከተል ጠቃሚ ይመስለኛል፡፡

**ተገቢ የሆነ የታሪክ አያያዝ ብንከተል፡-** ታሪክ ያለፈ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን ድርጊቱ ቢያልፍም ትውስታው፣ እውቀቱ እና ሀሳቡ ስላለ የመደገም እድሉ ሰፊ ነው፡፡ ስለዚህ ቆም ብለን እናስተውል፡፡ የትኛው ታሪክ ይደገም ከየትኛው ደግሞ ተምረን ላለመድገም እንወስን፡፡ ለሚቀጥለው ትውልድ በምን መንገድ እናስተላልፍ የሚሉትን ነጥቦች በጥልቀት ልናጤን ይገባናል፡፡

**ወደ ፊት ማየት፡-** የወደፊት የእድገት ተስፋችን የሚፈነጥቀው ህያዋን ተባብረን በአንድነት ስንነሳ  እንጂ ያለፈውን የተበላሸ ታሪክ እንደ መልካም ትውስታ ስንቃኘው አይደለም፡፡ እግዚአብሔር ምድራችንን የሚቀይረው በህያዋን እንጂ አሁን በሕይወት በሌሉ ሰዎች አይደለምና የጦርነት እና የመከፋፈልን ሃሳብ ቀብረን ውብ እና ደማቅ ታሪኮችን እያሰብን መሄዱ ብቻ ይበጃል፡፡

የኢትዮጵያን ልማት እና ሁለንተናዊ ብልጽግና በፍጥነት ለማስኬድ ካለፈው ዘመን ተገቢ ትምህርት ቀስመን ወደ ፊት እንራመድ፡፡ ይህ ካልሆነ በአንድ በኩል በቂም እና በበቀል ተጠፍንገን አሁን መሠራት ያለበትን ሳንሰራ በሌላ ጎን ደግሞ የሞቱ ሰዎች ትዝታ ነግሶብን ብሶተኛ ሆነን ከጉስቁልና ጋር መኖር ብቸኛው አማራጫችን ይሆናል፡፡

## 3.2. የኢትዮጵያ ብሔሮች ንክሻ!

*“ትክረታችንን ፍለጋ የሚጮኽ ብዙ ኢፍትሓዊነትና ሥቃይ አለ የራብ፣የዘረኝነት እና የፖለቲካ ሥቃይ ሰለባዎች ።” ኤሊ ዊዝል*

ለመጣላት የመጀመርያው ቅድመ ሁኔታ መቀራረብ ነው። አብሮ የማይኖር ሊጣላ አይችልምና። አዲስ አበባ የሚኖረው አቶ ታደሰ በአውስትራሊያ ካለው ጆን ጋር የሚጣሉበት ምንም አይነት ምክንያት የለውም። ሊጋጭ የሚችለው አጠገቡ ካለው ዴንታሞ ጋር ነው። ለመነካከሱም መቀራረቡ የመጀመሪያ እርምጃ ነው። መቀራረቡ ካለ መሳሳም ሲቻል መቧቀሱ ነው መጥፎው።

አገራችን ከ85 በላይ የሚሆኑ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ህዝቦች የሚኖሩባት ምድር ነች። ይህ ደግሞ እንደ ተአምር የሚታይ ነገር አይደለም። ለምሳሌ ህንድ 2332፣ ቻይና 499፣ፓኪስታን 401፣ባንግላዴሽ 370 እንዲሁም ኔፓል ከ315 በላይ የሆኑ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የሚኖሩባቸው አገራት ናቸው።[29]

በእያንዳንዱ አገራት ውስጥ ያለ እያንዳንዱ ብሔር የራሱ የሆነ ልዩ መገላጫዎች አሉት። እነዚህም ቋንቋ፣ባህል፣ታሪክ እና የመሳሰሉት ናቸው። በሁሉም ክልሎች ውስጥ የተለያዩ የተፈጥሮ ሃብቶች እና ጠቃሚ እሴቶች ይገኛሉ። ይህ አብሮ ለማደግ ተደጋግፎ ለመኖር ጥሩ አጋጣሚ ነበር። መቀራረብን ለመልካም ከመጠቀም ይልቅ መባላትን መረጥን እንጂ! አብረን ያሳለፍናቸውን ጥሩ ዘመናት የተጋፈጥናቸውን የጋራ ጠላቶቻችንን ዘንግተን እርስ በርስ ጠላቶች ሆንን። ይህ ነውር በቅዱሳን መካከል ተንሰራፍቶ መገኘቱ ደግሞ ከምንም በላይ ችግሩን አሳሳቢ ያደርገዋል።

---

[29] Ralph Winter and Steven C. Hawthorne (2009). Perspectives on World Christian Movement. Pp 240

የኢትዮጵያን ብሔሮች የሚያናክሱ መንስኤዎች የድንበር ጉዳይ፣ የፖለቲካ አመለካከት፣ ኢፍትሃዊ የሆነ የሃብት ክፍፍል እና ባለቤትነት፣ የስልጣን ሽሚያ እና የመሳሰሉት ነጥቦች እንደ ዋና ምክንያቶች ሊወሰዱ ይችላሉ።

ምንም እንኳ ሁሉም ብሔሮች እኩል የሆነ የህዝብ ብዛት፣ የፖለቲካ ተሳትፎ እንደሌላቸው ቢታወቅም ለአገራችን ሰላም መስፈን ትልቅ ኃላፊነት እና ግዴታ ግን አለባቸው። ሁሉም ብሔሮች የግላቸውን ፍላጎት መስዋዕት ማድረግ ካልቻሉ በአንድነት ብቻ የሚገኘው ልማት የማይደረስበት የህልም እንጀራ ሆኖ ይቀራል። ተቀራርቦ ከመነጋገር ይልቅ በግል ፍላጎት ላይ ብቻ ያጠነጠነ አጀንዳ ስናራግብ በእጃችን ያሉት ወርቃማ እድሎች እንዳያመልጡን እሰጋለሁ።

አሁን በቅርብ ጊዜ እንኳን በ2006 በባህርዳር ከተማ በተካሄደው የመላው ኢትዮጵያ ጨዋታዎች ላይ የታየው በአማራ እና ኦሮሞ ብሔሮች መካከል የተቀሰቀሰው ግጭት አስፈሪ እና አሳፋሪ ክስተቶችን ጭሮ አልፎአል። ይህንን ተከትሎ በአምቦ፣ በወለጋ፣ በመቱ በባሌ እና በአንዳንድ ቦታዎች በሁለቱ ብሔሮች መካከል ግጭቶች ተነስተዋል። እነዚህ ግጭቶች በእንጭጩ ካልተቀጩ ነገ አስከፊ የሆነ የእርስ በርስ ጦርነቶችን ማስከተላቸው አይቀሬ ነው።

እነዚህን ስህተቶች ለማስተካከል የአገር ሽማግሌዎች፣ ቤተክርስቲያን እና የመንግስት አካላት ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። ዶ/ር መረራ ጉዲና በዚህ ጉዳይ ላይ "አንድ እርምጃ ወደፊት ለመሄድ አብዛኛዎቹ የሁለቱ ብሔር ልህቃን እስከ አሁን ስንገፋበት አንዱ ሌላውን ከማይሰማበት የደንቆሮዎች ውይይት (Dialogue of a deaf) ጨክኖ መውጣት እጅግ ወሳኝ ጉዳይ ነው ብለዋል።[30]

በሁለቱ ብሔሮች መካከል እየታየ ላለው ያለ መግባባት እንደመነሻነት የሚጠቀሰው የሁለቱ ብሔሮች ፖለቲከኞች የያዙት አጀንዳ የተለያየ መሆኑ ነው። የቀየሱት የግል ፕሮግራም የተለያየ ቢሆንም አብሮ መሥራት አንድ መሆን ባለባቸው ጉዳዮች ላይ መስማማት ጠቃሚ ነው።

---

[30] ዳንኤል ተፈራ ዳንዲ የነጋሶ መንገድ 2003 ገጽ. 262

ንትርክ እና ያለመግባባትን እየዘራን የምንሄድ ከሆነ ጉስቁልና እና ደም መፋሰስን ማጨዳችን አይቀሬ ነው። ከዚህ ፕሮጀክት ዋና ተጠቃሚው ደግሞ ዲያብሎስ ነው። መለያየትንእና በቀልን የምናስብ ከሆነ የሰይጣን አገልጋይ መሆናችን አይደለምን?

በአገራችን ካሉ ከ85ቱ ብሔሮች አማራና ኦሮሞ የበለጠ የህዝብ ብዛት ያላቸው እንደ መሆናቸው ለሌሎች አርአያ መሆን ይጠበቅባቸዋል። ያረጁ እና ለዚህ ትውልድ የማይመጥኑ የትዕቢት ሃሳቦች መቀበር አለባቸው። ፍቅር እና መቀራረብ ብቻውን አዋጪ መንገድ ነውና።

የእግዚአብሔር አገልጋዮች እና የእርቅ አምባሳደሮች የሆንን ክርስቲያኖች ዘረኝነትን ነቅተን መዋጋት አለብን። ተቀራርቦ መነጋገርመወቃቀስ ተገቢ ነው። የቤተክርስቲያን ድምጽ መሆን ያለበት አንድ ነው እርሱም እርቅ! ክርስቲያኖች በልባችን ውስጥ ምናልባት የተተከለውን የበቀል እና የጥላቻ ዛፍ መንቀል፣ እራሳችንን ከዚህ ችግር ማጽዳት፤አልፎም የምንኖርበትን ማህበረሰብ የማስተማር ግዴታ አለብን። በእርቅ እና መቻቻል የምንኖር ከሆነ አገራችን ብዙዎች በፍቅር እጦት፣በፍትህ-አልበኝነት እና በረሀብ ግርፋት ተጠብሰው የሚሰደዱባት ሳትሆን እንደ ኤዴን ገነት ተዘልለው የሚኖሩባት ትሆናለች።

## 3.3. የትግል አቅጣጫችን

አማኞች መታገል አለባቸው ወይ? አዎ! ያውም ከጨለማው ገዢ ጋር። ዘረኝነት እና ጥላቻን በመዝራት የብዙ ንጹሃንን ደም መጠጣት ከለመደው አውሬ ጋር።

*“የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ። መጋደላችን ከደምና ከሥጋ ጋር አይደለምና፥ ከአለቆችና ከሥልጣናት ጋር ከዚህም ከጨለማ ዓለም ገዦች ጋር በሰማያዊም ስፍራ ካለ ከክፋት መንፈሳውያን ሠራዊት ጋር ነው እንጂ።”* ኤፌ 6፡11-12

*“የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፥”* 2ቆሮ 10፡5

## አመጽን እና ሰላማዊ ተቃውሞን እንለይ

በየትኛውም አለም ማህበራዊ ለውጥ የሚመጣው በሰላማዊ ትግል ወይንም በአመጽ ነው፡፡ ክርስቲያኖች በአመጽ ውስጥ መሳተፋቸው ተገቢ ነው ወይንስ አይደለም? ለሚለው ጥያቄ መሳተፍ ተገቢ ነው የሚሉ አንዳንድ ሰዎች አሉ፡፡ በአብዛኛው ግን በአመጽ ውስጥ መሳተፍ ከእኛ አይጠበቅም በማለት ይሞግታሉ፡፡ ሰላማዊ ትግል ከጦርነት የተሻለ ነው በማለት ይከራከራሉ፡፡ በተለይ ማርቲን ሉተር ኪንግ “አመጽ ሌላ አመጽ እንዲመጣ ከማድረግ ውጪ ፋይዳ የለውም፡፡ ጦርነት ጦርነትን ይወልዳል፡፡ አመጽን በአመጽ የምንመልስ ከሆነ ክፋትን በሌላ መስታወት እንደማንጸባረቅ ነው፡፡” ብለዋል፡፡ ምክንያቱም ሰይፍ የእግዚአብሔርን አላማ አይፈጽምምና፡፡

*“በዚያን ጊዜ ኢየሱስ እንዲህ አለው፦ ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ፡፡” ማቴ* 26፡52

በአመጽ ውስጥ መሳተፍ የለብንም የሚለውመርህ ጌታ ኢየሱስን እንደ አዳኙ ለተቀበለ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ ህያው፣ የሚሰራ የመለኮት ቃል ለሚከተል ሰው የተሰጠ መመርያ ነው፡፡ እኛ ለአመጽ አልተጠራንም ማንንም የመጥላት መብትም የለንም፡፡ ከታላቁ የፍቅር ታጋይ ከጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያየነው እና የሰማነው አመጽ እና ነፍስ መግደልን አይደለም፡፡ በእርግጥ ከእርሱ የተወለደ ሰዎችን መጥላት አይችልም፡፡ እኛ ከፍቅር የተወለድን የፍቅር ልጆች ነን፡፡ የምንመራበት መመሪያ ወንጌል የፍቅር መልዕክት የያዘ እንጂ መለያየትን የሚናገር አይደለም፡፡

የትግል አቅጣጫችን እንደ አለማዊያን ለስልጣን ሽሚያ እና ለጥቅም አይደለም፡፡ የሰው ልጅ ትልቁ ችግሩ ከፖለቲካ ጥያቄ ይልቅ የኃጢአት ባርነት ነው፡፡ ከጌታ ጋር ያልታረቁ ይህ ምን ያህል ከባድ እንደ ሆነ

*መገንዘብ እስከማይችሉ ድረስ ታውረዋል፡፡ ሰው ከኃጢአት ባርነት ነጻ ከሆነ የሀገራችን ፖለቲካ፣ኢኮኖሚ እየተሻሻለ መሄዱ አይቀሬ ነው፡፡*

ክርስቲያኖች ባሉበት ቦታ ሁሉ የጌታን ባሕርይ በማንጸባረቅ ለፍትህ እና እውነት መታገል አለባቸው፡፡ የተጠራነው ከክፉት እና አመጽ ጋር እያመቻመችን እንድንኖር አይደለም፡፡ ፍቅር በባሕሪው ከአመጽ ጋር የሚቆም ሳይሆን በጽድቅ ደስ የሚሰኝ ህያው ተግባር ነው፡፡ ፍቅር "*ከእውነት ጋር ደስ ይለዋል እንጂ ስለ ዓመፃ ደስ አይለውም፤*" 1ቆሮ 13:6፡፡ በምድር ላይ የመኖራችን አንዱ አላማችን የጨለማን ስራ መግለጥ ነው፡፡

*"ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፥ ይልቁን ግለጡት እንጂ፥"* ኤፌ 5:11፡፡

ፍቅር ማለት ግን ቸልተኝነት አሊያም ዳተኝነት ማለት አይደለም፡፡ በአገራዊ ጉዳዮች ላይ በንቃት መሳተፍ ይኖርብናል፡፡ የጨለማን ስራ በቃሉ ብርሃን እያጋለጥን ወደ ብርሃን ማምጣት አለብን፡፡ ለለውጥ እስከ ተፈለግን ድረስ ነገሮችን ለማሻሻል ጠመንጃ ሳይሆን ፍቅርን መያዝ አለብን፡፡ ደምን በማፍሰስ ሳይሆን ደምን በመለገስ ህይወትን መታደግ ከክርስቶስ የተማርነው ተግባር ነው፡፡ ይህ ነው ሰላማዊ ትግል ማለት፡፡

እግዚአብሔር ከሌሎች በተለየ በፍቅር መኖር እንዳለብን መክሮናል፡፡

*"ባልንጀራህን ውደድ ጠላትህንም ጥላ እንደተባለ ሰምታችኋል። እኔ ግን እላችኋለሁ፥ በሰማያት ላለ አባታችሁ ልጆች ትሆኑ ዘንድ ጠላቶቻችሁን ውደዱ፥ የሚረግሙአችሁንም መርቁ፥ ለሚጠሉአችሁም መልካምአድርጉ፥ ስለሚያሳድዱአችሁም ጸልዩ፤ እርሱ በክፉዎችና በበጎዎች ላይ ፀሐይን ያወጣልና፥ በጻድቃንና በኃጢአተኞችም ላይ ዝናቡን ያዘንባልና። የሚወዱአችሁን ብትወዱ ምን ዋጋ አላችሁ? ቀራጮችስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? ወንድሞቻችሁንም ብቻ እጅ ብትነሡ ምን ብልጫ ታደርጋላችሁ? አሕዛብስ ያንኑ ያደርጉ የለምን? እንግዲህ የሰማዩ አባታችሁ ፍጹም እንደ ሆነ እናንተ ፍጹማንሁኑ።"* ማቴ 5:43-48

ማርቲን ሉተር "ጥላቻ ጥላቻን ማስወገድ አይችልም ጥላቻን ያበዛል እንጂ። ጨለማ ጨላማን ማስወገድ አይችልም ያንን የሚያደርግ ብርሃን ብቻ ነው።" ይላሉ።

በዚህ ወቅት የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታ ስንፈትሽ ከሞላ ጎደል ለዲሞክራሲያዊ ትግል ክፍት ነው። በነጻነት በሰላማዊ መንገድ ክርስቶስን መስበክ እንችላለን። እነዚህን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀም ትልልቅ ስራዎችን መስራት ይቻላል። ይህንን የማንጠቀም ከሆነ በጭቅጭቅ እና ንትርክ ዘመናችንን ካሳለፍነው በእርግጠኝነት ትልቅ ኪሳራ ከፊታችን ተደቅኖ ይጠብቀናል።

የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ቢል ክሊንተን አንድን አገር ለመገንባት እና ለማሳደግ ወንጀልን ማስወገድ ተገቢ እንደሆነ ያምናሉ። "ስለ ወንጀል አንድ ነገር ካላደረግን ይህችን አገር ለመጠገን ምንም ነገር ማድረግ አንችልም።" ይላሉ። ፍትህ አገርን ለመገንባት ትልቅ ግብዓት ነው። አንድነት እና በጋራ መስራት ለውጥን ለማምጣት ብቸኛ አማራጮች ናቸው።

የፖለቲካ ትግል አቅጣጫችን መሆን ያለበት በአመጽ ሳይሆን በሰላም ነው። መንግስትን የሚያስቀምጥ እግዚአብሔር ነውና።

*"ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፤ ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። ስለዚህ ስለ ቍጣው ብቻ አይደለም ነገር ግን ስለ ሕሊና ደግሞ መገዛትግድ ነው።" ሮሜ 13፡1-5*

መንግስትን ማቆየት ወይንም መጣል የክርስቲያኖች ዋነኛ አጀንዳ አይደለም፡፡ እንዲያውም እንዲሻሻል መጸለይ አለብን፡፡ ምክንያቱም አንዱ መሪ ሲነሳ መልአክ ሳይሆን ሌላ የራሱ ድካም ያለበት ሰው ስለሆነ የሚተካው አሁን በስፍራው ላይ እግዚአብሔር እንዲመራ የፈቀደለትን መሪ ለፍትህ እና ለእኩልነት የሚሰራ እንዲሆን መጸለይ አለብን፡፡

*"እንግዲህ እግዚአብሔርን በመምሰልና በጭምትነት ሁሉ ጸጥና ዝግ ብለን እንድንኖር፥ ልመናና ጸሎት ምልጃም ምስጋናም ስለ ሰዎች ሁሉ ስለ ነገሥታትና ስለ መኳንንትም ሁሉ እንዲደረጉ ከሁሉ በፊት እመክራለሁ።"* 1ጢሞ 2፡1

የእኛ ጥያቄ አሁን ያለው መንግስት በእውነት፣ በጽድቅ፣ ለህዝብ ጥቅም እየሰራ ነው ወይ የሚል መሆን አለበት፡፡ አንድ ነገር ልብ እንበል የእኛ አትኩሮት የሰው መለዋወጥ ላይ ብቻ ሳይሆን በአሰራር ላይ መሰረታዊ ለውጥ እንዲመጣ ግፊት በማሳደር ላይ መሆን አለበት፡፡ በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ከህግ ውጪ የሚሰራ ከሆነ ለህዝቡ የገባውን ቃል የማይጠብቅ ከሆነ በእርግጥ ፍትህ እና ቅን ፍርድን የሚያዛባ ነውና የእግዚአብሔር ቁጣ በራሱ ላይ እየጠራ ነው፡፡ ይህ ከሆነ እንደ ክርስቲያኖች በመጀመሪያም እውነትን በፍቅር መናገር አለብን፡፡ ልክ እንደ መጥመቁ ዮሐንስ ፍትህ ሲጣመም መናገር ማለት ነዉ፡፡ የእኛ ትኩረት በሚሰጠን ምላሽ ላይ ሳይሆን ለእውነት መኖር ላይ ነው፡፡ ምላሹ የምስጋና የምስክር ወረቀት ሊሆን ይችላል ወይንም ወህኒ ቤት መጣል ሊሆን ይችላል፡፡

*"የዚያን ጊዜም ንጉሡ አዘዘ፥ ዳንኤልንም አምጥተው በአንበሶች ጕድጓድ ጣሉት ንጉሡም ተናገረ ዳንኤልንም። ሁልጊዜ የምታመልከው አምላክህ እርሱ ያድንህ አለው።"* ዳን 6፡16

በመቀጠል መጸለይ ነው፡፡ ስልጣን እና ኃይል የእግዚአብሔር ነው፡፡ ጌታ አፋጣኝ ምላሽ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ሊዘገይም ይችላል፡፡

*"ሕዝቡም የእግዚአብሔር ድምፅ ነው የሰውም አይደለም ብለው ጮኹ። ለእግዚአብሔርም ክብር ስላልሰጠ ያን ጊዜ የጌታ መልአክ መታው በትልም ተበልቶ ሞተ።"* ሐዋ 12፡22-23

*"በዚያም ሰዓት ነገሩ በናቡከደነፆር ላይ ደረሰ ጠጕሩም እንደ ንስር፥ ጥፍሩም እንደ ወፎች እስኪረዝም ድረስ ከሰዎች ተለይቶ ተሰደደ፥ እንደ በሬም ሣር በላ፥ አካሉም በሰማይ ጠል ረሰረሰ።"* ዳን 4፡33

ስለዚህ ቅዱሳን በተቀመጥንበት ቦታ ላይ ሆነን ለፍትህ መኖርን መለማመድ አለብን፡፡ ለስልጣን መሻማት የለብንም ነገር ግን ባለንበት ቦታ ታማኝ እንሁን የጌታ ባህርይ በእኛ ላይ ይታይ፡፡

## 3.4. ልማት፣ ልማት፣ ልማት

*"እንዲህም ይሆናል የአምላክህን የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ፥ ዛሬም ያዘዝሁህን ትእዛዙን ሁሉ ብታደርግ ብትጠብቅም አምላክህ እግዚአብሔር ከምድር አሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ ያደርግሃል። የአምላክህንም የእግዚአብሔርን ቃል ብትሰማ እነዚህ በረከቶች ሁሉ ይመጡልሃል ያገኙህማል። አንተ በከተማ ቡሩክ ትሆናለህ፥ በእርሻም ቡሩክ ትሆናለህ።"* ዘዳ 28፡1-3

*"ሁሉን አብዝቶ ስለ ሰጠህ አምላክህን እግዚአብሔርን በፍሥሐና በሐሤት አላመለክህምና በራብና በጥማት በዕራቁትነትም ሁሉንም በማጣት እግዚአብሔር ለሚልክብህ ለጠላቶችህ ትገዛለህ እስኪያጠፉህም ድረስ በአንገትህ ላይ የብረት ቀንበር ይጭናል።"* ዘዳ 28፡47-48

ድሃ መሆንን ወዶና ፈልጎ ያገኘው ሰው የለም፡፡ የተከተሉት የህይወት መርህ ውጤት ስለሆነባቸው ብቻ ይጋፈጡታል እንጂ፡፡ በአገር ደረጃም ስናይ እንደ ምኞታችን ከአሜሪካ እና ጀርመን ጎን በተሰለፍን ነበር፡፡ ልማትና የኢኮኖሚ እድገት በምኞት የሚደረስባቸው ሳይሆኑ የሚጠይቁትን ውድ መስዋእትነት በመክፈል የሚመጡ ናቸው፡፡ ከእነዚያው አንዱ እና ዋነኛው ዋጋ አንድነት ነው፡፡ በተናጠል ከሚደረጉ በጥላቻ ከተቃኘ ጥረት ወጥተን እንደ አገር በጋራ ማሰብ መቻል አለብን፡፡

መረዳዳት እና መተባበር ለአገር  እድገት ግብአት ነው ካልን አሁን ላለንበት ጉስቁልና ደግሞ መከፋፈል እና ዘረኝነት ምክንያት የማይሆንበት ምክንያት የለም፡፡

ዓለማችን በትዕቢት እና እኔነት ተከፋፍላ ጎራ በመፍጠር ስትዋጋ በነበረችበት የአንደኛው እና ሁለተኛው የዓለም የጦርነቶች ጊዜ ብቻ ከ100 ቢሊየን ዶላር በላይ ኪሳራ ሲደርስባት ከሰባ ሚሊየን በላይ የሚሆኑ ሰዎች ተገድለዋል፡፡ የመከፋፈል ትርፉ ሞት እና የኢኮኖሚ ድቀት ብቻ ነው፡፡

የአንድነት እና የመተባበር መንፈስ ባልነገሰበት አገር  ልማት የማይታሰብ ነገር ነው፡፡ ለአንድ አገር አኩራፊ እና የተጣላ ህዝብ ይዞ መኖር ጫጩት የሌለበትን እንቁላል ታቅፋ እንደምትኖር ዶሮ መሆን ነው፡፡ ለማን መኖር እንዳለበት ያልገባው ለአገር እና ህዝብ ጥቅም ቅድሚያ የማይሰጥ የአገር እና የህዝብ ፍቅር ልቡን ያልነካው ዜጋ የልማት ኃይል ሳይሆን የጥፋት መሳሪያ ነው፡፡ በተለይ እንደዚህ አይነት ዜጎች በስልጣን ቦታ ላይ ከተገኙ በቃ ለዚያች አገር  ወዮላት፡፡ ያቺን አገር  አንበጣ የወረደባት ዛፍ አስመስለው ነው የሚግጧት፡፡ በአገራችንም አንዳንድ ቦታዎች ላይ እንደታየው በሞተ እንስሳ ላይ የወረዱ አሞራዎችን ይመስል የከተማን መሬት የሚቀራመቱ ገዢዎች በገሃድ ተስተውለዋል፡፡ ለኢትዮጵያ  አገር ድህነትን ይዘን ከመኖር የከበደን ጉዳይ እለት እለት የህዝቡን ደም የሚመጡ ቫምፓዬሮች ተሸክመን መጓዝ ነው፡፡ ትልቁ ሃፍረታችንም ያሳደጋቸውን፣ ያስተማራቸውን እና ያስተዳድሩኛል ብሎ የሾማቸውን ህዝብ በጭካኔ የሚግጡ አንዳንድ መሪዎች  ይዘን መኖራችን ነው፡፡

ልማት ሀብትን ማካበት ሳይሆን ስለ ልማት ትክክለኛ አመለካከትን ከመያዝ የሚጀምር ጉዳይ ነው፡፡ አገር  እና ህዝብን ከመውደድ እና ከማክበር መጀመር አለበት፡፡ በተገኘ አጋጣሚ ህዝብን እና መንግስትን የሚሰርቅ ሌባ ካለ የድህነት ምንጭ እርሱ ነው፡፡ አገርን መውደድ ደግሞ ሰውን መውደድ ነው፡፡ ሰውን ስንል በአምላክ አምሳል በመሠራቱ ብቻ ወገኑን ጉሳውን ግምት ውስጥ ሳናስገባ መቀበል እና መርዳት ማለት ነው፡፡ ሌላው የልማት ነቀርሳ አሁን አሁን በመንግስትም ሆነ በተለያዩ ቢሮዎች ለመቀጠር እና አንድ ጉዳይን ለማስፈጸም ዘመድ አለህ ወይም

የለህም ነው እንጂ ችሎታ ግምት ውስጥ ይገባል የሚለው ሃሳብ እየጠፋ ነው፡፡ ልክ ባልሆነ አሰራር ዘመዶቻችን ካልሆነም ከብሔራችን የሆነውን ሰው መርዳት በመርህ ደረጃ እንደ ብልሹ አሰራር የሚፈረጅ በተግባር ደግሞ የግድ መፈጸም አለበት የተባለ ይመስል በትጋት እየተተገበረ ያለ አውዳሚ አካሄድ ነው፡፡ አገራችን ለምን አላደገችም የሚለውን ጥያቄ ካነሳን መልሶቻችን በጣም ብዙ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ በዋናነት ግን እንደ ጥላቻ፣ ቂም፣ መከፋፈል አገርን የኋልዮሽ የሚያስኬድ ነቀርሳ የለም፡፡

ኢትዮጵያ እንደ ማንኛውም የዓለማችን አገራት አንዲት ሉአላዊት አገር ነች፡፡ በዚህች አገር ለመወለዳችን ምርጫው የእኛ ሳይሆን የፈጣሪ ስለ ሆነ በደስታ ልንቀበል ይገባናል፡፡ የእኛ ሥራ ስላልሆነ እግዚአብሔር ልክ ነው ብለን በጸጋ መቀበል አለብን፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር ልብ እንበል ጌታ ነገሮችን ሲያደርግ በአላማ እንጂ ድንገት ስላልሆነ በኢትዮጵያ ውስጥ የተወለድነው ለሥራ እንጂ በዘፈቀደ አይደለም፡፡ ይህንን የእግዚአብሔር አላማ በውል ከተረዳን ህዝባችንን በታማኝነት እናገለግላለን፡፡ ብዙዎች ያሉትን ተግዳሮቶች በአንድነት ከመጋፈጥ ይልቅ ፍርጥጫን መርጠናል፡፡ ግድ የለም እኛ በእውነት እና በጽድቅ እንስራ እንጂ የማይለወጥ ነገር የለም፡፡

ከምን ጊዜውም የበለጠ የመተባበር ስሜት መፍጠር አለብን፡፡ የአማራ ልማት ማህበር መፈክር ይመቸኛል "አንድ ሆነን እንደ ሺ፤ሺ ሆነን እንደ አንድ" የሚሉት፡፡ አብረን ቆርሰን መብላት ልምዳችን እና የምንታወቅበት ባህላችን እንደሆነ ሁሉ አብረን መስራትንም እንልመድ፡፡ ልማት የመተባበር ውጤት ነው፡፡ አንድ ክልል ላይ ያለውን ሀብት ከሌላ ክልል ጋር እንካፈል፡፡ በንግድ እንተሳሰር፡፡ ልምዶቻችንን ተለዋውጠን አብረን እንስራ፡፡ ይህን ካደረግን የሰማይ ያክል የራቀንን እድገት በመዳፋችን ላይ እናስገባለን፡፡

## በእጃችን ላይ ያለው ወርቃማው እድል

አሁን ያለንበት ወቅት አንድነት ለመፍጠር፣ ልማቱን ለማቀጣጠል፣ በዲሞክራሲያዊ መንገድ ለሰላም ለመታገል በሮቹ ክፍት ናቸው፡፡ በእጃችን ላይ ያሉትን ጥሩ አጋጣሚዎች እያመከንን የተሻለ ነገርን ስንጠብቅ በከንቱ

ዘመናችንን እንዳንጨርስ፡፡ የኢትዮጵያ ሕገ-መንግስት የብሔር ብሔረሰቦችን እኩልነት እስረግጦ አስቀምጧል፡፡ በተለይ አንቀጽ 39 ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ላይ፡፡ ስለዚህ የትኛውም ብሔር የበላይ አይደለም የትኛውም ደግሞ የበታች አይደለም ሁሉም እኩል መብት አላቸው፡፡

በግፍ እና ክፋት በተሞላች ምድር ላይ ተወልደን የጥላቻ ታሪኮች ሲተረኩልን አድገን በቀልን እያሰብን አንሞትም፡፡ እግዚአብሔር ለኢትዮጵያ የተሻለ በጎ ዓላማ አለው፡፡ ይህንን የተሻለ የእግዚአብሔርን ዓላማ ለመፈጸም ጌታ እንዲጠቀምብን እራሳችንን የተሻለ እቃ አድርገን ልናቀርብ ይገባናል፡፡

ያደገች ኢትዮጵያን ለመፍጠር ህብረት እና ፍቅር ትልቅ ግብአቶች ናቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ የሚያስፈልገውን ዋጋ ለመክፈል ዝግጁ መሆን አለብን፡፡ በግፍ እና በጥላቻ የተሞላ ታሪካችንን በፍቅር እና ትብብር አስውበን መጠገን አለብን፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የዘረኝነት አስከፊ አደጋዎች

*"ዘረኝነት የአገራችንን እድገት የሚገታ ካንሰር ነው"* ዳንኤል አራፕ ሞይ የቀድሞ የኬንያ ፕሬዝደንት

የሩዋንዳ ሊቀ ጳጳስ ጆን ሩሴና በሁቱ እና ቱትሲ ጎሳዎች መካከል ተከስቶ ለነበረው ችግር ቤተክርስቲያን ተዋናይ እንደ ነበረች እንዲህ ይናገራሉ "በቤተክርስቲያን ሕንፃ ተጠልለው ለሕይወታቸው ምህረትን ሲማጠኑ ለነበሩ ምዕመናን ላይ ቡልዶዘሮች በመስደድ ሕይወታቸው በፍርስራሽ ክምር ስር እንዲቀበር ያደረጉ ቀሳውስት ታይተዋል፡፡ 'አይዟችሁ' በሚለው የማባባያ ቃል ምዕመናንን ወደ መታረጃ ስፍራ የጎተቱ አገልጋዮች በጣት የሚቆጠሩ አይደሉም፡፡ በአጠቃላይ በሩዋንዳው እልቂት ውስጥ መንፈሳዊ አባቶች እጃቸው የረዘመ የጥፋት ተዋንያን ሆነውተስተዋውለል፡፡"[31]

ባለፉት ምዕራፎች ለመቃኘት እንደ ሞከርነው ዘረኝነት ዓለም አቀፋዊ ችግር መሆኑን አይተናል፡፡ አህጉራችን እና አገራችንም የዚህ ካንሰር ሰለባ ናቸው፡፡ በተለይ 85 ብሔር ብሔረሰቦች እና ህዝቦችን ታቅፋ የምትኖር እናት አገራችን በልጆቿ መካከል ፍቅር እና መቀባበልን በማጣት እየተጎሳቆለች ትገኛለች፡፡ ዘረኝነት አስከፊ ነገር ነው፡፡ ይህም በግለሰብ፣ በቤተሰብ፣ በቤተክርስቲያን እና በአገር ግንባታ ላይ ትልቅ እንቅፋትን ያስከትላል፡፡

## 4.1. በግለሰቦች ሕይወት ላይ

*ነገር ግን በመከራው ቀን ወንድምህን ትመለከት ዘንድ፥ በጥፋታቸውም ቀን በይሁዳ ልጆች ላይ ደስ ይልህ ዘንድ፥ በጭንቀትም ቀን በትዕቢት ትናገር ዘንድ አይገባህም ነበር፡፡* አብ 1፡12

---

[31] ፀጋአብ በቀለ (2005) ባለ ራእይነት ክፍል 2 ገጽ 249

በዘረኝነት እና በጥላቻ የተሞላ ሰው መጀመሪያ የሚጎዳው እራሱ ነው። ማንኛውም ሰው በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነው። ስለዚህ መከበር አለበት የሚለው አመለካከት የተለየው ሰው ፍጻሜው መልካም አይሆንም። በዘረኝነት ውስጥ ያሉሰዎች የሚከተሉት ችግሮች ዘመናቸውን ያቆረቁዛሉ።

**ውስን እይታ ውስጥ ለመኖር ይገደዳሉ፡-** እነዚህ ሰዎች አለማቸውን የሚገነቡት በቋንቋቸው፣ በባህላቸው እና በብሔራቸው ልክ ብቻ ስለሆነ ከቀሩት ሰዎች ተገንጥለው የሚኖሩ ናቸው። ከአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ውጪ ሌላ ቋንቋ መጠቀም አይፈልጉም ቢጠቀሙም በውስንነት እና በጥላቻ ነው። ሰው እንስሳ አላምዶ አብሮ በሚኖርበት ምድር ላይ ከሰው ጋር ተስማምተው መኖር ይከብዳቸዋል። ወንጌል ለዓለም ሁሉ የሚለው በእነርሱ ዘንድ አይሰራም። በራሳቸው ብሔር ፍቅር ስለ ተነደፉ የሌሎች ብሔሮች ያለ ክርስቶስ ወደ ዘላለም ጥፋት መሄድ አይታያቸው። ምናልባትም እግዚአብሔር ለዓለም አቀፍ አገልግሎት የፈለጋቸው ሰዎች በዘረኝነት ሰንሰለት ተጠፍንገው ስለ ታሰሩ ጥሪያቸው ከመንደር ሳያልፍ ሲጨነግፍ ይታያሉ።

**በቅሌት እና ውርደት ውስጥ ለመኖር ይገደዳሉ፡-** ዘረኝነት የሚያስከብር ተግባር አይደለም። ይልቁንስ የጠባብነት እና የትንሽነት ምልክት ስለሆነ አስነዋሪ ነው። በዘራችን ለመመካት የሚያስችለን ነገር የለንም። ሰው ቢመካ እንኳ እራሱ በሰራው ተግባር መሆን አለበት። ከብሔራችን ለመወለድ ያደረግነው አንድም ጥረት የለም ማድረግም አንችልም። ምርጫችንም አይደለም ታድያ የሚያስመካን ነገር ምንድነው?

*“ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ ሥራህ ድንቅነው፥ ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች። እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፥ አካሌም በምድር ታች በተሠራ ጊዜ አጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም።”*
*መዝ* 139፡15-16

ከመወለዳችን በፊት ከእግዚአብሔር ጋር የመወያየት እድል ቢኖረን ኖሮ ቤተሰቦቻችን እና የምንወለድበትን አገር መርጠን በጠየቅነው ነበር። ይህ በጭራሽ የማይቻል ነገር ነው። ጉዳዩ በሉዓላዊው የእግዚአብሔር ምርጫ

የሚሆን ነው። የተወለድንበትን ብሔር እና አገር አልቀበልም ማለት የእግዚአብሔርን ምርጫ ማቃለላችን ነው። በሌላ በኩል ልክ እንደ አንተው ሳይመርጥ ከአንድ ብሔር የመጣን ሰው መጥላቱ ለምን አስፈለገ? ይህ ነው መሠረታዊ ችግሩ። ብዙ ሰዎች እራሳቸውን የሚያታልሉት ባለፉት ዘመናት በብሔሬ ላይ ግፍ ስለ ተፈጸመ እኔም መበቀል አለብኝ የሚል የሞኝነት ምክንያት ያቀርባሉ። ፍትህን መፈለግ ተገቢ ነገር ሆኖ ሳለ ፍትሓዊ ባልሆነ መንገድ የሚመጣ መፍትሄ አለመኖሩን ግን አያስተውሉትም። በመጀመሪያም በቀል የእግዚአብሔር ነው።

*"ክፉ እመልሳለሁ አትበል እግዚአብሔርን ተማመን፥ እርሱም ያድንሃል።"* ምሳ 20፡22

ሁለተኛ ከበቀል በፊት ሰውየውን ሳይሆን ችግሩን ለማስወገድ መሞከር ነው። በአጠቃላይ ዘረኝነት የጥላቻ ፍሬ ስለሆነ ፍጻሜው ጥፋት እንጂ መልካም ነገር አይደለም።

**የተሰጠንን ነጻነት በአግባቡ እንዳንጠቀም ያደርጋል፡-** የተሰጠን መብት ሁሉ የምንጠቀምበት አይደለም። አንዳንዶችን መስዋዕት በማድረግ ለወንጌል አገልግሎት እንጠቀምባቸዋለን እንጂ።

*"እኔ ደግሞ ብዙዎቹ ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር ሰውን ሁሉ ደስ እንደማሰኝ፥ ለአይሁድም ለግሪክም ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያንም ማሰናከያ አትሁኑ።"* 1ቆሮ 10፡32-33

የጌታ ደስታ ልጆቹ የተሰጣቸውን መብት አሚጠው ሲጠቀሙ ሳይሆን ነጻነታቸውን መስዋዕት በማድረግ ከሌሎች ጋር በፍቅር ሲኖሩ ማየት ነው። ዘረኝነት ግን መብቴን ጥቅሜን የሚል መርሆችን የሚከተል በመሆኑ ከክርስትና አስተምህሮ ጋር የሚጣረስ እኩይ ተግባር ነው።

**ልባችን የክፉ ዘር ማሳ እንዲሆን ያደርጋል፡-** ልባችን የህይወታችንን አቅጣጫ የመወሰን አቅም አለው።

*“አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ፥ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና።”* ምሳ 4፡23።

ልብ ከተበላሸ ተግባራችንም ብልሹ ይሆናል። ልባችን በመልካም ነገር የተሞላ ከሆነ ተግባራችን ጌታን ያከብራል። ጥላቻ ውስጣችንን ካጨናነቀው ግን ተግባራችን በቀልና መለየት መሆኑ አይቀሬ ነው። ዘረኝነት ጥላቻ ነው ውጤቱም ከእግዚአብሔር ተለይቶ መኖር ፍጻሜው ደግሞ ሞት ነው። ወደ አውሮፕላን ማረፍያ ሄደን መርከብ እንደማናገኝ ሁሉ ጥላቻ ቋጥረን ሰላምን አናጭድም። ዘረኝነት በልባችን ላይ እንዲነግስ ከፈቀድንለት ፍጻሜአችን የዘላለም ሞት መሆኑ አይቀሬ ነው። ኃጢአትን የምናደርገው ለጊዜውም ቢሆን ጥቅም እና ደስታን ስለማያስገኝ አይደለም። ሰይጣንም ሰዎችን የሚያታልለው ሞትን በመሸፈን እና የኃጢአትን ጥቅም በማግዘፍ ነው። ዛሬውኑ በእግዚአብሔር ቃል ልባችንን መፈተሽ አለብን።

ግለሰቦች በዘረኝነት ሲጠቁ ችግሩ ወደ ቤተክርስቲያን እና አገር የማይዛመትበት ምክንያት የለም። ስለዚህ እከሌ ሳንል እራሳችንን በእግዚአብሔር ቃል ማየት ግድ ይላል።

## 4.2. በቤተክርስቲያን ላይ የሚያመጣው እክል

የሩዋንዳው ካህን አውግስቲን ካርክዚ በ1994 እ.ኤ.አ.በነበረዉ የእርስ በእርስ ግጭት ዙርያ የቤተክርስቲያን ድርሻ ምን እንደ ነበር ተጠይቀው በሰጡት ምላሽ “እንደዚህ አይነት አስከፊ ክስተት ብዙ ክርስቲያኖች በሚኖሩባት በአገሬ ይመጣል ብዬ እስቤው አላውቅም። አሁን ሁሉ ነገር ከሆነ በኋላ እንደ ክርስቲያን እና ካህን ምን ማድረግ እንዳለብኝ አላውቅም፤ከዚህ በኋላ የክርስቶስን ፍቅር እንዴት መስበክ እንችላለን? የእግዚአብሔርን ርህራሄ እንዲህ ባለ ሁኔታ ውስጥ እንዴት መናገር

እንችላለን? እነዚህ ጥያቄዎች ክፋትን ያመጣብን መዘዝ ነው።[32] በማለት ጥልቅ ቁጭታቸውን ይናገራሉ።

*“በዚህም ወራት ደቀ መዛሙርት እየበዙ ሲሄዱ ከግሪክ አገር መጥተው የነበሩት አይሁድ በይሁዳ ኖረው በነበሩት አይሁድ አንጐራጐሩባቸው፥ በየቀኑ በተሠራው አገልግሎት መበለቶቻቸውን ችላ ይሉባቸው ነበርና።”* ሐዋ 6፡1

ቤተክርስቲያን የተጋፈጠችው የመጀመሪያው ችግር የዘረኝነት ችግር ነው። በአግባቡ ካልተቆጣጠርነው የመብዛት አንደኛው አስቸጋሪ ገጽታ መከፋፈልን ማስከተሉ ነው። በሐዋርያት ዘመን የነበሩ አማኞች አስፈሪነታቸው፣ ሞገሳቸው እና ስኬታቸው አንድነታቸው ነበር። ቤተክርስቲያን አንድነቷን ከክርስቶስ ባገኘችው አዲስ ማንነት ላይ አጥብቃ ካልተከለች በስተቀር በየጊዜው የሚወጡ መስፈርቶች የክርስቶስ አካል የሚበታትኑ አውሎ ነፋስ ይሆናሉ። ስንሰባሰብ ለአንድነታችን በክርስቶስ ካገኘነው ማንነት ውጪ ሌላ መስፈርት ከተፈለገ ቤተክርስቲያን መንኮታኮት ትጀምራለች። ጌታ አለሁበት የሚል ብቸኛው ህብረት በእርሱ ማንነት እና ከእርሱ ዳግም መወለድ ብቻ ምክንያት በሆነበት ህብረት ነው። ሌላ ምክንያቶች ቋንቋ፣ ባህል፣ ብሔር ለመሰባሰባችን ምክንያት ከሆኑን ጌታን በዚያ ጉባኤ ውስጥ መፈለግ በኤርታሌ ውስጥ የበረዶ ግግርን እንደ መፈለግ ነው። በዋናነት ዘረኝነት ቤተክርስቲያንን በሚከተሉት አቅጣጫዎች ይጎዳል።

## ጋብቻ ላይ የሚያጠላው ክፉ ድባብ

የጋብቻ አጣማሪዎች እንደሚነግሩን እግዚአብሔር መንግስትንና ቤተክርስቲያንን ለመመስረት ቤተሰብን እንደ መሰረት ድንጋይ እንደሚጠቀም ነው። ጋብቻ ደግሞ በቤተሰብ ግንባታ ላይ ማዕከላዊውን ቦታ ይወስዳል። እግዚአብሔር አንድ ወንድና ሴት ተጋብተው በፍቅር

[32] Dr. Aquiline Tarimo. (Sept 25, 2000). Ethinicity, Common Good and the Church in Contemporary Africa.

እንዲኖሩ መልካም ፍቃዱ ነው፡፡ ለአቅመ አዳምና ሔዋን የደረሱ ወጣቶች ለማግባት የሚያስቡትን ሰው ለመምረጥ የራሳቸውን መስፈርት አስቀምጠው ፍለጋውን ያጧጡፉታል፡፡ አንዳንድ ጊዜ መስፈርቶቹ በቃለ እግዚአብሔር ሲፈተሹ ገለባ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ወጣቱ ይህንን አስተካክሎ ካልተጓዘ ባልተገባ ሁኔታ ላይ መውደቁ አይቀሬ ይሆንበታል፡፡ በተለይ በጋብቻ ጉዳይ ውስጥ ዘረኝነት ከገባ ከፍተኛ ችግር ያስከትላል፡፡ በምርጫ ወቅት ቤተሰቦች ከብሔራችን ካልሆነ እንዳትሞክረው በማለት በወጣቱ አእምሮ ላይ አደገኛ አጥር ይሰራሉ፡፡ ወጣቱም ሲርበተበት ሳያገባ እድሜው ገፍቶ መጨረሻ ከዚህ ትልቅ በረከት ሊጎድል ይችላል፡፡ በዩጎዝላቪያ ውስጥ በተደረገው ጥናት በተለያዩ ጎሳዎች መካከል የተካሔደው ጋብቻ እ.ኢ.አ. በ1950ና 1960 ዎች የጨመረ ነበር፣ ነገር ግን በጎሳዎች መካከል በነበረው ግጭት ፍርሃት ምክንያት ከ1966-69 ድረስ ስያሽቆለቁል በ1970 ዎች ውስጥ ትንሽ እድገት ካሳዩ በኋላ ከ1981 በግጭት ፍርሃት ምክንያት እንደገና ተመልሶ ወረደ፡፡ ይህ የሚያሳየው ጋብቻ ከጎሳ ግጭት ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ [33]

በፍቅር ከተለያየ ብሔር የተጋቡ ሰዎችም ልዩነታቸውን በአግባቡ መያዝ ካለመቻላቸው የብዙ ሰው ትዳር ሲናጋ አይተናል፡፡ ያሳዝናል! አለም ግብረሰዶማዊነትን እንደ ስልጣኔ አቅርባ ወንድና ወንድ በአደባባይ ሲጋቡ እኛ ከጎሳዬ ካልሆነ ብለን አቃቂር ስናወጣ እግዚአብሔር ያዝናል፡፡ አንድ ወንድና ሴት ተባለ እንጂ አማራና አማራ ወይም ኦሮሞና ኦሮሞ ብቻ አላለም፡፡

## ቤተክርስቲያን ከጌታ ጋር ህብረት በሌላቸው ሰዎች የተሞላች እንድትሆን ያደርጋል

ከጌታ ጋር ያለን ህብረት ከወንድሞች ጋር ባለን ህብረት የሚወሰን ነው፡፡ ወንድሞችን እየጠላን ጌታን እወደዋለሁ ማለት እንደማይቻል ሐዋርያው ዮሐንስ አስረግጦ ነግሮናል፡፡

---

[33] The Ethnic Identity of Parents and Children," *Yugoslavia Survey,* Vol. 32, No. 2
(1991), pp. 63--76, 64;

*“የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች ተለይተዉ የሚታወቁት በዚህ ነዉ። ጽድቅን የማያደርግ ወንድሙንም የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።”* 1ዮሐ 3፡10

የሚበድሉንንም ይቅር የማንል ከሆነ ከሰማይ አባታችን ዘንድ ይቅርታ አናገኝም።

*“ከእናንተ እያንዳንዱ ወንድሙን ከልቡ ይቅር ካላለ፥ እንዲሁ ደግሞ የሰማዩ አባቴ ያደርግባችኋል።”* ማቴ 18፡35

## የቤተክርስቲያን እሴቶች ይዛባሉ

እሴት በአንድ ተቋም ውስጥ በቋሚነት የሚተገበር የማይሸጥ የማይለወጥ አቋም ነው። ቤተክርስቲያን ከጌታ የተቀበለቻቸው እሴቶች አሉዋት። ከእነዚያም መካከል የአማኞች አንድነት አንዱና ዋነኛው ነው።

*“ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ፥ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም፤ አንተ እንደ ላክኸኝ ዓለም ያምን ዘንድ፥ አንተ፥ አባት ሆይ፥ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ፥ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ።”* ዮሐ 17፡20-21

ብዙዎች ይህን የክርስቶስ የጣር ጸሎት አፈር ድሜ የሚያስበላ ኑሮ ይኖራሉ። እንዲያውም ጌታ የጸለየበትን ጸሎት በማቃለል ለራሳቸው የሚበጀውን ዘርን መሠረት ያደረገ ህብረት ይመሠርታሉ። ህብረትን በራሳቸው ቋንቋ እና ብሔር ዙሪያ የሚገነቡ ደፋሮች ከበዙ መንጋውን ከእውነተኛ የወይን ግንድ ገንጥለው ለጥፋት የሚያዘጋጅ ይሆናሉ።

## ህገወጥ ግንባታዎች ይበረክታሉ

*“ከተመሠረተው በቀር ማንም ሌላ መሠረት ሊመሠርት አይችልምና፥ እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።”* 1ቆሮ 3፡11

*“በሐዋርያትና በነቢያት መሠረት ላይ ታንጻችኋል፥ የማዕዘኑም ራስ ድንጋይ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ በእርሱም ሕንጻ ሁሉ እየተጋጠመ በጌታ*

*ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንዲሆን ያድጋል፤በእርሱም እናንተ ደግሞ ለእግዚአብሔር መኖሪያ ለመሆን በመንፈስ አብራችሁ ትሠራላችሁ።"* ኤፌ 2፡20-22

ቤተክርስቲያን የታነጸችው በአንድ መሠረት ላይ ነው። እርሱም ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቤተክርስቲያን ሌላ መሰረት የላትም። ከዚህ ውጪ የሆኑ መስፈርቶች ሁሉ ከክፉ ናቸው። በተለይ ዘር፣ ባህል፣ ቋንቋ እና የወንዜ ልጅ በሚል የሚቋቋሙትን ቤተክርስቲያን የሚል ታፔላ ነቅለው መረዳጃ እድር ቢሉት ይሻላል። እነዚህ በእርግጥ ዲያብሎስ በክርስቶስ የመስቀል ሥራ ላይ ለመቀለድ ያከማቻቸው ማህበር ናቸው። ስለዚህ ማንኛዋም ቤተክርስቲያን መሠረቷ ክርስቶስ ካልሆነ ህገ ወጥ ግንባታ ነው። መሃንዲሱ መጥቶ መንጥሮ ወደ ዘላለም እሳት ሳይጥል ግንባታውን በንሰሐ አስተካክለን ከክርስቶስ ጋር መታረቅ ያዋጣል።

## በቤተክርስቲያን ውስጥ ባይተዋሮች ይበዛሉ

*እንግዲያስ ከእንግዲህ ወዲህ ከቅዱሳን ጋር ባላገሮችና የእግዚአብሔር ቤተ ሰዎች ናችሁ እንጂ እንግዶችና መጻተኞች አይደላችሁም።* ኤፌ 2፡19

የቤተክርስቲያን አባላት የአንድ አባት ልጆች፣ ከጌታ ዳግም የተወለዱ፣ ከልብ የሚፋቀሩ ናቸው። አሁን ባለው የማህበረሰብ አደረጃጀት ሰዎች ከተወለዱበት አካባቢ ለትምህርት፣ ለንግድ፣ ለመንግስት ሥራ እና ለመሳሰሉ ጉዳዮች ከቦታ ቦታ በመዘዋወር ይኖራሉ። ከነበሩበት ቤተክርስቲያን ወጥተው ወደ አዲስ ማህበረሰብ ሲቀላቀሉ ቤተክርስቲያንን መፈለግ ይጀምራሉ። ከዚያ ሲያገኙ በታላቅ ደስታ ወንድሞቼን አገኘሁ ብለው ህብረት ለማድረግ ሲሞክሩ የጠበቁትን ፍቅር ሳያገኙ ይቀራሉ። ምናልባት ቤተ-ክርስቲያኒቷ በጌታ ፍቅር ሳይሆን በቋንቋ እና በብሔር ፍቅር ውስጥ ተዘፍቃ ይሆናል። ከሌላ ብሔር የመጡትን የምትቀበልበት ቦታ እስከምታጣ ድረስ ልበ ጠባብ ትሆናለች። አዳዲስ ሰዎች ይህንን በሚያዩበት ጊዜ ጥያቄ ይፈጠርባቸዋል። ግራ መጋባት ይጀምራሉ። ለጌታ ብለው የተውትን የድሮ ማንነት ማሰብ ይጀምራሉ።

ዘማሪ እሸቱ ይባላል በቀጨኔ ባለችው ቤተክርስቲያን እያገለገለ ነው። በቀጨኔ አከባቢ የሚኖሩ ቤተ-እስራኤላውያን/ፈላሻዎች/ ከዘመናት በፊት ከጎንደር እና መራቤቴ መጥተው እንደ ሰፈሩ ይናገራል። ዘማሪ እሸቱ በዘራቸው ምክንያት ስለ ደረሰባቸው መድሎ እንዲህ ይናገራል " ቀጨኔን ሌላኛው ህብረተሰብ ቡዳ ወይም ወደ ጅብ የሚለወጡ ህብረተሰቦች የተሰበሰቡበት አድርጎ ነው የሚያስበው።" ይህ አፈ-ታሪክ ህብረተሰቡ ላይ ሰርጾ 'በእናንተ ያለው በአለም ካለው ይበልጣል' የሚለውን በተሸከመች የክርስቶስ ቤተክርስቲያን እንኳን ሳይቀር በዚህ አፈ-ታሪክ ተፅእኖ ስር ወድቃለች። ለቀጨኔ ህዝብ ያላት አመለካከት ልክ ሌላኛው ህብረተሰብ እንደሚያስበው ይመስለኛል። በጣም የሚገርምህ ቤተክርስቲያን ወደ ቀጨኔ ሳትመጣ አንዳንድ የቀጨኔ ሰዎች ጌታን ፈልገው ወደ አንዳንድ ቤተክርስቲያን ሄደው ጌታን ቢቀበሉም ቀጨኔ በመሆናቸውብቻ ከአንዳንድ ሰዎች ባለማስተዋል አድሎ እና መገለል ሆኖባቸው ህብረተሰቡ እንደሚለው እየተባሉ ተሸማቀው ክርስቶስን ከማመን ወደኋላ የሚሉ ብዙዎች አሉ።"[34]

በዚህ ምክኒያት ተሰናክለው ከጌታ ቤት የወጡ ብዙ ሰዎች በግሌ አጋጥመውኛል። የቀሩት ደግሞ ባይተዋር ሆነው የጌታ መአዛ ሳይሆን ዘረኝነት በሚሸትበት ጉባኤ ውስጥ በምጥ የሚኖሩም አሉ። በግብዝነት እና በኃይማኖት ጭንብል ሳይሆን እንደ ባለ አእምሮ ካሰብን አንድ ሰው አንድ ጫት ቤት ዛሬ ቢገባ ወይንም የአልኮል መጠጥከሚጠጡ ሰዎች ጋር ቢቀላቀል ያለ አንዳች ጥያቄ "እንኳን ደህና መጣህ" በማለት ይቀበሉታል ካላቸው አካፍለው የማህበራቸው አባል ያደረጉታል። በቀጣይነትም ይገባበዛሉ በባህርይ ይጣጣሙ እንጂ የብሔር ጉዳይ አሳሳቢ አይሆንባቸውም። እንዲያውም በዘራችው ዙሪያ እየተቀላለዱ ሲጫወቱ ይታያሉ። ቅጠል እና አልኮል ሰውን ይህን ያህል አንድ ማድረግ ከቻለ የክርስቶስ ደም እንዴት ዘራችንን አያስረሳንም?

ሰዎች በብሔር የሚከፋፈሉበት፣ ቋንቋ እና ባህል ቀዳሚ ጉዳዮች ሆኖ ከወንጌል እውነት በላይ የሚገኙ ጥላቻ እና እርስ በርስ መለያየት

[34] ትሪኒቲ 2003፣ቁጥር 8 ገጽ 15

የሞላበትን ህብረት አንዳንዶች ሊሉት ይችሉ ይሆናል እኔ ግን ክርስቶስ የመሠረታት ቤተ-ክስቲያን ለማለት አልደፍርም፡፡

## ቤተክርስቲያን ተጽኖ እና ተልዕኮ አልባ ትሆናለች

የቤተክርስቲያን ኃይለኝነት እና ተጽዕኖ አምጪነት በጌታ ትዕዛዝ ውስጥ እስከ ኖረች ብቻ ነው፡፡ ጌታ ሰጥቶን የሄደውን የቤት ስራ ማከናወን የምንችለው የጽድቅ ህይወት ስንኖር ብቻ ነው፡፡

*"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ፡፡"* ሐዋ 1፡8

ከአክሰስ ቱዘስክሪፐቸር- ዊክሊፍ ትራንስሌተርስ የተገኘው መረጃ በአለማችን ላይ ካሉት ቋንቋዎች ውስጥ በአሁኑ ጊዜ 64.5% የሚሆኑት የትኛውም የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ትርጉም የሌላቸውሲሆን 12.27% የተወሰነ ክፍል 16.90% የአዲስ ኪዳን ትርጉም ሲኖራቸዉ 6.34% ብቻ ናቸው ሙሉው የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም ያላቸው፡፡[35]
በአገራችን ውስጥ ያለው እውነታ ከዚህ የተለየ አይደለም፡፡ 85 ብሔር ብሐረሰቦች እና ህዝቦች ያሉባት አገራችን በወንጌል ጥማት የሚንከራተቱ ሰዎች ቀላል አይደሉም፡፡

ቤተክርስቲያን መስራት ያለባት ይህን ሰፊ ማሳ እያሰበች መሆን አለበት፡፡ ከራሳችን አካባቢ ከጎሳችን ያላፈ ተልዕኮ ይዘን የምንኖር ከሆነ "*ከዚህም በኋላ አየሁ፤ በዙፋኑና በበጉ ፊት ማንም ሊቆጥራቸዉ የማይችል ከሕዝብ፣ ከነገድ፣ ከወገን፣ ከቋንቋ ሁሉ እጅግ ብዙ ሕዝብ ቆመዉ ነበር፤ እነርሱም ነጭ ልብስ ለብሰዉ፣ የዘንባባ ዝንጣፊ በእጃቸዉ ይዘዉ ነበር፡፡ ራእ 7፡9* የሚለው ቃል እንዴት ይፈጸማል፡፡
የእግዚአብሔርን የፍቅር መልዕክት ከጣልን ቋንቋችንን የማንሰብክበት ምክንያት የለም፡፡ በአንድ ጊዜ የጌታ እና የሰይጣን አገልጋይ መሆን ግን አይቻልም፡፡ ቤተክርስቲያን የክርስቶስ መሆኗ የሚቀረው እውነተኛ

[35] Ralph Winter and Steven C. Hawthorne (2009). Perspectives on World Christian Movement. Pp 270

መስዋዕትነት ያለበት ፍቅር ጠፍቶ የብሔር ጦርነት የሚካሄድባት አውድማ፣ የጥላቻ እና የመከፋፈል መኖሪያ የሆነች ጊዜ እንጂ አዳራሹ የእህል ማከማቻ መጋዘን የሆነበት ቀን አይደለም፡፡

*“ያመኑትም ሕዝብ አንድ ልብ አንዲትም ነፍስ ነበሩአቸው፥ ገንዘባቸውም ሁሉ በአንድነት ነበረ እንጂ ካለው አንድ ነገር ስንኳ የራሱ እንደ ሆነ ማንም አልተናገረም። ሐዋርያትም የጌታን የኢየሱስ ክርስቶስን ትንሣኤ በታላቅ ኃይል ይመሰክሩ ነበር፤ በሁሉም ላይ ታላቅ ጸጋ ነበረባቸው። በመካከላቸው አንድ ስንኳ ችግረኛ አልነበረምና፤ መሬት ወይም ቤት ያላቸው ሁሉ እየሸጡ የተሸጠውን ዋጋ ያመጡ ነበርና፥ በሐዋርያትም እግር አጠገብ ያኖሩ ነበር፤ ማናቸውም እንደሚፈልግ መጠን ለእያንዳንዱ ያካፍሉት ነበር።”* ሐዋ 4፡32-35

የመጀመሪያዋ ቤተክርስቲያን የኃይለኝነቷ ሚስጥር አንድ ነው እርሱም አንድነታቸው ነው፡፡ አሁን ግን መቋቋም ያልቻልነው የዘረኝነት አውራቂስ ከቤታችን ውስጥ ተነስቶ እያናጋን ይገኛል፡፡ በሰው ሁሉ ፊት እንድናበራ የተሰጠን ሻማ ከቤት ውስጥ በተነሳው አውሎንፋስ እየተንገላታ ነው፡፡ የትኛውም የዓለም ተግዳሮት የማይበግረው ጉልበት በመከፋፈላችን ምክንያት ተሽመደመደ፡፡

## ወንጌልን ለሁሉ እንዳታደርስ ያደናቅፉታል

ጌታ ቤተክርስቲያንን በምድር ላይ እንድትሰነብት ሲያቅድ አንድ ኃላፊነት ሰጥቷት ነው፡፡ እርሱም ተመልሶ እስከሚመጣ ድረስ የመንግስቱን ወንጌል እንድትሰብክ ነው፡፡

*“ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።”* ማቴ 24፡14

*“ይህ ሁሉ እንዲህ የሚቀጥል ከሆነ፥ የእግዚአብሔርን ቀን መምጣት እየጠበቃችሁና እያስቸኰላችሁ፥ በቅዱስ ኑሮ እግዚአብሔርንም በመምሰል እንደ ምን ልትሆኑ ይገባችኋል? ስለዚያ ቀን ሰማያት ተቃጥለው ይቀልጣሉ የሰማይም ፍጥረት በትልቅ ትኵሳት ይፈታል፤”*2ጴጥ 3፡11-12

መምጫውንም ከእኛ የወንጌል እንቅስቃሴ ጋር አስተካከለው፡፡ ስለዚህ የወንጌል ስርጭት ጉዳይ በሰማይ ትልቅ የቀን መቁጠሪያ ነው፡፡ በአገራችን ሁኔታ እንኳን ስናይ የወንጌል ስርጭቱ ሁኔታ የተራራቀ ነው፡፡ በኦሮሚያ እና ደቡብ አካባቢ ክርስቲያኖች በብዛት ይገኛሉ፡፡ በሱማሌ ውስጥ ግን አሁንም 99% የሚሆኑት ጌታን ሳያውቁ ወደ ጥፋት እየሄዱ ነው፡፡ እኛ በብሔር ፍቅር አይኖቻችን ታውረው ስላሉ ከተወለድንበት መንደር ውጪ አሻግረን ማየት ተስኖናል፡፡ ከሰማይ የተቀበልነው ይመስል በቋንቋችን ፍቅር ስለ ተሞላን ሌላ ቋንቋ ተምረን ሌሎች ብሔሮችን በምስራቹ ቃል ለመድረስ አንሞክርም፡፡
ምናልባት አንድ ሰይጣናዊ አባባል አግኝቶን እንዳይሆን እሰጋለሁ፡፡ "The blood is thicker than water of baptism" የስጋ ዝምድናን በማስበለጥ ከጌታ የመወለድ ተምሳሌት የሆነውን ጥምቀት አቃሎ የሚያሳይ አባባል ነው፡፡

## 4.3. በአገራችን ሁለንተናዊ እድገት ላይ

በ2012 እ.ኤ.አ የተደረገው የህዝብ ቆጠራ ዳሰሳ እንደሚያመለክተው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙት የወንጌላውያን አማኞች ቁጥር 20% አካባቢ እንደሆነ ያስረዳል፡፡ ስለዚህ በአገራችን ሁለንተናዊ እድገት ላይ 1/5ኛው የክርስቲያኑ ነው ማለት ነው፡፡ ለውጥን ለማምጣት ይህ ቁጥር ከበቂ በላይ ነው፡፡ በ18ኛው ክፍለ ዘመን የነበሩት በዓለም አቀፍ ደረጃ ቁጥራቸው አናሳ የነበሩ አማኞች ከነበሩት የፈጠራ ስራዎች ከ50% በላይ የእነርሱ ነበር፡፡

ቁጥራችን ለውጥን ለማምጣት በቂ እንደመሆኑ መጠን ልባችን ግን ዝግጁ አይደለም፡፡ ባለንበት ማህበረሰብ ውስጥ ምሳሌ መሆን የቻልን አይመስለኝም፡፡ በተለይ ድሮ መገለጫችን የነበረው አንድነት ዛሬ ደብዛው እየጠፋ ነው፡፡ ከዚህ በመቀጠል ዘረኝነት በአገራችን ላይ የሚያስከትለውን ተጽዕኖ በአጭሩ እንመልከት:-

### የተዛባ የቋንቋ አጠቃቀም እንዲኖር ያደርጋል

*"ኑ፥ እንውረድ አንዱ የአንዱን ነገር እንዳይሰማው ቋንቋቸውን በዚያ እንደባልቀው።"* ዘፍ 11፡7

*“በሁሉም መንፈስ ቅዱስ ሞላባቸው፥ መንፈስም ይናገሩ ዘንድ እንደ ሰጣቸው በሌላ ልሳኖች ይናገሩ ጀመር። እኛም እያንዳንዳችን የተወለድንበትን የገዛ ቋንቋችንን እንዴት እንሰማለን?”* ሐዋ 2፡4፣8

*ቋንቋ የአንድን ማህበረሰብ ማንነት ለመግለጽ አይነተኛ መሣሪያ ነው።በኢትዮጵያ ውስጥ ከ85 ቋንቋዎች በላይ ይነገራሉ። ይህንን እንደበረከት የሚያዩ አሉ በሌላ ጽንፍ ደግሞ እንደ ተግዳሮትም ይወሰዳል። ቋንቋዎቹ እንዲህ ናቸው ብለን መተቸት መልካም አይሆንም። አሁን ግን አንድ ነገር ማድረግ ተገቢ ነው። የተወለድንበት እራሳችንን ያገኘንበትን ማህበረሰብ በመልካም ሁኔታ መቀየር ግን እንችላለን።*
*ስለ ቋንቋ ሳስብ ለእኔ የሚገባኝ መግባቢያ መሆኑ ነው። ብዙ ሰዎችም ወይንም ሁለት ሰዎችቢግባቡበት ቋንቋ ሁሉ አንድ ዓላማ አላቸው እርሱም ለመግባቢያነት ማገልገሉ ነው። ነገር ግን የቋንቋ የእድገት ደረጃ ስናስብ ከፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እድገት፣ ከጭቆና ታሪክ ጋር ስለምናገናኘው ጤናማ የሆነ አመለካከት ይዘን መጓዝ ይከብደናል። ከትላንትና ታሪካችን በይቅርታ መላቀቅ ስለሚያቅተን ቋንቋን ለመግባቢያነት ብቻ ለመጠቀም ያዳግተናል።*
*በአገራችን ውስጥ ያሉት ቋንቋዎችም ላይ የሚታየው ችግር ይሄው ነው። አንዱ ብሔር በፍቅር ሳይሆን የበላይነትን ለመያዝ ሲፈልግ ካለ ቋንቋዬ አልናገርም ከባሰበት ደግሞ እንዲያውም ሌሎችም የእኔን ብቻ መናገር አለባቸው ይላል። ሌላኛው ወገን ደግሞ የራሴ እያለኝ ለምን የሌላ ልጠቀም ይላል። እያንዳንዱ ብሔር የራሱን ቋንቋ ቢጠቀም አይከፋም ነገር ግን ለመግባባት አንዳችን የሌላውን ብሔር ቋንቋ ማወቅ አስፈላጊና ጠቃሚ ነው።*
*እኔ እንዲያውም በዘፍ 11፡7 ላይ የተከሰተውን መርገም ለመስበር ይመስለኛል በሐዋ 2፡1-4 አዲስ ቋንቋ የተለቀቀው። በተለይ እኛ ክርስቲያኖች ከቋንቋ በላይ በልብ መግባባት እንችላለን። ይህንን በረከት የምናገኘው የራሳችን ብቻ ይሁን የሚለውን ትተን ለአገርእድገት የሚጠቅመውን አማራጭ መንገድ መከተል ስንችል ነው።*

## ያለንን ሀብት ተካፍለን እንዳንኖር ያደርጋል

*"ጥላቻም ፈጣሪ ነዉ ምክንያቱም ብዙ ጥላቻዎችን መፈብረክ ይችላልና"* ሔነሪ ዱማስ

*"አምላክህ እግዚአብሔር በሰጠህ በአገርህ ደጅ ውስጥ ከሚኖሩ ከወንድሞችህ አንዱ ቢደኸይ፥ ልብህን አታጽና፥ በድሀው ወንድምህ ላይ እጅህን አትጨብጥ። ነገር ግን እጅህን ለእርሱ ክፈት፥ የለመነህንም አስፈላጊውን ነገር አበድረው።"* ዘዳ 15፡7-8

ዘረኝነት ስግብግብነትን ያስከትላል፡፡ የእኔ ዘር ብቻ ይኑር፤ የእኔ ዘር ብቻ ይጠቀም ባይ ነው፡፡ ይህ ደግሞ በአገሪቷ ውስጥ ያለው ሀብት ከአንድ ክልል ወደ ሌላ ክልል እንዳይዘዋወር እንቅፋት ይሆናል፡፡ ጎሳዎች እና ብሔሮች በአግባቡ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ያላቸውን ሀብት ተካፍለው መኖር ከተሳናቸው የደህነቱን ዘመን በራሳችን ላይ የምናራዝም ሌላ ሰው ሳይሆን እኛው እንሆናለን፡፡

## መተማመን እና መቀራረብ በዜጎች መካከል እንዳይፈጠር ያደርጋል

*"ከዘረኝነት በላይ ጠባብነት የለም"* ካርል ክራውስ

ዘረኝነት ህዝቦች ተዋደው እንዳይኖሩ ደርጋል፡፡ አሁን ባለው የዓለም ስርዓት ሰው በተወለደበት አድጎ፣ ተምሮ፣ እዚያው ስራ አግኝቶ አርጅቶ ይሞታል ማለት ዘበት ነው፡፡ ስርዓቱ ሰው ለመኖር መዞር ግዴታው የሆነበት ነው፡፡ ስንዞር ደግሞ ከተለያየ ሰው ጋር እንገናኛለን፡፡ ሰውን ካልወደድነው ከዚያ ሰው ተጠቃሚ አንሆንም፡፡ ለምሳሌ አንድ ጉራጌ አማራ ወይንም ኦሮሞ ይጎዳኛል ብሎ የሚያስብ ከሆነ ከእርሱ ጋር ረዥም ርቀት መጓዝ አይችልም፡፡ ከሰው ጋር ሳይሆን ልክ ከአውሬ ጋር እንደሚሄድ አይነት እየበረገገ ይኖራል፡፡ መተማመን ከሌለ አብሮ መስራት መበዳደር አይቻልም፡፡

በአጠቃላይ ዘረኝነት ጸረ ልማት፣ ጸረ-መንፈሳዊ ህይወት እና ወደ ኋላ የሚጎትት አስከፊ አስተሳሰብ ነው፡፡ ይህንን አውቀን በግል ከችግሩ መላቀቅ በተጨማሪ ደግሞ መዋጋት አለብን፡፡

# ምዕራፍ አምስት

## የቤተክርስቲያን አደራ እና ኃላፊነት

*"ሰው በክርስቶስ ውስጥ ከሆነ ምንም ነገር ግምት ውስጥ አይገባም። ዘሩም የመጣበት የቀድሞ ማንነቱም ጭራሽ አይታሰብም ትልቁ ነገር በጌታ ውስጥ መሆን ነው። "* ማርቲን ሉተር

*"ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።"* ገላ 3፡27-28

### 5.1 የአንድነታችን ሚስጥር

*"በትሕትና ሁሉና በየዋህነት በትዕግሥትም፤ እርስ በርሳችሁ በፍቅር ታገሡ፤ በሰላም ማሰሪያ የመንፈስን አንድነት ለመጠበቅ ትጉ። በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤ አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።"* ኤፌ 4፡2-6

የቤተክርስቲያን አንድነት በአንድ አዳራሽ ውስጥ ከመሰብሰብ ያለፈ ነው። አንድ የሆንነው በጋራ ስላመለክን አይደለም። ምናልባት ፈሪሳውያን የተታለሉበት የቤተ-መቅደስ ጉዳይ የቤ-ተክርስትያን አዳራሽ አታሎን እንዳይሆን እፈራለሁ። የመቅደሱን ጌታ ፈቃድ ህግ እና ዓላማ ረግጠው በህንጻው ይመጻደቁ ነበርና። ከዚህ የተነሣ ቤተ-መቅደሱን በሂደት ደንበኛ መርካቶ አደረጉት። የእግዚአብሔር ፈቃድ በሕይወታችን የማይከናወን ከሆነ መገናኘታችን በራሱ ለአንድነታችን ዋስትና አይሆንም። አንድነትን እኛ አይደለም የምናመጣው። እርሱ በክርስቶስ የቤዛነት ሥራ የተገኘ ነው። እኛየተባልነው በነጻ ያገኛችሁትን ህብረት ጠብቁትነው።

## የአንድነታችን መሠረቶች

### 1. ከአንድአባትተወልደናል።

*“እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።”* ዮሐ 1፡13

ከሥጋ ለመወለድ የሰው እቅድና ፍላጎት መኖር አለበት። በሥጋ መወለድ በአካል ለመገኘትና የቤተሰቦቻችን አባላት እንድንሆን ያደርገናል። ከመንፈስ ዳግም ለመወለድ ኢየሱስ ክርስቶስን መቀበልና በእርሱ ማመን ቅድመ ሁኔታዎች ናቸዉ። ከጌታ ዳግም መወለድ በመንፈስ ህያዋን ያደርገናል። እንዲሁም የእግዚአብሔር ቤተሰቦች አባላት የመሆንን እድል ያጎናጽፈናል። የመጀመሪያውና ዋነኛው የክርስቲያኖች የአንድንት መሰረት ከጌታ ዳግም መወለዳቸው ነው።

### 2. በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት ነን።

*“ስለዚህ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው፤ አሮጌው ነገር አልፎአል፤ እነሆ፥ ሁሉም አዲስ ሆኖአል።”* 2ቆሮ 5፡17

አዲስ ፍጥረት መሆን በሂደታዊ መንገድ በመለወጥ የምንደርስበት ሳይሆን ከሰው እውቀትና መረዳት በላይ ከሆነ ምንጭ እንደገና መገኘት ነው። ይህም አዲስ ፍጥረት የመሆን ጉዞ በግል የሚጀምር ሲሆን እዚያ ጋ ብቻ የሚቆም አይደለም። እንደርሱ ዳግም ከተወለደ አማኝ ጋር ክርስቶስ ራስ በሆነበት የአካል ብልት በመሆን በፍጹም አንድነት ይኖራል።

### 3. የአንድ አካል ብልቶች ነን።

*"እያንዳንዳችን በአንዱ አካላችን ብዙ ብልቶች እንዳሉን፣እነዚህም ብልቶች አንድ አይነት ተግባር እንደ ሌላቸዉ ሁሉ እንዲሁም እኛ ብዙዎች ስንሆን በክርስቶስ አንድ አካል ነን። እያንዳንዳችንም የሌላው ብልት ነን።"* ሮሜ 12፡4-5

ዳግም ልደት ካገኘን በኂላ አዲስ ፍጥረት በመሆንአገልግሎታችንን በጋራ መፈጸም እንጀምራለን። ከተለያዩ የአካል ብልቶች በተገነባዉ ሙሉ አካል

በተመሰለችው ቤተክርስቲያን ውስጥ በፍቅርና እውነተኛ ሕይወት መኖር እንጀምራለን፡፡

4. አንድ ተልዕኮ ተሰጥቶናል፡፡

*“እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ፡፡”* ማቴ 28፡19-20

በአንድ አካል ውስጥ የተለያዩ ተግባራት ብንፈጽምም በዋናነት አንድ ታላቅ ተልዕኮ ተሰቶናል፡፡ እርሱም ከላይ እንደተመለከትነዉ፣ ወንጌል መመስከርና ያመኑትን በማስተማር የክርስቶስ ደቀመዝሙር ማድረግ ነው፡፡ አንድ ተልዕኮ ከተሰጠን ተመሳሳይ ተግባር አለን ማለት ነው፡፡ ይህ ደግም በተለያዩ ክፍላተ አለም በምንኖር አማኞች መካከል አንድ ልብ እንዲኖረንና በፍቅር አብረን እንዲንሰራ ይረዳናል፡፡

የአንድነታችን ሚስጥር በአንድ አካባቢ መኖር የሥጋ ዝምድና ወይንም አንድ አይነት ቋንቋ መናገራችን አይደለም፡፡ እንደ ጄ.ካሚንግ ገለጻ የአማኞች አንድነት የጥንካሬው መጠን ወደ ክርስቶስ መጠጋታቸውእንደሆነ ያስቀምጣሉ፡፡ [36] መገንጠል እናበራሱ ዘር

[36] *Near Christ, near Christians*: -- Observing in a large circle a number of lines called by mathematicians "radii," we perceive that in proportion as each radius approaches the centre, it approaches the radius that is next to it; just in proportion to its nearness to the centre is its nearness to the others; and so it is with the Christian Church. It is one vast circumference, and just as we approach to Christ, in life and character, in the same proportion we draw near each other. (*J. Cumming, D. D.*) The Biblical Illustrator Copyright © 2002, 2003, 2006 Ages Software, Inc. and Biblesoft, Inc.)

መኩራራት ለሚፈልግ የተሻለ አድርጎ እራሱን ለሚያስብ ሰው እኩል ነን አንድ ነን ስትለው ኮሶ የመጠጣት ያህል ሊያንገሸግሸው ይችላል፡፡ ክርስቲያን ነኝ ለሚል ግን እውነቱ ከክርስቶስ ባገኘው ህብረት ውስጥ መኖሩ ነው፡፡ ክርስቶስ ትልቅ ዋጋ ከፍሎ አንድ አርጎናልና፡፡ ከአብ ጋር ካስታረቀን በኃላ በመካከላችን በእርቅ እና አንድነት እንድንኖር አስተማረን፣ጸለየልን፣በተግባርምአሳየን፡፡

*"አሁን ግን እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል።"* ኤፌ 2፡13 ያገኘነው አንድነትና እርቅ ቀላል አይደለም፡፡

*ስለዚህ እናንተ አስቀድሞ በሥጋ አሕዛብ የነበራችሁ፥ በሥጋ በእጅ የተገረዙ በተባሉት ያልተገረዙ የተባላችሁ፥ ይህን አስቡ፤በዚያ ዘመን ከእስራኤል መንግሥት ርቃችሁ ለተስፋውም ቃል ኪዳን እንግዶች ሆናችሁ በዚህም ዓለም ተስፋን አጥታችሁ ከእግዚአብሔርም ተለይታችሁ ያለ ክርስቶስ ነበራችሁ።* ኤፌ 2፡11-12

ኦክታቭየስ ዊንስሎው የተባሉ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሁር በጌታ ውስጥ ስላለን አንድነት ሲናገሩ በክርስቶስ ውስጥ ከሆንን እርሱ የአንድነታችን ስፍራ ነው፡፡ ስለዚህ በጌታ ውስጥ የሆነ ሰው የትም ብናገኘው እንደ ወንድም ልንቀበለው ይገባል፡፡ አለም ከልዩነታችን ይልቅ አንድነታችንን ማየት ትፈልጋለች፡፡ ወንድሞች ሆይ! ስለዚህ በጌታ ባገኘነው ህብረት ላይ እናትኩር ይህ ደስታን ብቻ የምናገኝበት ሳይሆን የቅድስናም ብቸኛው መንገድ ነው፡፡ [37]

---

[37] *Octavius Winslow, D. D.* The Biblical Illustrator Copyright © 2002, 2003, 2006 Ages Software, Inc. and Biblesoft, Inc.)

## ኢየሱስ - ከወገኖቹ በላይ የሆነ ተልዕኮ

*“የእርሱ ወደ ሆነው መጣ፥ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም። ለተቀበሉት ሁሉ ግን፥ በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው፤እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም።”* ዮሐ 1፡11-13

ኢየሱስ በስጋ ከአብረሃም ነው የመጣው ያውም በዘፍ 12፡1-2 የተገባውን ተስፋ ለመፈጸም። በፓለስቲን ተወልዶ ቤተሰቦቹንም ሲያገለግል ነበር። ምንም እንኳ የገዛ ቤተሰቦችን እና ወገኖችን ከማገልገል ቢጀምርም እዚያ ጋር የእርሱን ተልዕኮ ለማደናቀፍ ሲሞክሩ ለገዛ ቤተሰቦቹ የመለሰው ቃል አስገራሚ ነው።

*“መልሶም እናቴ ማን ናት? ወንድሞቼስ እነ ማን ናቸው? አላቸው። በዙሪያው ተቀምጠው ወደ ነበሩትም ተመለከተና። እነሆ እናቴ ወንድሞቼም። የእግዚአብሔርን ፈቃድ የሚያደርግ ሁሉ፥ እርሱ ወንድሜ ነው እኅቴም እናቴም አለ።”* ማር 3፡32-35

## ጳውሎስ - ለጥሪው የኖረ ጀግና

*“ነገር ግን በእናቴ ማኅፀን ሳለሁ የለየኝ በጸጋውም የጠራኝ እግዚአብሔር በአሕዛብ መካከል ስለ እርሱ ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ልጁን በእኔ ሁኔታ ሊገልጥ በወደደ ጊዜ፥ ወዲያው ከሥጋና ከደም ጋር አልተማከርሁም፥”* ገላ 1፡15-16

*“ተመልሰው ግን ጴጥሮስ ለተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠው እንዲሁ ለእኔ ላልተገረዙት የሆነው ወንጌል አደራ እንደ ተሰጠኝ አዩ፤”* ገላ 2፡7

የጳውሎስ ጥሪ ወገኖቹ ላልነበሩት አህዛብ ነበር። በወቅቱ ብንኖር ኖሮ ከአይሁድ ተወልዶ ፈሪሳዊ ሆኖ አህዛብን ለማገልገል ዋጋ መክፈል ምን ያህል እንደሚከብድ እንረዳ ነበር። ነገር ግን ለእርሱ ትልቁ ነገር ጥሪው እንጂ ሌላ መስፈርት ማዘጋጀት አይደለም።

ይህንን እውነት ለመስበክ ሲነሳ ከገዛ ወገኖቹ የምስጋና ደብዳቤ ሳይሆን ስደት እና ነቀፌታ ነው የገጠመው፡፡ አሕዛቦች ካሳደዱት ይልቅ በአይሁዳውያን ያደረሰበት መከራ የከፋ ነበር፡፡ እርሱ ግን የማን ዘር እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቅ ስለነበረ ወንጌሉን አልሸቃቀጠም፡፡

*"ነገር ግን ኬፋ ወደ አንጾኪያ በመጣ ጊዜ ፊት ለፊት ተቃወምሁት፥ ይፈረድበት ዘንድ ይገባ ነበርና፡፡"* ገላ 2፡11

የአንድነታችን መሰረታዊ እውነት ከጌታ ዳግም መወለዳችን ነው፡፡ ሊያስተሳስረን የሚገባ ወሳኝ ነጥብ እርሱ ነው፡፡ በአዲስ ኪዳን ዘመን የተገለጠው አካል በብሉይ ኪዳን ዘመን ጥላው ብቻ ነው የሚታየው፡፡

*"ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፥ ስለዚህም በየዓመቱ ዘወትር በሚያቀርቡት በዚያ መሥዋዕት የሚቀርቡትን ሊፈጽም ከቶ አይችልም፡፡"* ዕብ 10፡1

አሁን በአካል በሰማይ ላይ ያለው ክርስቶስ ጥላው በቤተክርስቲያን ላይ እንዲሆን ይፈልጋል፡፡ እኛም የእርሱን ምስል በህይወታችን የምናሳይ ልጆቹ ነን፡፡ በሰማይ በእግዚአብሔር ዘንድ የሚታወቁት ክርስቶስን የሚኖሩት እና እርሱን የመሰሉ ናቸው እንጂ በስሙ የሚነግዱት አይደለም፡፡

## 5.2. የቤተክርስቲያን ቅንብር መጠበቅ

ቤተክርስቲያን ምንነት ከሰው አእምሮ በላይ ስለሆነ ይህችን ሚስጥር ለማስረዳት የግድ ምድራዊ ተምሳሌቶችን መጠቀም ያስፈልግ ነበር፡፡ ጌታችንም ከሰው መረዳት ተፈናጥሮ ያለውን እውነት ስቦ ለማምጣት ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ክስተቶችና ሂደቶችን ተጠቅሞአል፡፡ ከኃጢአት ውጪ ያለ ነገር ሁሉ ጌታችንና ቤተክርስቲያንን ለመግለጽ ይረዳሉ፡፡ አንድ ተማሪ በእያንዳንዱ ትምህርት ውስጥ ክርስቶስን ማየት ካልቻለ እርሱ ትክክለኛ ተማሪ አይደለም፡፡ እኔም ቤተክርስቲያንን ለመግለጽ ሶስት የትምህት ዘርፎችን በአንክሮት እንመልከት፡-

**የቤተክርስቲያን ባዮሎጂ፡-** አማኞች ከእርሱ ጋር ያላቸውን አንድነት ለመግለጽ በወይን ተክል መስሎ ሲናገር የአዝርዕት ጥናት ያካሄደ ሊቀእጽ (botanist) ይመስላል፡፡ በዚህ ግንድ ላይ በቅሎ ሊያድግ የሚችል የግንዱ ዝርያ ያለው የራሱ ክፋይ የሆነ ብቻ ነው፡፡ አንድ ዘር ያለው ቅርንጫፍ ብቻ ነው በአንድ ዛፍ ላይ ሊኖር የምችለው፡፡ ኢየሱስ እውነተኛ የወይን ተክል ነው ( ዮሐ 15፡1-8 ) እኛ ደግሞ ቅርጫፎቹ የሆንን እለት ነው ዋንዛ፣ ዝግባ፣በለስ፣ዶቅማ መሆናችን የቀረው፡፡ በቤተክርስቲያን ውስጥ ሆነን በዘር ምክንያት ስንከፋፈል ለጌጥ ከፊት ያስቀመጥነው የአበባ ተክል የሚስቅብን ይመስለኛል፡፡ ከስብከት ብቻ ሳይሆን ከተፈጥሮ መማር እንችል ነበር፡፡

በአካል ብልቶችም ተመስለናል፡፡ ጳውሎስ የሰውነት አሰራር/ቅርጽ ጥናት ምሁር (physiologist /anatomist) ይመስላል በ1ቆሮ 12፡12-27)፡፡ ወንድማችን በዚህ የመሰለን የማንለያየው ላለ መስራት ብቻ ሳይሆን ላለ መሞትም መሆኑን ለማስጠንቅ ነው፡፡ ብቻህን መሆኑን ከመረጥክ ትሞታለህ መባባልም ጥሩ ነው፡፡ አንዳችን ያለ ሌላችን የማንጠቅም ነንና፡፡

**የቤተክርስቲያን ኢንጅነሪንግ፡-** ወንድማችን ጳውሎስ የእግዚአብሔር ሕንጻ ናችሁ ይለናል (ኤፌ 2፡20-22) ግንባታ ላይ ነን! በአንድ በኩል ግንበኞች ነን (1ቆሮ 3፡9-17) በሌላ አቅጣጫ እራሳችን የጌታ መኖሪያ ለመሆን እየተሰራን ነው፡፡ አንድን ሕንጻ ለመገንባት ጭራሽ የማይመሳሰሉ የተለያዩ ግብአቶችን እንጠቀማለን፡፡ ውሃና ድንጋይ፣ እንጨትና ፕላስቲክ፣ ብረትና ጨርቅ፣ ቀለምና መስታወት፡፡ ገና የመሰረት ድንጋይ ለመጣል ስናስብ ውሃና ሲሚንቶ ደባልቀን ለማብኳት ስንነሳ የማይገናኙ ነገሮች ተዋህደው ድንጋይን አጣብቀው መሰረት መሆን ይጀምራሉ፡፡

የምናመልክበት ግዑዙ ሕንጻ ምንም የማይገናኙ ንጥረ ነገሮች ተዋህደው መጠለያ መሆን ከቻሉ እኛ አንድ ዘር የሆንን የአዳም ልጆች ከዚያም አልፎ ከጌታ ዳግም የተወለድን እንዴት ተስማምተን በፍቅር መኖር ያቅተናል?

**የቤተክርስቲያን ኬሚስትሪ፡-** ክርስቶስ ቤተክርስቲያን የአካሉ መገኛ መነሻ ነጥብ (element) ነው፡፡ እኛ ደግሞ በእርሱ ላይ የተሰባሰብን፣

የተዋሃድን፣የተደባለቅን ቅይጥ (compound) ነን። ኢየሱስ የቤተክርስቲያን የማዕከሉ ስፍራ (nucleus) ነው። አማኞች ደግሞ በእርሱ ዙርያ የተከማቸን በፍቅሩ ስበት አብረን ሳንለየው የምንኖር (electron) ነን። የዚህ ሕያዋን ህብረት ውህደትና እሽክርክሪት በደንብ መጠበቅ አለበት። ቤተክርስቲያን የመንግስት ተቃዋሚዎችና ደጋፊዎች፣ የአኗኗር ደረጃቸው ሰማይና የምድር ያህል የሚራራቅ ሰዎች፣ የተማረና ያልተማረ ህዝብ፣ የተለያየ ባህልና ቋንቋ ያላቸው ሰዎች በጋራ የሚሰባሳቡባት በጉዞ ላይ ያለች መርከብ ነች። ይህንን ውህደት መስራት ከባድ ኃላፊነት ነው።

ከጫጫታችን የተነሳ መስማት ተሳነን እንጂ ተፈጥሮዎች እንኳን እየታዘቡን ነው። ነገሮችን በእርጋታ ለሚያደምጥና ሁኔታዎችን በጥሞና ለሚመረምር ሰው ጌታ ከስርአተ ፍጥረት እስከ ቃሉ ከአገልጋዮቹ ጀምሮ እስከ መንፈሱ እየተናገረን ነው። ሰው እነዚህን እውነታዎች መቀበል ህብረታችን ተራ ሳይሆን የከበረ፣ ዘለዘለማዊ አንደምታ ያለው መሆኑን መገንዘብ እንችላለን።

## 5.3. እያሉ ያለ መኖር

*“እንግዲህ ታላቅ ብድራት ያለውን ድፍረታችሁን አትጣሉ። የእግዚአብሔርን ፈቃድ አድርጋችሁ የተሰጣችሁን የተስፋ ቃል እንድታገኙ መጽናት ያስፈልጋችኋልና።”* ዕብ 10፡35-36

### ያሉ ሰዎች አሉ?

*“ወንድሞች ሆይ፥ ምናልባት ሕያው እግዚአብሔርን የሚያስክዳችሁ ክፉና የማያምን ልብ ከእናንተ በአንዳችሁ እንዳይኖር ተጠንቀቁ፤”* ዕብ 3፡12

በተለምዶ አንድ አማኝ በቤተክርስቲያን ግቢ ውስጥ ከተገኘ፣ መደበኛ የአምልኮ ፕሮግራሞችን ከተካፈለ እከለ ብርቱ ክርስቲያን ነው ለማለት አናፍርም። እንዲያውም ጌታን የሚወድ፣ጥሩ ክርስቲያን፣ ትጉ ወንድም የሚሉትን ማዕረጎች እንደርብለታለን። እውነታው ግን ከዚያ ያለፈ ነው። የእውነተኛ ክርስትና መለኪያው በአካል በቅዱሳን ጉባዔ ውስጥ መገኘት ላይ ሳይሆን በልብ ከጌታ ጋር መኖሩ ላይ ነው።

ስለዚህ ፍተሻ ይደረግ ! በቤተክርስቲያን ውስጥ በአካል የተገኙት ሥማቸው በቤተክርስቲያን የአባልነት መዝገብ ላይ የሰፈረ በጌታ ውስጥ ተጠብቀው እየኖሩ ነውወይ?በዘረኝነት ማዕበል እየተናጡ በመንገላታት ላይ ቢሆኑስ? መመለስ ያለባቸው ወሳኝ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ በጥላቻ ቀስት ተወግተው ነፍሳቸው በደዌ ተይዛ የምትማቅቅ ብዙ አማኞች በቅዱሳን ጉባዔ ውስጥ በግልጽ እየታዩ ነው፡፡ የነፍስ ደዌ ከባድ ነው፡፡ ሃኪሞች አያገኙትም የስነ-ልቦና ጠበብትም አይደርሱበትም፡፡ ህመሙ ጥልቅ ነው የቃሉ ጨረር ካልመረመራቸው ማንም አያውቃቸውም፡፡

*"የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፥ የሚሠራም፥ ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው፥ ነፍስንና መንፈስንም ጅማትንና ቅልጥምንም እስኪለይ ድረስ ይወጋል፥ የልብንም ስሜትና አሳብ ይመረምራል፤" ዕብ 4፡12*

የጠፉ ስላሉ ፍለጋው ይጧጧፍ፡፡ በቤት ውስጥ የጠፋን ፍልጎ ማግኘት እጅግ ከባድ ቢሆንም ይህ የንሰሃ ጊዜ የምህረት ወራት ሳይጠናቀቅ እንትጋ፡፡ የአማኞችን ህይወት ከጥላቻ ነጥለን በክርስቶስ ውስጥ ለመጠበቅ እንትጋ፡፡ እያጣንያላነውገንዘብሳይሆን የሰው ሕይወት ስለሆነ ጉዳዩ ትኩረት ያሻዋል፡፡

## የዘረ-መል (DNA) ምርመራ ይደረግ

*"ከእግዚአብሔር የተወለደ ሁሉ ኃጢአትን አያደርግም፥ ዘሩ በእርሱ ይኖራልና፤ ከእግዚአብሔርም ተወልዶአልና ኃጢአትን ሊያደርግ አይችልም፡፡" 1ዮሐ 3፡9*

ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ዳግም የተወለዱ ሰዎች ስብስብ ነች፡፡ ኃጢአትን አስቦ እና ፈልጎ የሚያድርግ ዘር በእኛ ውስጥ የለም፡፡ አማኙ ሆነ ብሎ አስቦበት ኃጢያትን የህይውቱ አንዱ ክፍል አድርጎ የሚኖር ከሆነ ከጌታ የተወለደ ነው ለማለት አይቻልም፡፡ የጌታ ዘረመል ያለበት ኃጢያአት የመጥላት ባህርይ አለው፡፡ ዘረኝነት ድንገት የምናደርገው ነው ለማለት ይከብዳል፡፡ ታስቦበት፣

ታሪክ ተጠንቶ፣ ፓለቲካ ተቃኝቶ የሚከናወን ተግባር ነው። ስለዚህ ብሔርተኞች ከጌታ የተወለዱ ናቸው ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም ወንድምን መጥላት ነፍሰ ገዳይነት ነውና።

## 5.4. አንገብጋቢ ጥሪ ወደ እውነተኛ ህብረት

*"ለፍቅርና ለመልካምም ሥራ እንድንነቃቃ እርስ በርሳችን እንተያይ፤ በአንዳንዶችም ዘንድ ልማድ እንደ ሆነው፥ መሰብሰባችንን አንተው እርስ በርሳችን እንመካከር እንጂ፤ ይልቁንም ቀኑ ሲቀርብ እያያችሁ አብልጣችሁ ይህን አድርጉ።"* ዕብ 10፡24-25

*"የወንጌል ግብ ማዳን ብቻ ሣይሆን አንድ ማድረግም ጭምር ነው።"* ጂ.ከሚንግ

የሰማነው ሰማያዊ ጥሪ ነው። የተጋበዝነው ከልጁ ጋር እንዲሁም ከአብ ጋር ቤተሰብ እንድንሆን ነው። ይህ ጥሪ የደረሳቸው እና ምላሽ የሰጡ ሁሉ ወንድማማቾች የመሆን ትልቅ እድል ያገኛሉ። ወደ ክርስቶስ በተጠጋን ቁጥር በፍቅር ስለምናድግ ወደ ወንድሞቻችንም እንጠጋለን።

ይህንን ህብረት ለመገንባት ሙሉውን ዋጋ ኢየሱስ ከፍሎታል። የእኛ ድርሻ ለሥራው እውቅና መስጠት እና ህብረቱን በመንፈስ ቅዱስ መጠበቅ ብቻ ነው። አሁን አንዳንዶች እያፈነገጡ ያሉት ያወቁ መስሎአቸው ፈር እየለቀቁ በስህተት ውስጥ በመዘፈቃቸው ነው። ጌታ ለህብረት ትልቅ ትኩረት ይሰጣል አምጦ የጸለየበት ጉዳይ ስለሆነ ምላሹን ከእኛ ይጠብቃል።

ህብረታቸውን ከወይን ግንድ እና ቅርንጫፍ ጋር ያመሣሰለው ያለ ምክንያት አይደለም። በአጭሩ ካለ ህብረት ህይወት የለም ። (ዮሐ 15) ከግንድ ተገንጥሎ አለሁ የሚል ቅርንጫፍ መሞቱን ያልተረዳ ሬሳ ነው። ስለዚህ ህብረት አማራጭ ሳይሆን ግዴታ ነው።

## የቤተክርስቲያን ሰቆቃ

*“ሀብታም ነኝና ባለጠጋ ሆኜአለሁ አንድም ስንኳ አያስፈልገኝም የምትል ስለ ሆንህ፥ ጐስቋላና ምስኪንም ድሀም ዕውርም የተራቆትህም መሆንህን ስለማታውቅ፥” ራዕ* 3፡17

*“የድሮ አማኞች የተከተሉትን መርህ የረሳን ይመስላል አንድ ስሆንን ጸንተን እንቆማለን ስተከፋፈልን ግን እንወድቃለን"* ማይልስ ሞንሮ

በወንጌላዊያን አማኞች ቤተክርስቲያን ውስጥ ያለው አጠቃላይ የወንጌል እንቅስቃሴ ጌታ ከሰጣቸው ምሪት እና ተልዕኮ ጋር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም፡፡

ጠንካራ ትምህርቶች እና ስብከቶች በእጅጉ መቀነሳቸው በጾም እና ጸሎት የጌታን ፊት መሻት መመናመናቸው በምትኩ አሰልቺ ድግግምሽ እና ጩኸቶች መበራከታቸው የት ነው ያለነው? ወዴትስ እየሄድን ነው? ብለን እራሳችንን እንድንጠይቅ ያስገድዱናል፡፡

በየጊዜው ከመድረኮች ወደ ህዝቡ የሚተላለፉ መልዕክቶች ቤተክርስቲያንን ለማስታጠቅ አይነተኛ መሳሪያ ነበሩ፡፡ ነገር ግን ስብከቶቻችን እንደ እግዚአብሔር ቃል እና ከህዝቡ ሁኔታ ጋር ያልተገናዘቡ ባዶ ተስፋ ብቻ ሆነዋል፡፡ በተለይ ሃገራችን እየተጋፈጠች ያለችውን የኢኮኖሚ፣ የሙስና እና የፍትህ እጦት ችግሮች አንስተን ለመናገር አልፈልግም፡፡ ዝምታን መርጠናል፡፡ በእነዚህ ችግሮች ላይ ከመጽሐፍ ቅዱስ ምላሽ ፈልገን ከመመከት ይልቅ አይተን እንዳላየ በመሆን እራሳችንን እያታለልን ነው፡፡ የዝምታ ውጤት ለቅሶና ቁጭት ነው፡፡ የሩዋንዳ ቤተክርስቲያን መጋቢ በሃገራቸው የዘር ጭፍጨፋ ከተከሰተ በኋላ ተጠይቀው በሰጡት መልስ “እግዚአብሔር ሲናገረን ቸል ብለን ነበር አሁን ግን በሆነው ነገር በጣም አዝነናል” ብለዋል፡፡

አገልጋዮቻችን በጌታ ፊት በእርጋታ ጊዜ በመውሰድ መንፈስቅዱስ የሚሠጣቸውን የጊዜውን መልዕክት ሊያመጡልን ይገባ ነበር፡፡ ይህ ካልሆነ ደግሞ ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ የህዝቡ ፍላጎት ተጠንቶ ፣ ነባራዊ ሁኔታ ታይቶ ከእግዚአብሔር ቃል ቢያስተምሩን መልካም ነው፡፡ ይህንን የምለው ከከንቱ ድግግሞሽ ይሻላል ብዬ እንጂ የወቅቱን መልእክት የሚሰጠው መንፈስ ቅዱስ መሆኑን ዘንግቼው አይደለም፡፡ ቄስ በሊና ሰርካ "የከፍታ ዘመን ለኢትዮጵያ" የሚለውን መልእክት የተቀበሉልን ከ10 ዓመት በፊት ያገለገሉበት ማስታወሻ ሲያገላብጡ ሳይሆን ስለአገራችን ሲያምጡ ነው፡፡

እንደ እውነቱ ከሆነ የተሻለ እና ለአገር ሁለንተናዊ እድገት የሚበጅ አቅጣጫ ከቤተክርስቲያን መፍለቅ ነበረበት፡፡ እግዚአብሔር በመንፈሱ አማካኝነት ስለ ምድራችን የሚያመጣልንን መልእክቶች ተከትለን ተግባራዊ እንዲሆኑ ፕሮጀክቶችን መቅረጽ ፣ የረዥም ጊዜ እቅዶችን በአገር አቀፍ ደረጃ ማዘጋጀት ፣ ስትራቴጅዎችን መንደፍ ይገባን ነበር፡፡ የክርስቶስ ህያው የእድገት መርሆች በ21ኛው ክፍለ ዘመን መተግበር አለባቸው፡፡ አሁን ያሉት ነባራዊ የአገራችን ችግሮች መጽሐፍ ቅዱስ ባስቀመጣቸው ዘላለማዊ ድንጋጌዎች እና መንፈስ ቅዱስ በሚያመለክተን መንገድ በመጓዝ መፍትሄ ሊገኙላቸው ይገባል፡፡ አገልጋዮች ከተዘፈቁበት የድግግሞሽ አዙሪት እና ንክሻ ወጥተው ህዝቡን በማስታጠቅ በመልካም ስራ አስተምረው ማሰማራት አለባቸው፡፡ የተማሩ ክርስቲያኖች ሙያቸውን ለእግዚአብሔር መንግስት መስፋፋት እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ማስተማር አለባቸው፡፡ ባለፉት ጊዜያት በአገሪቱ የገጠር አካባቢ ቤተክርስቲያን የተከሉት ከሚሽነሪዎች ባልተናነሰ የግብርና ባለሙያዎች እና መምህራን ነበሩ፡፡

*"ሁላችን የእግዚአብሔርን ልጅ በማመንና በማወቅ ወደሚገኝ አንድነት፥ ሙሉ ሰውም ወደ መሆን፥ የክርስቶስም ሙላቱ ወደሚሆን ወደ ሙላቱ ልክ እስክንደርስ ድረስ፥ ቅዱሳን አገልግሎትን ለመሥራትና ለክርስቶስ አካል ሕንጻ ፍጹማን ይሆኑ ዘንድ።"* ኤፌ 4፡12

ስለዚህ የሚያስማማንን የጋራ አጀንዳ ቀርጸን በአንድ ልብ በመነሳት የመጨረሻውን መከር መሰብሰብ ይኖርብናል፡፡ ሁላችንም የተለያየ ሃሳብ እንዳለን፣ የተለያየ ጸጋ እንደተሰጠን፣ በተለያየ የመንፈሳዊ እድገት እና ብስለት ላይ እንዳለን ግልጽ ነው፡፡

*"እንግዲህ ፍጹማን የሆንን ሁላችን ይህን እናስብ፤ በአንዳች ነገርም ልዩ አሳብ ቢኖራችሁ፥ እግዚአብሔር ይህን ደግሞ ይገልጥላችኋል፤ ሆኖም በደረስንበት በዚያ እንመላለስ፡፡"* ፊል 3፡15-16

ነገር ግን መለያየት እና ጥላቻ የግሌ መረዳት ነው ስለዚህ መተግበር አለብኝ የሚል ካለ እርሱ ከሰይጣን ነው፡፡ የእኔ ሸክም የራሴን ብሔር ብቻ ማገልገል ነው የሚል ከመጣ ያገልግል ነገር ግን ሌሎች ብሔሮችን የሚጠላ እና የማይቀበል ከሆነ እርሱ የክርስቶስ አገልጋይ ሳይሆን በበጎች መካከል ያለ ተኩላ ነው፡፡ መንጋውን ለመበተን ከጥልቅ ተልዕኮ ያነገበ የሰይጣን ሐዋሪያ ነው፡፡

**ይቆረጥ !!**

*"ፍሬ የማያፈራውን በእኔ ያለውን ቅርንጫፍ ሁሉ ያስወግደዋል፤ ፍሬ የሚያፈራውንም ሁሉ አብዝቶ እንዲያፈራ ያጠራዋል፡፡"* ዮሐ 15፡2

ካልተቆረጠልን እኛው እንቆረጣለን፡፡ ፍሬ አልባ ያደረጉን ፣ የበለጠ አፍርተን ለጌታ ክብር የሚበቃ ህይወት እንዳይኖረን እክል የሆኑብን ከንቱ ልምምዶች ከህይወታችን መወገድ አለባቸው፡፡ ካልሆነ ግን ሞትን ይወልዱብናል፡፡ አሁን አሁን በሃሩር እንደ ተመታ ሰብል ፍሬ የለሽ ዛፍ የሆንን ይመስለኛል፡፡ የጸጋ ስጦታ በብዛት የታየብንን ያህል የመንፈስን ፍሬ እያፈራን አይደለም፡፡ ይህ እንዳይታይብን ያደረጉን ብዙ ነገሮች በልባችን ውስጥ ተሰንቅረው ይገኛሉ፡፡ መወገድ ካለባቸው ነገሮች አንዱ በክርስቶስ ያገኘነው ሕይወት ብቻ ምክንያት አድርገን ከመቀበል ይልቅ ሌላ መስፈርት በማዘጋጀታችን በጌታችን የቤዛነት ስራ ላይ እየተሳለቅን ያለነውለምንድን ነው? ይህ ባህርይ ብዙዎችን ከእግዚአብሔር ቤተሰብ ተነጥለው ባይተዋር ሆነው እንዲኖሩ

ያደረገ ክፉ መርገም ነው፡፡ታዲያ የዚህ የሰይጣንን ሰርጎገብ ስርዓት እያራመድን በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ እንዴት እንቀጥላለን?

ዘረኝነት በአንድ ጊዜ ብዙ የዋሃንን እየመረዘ ያለ ገዳይ መርዝ ነው፡፡ ብሔርተኝነትን ሆነ ብለው በማቀጣጠል ጥቅማቸውን የሚቀምሩ አደገኛ ሰዎች በቤተክርስቲያን ውስጥ አሉ፡፡ ለአካሉ ደህንነት ሲባል እነዚህን ማጋለጥና ተገቢ እርምጃ መውሰድ አለብን፡፡

*“መንፈሱ በጌታ በኢየሱስ ቀን ትድን ዘንድ እንደዚህ ያለው ለሥጋው ጥፋት ለሰይጣን እንዲሰጥ ፍርዴ ነው። መመካታችሁ መልካም አይደለም። ጥቂት እርሾ ሊጡን ሁሉ እንዲያቦካ አታውቁምን?”* 1ቆሮ 5፡5-6

በምድራዊ አሰራርእንኳን ወንጀለኞች ከእኩይ ተግባራቸዉ እንዲታቀቡ እና ህብረተሰቡን እንዳይበክሉ በማረሚያ ቤት እንዲቆዩ ይደረጋል፡፡ ቅዱስ እና እውነተኛ ፍቅር መገለጫው የሆነው የህያዋን ህብረት እንዴት የበለጠ ጥንቃቄ አያስፈልገውም?

*“የገመድም ጅራፍ አበጅቶ ሁሉን በጎችንም በሬዎችንም ከመቅደስ አወጣቸው፥ የለዋጮችንም ገንዘብ አፈሰሰ ገበታዎቻቸውንም ገለበጠ፥”* ዮሐ 2፡15

ኢየሱስ አገልግሎቱ ሊያከትም ጥቂት አመታት ብቻ የቀረውን ቤተ-መቅደስ በታላቅ ቅናት ካጸዳው የገሐነም ደጆች የማይቋቋማት ፣ ከጌታ ጋር አብራ የምትሰራ ቤተክርስቲያን እንዴት በተሻለ ሁኔታ በቅድስና መጠበቅ የለባትም?

ባለማወቅ ወይም በፖለቲካ ግፊት፣ ስሜታዊ በመሆን እና በተለያዩ ምክንቶች የዘረኝነት ቫይረስ ሰለባ የሆኑትን ማስተማር፣ መምከር፣ መገጸጽ ተገቢ ነው፡፡ ግዴታችም ነው! ይህ ክፋት ከአእምሮአቸው መንምኖ እስኪጠፋ መታገል አለብን፡፡ ነገር ግን ሆን ብለው

ዘረኝነትን እንደ መሳሪያ በመጠቀም መንጋውን የሚያመሳቅሉትን በጌታ ትልቅ ገድል በተገነባው አንድነት ላይ የሚሳለቁትን መታገስ እሳትን በጉያ የማቀፍ ያህል ከባድ እና አደገኛ ነው። የጥፋት አጀንዳቸውን እንዲያራምዱ እድል መፍጠር ነው። ስለዚህ ዘረኝነት በማጋለጥሰዎች ከችግሩ ነጻ እንዲወጡ መርዳት አለብን። ከልተቻለ ግን ከህብረቱ በማግለል የክርስቶስን አካል ጤንነት መጠበቅ እስፈላጊ ነው።

## ቤተክርስቲያን የባህል እና የቋንቋ ማስፋፊያ ስፍራ አይደለችም

*"እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን በሚተክልበት ቦታ ሁሉ ሰይጣንም የራሱን ጎጆ ይቀልሳል" ማርቲን ሉተር*

ስቴቨን ኢቫንስ የቢቢሲ ጋዜጠኛ ነው። ከበርሊን ሆኖ በጀርመን በፖትስዳም ከተማ ለመገንባት ስለሚታሰበው የጎሪሰን ቤተክርስቲያን ሲዘግብ እንዲህ ብሎአል "ቤተክርስቲያን የክፋት ምልክት ተደርጋ ስትወሰድ" የሚል አስደንጋጭ ርዕስ ሰጥቶታል ለዘገባው። እንዴት? ነገሩ እንዲህ ነው። ወቅቱ 1933 ነውእ.ኤ.አ.የአለማችን ደም አፍሳሹ ሰው አዶልፍ ሂትለር ሙሉ ስልጣን የጨበጠበት። ወደዚህ ትልቅ ማማ ለመውጣት የተጠቀመበት አንደኛው እና ዋነኛው የዘረኝነት ፖሊሲውን በመንዛት የአሪያንስ ዝርያ የሆኑትን የፕሩዥያን የንጉስ ቤተሰቦች መጠቀም ነበር። ጎሪሰን የፕሩዥያን ቤተሰቦች እና ወታደሮች ቤተክርስቲያን እንደ መሆኗ መጠን የዘረኝነት ሃሳቡን ከማስተናገድ ጀምሮ ለንግስና እንዲበቃ ትልቅ ሚና ተጫውታለች። ዘደይ ኦፍ ፖትስዳም በመባል በሚታወቀው እለት በቤተ-ክርስቲያኒቱ እርዳታ እና ድጋፍ ስልጣንን ለመጎናጸፍ በቃ።[38]

ይህ በአለማችን ቤተክርስቲያን ከሰራቻቸው ስህተቶች እና ጥፋቶች ተስተካይ የሌለው ተደርጎ በኢቫንስ ቢወሰድ አይገርምም። ይህ ብቻ ሳይሆን የሩዋንዳ እና ቡሩንዲ አብያተ-ክርስቲያናትም ይህንን ዘግናኝ ስህተት ደግመውታል።

---

[38] http:www.bbc.com/news/magazine29141925

ቤተክርስቲያን የባህል አዳራሽ ፣ የቋንቋ ትምህርት ቤት፣ የፖለቲካ ሃሳብ ማስተናገጃ መድረክም አይደለችም። ቤተክርስቲያን ከመጀመሪያው የተሰጣት ግልጽ እና የማያሻማ ተልዕኮ አላት።

*"እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።"* ማቴ 28፡19-20

*"ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በእናንተ ላይ በወረደ ጊዜ ኃይልን ትቀበላላችሁ፥ በኢየሩሳሌምም በይሁዳም ሁሉ በሰማርያም እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ አለ።"* ሐዋ 1፡8

የአንድ ነገር አስፈላጊነቱ የተፈጠረበትን አላማ እስከ ፈጸመ ድረስ ብቻ ነው። ቤተክርስቲያን ተልዕኮዋን ሽጣ ጮሌዎች ሃሳባቸውን የሚያከናውኑባት ከሆነች ክርስቶስን መወከሏ ያከትምላታል። ተልዕኮዋን ለመፈጸም ቋንቋ እና ባህልን ትጠቀማለች። ነገር ግን ቋንቋ እና ባህል ማስተዋወቅ ስራዋ አይደለም። አንድ ባለሀብት በገጠር ፋብሪካ ለማቋቋም ቢፈልግ ወደተፈለገው ቦታ ማሽኖችን ለማድረስ መንገድ መሰራቱ ግድ ይላል። ባለሀብቱም መንገድ ከገነባ በኋላ የሚያስፈልገውን ቁሳቁሶች ፋብሪካው ወደሚተከልበት ያደርሳል። መንገድ መገንባት ዓላማው ባይሆንም ዓላማውን ለማሳካት መንገድ ማዘጋጀት ግድ ይሆንበታል። ቤተክርስቲያንም ቋንቋን ማስፋፋት የአንድን ብሔር ባህል ማንጸባረቅ ዓላማዋ አይደለም። ነገር ግን ወንጌልን ለማድረስ እነዚህን መጠቀም ግድ ይላታል።

መገንዘብ ያለብን ትልቅ እውነት ቤተክርስቲያን የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈጸሚያ ከሆነች እና የአንድ ብሔር ማምለኪያ ስፍራ ተደርጋ ስትወሰድ እግዚአብሔር የሰጣትን እድል በምድራዊ አጀንዳ ስለምትበርዝ ኃይል አልባ ትሆናለች። የሌሎች ብሔሮችን ቋንቋ ተጠቅማ ወንጌልን ለሁሉም ሰው ማብሰር ስትችል በአንድ ቋንቋ ሙጭጭ ብላ እድሏን ታበላሻለች። አሁንም እድሉ አለን! የአካሄድ ለውጥ ብናደርግ ወንጌልን ለመስራት በሩ አልተዘጋምና።

## 5.5. ሌሎች ብሔሮችን የመውደድ ግዴታ አለብን

*"የእግዚአብሔር ልጆችና የዲያብሎስ ልጆች በዚህ የተገለጡ ናቸው፤ ጽድቅን የማያደርግና ወንድሙን የማይወድ ሁሉ ከእግዚአብሔር አይደለም።"* 1ዮሐ 3፡10

ክርስቲያኖች ሌሎችን መውደድ እና በእኩልነት ማየት እንዳለባቸው ማስተማር የዩኒቨርስቲ ተማሪዎችን ፊደል የማስቆጠር ያህል ነው። ጌታ ኢየሱስ ኃጢአተኛ ሆነን ሳለ ታላቅ ምህረቱን እና ፍቅሩን ገልጦልን ልጆቹ ያደረገን እለት የተቀበልነው የእግዚአብሔር መውደድ እጅግ ታላቅ ነዉ። ይህ ፍቅር ጌታ እራሱ በልባችን ጽላት ላይ ያተመልን የሁልጊዜ ትዝታችን ነው። ይህን እውነት እንዳንኖር እንደ ገላትያ ሰዎች ማን አዚም አደረገብን?

*"የማታስተውሉ የገላትያ ሰዎች ሆይ፥ በዓይናችሁ ፊት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ተሰቀለ ሆኖ ተሥሎ ነበር፤ ለእውነት እንዳትታዘዙ አዚም ያደረገባችሁ ማን ነው?"* ገላ 3፡1

እውነተኛ ፍቅርን ማንም ሊጎተጉተን እስከማያስፈልገን ድረስ ከክርስቶስ አይተናል። ነገር ግን አጉል መንፈሳዊነት እና ስልጣኔ የሚመስሉ ግብዝነቶች ከልባችን ላይ እየፋቁት ይገኛሉ። እንዲያውም አንዳንድ ሰዎችን መውደድ ከጌታ የተካፈልነውን ባህርይ የምንገልጽበት ወርቃማ እሴታችን ሳይሆን፤ እንደ ቀንበር የተጫነብን አድርገን ስለምናስበው አቀበት እንደ መውጣት ያዳግተናል። እውነታው ግን ጌታችን ኢየሱስ ዳግም ተመልሶ እስኪመጣ ድረስ በጥላቻ እና ጦርነት ለተወጠረች ዓለም የሚበቃ የፍቅር በጀት ለቤተክርስቲያን ሰጥቷታል። ይህንን ፍቅር በማሳየት ሰዎችን ከሞት እና ከሲዖል በር በመንጠቅ ለድነት ማብቃት ኃላፊነታችን ነዉ።

ታዲያ መዋደድ የተሳነን ለምንድን ነው? በፍቅር እጦት እየጠወለጉ ያሉትን መድረስ ለምን አቃተን? በተለያየ ጥላቻ ተይዘው በወንጀል ላይ ለተሰማሩ ሞታቸውን ለምን ተመኘን? ስለ አሸባሪዎች በተነሳ ቁጥር ወደ አገር መከላከያ እያማተርን ጌታ እነዚህን ተጠቅሞ ድራሻቸውን ያጥፋ

ማለትን ምን አመጣው? "መንፈስ ቅዱስ ነፍስ ገዳዮችን ለውጦ የክርስቶስ ባሪያ ያደርጋቸዋል" የሚለው ወኔያችንን ማን ነጠቀው? የአሚሶም እና የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ወደ ሶማሊያ በመሄድ ከአልሸባብ ጋር ሲፋጠጡ የወንጌልን ሰይፍ መዞ ከጨለማ ገዢ ጋር በመጋጠም እነዚህን ኃይሎች ለክርስቶስ ለመማረክ የቆረጠ ጀግና ከቤተክርስቲያን ለምን ታጣ?

*"እውነትን ወደ ማወቅ ይደርሱ ዘንድ፤ እግዚአብሔር ንስሓን እንደ ሚሰጣቸው ተስፋ በማድረግ የሚቃወሙትን በየዋህነት የሚያቀና መሆን ይኖርበታል"* 2ጢሞ 2፡25

በቤተክርስቲያን መድረኮች ላይ ከጫካ እየወጣ የሚያገሳ አንበሳ የሚመስሉ አገልጋዮች ወደ አገራችን ዳር ድንበር ዘልቀው መተንፈስ ለምን ተሳናቸው? ለቀይ መስቀል እንጂ ለወንጌል የሚለገስ ደም ከቤተክርስቲያን እንዴት ጠፋ? ልብ የሚሰብር ነገር በጓዳችን ተገኝቷል! አንድነት የህልውናው መገለጫ የሆነው ህዝብ በዘር እና በቋንቋ መለያየትን መርጦአል። ዋናው የወንጌል ጉዳይ እንደ ኢምንት ተቆጥሮጥቃቅንጉዳዮቻችን ደግሞ እንደ ዝሆን ገዝፈው ተልዕኮአችንን አዛብተውብናል።

ጨቅላዋን ቤተክርስቲያን ገና ከመተከሏ የተከሰተባት የዘረኝነት ችግር የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን እየሰነጣጠቃት ይገኛል። ወታደሮች ጠላትን መውጋት አቁመው ቁማር መጫወት ስራቸው ከሆነ ለጠላት ያዘጋጁትን ጥይት በወዳጃቸው ግንባር ላይ መቀርቀራቸው አይቀሬ ነው። ዛሬም እየሆነ ያለው ይኸው ነው። ቤተክርስቲያን ተልዕኮዋን ስትዘነጋ ሰይጣን ሌላ ተልዕኮ አስይዞ ተንከራታች እያደረጋት ነው።

## 5.6. አሁንም ተስፋ አለ!

*“ለፍፃሜሽም ተስፋ አለ” ኤር 31፡17*

በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በብሔራቸው ምክንያት በግፍ የተገደሉ ሰዎች ደም፣ በዘራቸው ምክንያት የተገፉት ሰዎች የሰቆቃ ኑሮ፣ በመስሪያ ቤት ዘመድ ስለ ሌላቸው መብታቸውን ተነፍገው የሚያለቅሱት ሰዎች እምባ

የምድራችንን እድገት የሚገቱ እና ተስፋችንን የሚያዘገዩ እንቅፋቶች ናቸው። እነዚህ ውስብስብ ችግሮች መፍትሄ ይሻሉ።

አዲስ አሰራር እና አመራር ከአዲስ እና የተለወጠ አመለካከት ይመነጫሉ። አንዱን ጎድተን ሌላውን ለመካስ መሞከር አሁንም የባሰ በቀልን ከመቀስቀስ ውጪ ሌላ ፋይዳ የለውም። በደልን መፈጸም መፍትሄ ሳይሆን ሌላ ችግር ነው የሚያመጣው።

ቤተክርስቲያን ለምድሪቱ እንቆቅልሽ ተስፋ ሆና መገለጥ አለባት። ይህ ከመሆኑ በፊት ግን ጓዳችንን ማጽዳት የቤት ሥራችንን ፈጥነን መጨረስ አለብን። እርስ በርስ ተባልተን ከመጨራረሳችን በፊት በምህረት በጌታ ፊት መሆን ይኖርብናል።

ጨውን እና ድንጋይን የሚለያቸው ጣዕማቸው ብቻ ነው። ጨውን ከመረገጡ የሚያተርፈው ጣፍጦ መገኘቱ ነው። መኪና ሰውን እና እቃን ማጓጓዝ አቅቶት ተበላሽቶ መንገድ ላይ ከቆመ ማንም ለመኪና የሚሰጠውን ስፍራ አይሰጠውም። ለመገልገያነትም አይፈልገውም። እንቅስቃሴው ሲቆም  እንቅፋት ስለሆነ ይጣላል። የእኛም አስፈላጊነት እንደዚሁ ነው። የአንድ በሽተኛ ተስፋው ድኖ እንደ ጤናማ ሰው መስራት ነው። ካልሆነ ግን ብዙ ዓመት በሆስፒታል እየማቀቀ የዶክተሮች እና የአስታማሚዎችን ጊዜ መፍጀቱ አይቀሬ ነው። አማኞችም ወይ አላደግንወይ አላሳደግን ወይ ተለውጠን ለሌሎች የመዳን ምክንያት አልሆንን የመኖራችን ትርጉም ግራ እስኪሆንብን እንዲሁ በከንቱ ዘመንን እየፈጀን ነው። ጌታ ይለውጠን ይድረስልንም!

## እውነተኛ ለውጥ ከቤት ውስጥ

*"ለውጥን ለመቀበል ፈቃደኝነት የሌላቸው አመጽን አይቀሬ ተተኪ ያደርጉታል። ፕሬዝዳንት ኬነዲ*

ለውጥ አይቀሬ ነው። ሚዛናዊ የሆነ ለውጥ ደግሞ ጥሩ ነው። ዶክተር ማርቲን ሉተር ኪንግ "ለዉጥ አይቀሬ በሆነዉ ሽክርክሪት ላይ ሳይሆን ቀጣይነት ባለዉ ትግል የሚገኝ ነዉ። ስለዚህም ወገባችንን ጠበቅ አድርገን

ለነጻነታችን መስራት መጣር ይገባናል" ብሎአል፡፡ ፕሮፌሰር ዓለማየሁ ገ/ማርያም እንደሚሉት "ማንም ራሱን ከቅሬታ ወደ ይቅር ባይነት፣ ከቀላማጅነት ወደ ታማኝነት፣ ከተስፈንጣሪነት ወደ መለስተኝነት ሕሊና መለወጥ ያልቻለ በምንም መልኩ ጥላቻን ወደ ፍቅር ከቁጠኝነት ወደ መግባባት፣ ከልዩነት ወደ አንድነት፣ከጥርጥር ወደ መተማመን፣ ከዝምታ ወደ ራስን መግለጽ ፣ ከመሰለቻቸት ወደ መቻቻል ወዘተ… ለውጥ ሊያመጣ አይችልም፡፡[39]

*"የእግዚአብሔር ፈቃድ እርሱም በጎና ደስ የሚያሰኝ ፍጹምም የሆነው ነገር ምን እንደ ሆነ ፈትናችሁ ታውቁ ዘንድ በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትምሰሉ።"* ሮሜ 12፡2

መለወጥ ያሻናል፡፡ ማደግ አለብን፡፡ ከግል እንጀምር፡፡ በራሳችን ጉዳይ ላይ አትኩረን ልባችንን እንፈትሽ፡፡ ጌታ አድርገን የተቀበልነው ክርስቶስ እንዲከብር የከበርነው እኛ እንዋረድ፡፡

*"እኔስ ለንስሐ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን እሸከም ዘንድ የማይገባኝ ከእኔ በኋላ የሚመጣው ግን ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ በመንፈስ ቅዱስ በእሳትም ያጠምቃችኋል፤"* ማቴ 3፡11

የእኔነታችንን ትዕቢት ለመስቀል ወደ ጎልጎታ መጓዝ ግድ ነው፡፡

*"ነገር ግን ዓለም ለእኔ የተሰቀለበት እኔም ለዓለም የተሰቀልሁበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላ ትምክህት ከእኔ ይራቅ።"* ገላ 6፡14

የቤተክርስቲያን ልጆች የራሳቸውን ብሔር የመውደድ ሌላውን ደግሞ የመጥላት መብት እንዳላቸው ካመኑ ለጌታ የመሸኛ ደብዳቤ ሰጥተው ከህይወታቸው ማሰናበት ይኖርባቸዋል፡፡ *"መለያየት በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ሞት እና ትንሳኤ የተመሠረተውን የመንፈስ አንድነት ለማፍረስ መጣር ነው።" ዶ/ር መልሳቸው መስፍን።*

---

[39] ሎሚ መጽሔት ቅጽ 2 ቅጥር 62 ሐምሌ 2005 ዓ.ም ገጽ 5

በአደባባይ በቅዱሳን ጉባኤ ፊት በግልጽ ከጌታ ጋር የታረቁት። በሰማይ ቅዱሳን መላዕከት አጨብጭበው በእልልታ ስለ እነርሱ የታረደውን በግ ያከበሩትን። ይህንን ጌታ በጓዳቸው ማንም ሳያያቸው አስቆዝመው የሸኙት በምትኩ ጥላቻ እና በቀልን ያነገሱ ጥቂት አይደሉም። በዚህ የፍቅር ንጉስ ላይ ብዙዎች መፈንቅለ መንግስት አካሂደውበታል። ለውጥ…ለውጥ…።

## አምባሳደሩ ዜግነታቸውን ቀየሩ

*"እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን።"* 2ቆሮ 5፡20

ኢትዮጵያ የአገሯን ጉዳይ በጃፓን አገር ሆኖ እንዲከታተል የዲፕሎማሲ ስራ እንዲተገብር ኃላፊነት አሸክማ የላከችው አምባሳደር ከበደ ጌታቸው ስማቸውን ወደ ቺ ሱንግ ዜግነታቸውን ወደ ጃፓናዊነት ቀይረው ኑሮአቸውን በቶኪዮ አማሙቀው ተልዕኮአቸውን ዘንግተው ቢቀጥሉ ምን ይባላል? ክህደት፣ ዝንጉነት፣ ኃላፊነትን ያለ ማወቅ፣… ሁሉንም ካላችሁ መልስ ነው።

በምድር ላይ እንድንቆይ የተፈለገው የአምባሳደርነትን ሚና እንድንጫወት ነው። ልጅን የመሠለ ነገር አጸያፊ እና ከባድ በሆነች ዓለም ውስጥ አንጀቱ እየተላወሰ ያ የፍቅር ጌታ ወክሎን የሄደው አንድ ታላቅ ሚስጥር ቢኖረው ነው። ያንንም ግልጽ አድርጎታል። እርሱም ዓለምን ለማዳን የከፈለውን የፍቅር ዋጋ ላላወቁ በማሳወቅ ሰዎች በእርሱ ሥራ በማመን ከዘላለም ቅጣት እንዲያመልጡ በማድረግ ጌታን ማስደሰት ነው። የቤተክርስቲያን የመኖሯ ህልውና ይህንን ሚስጥር ማወቅ እና በትጋት መተግበሯ ላይ ነው።

ክርስቶስን እንከተልሃለን የተሰጠንንም ኃላፊነት እንፈጽማለን እያልን ጥቅም በተገኘበት ሁሉ የምናጎበድድ ከሆነ ልክ እንደ ይሁዳ ኢየሱስ *"ያ ሰው ሳይወለድ ቢቀር ይሻለው ነበር" ማቴ 26፡24* እንደተባለው መሆናችን ነው። ሚዛናችንን መጠበቅ አለብን። ሚዛን ከተሳተ መውደቅ ይመጣል።

አማኞች ባሉበት ስፍራ ሁሉ ክርስቶስን የመወከል ግዴታ አለባቸው። ክርስቲያን ማለትም ይሄው ነው።

## አንድነት የቤተክርስቲያን ኃይል ነው!

*"በአንድ አሳብ በጌታ እንዲስማሙ ኤዎድያንን እመክራለሁ ሲንጤኪንንም እመክራለሁ።"* ፊል 4:2

አማኞች የብሔርን ልብስ አውልቀው ክርስቶስን ለብሰው በኃጢአት የተጎሳቆለው ገመናቸውን መሸፈን አለባቸው። እርሱ ነው የአማኞች የጽድቅ ልብስ።

ዋናተኞች ወደ መዋኛ ገንዳ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት የለበሱትን በማውለቅ ተመሳሳይ የዋና ልብስ እንደሚለብሱ ሁሉ አማኞችም በህብረት በሚሆኑበት ሁሉ ተመሳሳይ ማንነት ሊኖራቸው ይገባል። አሮጌውን ማንነት አውልቀን ትህትናን መልበስ አለብን።

*"በክርስቶስም አንዳች ምክር ቢሆን፥ የፍቅር መጽናናት ቢሆን፥ የመንፈስ ኅብረት ቢሆን፥ ምሕረትና ርኅራኄ ቢሆኑ፥ ደስታዬን ፈጽሙልኝ፤በአንድ አሳብ ተስማሙ፥ አንድ ፍቅር አንድም ልብ አንድም አሳብ ይሁንላችሁ፤"* ፊል 2:1-2

## የፍትህ መልእክት ከቤተክርስቲያን መነሳት አለበት

*"የሚያስተራርቁ ብፁአን ናቸዉ፤የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።"* ማቴ 5:9 (1954 ትርጉም)

ስለ ቤተክርስቲያን የፍትህ ተሟጋችነት እና የእርቅ አምባሳደርነት ፕሮፌሰር ሳሙኤል ዋጄ እንዲህ ይናገራሉ "ስለ እርቅ የሚናገሩ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎችን በማጣቀስ ሰው ሁሉ ለበላይ አካል መገዛት አለበት፣ግራ ጉንጭህን ለሚመታህ የቀኙንም አዙርለት፣ ሰይፋቸውን የሚመዙ በሰይፍ ይጠፋሉ የሚለውን በመጥቀስ ሰዎችን ለእርቅ ማነሳሳት

ብቻ በቂ አይደለም፡፡[40] የቤተ-ክስቲያን መሪዎች እርቅን በሚሰብኩበት ጊዜ በተጎዳው ወገን ጎን በመቆም በፍትህ መፍትሄ ለማምጣት የማይሚገቱ ከሆነ ተጨባጭ ፈውስ ማምጣት ይሳናቸዋል፡፡ ማእከላዊ ቦታ ላይ ቆመን የምናመቻምች ከሆነ ያለውን ሁኔታ ከማስቀጠል ውጪ ዘላቂ የሆነ መፍትሄ መሆን አንችልም፡፡ ግጭትን ለይስሙላ መፍታት እና ጊዜያዊ መረጋጋትን ማምጣት የክርስቲያን ግብ አይደለም፡፡ ግባችን ፍትህን ማስፈን ነው ይህ ደግሞ ብዙ ዋጋ የሚያስከፍል ተግባር ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ኢ-ፍትሃዊነትን እና ዘረኝነትን በንቃት መዋጋት አለባት፡፡[41]

ከብርሃን መጽሔት ላይ ያገኘሁትን አንድ በጣም የማረከኝን እና የተደመምኩበትን የምህረት ልብ ላካፍላችሁ፡፡ "ሩዋንዳ፤ኪጋሊ ከሁቱ እና ቱትሲ ዘር የሚካፈሉት መሸሮች የሰርጋቸዉን ስርአት ለመፈጸም በካህኑ ፊት ቆመዋል፡፡ ወንዱ ሙሽራ ከጎኑ በቆመችው የትዳር አጋሩ ጣት ላይ የቃል ኪዳኑን ቀለበት ለማኖር እጁን ዘረጋ፡፡ በዚህ ጊዜ መሸሪት የግራ እጇን ሸቅብ አሳይታ ጣቶችዋን ለታዳሚዎች አሳየች፡፡የቀለበት ጣቷንም ጨምሮ ሌሎች ሦስት ጣቶችዋ በስፍራቸው የሉም፣ 'የዘር ማጥራት' በተሰኘው ጽልመታዊ ዘመን ከጎንዋ በቆመው ከሁቱ ዘር በሚከፈለው በእጮኛዋ ዘሮች አማካኝነት ጣቶችዋ በስለት እየተቀጠቀጡ ረግፈዋል፡፡ 'በግልጽ እንደምትመለከቱት' ስትል ንግግሯን ጀመረች 'በግልጽ እንደምትመለከቱት በግራ እጄ ላይ የነበሩት ሦስቱ ጣቶቼ በተለይ ደግሞ ለዛሬው የደስታ ዕለት ይበልጥ የሚያስፈልገኝ የቀለበት ጣቴ በስፍራውየለም፣ የእጮኛዬ ዘሮች በሰነዘሩብኝ ስለት ከእጄ ላይ እየተጎመዱ ወድቀዋል በዚህ ምክንያት እጮኛዬ ቀለበቱን የሚያጠልቅበት ጣት በስፍራው የለም፡፡ ይሁን እና በእግዚአብሔር ቸርነት የቀኝ እጄ ጣቶች በመትረፋቸው እጮኛዬ የቃል ኪዳኑን ቀለበት በዚያ ቦታ ማድረግ ይችላል' አለች፡፡[42]"

---

[40] Samuel Waje Kunhiyop (2008). Africa Christian Ethics. Zondervan, Hippo Books. Nairobi. P. 121

[41] Ibd p. 122

[42] ብርሃን መጽሐት 64/2006 ዓ.ም ገጽ 2

ምዕራፉን ከመሰናበታችን በፊት የፓስተር ታምራት ኃይሌን አንድ ዝማሬ ልጋብዛችሁ!!

የቀራንዮ ፍቅሩ የአንድ አባት ልጆች አድርጎናል
ታዲያ መለያየታችን ለምን ይረባናል (2)
(ዮሐ 15፡1-26 ሮሜ 14፡1-23 ኤፌ 4፡1-16)

# ምዕራፍ ስድስት

## የመፍትሔ አቅጣጫዎች

*"የሆነው ሁሉ እንዳለ ሆኖ አሁንም ቢሆን ሰዎች ከስርመሰረታቸው ጥሩዎች ናቸው ብዬ አምናለሁ" አና ፍራንክ፡፡*

### 6.1. ድል ነሺ ማንነት!

የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ፍልምያ፡፡ የክርስቶስን የፍቅር ኃይል በጉልህ ያየሁበት ግጥምያ፡፡ የአንድነታችን ሚስጥር በሆነው ከጎልጎታ በፈለቀው የክርስቶስ ደም ውስጥ ስንዋኝ የተገናኘን ወዳጄ ኃብቱ ግርማይ፡፡ በ1997 እ.ኢ.አ ዓ.ም ከትግራይ ክልል ተመድበው ወደ የሐረማያ ዩኒቨርሲቲ ከገቡ ተማሪዎች ብቸኛው አማኝ፡፡ በመካከላችን የነበረው የጥል ግድግዳ በመስቀሉ ፈርሶ በአንድ ሳሎን ውስጥ ተቀምጠን የተገናኘን ወንድሜ፡፡ ከእግዚአብሔር ቃል ዳግም መወለዳችን አንድ ዘረ-መል በውስጣችን እንዲኖር አደረገ፡፡ ፍቅር ብቻውን ገዢ ሆኖ በእውነተኛው ህብረት ውስጥ አብረን ሰነበትን፡፡ 1998 እ.ኢ.አ በጊቢያችን መልካም የጥላቻ አዝመራ ነበር፡፡ መከፋፈል ተዘርቶ የዘረኝነት ፍሬ የጎመራበት የመኸር ወቅት፡፡ በተለይ ኦሮሞና ትግሬዎች በብሔር ተከፋፍለው ሰይፍ የተማዘዙበት ልብ ሰባሪ ትዕይንት፡፡ የአንድ አገር ልጆች ከአንድ ዶርም ወጥተው ከአንድ ማዕድ አብረው በልተው ሊገዳደሉ የተነሱበት አሳዛኝ ጠባሳ፡፡ በአንድ ክፍል ውስጥ ቁጭ ብለው አብረው የተማሩበት፣ አንድ ላይ ተጨንቀው የተፈተኑበት፣ የዩኒቨርሲቲ የጭንቀት ሕይወት በቀልድና ጫወታ የተጋፈጡበት ትውስታዎች ሁሉ እንደ ጉም በነነ፡፡ የወንድማማችነት ፍቅር በትል እንደ ተወጋ የበቆሎ ተክል ተኮማሸሸ፡፡

የእለቷ ተረኛ ፀሐይ በቂምና በቀል ታፍነው የተኙትን ተማሪዎች ቀሰቀሰቻቸው፡፡ እንደ ተለመደው ተማሪዎች ከአንዱ ማዕድ አብረው ለመመገብ ወደ ካፌ አቀኑ፡፡ ከቁርስ በኋላ ጎራ መያዝና መቧደን ተጀመረ፡፡ የጥፋት አባት ድምጽ የዲያብሎስ ሽንገላ የታከለበት የጦርነትና የዘረኝነት

ነጋሪት መጎሰም ተጀመረ፡፡ ድምጹም በኃይል አስተጋባ፡፡ ልባቸው ውስጥ የታፈነውም የጥላቻ ፈንጂ ፈነዳ፡፡ የድብድቡም ፊሽካ ተነፋ፡፡ ድንጋይና እንጨት በጓደኞቻቸው ላይ በመወርወር መፈነካከት ተጀመረ፡፡ የጊቢው ሰላም አስከባሪ ኃይል ረብሻውን መቆጣጠር ተስኖት እጅ ሰጥቶአል፡፡ ወዲያው የፌደራል ፖሊሲና የመከላከያ ሰራዊት በአከባቢው ላይ ማንዣበብ ጀመረ፡፡ የተቻላቸውን አደረጉ፡፡ ዳሩ ግን ወጣቶቹ የያዙትን ድንጋይና ዱላ ማስጣል እንጂ በልባቸው ውስጥ የተቋጠረውን ጥላቻና ክፋት መፋቅ እንደማይችሉ የተገነዘቡ አይመስለኝም፡፡

እኔ ግን ድብድብና ጥላቻ ስለማይመጥነኝ፣ ለዚህ እንዳልተጠራሁ ስለማምን ከማንም ጋር መወገን ስለማልችል ስለ ተፈጠረው ነገር እያዘንኩ ገለልተኛ ቦታ ላይ ቆሜ በትካዜ የሚሆነውን መመልከት ጀመርኩ፡፡ ድንገት ኃብትሽ ቁና ቁና እየተነፈሰ ሮጦ መጣ፡፡ ከትግራይ ልጆች ጋር እንዳይሆን የገባው እውነት በጥላቻ ተረግዞ ድብድብን በወለደው ድራማ ውስጥ እንዳይተውን አድርጎታልና፡፡ ከራሱም ወገኖች መሸሽ ነበረበት፡፡ ከዚህ የጥፋት ማዕበል ተያይዘን ወደ ቅርጫት ኳስ ሜዳ ገለል አልን፡፡ በውስጣችን ያለው አንዱ መንፈስ ወደ ፀሎት መራን፡፡ እጅ ለእጅ ተያይዘን በጌታ ፊት አነባን፡፡ የመጡት ፖሊሶች የተማሪዎችን ጀርባ በዱላ እየነረቱ ለያዩአቸው፡፡ በልባቸው ውስጥ ያለው የጥላቻ እድፍ ግን የሚታጠበው በእንባችን እንደ ሆነ ገብቶን ስለ ነበር ጉዳይን በትህትና በጌታ ፊት አቀረብን፡፡ መከፋፈልና ጥላቻን የሚዘራውን የአየር ላይ አለቃ የሚጥለው በሰላም አስከባሪዎቹ የሚንጣጣው ጥይት ሳይሆን የጸሎት ኃይል እንደሆነ ስላወቅን በእምነት ተቃወምነው፡፡

ይህችን ክፉ አለም ተሰናብተን እላይ በመንግስተ ሰማይ ከሁሉም ብሔሮች ጋር በአንድነት ጌታን እያመለክን የሚኖረንን ቆይታ በአይነ ህሊናዬ ቃኘሁ፡፡ ልዩ ደስታ በልቤ ተሰማኝ፡፡ በደሙ አንድ የመሆን ትርጉም በራልኝ፡፡

የጥላቻን ጥሪ ተከትሎ በጦርነት ውስጥ መሳተፍ ማንም ሰው የሚደረገው ተራና እኩይ ተግባር ነው፡፡ ከባዱ ነገር ጥላቻ እንደ ጉም ምድሪቱን በሸፈነበት ስፍራ ከጭጋጉ በላይ በተገነባው የፍቅር ጎጆ ውስጥ አብሮ

መሆን ነው፡፡ ዳግም ባልተወለደ አሮጌው ማንነት ይህንን ማድረግ ተራራ የመግፋት ያህል ሊከብድ ይችላል፡፡ ነገር ግን ድል ነሺ የሆነው የክርስቶስ ዘር በእኛ ውስጥ ስለ ነበር በቀላሉ የኑሮአችን አካል አድርገነዋል፡፡ ከፍቅር የተወለድን የፍቅር ልጆች ስለሆንን ተቻለ!!

## ወዳጆቼ ሆይ እንወስን!

ከዘረኝነት ጋር ለመቆየት ማሰብ ገዳይ በሽታን የመንከባከብ ያህል አደገኛ ነው፡፡ በየዘመናቱ መልኩን ከስልጣኔ ጋር እየቀያየረ ሁለንተናዊ እድገታችን ላይ ክፉ ጥላ እያጠላ ያለውን ጽልመት የመግፈፊያ ዘመን አሁን ያለንበት ጊዜ ነው፡፡ ሽፋፍነን ማለፍ መፍትሔ ካላመጣ ችግሩን ፈንቅለን እውነቱን መጋፈጥ ብቸኛ የፈውስ አቅጣጫ ነው፡፡ መወቃቀስ ካለብን በቅንነት እንዋቀስ፣ ቤተክርስቲያን የክርስቶስን የእርቅ መልዕክት አንግባ ትነሳ! የአገር ሽማግሌዎች የማስታረቅ ጥበባቸውን አሚጠው ተጠቅመው ለዚህ ትውልድ ትልቅ ቁምነገር ይስሩ፡፡ ለፍትህ ፣ ለአንድነት ፣ ለዜጎች የጋራ ጥቅም መንግስት ይወስን፡፡ የህዝብ በፍቅር በጋራ አብሮ ተቀባብሎ የመኖር እሴቶች ከተቀበሩበት ይውጡ፡፡ ዙፋን ይዘጋጅላቸው እነርሱ ይግዙን እውነት እና ፍትህ ይደግፉት፡፡

ያኔ ኢትዮጵያ የአፍሪካ ህብረት ዋና ጽሕፈት ቤት መገኛ ብቻ ሳትሆን ለአህጉራችን የመልካም አስተዳደር እና የልማት ፋና ወጊ ትሆናለች፡፡ የአፍሪካ አባቶች "ኢትዮጵያ እጆቿን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች አፍሪካ ትከተላለች" ያሉት የእነ ኩዋሜ ኑኩሩማ ትንቢት እውን ይሆናል፡፡

ክርስቶስ ለፍቅር ውድ ዋጋ ከፈለ እኛ ደግሞ በየጓዳው እየፈነዳ የዋሆችን የጥላቻ ሰለባ እያደረጋቸው ያለውን የዘረኝነት ፈንጂ ለማምከን ወገባችንን ታጥቀን እንነሳ፡፡ የዘረኝነትን አውራቂስ ተጋፍጠን መከፋፈልን ከመሰረቱ ለመንቀል ታላቅ መስዋዕትነት ከፍለን ለቀጣዩ ትውልድ ፍቅርን ለማውረስ ልባችንን እናዘጋጅ፡፡

ዘረኝነትን ለማጥፋት እርምጃዎችን በሦስት ደረጃ መውሰድ ይኖርብናል፡፡ እነርሱም፡-

1. የግል ውሳኔ
2. የቤተክርስቲያን ኃላፊነት
3. ከእያንዳንዱ ብሔር የሚጠበቅ ግዴታ

## 6.2. የግል ውሳኔ

አገር የግለሰቦች ስብስብ ነች፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ ከዘረኝነት ቢጸዳ አገሪቱ በፍቅር፣ በእውነት እና ህብረት የተሞላች ትሆናለች፡፡ ይህ የማይሆን ቢመስልም ሊደረስበት የሚችል ግብ ነው፡፡ በተለይ ከማንም በላይ ከአማኞች ትልቅ ምሳሌነት ይጠበቃል፡፡ ብዙ ከተሰጠው ብዙ ይፈለጋልና፡፡ የተቀበልነው ትልቁ ሀብት ክርስቶስን ነው፡፡ ሰው የፍቅርን ምንጭ ተቀብሎ ጥላቻን ማፍለቅ የለበትም፡፡ እንኳን ለጎረቤት አይደለም ለአገር የሚበቃ የፍቅር ክምችት ከእኛ ዘንድ አለ፡፡ ስለዚህ በግላችን ትልቅ ውሳኔ ማድረግ ይኖርብናል፡፡

### የ "ማ" መርሆች

በግላችን ከችግሩ ለመላቀቅ፣ ከዚህ ቀጥሎ ያሉትን እንከተል፡፡

ሀ. ማወቅ
ለ. ማጋለጥ
ሐ. ማፍረስ

### ሀ. ማወቅ

ስለ ዘረኝነት፣ አንድነት፣ ፍቅር ያለንን መረዳት በእግዚአብሔር ቃል መመዘን አለብን፡፡ መረዳታችንን በጥልቀት መፈተሽ ይኖርብናል፡፡ የብዙዎቻችን መረዳት በተረት ተረት መልክ ቤተሰቦቻችን የነገሩን ተዓማኒነት የሌላቸው ታሪኮች ላይ ተመስርቶ እንደሆነ እገምታለሁ፡፡ ብዙ ቤተሰቦች ልጆቻቸውን ስለ ፍቅር እና አንድነት ሳይሆን የእነርሱ ቤተሰብ ከተሻለ ዘር እንደ መጡ ሲተርኩላቸው ነው ያሳደጓቸው፡፡ ይህ ደግሞ

ሌሎችን እንዲንቁ እና በትዕቢት ተሞልተው እንዲኖሩ አድርጎአል፡፡ በሌላ በኩል የምናነባቸውም ጽሑፎች ሚዛናዊ ናቸው ለማለት አያስደፍርም፡፡ ማንኛውንም ነገር ማንበብ ተገቢ ቢሆንም አእምሮአችንን በማይመጥን እውቀት እና በተዛባ መረዳት መሙላት ግን ርካሽ ሕይወት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡

*"ሕዝቤ እውቀት ከማጣቱ የተነሣ ጠፍቶአል አንተም እውቀትን ጠልተሃልና እኔ ካህን እንዳትሆነኝ እጠላሃለሁ የአምላክህንም ሕግ ረስተሃልና እኔ ደግሞ ልጆችህን እረሳለሁ።" ሆሴ 4፡6*

ያለ እውቀት መሆን ለጥፋት ይዳርጋል፡፡ የተዛባ ነገርን እንደ እውቀት ተቀበሎ በዚያ ህይወታችን ለመምራት መወሰን ደግሞ የማይረባና ተጽኖ አልባ ህይወት እንዲኖረን ያደርጋል፡፡ ዝምታ፣ ቸልተኝነት እና ስንፍና በብዙዎቻችን ላይ ጎጆ የሰሩ ይመስለኛል፡፡ ችግሮችን ገና በእንጭጩ መቅጨት ካልቻልን በዝምታችን ምክያንያት ብዙ ነገሮች ከቁጥጥራችን ውጪ ይሆናሉ፡፡

ስለ ዘረኝነት በቂ ግንዛቤ መያዝ ከቻልን ማህበረሰቡ የአንድነት አርበኛ የእርቅ ምክንያት እንዲሆን አንደ ትልቅ ግብዓት ያገለግላል፡፡ እውቀት በራስ መተማመናችንን ይጨምራል፡፡ እውቀት ተሰሚነትን ያስገኝልናል፡፡

*"የፈጠረውንም ምሳሌ እንዲመስል እውቀትን ለማግኘት የሚታደሰውን አዲሱን ሰው ለብሳችሁታል። በዚያም የግሪክ ሰው አይሁዳዊም የተገረዘም ያልተገረዘም አረማዊም እስኩቴስም ባሪያም ጨዋ ሰውም መሆን አልተቻለም፥ ነገር ግን ክርስቶስ ሁሉ ነው፥ በሁሉም ነው።"* ቆላ 3፡10-11

### ለ. ማጋላጥ

*"ፍሬም ከሌለው ከጨለማ ሥራ ጋር አትተባበሩ፥ ይልቁን ግለጡት እንጂ፥"።* ኤፌ 5፡11

እውነተኛ እውቀት ሲመጣ እርምጃ እንድንወስድ ያግዘናል፡፡ አንድ ሃሳብ ስህተት መሆኑ ከታወቀ መጋለጥ አለበት፡፡ አንድ ነገር ጥፋት መሆኑን ስናውቅ ከመግለጥ ይልቅ መሸፈንን የምንመርጥ ከሆነ ጤናማ የክርስትና ሕይወት አለን ለማለት አይቻልም፡፡ ዘረኝነት ችግር መሆኑን ማወቅ ብቻውን በቂ አይደለም፡፡ አለመተባበር እና ማጋለጥ አለብን፡፡ ኃጢአት እና

ስህተት በጨለማ ይመሰላሉ ጠንካራነታቸውም መሰወራቸው ላይ ነው። በእግዚአብሔር ቃል ብርሃን ሲጋለጡ የመተግበራቸው እድል ይመነምናል። ኃጢአትን ያለመስራት እና ከክፉዎች ጋር ያለ መተባበር ብቻ ሳይሆን እንዲያውም ማጋለጥ ይኖርብናል። እግዚአብሔር ዝም እንድንል በማይፈልገው ጉዳይ ላይ ዝም ማለት አመጽ እንዲስፋፋ እድል መስጠት አልያም መተባበር ነው። የሰይጣን ኃይለኝነቱ በጨለማ ውስጥ እየሸነገለ መስራቱ ነው። የእግዚአብሔር ጥሪ አላማው ብርሃን ሆነን የጨለማን ሥራ እንድናጋልጥ ነው።

### ሐ. ማፍረስ

“*የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና፥ ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን ለክርስቶስም ለመታዘዝ አእምሮን ሁሉ እንማርካለን፥*” 2 ቆሮ 10፡4-5

ዘረኝነት ጸረ-ህብረት አስተምህሮ መሆኑን አብጠርጥረን ካወቅን ለቤተክርስቲያን እድገት እንቅፋት መሆኑን ማጋለጥ ግድ ይለናል። በመጨረሻ ደግሞ የተጋለጠውን በማፍረስ በምትኩ ፍቅር እና መተባበርን መትከል ይኖርብናል። በአእምሮ ውስጥ ተሰንቅሮ ፍቅርን እንደ አሲድ በልቶ ለማመንመን ጊዜ እንደወሰደባት ሁሉ ለእግዚአብሔር ቃል አስተምህሮ ስፍራ ለመልቀቅም ጊዜ ይወስድበታል። ዘረኝነት በአብዛኛው የሚበቅለው በእኔነት እና በትዕቢት ስለ ሆነ ለመንቀል ትንሽ አስቸጋሪ ነው። የአምላካችን ቃል ግን መዶሻ ስለሆነ ይህንን ክፉ ግንብ ሊያፈራርስ ይችላል።

የተፈጠርነው የጥላቻ ኮሮጆ በመሆን ዘረኝነትን ለመሸከም ሳይሆን የመንፈስ ቅዱስ ማደሪያ ለመሆን ነው። ይህ ግን ውሳኔ የሚጠይቅ ተግባር ነው። ሰው ሁሉ ደጁን ቢያጸዳ ፓሪስ ትጸዳለች እንደሚባለው በግላችን ልባችንን ፈትሸን ዘረኝነትን መንጥረን ካስወገድን ቤተክርስቲያን የፍቅር አምባ ትሆናለች።

## 6.3. የቤተክርስቲያን ኃላፊነት

*"ከክርስቶስ ጋር አንድ ትሆኑ ዘንድ የተጠመቃችሁ ሁሉ ክርስቶስን ለብሳችኋልና። አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።"* ገላ 3፡27-28

ሰዎችን በእውነተኛ የወንጌል ቃል በመድረስ ከዘላለም ሞት የሚያመልጡበትን መንገድ የመጠቆም የዳኑት ደግሞ ጸንተው እንዲቆሙ የጌታ ደቀ-መዝሙር እንዲሆኑ የማስተማር ኃላፊነት የተሰጣት ተቋም ናት ቤተክርስቲያን። እነዚህ ከባድ ተግባራት በመንፈስ ቅዱስ ኃይል እና አንድ በመሆን የሚፈጸሙ ናቸው። የእግዚአብሔር ኃይል በመካከላችን እንዲገለጥ የልብ አንድነት ሊኖረን ግድ ነው።ጌታ ቅዱስ ስለ ሆነ ቤተ-መቅደሱ ለመሆን መቀደስ አለብን። የሚቀድሰን የሚያነጻን የክርስቶስ ደሞ እያለልን በደላችንን ታቅፈን የምንቀመጥበት ምክንያት የለንም። ያን የሚያህል ርዝመቱ የማይለካ ጥልቀቱ የማይደረስበት ከአእምሮ በላይ የሆነ ፍቅር ፈሶብን ሰው ካረገን ሰውን በብሔሩ ብቻ ለመጥላት ስናስብ አእምሮ የጎደለን ማሰብ የተሳነን መሆናችን አይደለምን? እግዚአብሔር ወደ ልጁ ፍቅር ይመልስን።

### አንድነትን በተመለከተ ወጥ አስተምህሮ ማዘጋጀት

*"በመጠራታችሁ በአንድ ተስፋ እንደ ተጠራችሁ አንድ አካልና አንድ መንፈስ አለ፤አንድ ጌታ አንድ ሃይማኖት አንዲት ጥምቀት፤ከሁሉ በላይ የሚሆን በሁሉም የሚሠራ በሁሉም የሚኖር አንድ አምላክ የሁሉም አባት አለ።"* ኤፌ 4፡4-6

ዘረኝነት ሰው በመንፈሳዊ ህይወት ሲበስል የሚወጣበት የእድገት እርከን ሳይሆን ሲያሽቆለቁል የሚወድቅበት ሸለቆ ነው። በየዘመናቱ ከሚወጡት አስተምህሮዎች ጋር መክነፍ ህጻንነት እንጂ ታላቅነት አይደለም። ቤተክርስቲያን በመድረኮች የሚሰጡትን ትምህርቶች እና ስብከቶች መቃኘት ያለባት ይመስለኛል። ችግሮቻችን እና የሚሰጡ መፍትሄዎች አልገጣጠም አሉ። አማኙ ማህበረሰብ የገባበት ጉድጓድ እና ከአገልጋዮች

የሚሰጠው መፍትሄ የተገናኙ አይመስለኝም። ቀንበር የሆነብን ድህነት፣ የፍትህ መጓደል፣ መከፋፈላችን እና ሌሎች ጉዳዮች በብዙ በቤተክርስቲያን መሪዎች እና አገልጋዮች ዘንድ ትኩረት ተነፍገዋል። ህዝቡ ጥያቄያችን ነው ለሚለው ነገር ሁሉ አገልጋዮች አጥጋቢ መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል።

ሰው መልስ በማያገኝበት ቦታ ለረዥም ጊዜ መቆየት አይፈልግም። እነ ጳውሎስ ውስብስብ እና ከባድ በነበረው የማህበረሰብ ጥቁዎች ውስጥ አጥጋቢ የሆነ ምላሽ ሲሰጡ ነበር።

*"በአጭር ቃል በእናንተ መካከል ዝሙት እንዳለ ይወራል የዚያም ዓይነት ዝሙት በአሕዛብስ እንኳ የማይገኝ ነው፥ የአባቱን ሚስት ያገባ ሰው ይኖራልና።"*1 ቆሮ 5፡1

*"ከእናንተ አንዱ ከባልንጀራው ጋር ሙግት ቢኖረው በቅዱሳን ፊት በመፋረድ ፋንታ በዓመፀኞች ፊት ሊፋረድ ይደፍራልን?"* 1 ቆሮ 6፡1

*"ስለ ጻፋችሁልኝስ ነገር፥ ከሴት ጋር አለመገናኘት ለሰው መልካም ነው።"* 1 ቆሮ 7፡1

አሁን በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ውስጥ አንድ ወረርሽኝ ተነስቷል። እርሱም ዘረኝነት ነው። ይህ የሰውን ልብ እየሰነጣጠቀ ያለ በሽታ አፋጣኝ መፍትሔ የሚያስፈልገው ችግር በመሆኑ ክንዳችንን አስተባብረን መነሳት ያስፈልጋል።

ሰው የሚበላውን ነገር ነው የሚሆነው። ይህ ለሰው ሥጋዊ ክፍል እውነት የሆነ መርህ ለአእምሮአችንም የሚስራ ነው። አመለካከታችን በምናየው፣ በምንሰማው በምናነበው ነገር ነው የሚቀረጸው። በተለይ በዘረኝነት አቅጣጫ  በእኛ በቅዱሳን መካከል ያለው የአመለካከት ልዩነት የሚታየው የተዘበራረቀ፣ የተዝረከረከ፣ ወጥ ያልሆነ፣ ያልተፈተነ እና ያልተጣራ ሀሳቦችን ስለምናግበሰብስ ነው። በማንኛውም ጉዳይ ላይ በአንድ መጽሐፍ በሚያምኑ በክርስቲያኖች መካከል እጅግ የተራራቁ አመለካከቶች መፈጠራቸው አሳፋሪ ነገር ነው። ቢያንስ የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ

በሚናገርባቸው ጉዳዮች ላይ መስማማት አለብን፡፡ የፖለቲካ ጉዳይ ሲነሳ ንትርኮች ይፈጠራሉ፡፡ የሚያሳዝነው ነገር ደግሞ ሁሉም ሲከራከሩ እርግጠኛ ሆነው እንጂ ለመስተካከልና ለመማማር በተዘጋጀ ልብ አለመሆኑ ነው፡፡ ገዢው ፓርቲ የሚፈጽማቸው ግልጽ ስህተቶች አንተ የዚህ ፓርቲ አባል እና ደጋፊ ስለሆንክ ልክ እንደሆነ ህሊናህን ጥሰህ የእግዘአብሔርን ቃል ጥሰህ በድፍረት የምትናገር ከሆነ እውነትን ሸጠህ ውሸትን ሸምተሃልና ፈጥነህ ንቃ!

በተቃራኒው ገዢዉን ፓርቲ በክፉ አይን የሚመለከቱ ተቃዋሚዎች የሚያናፍሱትን ወሬ ሁሉ ልክ ነው በማለት በጥላቻ ተሞልተህ ከሆነ እራስህን ፈትሽ፡፡ ከወርቅ ይልቅ የነጠረ ሁሉን የመመዘን ብቃት ያለውን ቃል እንደ መስፈርት ሊያገለግል ይገባል፡፡ ይህ ቃል ከፖለቲካ አንጻር ከሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ምን ይላል? ብሎ መጠየቅ እራስን ከጥፋት መጠበቅ ነው፡፡ ቤተ-ክስርቲያንም በእያዳንዱ ጉዳይ ዙርያ ስርዓተ ትምህርት ቀርጾ ህዝብን የማስተማር ግዴታ አለባት፡፡ የማናስተምረውን ህዝብ ደቀመዝሙር ማድረግ አንችልም፡፡ ወጥ እና ጠንካራ ትምህርት በሌለበት ስፍራ ቆራጥ ደቀ-መዝሙር መፈለግ ከብቶች ባልዋሉበት ስፍራ ኩበት እንደ መፈለግ ነው፡፡ ለዚህ ነው አማኞች አንድ ጉዳይ በተነሳ ቁጥር ሁሉም የራሱን ግምት ተከትሎ የሚደናገሩት፡፡

በእያንዳንዱ ጉዳዮች ዙሪያ ትምህርት ስለማይሰጡ ህዝቡ ተበትኖአል፡፡ ወጥ የሆነ አስተምህሮ ከቤተክርስቲያን እየመነመነ የሰው ጩኸት እና ድግግሞሽ እያሰለቸን ነው፡፡ እንደ እውነቱ ግን ቤተክርስቲያን የጽድቅ ታጋዮችን የምታፈራ በእግዚአብሔር ቃል የምታስታጥቅ ህያው ተቋም መሆን አለባት፡፡ ስለዚህ አገልጋዮች፣ የቤተክርስቲያን መሪዎች እና መጋቢያን ረጋ ብለው ነገሮችን በማጤን ትምህርት እና ስልጠናዎችን ማዘጋጀት ህዝቡን በእግዚአብሔር ቃል እውነት ላይ መሰብሰብ ይጠበቅባቸዋል፡፡

## የተሻለ አማራጭ ይዘን መቅረብ ይኖርብናል

*“መልካሙን ሥራችሁን አይተው በሰማያት ያለውን አባታችሁን እንዲያከብሩ ብርሃናችሁ እንዲሁ በሰው ፊት ይብራ፡፡”* ማቴ 5፡16

የተሻልንሆነን ከሌሎች በልጠን ካልተገኘን ስለፎከርን ብቻ የሚሰማን የለም። ዓለም በብዙ መንገድ እየታወከች ነው። መፍትሔ ያስፈልጋል። በምድራችን ብዙ የምርምር ስራዎች ይደረጋሉ። ኑሮን ለማቃለል የማይፈነቀል ድንጋይ የለም። በዚህ ጊዜ ቤተክርስቲያን ለዓለም ሁሉ መፍትሄ የሆነውን ኢየሱስን ይዛ ብቅ ማለት አለባት። ለየትኞቹም ማህበራዊ ቀውሶች መልስ መስጠት የሚችለውን ክርስቶስን በጓዳ ልታማክረው ይገባል። ከዚያ የተሻለ አማራጭ መሆን ትጀምራለች። በዚያን ጊዜ መንግስታት እርዳታን ከቤተክርስቲያን ይሻሉ።

ይህ እንዲሆን ከማስታረቃችን በፊት መታረቅ አለብን። ቤተክርስቲያን ይህን ስታደርግ መፍትሄ መሆን ትጀምራለች። ቁጭ ብላ የምታማ ወደ ጓዳ ገብታ የምታማርር ሳትሆን በግለጽ የተሻለ አማራጭ ይዛ ትቀርባለች። በልማት ዙሪያ ከሁሉ ቀድማ ተዋናይ መሆን አለባት። ስለ ሰብዓዊ መብቶች ልትሟገት፣ ውርጃ እና ግብረሰዶማዊነትን ልታወግዝ፣ልመና የመሳሰሉ ችግሮች መፍትሄ ልትሰጥ ይገባታል። ችግሮች ሲከሰቱ ክርስቶስን መፍትሄ አድርገን የምናቀርብበት አጋጣሚ እንጂ ከአለም ጋር የምንታወክ ከሆነ እውነተኛ አማኞች መሆናችን አጠራጣሪ ነው።

ለዓለም የሚበቃ መብራቷን ከእንቅብ በታች ደብቃ መፍትሄ ፍለጋ የምትኳትን ከሆነ አሳፋሪ ነው። ለብዙዎች የሚተርፍ የምስራች ቃል ይዛ እርስ በርስ በመነካከስ በሀዘን ቆዝማ መቀመጧ መወገድ ይገባዋል።

## የግል ፍላጎታችንን ሰውተን ለህብረት እንኑር

*“በክርስቶስ ኢየሱስ የነበረ ይህ አሳብ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይሁን።እርሱ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ ከእግዚአብሔር ጋር መተካከልን መቀማት እንደሚገባ ነገር አልቈጠረውም፥ነገር ግን የባሪያን መልክ ይዞ በሰውም ምሳሌ ሆኖ ራሱን ባዶ አደረገ፥በምስሉም እንደ ሰው ተገኝቶ ራሱን አዋረደ፥ ለሞትም ይኸውም የመስቀል ሞት እንኳ የታዘዘ ሆነ።በዚህ ምክንያት ደግሞ እግዚአብሔር ያለ ልክ ከፍ ከፍ አደረገው፥ ከስምም ሁሉ በላይ ያለውን ስም ሰጠው፤”* ፊል 2፡5- 9

በተፈጥሮ ህግ አንዳንድ ጊዜ ሁለት ነገሮችን አንድ ላይ አናገኝም፡፡ አንዱን ለማግኘት ሌለኛውን እናጣለን፡፡ አዲስ አበባ እና ሐዋሳ በተመሳሳይ ሰዓት መኖር አንችልም፡፡ አዲስ አበባን ከመረጥን ሐዋሳን ማጣታችን ነው፡፡ የግሌ ፍላጎት ብቻ ይሳካልኝ የሚል ህብረትን መስዋዕት ያደርጋል፡፡ የሌሎችን ሀሳብ የማያስተናግድ በህብረት ውስጥ መኖር አይችልም፡፡

*"ለወገኔ ይጠቅማል በማለት ወይም በከንቱ ውዳሴ ምክንያት አንድ እንኳ አታድርጉ፥ ነገር ግን እያንዳንዱ ባልንጀራው ከራሱ ይልቅ እንዲሻል በትሕትና ይቍጠር፤እያንዳንዱ ለራሱ የሚጠቅመውን አይመልከት፥ ለባልንጀራው ደግሞ እንጂ።"* ፊል 2፡3-4

የቅዱሳን ህብረት በክርስቶስ ውስጥ መሆናችንን የምናረጋግጥበት ላብራቶሪ ነው፡፡ ብቻውን የሚኖር ብልት የለም፡፡ ከግንዱ ተገንጥሎ ፍሬ የሚያፈራ ቅርንጫፍም ታይቶ አይታወቅም፡፡ ጌታ ከቅዱሳን ተነጥለን የምንመጻደቅበት የሰጠን የጸጋ ስጦታ የለም፡፡ ስለዚህ ህያውነት፣ ማደግ፣ ማገልገል፣ በህብረት ውስጥ ነው፡፡ የክርስቲያኖች ህብረት ከጌታ የተቀበልነውን ጸጋ፣ ብርታት እና እውቀት የምንለግስበት ከሌሎች ደግሞ ምክርን፣ ትምህርትን እና የመሳሰሉ በረከቶችን የምንቋደስበት የፍቅር ባንክ ነው፡፡

ስለዚህ የክርስቲያኖች ህብረት ሲታሰብ ወደዚያ ከሄድኩ ምን አገኛለሁ የሚል የሸማችነት መንፈስ መሆን የለበትም፡፡እርሱ ይሁዳ የሄደበት መንገድ ነው፡፡ የግል ጥቅም እያሰብን በክርስቶስ ውስጥ መኖር አንችልም፡፡ የኢየሱስ ልመና ተቋማዊ አደረጃጀት ያለው ምድራዊ ትርፍ የሚሰላበት ማህበር ሳይሆን የወንጌሉን ተልዕኮ ለማድረስ ማንነታቸዉን ሰውተው በፍፁም አንድነት የሚንቀሳቀሱትን ህያዋው ህብረት ለመፍጠር ነው፡፡

*"ከዚህም በኋላ በዓለም አይደለሁም፥ እነርሱም በዓለም ናቸው፥ እኔም ወደ አንተ እመጣለሁ። ቅዱስ አባት ሆይ፥ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው።"* ዮሐ 17፡11

ስለዚህ የኢየሱስን ልመና ለመኖር ጎሰኝነቱን እናውልቅ፡፡ የሆነ ነገርን ብቻ ለማግኘት ወደ ቅዱሳን መሄድ የለብንም ለመስጠት እና ተፈላልገን መሆን ይገባል፡፡ በግለሰብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በቤተ-ዕምነት ደረጃም ህብረት መፍጠሩ ተጽዕኖ ለማምጣት በጣም ወሳኝ ነው፡፡ አሁን ያለው የወንጌለውያን አማኞች ህብረት በኃይሌስላሴ እና በደርግ ዘመን የነበረው ስደት የወለደው እንደሆነ ግልጽ ነው፡፡ ከዚያ ችግር ለማምለጥ መተባበር መደጋገፍ ነበረባቸው ከዚያ ህብረት ተፈጠረ፡፡ ይህንን አጋጣሚ እግዚአብሔር ለመልካም ከተጠቀመበት እኛም በበኩላችን ከልብ በሆነ ፍቅር በመዋደድ የጌታን ስራ በህብረት እንስራ፡፡

እውነት ሳይሆን ተረት ተረት አስኪመስለን ድረስ የሚያስደንቅ የፍቅር ታሪክ ነበረን አባቶች የሚነግሩን፡፡  አሁን አሁን ግን ያን በመከራ ጊዜ የነበረውን ህብረት ደግመው መኖር የተሳናቸው ይመስላል፡፡

አሁን ግን አባቶች እና መጋቢዎች በየቦታው ተበታትነው የራሳቸውን አርማ ቀርጸው በየአዳራሹ ውስጥ ከበሮ የሚጎስም ትውልድን የመስብሰብ የመምከር እና የማቅናት ኃላፊነታቸውን እየተወጡ ነው ለማለት ይከብዳል፡፡ ህብረት እና መተባበር በእኛ ዘንድ እንደ ኋላ ቀርነት ቢወሰዱም የማይሻረው ቃል አሁንም አንድነትን ቀዳሚ ተግባር እንደሆነ ያስቀምጣል፡፡

ከህብረት እየሸሸን ሌላ ህብረት መፈለግ የለብንም፡፡ የተጠራነው ወደ ልጁ ህረብት ነው፡፡ ይህንን የከበረ ጥሪ ትተን ከወንድሞቻችን ጋር መስማማት አቅቶን ወደ ህያው ህብረት ሳይሆን ወደ ሙታን ጉባኤ እየሄድን እንዳይሆን እሰጋለሁ፡፡

## የኤሳው የይቅርታ ልብ እና የዮሴፍ የምህረት ጉዞ

*እርሱም በፊታቸው አለፈ ወደ ወንድሙም እስኪደርስ ድረስ ወደ ምድር ሰባት ጊዜ ሰገደ:: ዔሳውም ሊገናኘው ሮጠ፥ አንገቱንም አቅፎ ሳመው ተላቀሱም:: ዘፍ 33፡3-4*

ያዕቆብ ከኤሳው ብኩርናውንና በረከቱን ሁሉ አሚጦ ማር እንደተቆረተባት ቀፎ ባዶ አድርጎት ኮበለለ፡፡ ከ20 ዓመት በኋላ ግን አምልጦት ከሸሸው

ሞት ጋር መፋጠጥ ግድ ሆነበት፡፡ ያዕቆብ ወንድሙ የታመቀ የበቀል ቁጣ እንደሚያፈስበት ፈርቶ ስለ ነበር በያቦቅ ወንዝ ዳር የምጥ ጸሎትና ትግል ሲያደርግ አደረ፡፡ አስተዋይነትና አርቆ ማሰብ ከራቀው የኤሳው ልብ ውስጥ ምህረት ግን እንደ ምድረበዳ ምንጭ ፈለቀ፡፡ ለገዳይነት የተፈራው ኤሳውና እንዳይሞት እየተርበተበተ የመጣው ያዕቆብ ከዚህ ምንጭ በጋራ ተጎነጩ፡፡ ደም ከመፋሰስ ተመልሰው የናፍቆት እንባ ተራጩ፡፡ በደሉ ተረስቶ ተቃቀፉ፡፡ በልጅነታቸው ያሳለፉትን የፍቅር ትዝታ ሊቀበር ከነበረበት ከቂምና በቀል ቋጥኝ ስር ጎትተው አወጡት፡፡

*ወንድሞቹም አባታቸው ከልጆቹ ሁሉ ይልቅ እንዲወደው ባዩ ጊዜ ጠሉት፥ በሰላም ይናገሩትም ዘንድ አልቻሉም። ዘፍ 37፡4*

*የምድያም ነጋዶችም አለፉ እነርሱም ዮሴፍን አንሥተው ከጕድጓድ አወጡት ለእስማኤላውያንም ዮሴፍን በሀያ ብር ሸጡት እነርሱም ዮሴፍን ወደ ግብፅ ወሰዱት፡፡ ዘፍ 37፡28*

ልባቸው በቅናትና ምቀኝነት ስለተሞላ አይናቸው ውስጥ ያለው መልካምነትና ከምላሳቸው ላይ የሚፈሰውን የርህራሄ ቃል ደረቀ፡፡ ቅንነትን የሚያስቡበት ጭንቅላታቸው ተኮላሸ፡፡ ወንድማቸውን ከምድረገጽ የሚያጠፉበትን ቀላል መንገድ ለመቀየስ የምክክር ጉባዔ ተቀመጡ፡፡ ለእስማኤላውያን ነጋዴ በ20 ብር ጆሮ ግንዱን በማለት ደብዛውን ማጥፋት ዮሴፍን የሚያስወግዱበት የመጨረሻ መላ ሆኖ ተወሰነ፡፡ ከሚወደው አባቱ ጉያ ፈልቅቀው ለማያቃቸውና ለማይራሩለት ባዳ ሸጡት፡፡ የአባታቸውን ልብ በሃዘን ጦር ወጉት፡፡ የጥላቻ ጫፍ የሆነውን አረመኔያዊ ድርጊት በገዛ ታናሽ ወንድማቸው ላይ ፈጸሙበት፡፡

በከነአን ምድር ረሃብ ሲሆን የአለም የመትረፍ ተስፋ ወደ ተንጠለጠለባት ግብጽ ምድር ያዕቆብ ልጆቹን መላክ ግድ ሆነበት፡፡ ዮሴፍ ተንከራታች ወንድሞቹን በጥበብ የታሸ፣ በምህረት የተለወሰ፣ በፍትህ ስልቻ ውስጥ እህልና የህሊና ጥያቄ ሰንቆላቸው ሸኛቸው፡፡ በደላቸውን ሲረዱ፣ ወደ ህሊናቸው ሲመለሱ፣ ምህረት ለመጠየቅ እጃቸውን ሲሰጡ በእንባ ተቀበላቸው፡፡ የይቅርታ ሙሉ ጉዞ ማለት ይህ ነው፡፡

ከዚህ በኋላ አገራችንን የሚለውጡት እንደ ዮሴፍ የምህረት ልብ ያለው ብቻ ናቸው፡፡ ከተቆረቆረችበት ጊዜ የጀመረው ደም መፋሰስ፣ የስልጣን ሽሚያ፣ ግፍና በደል፣ ረሃብና እርግማን አድቅቋታል፡፡ ኢትዮጵያ እንደ ኤሳው ወንድሞቿን ከተበታተኑባት በምህረት የምትሰበስብ መሆን አለባት፡፡ እንደ ዮሴፍ በይቅርታ የምታቅፍ ከሆነ ብቻ ነው ይህች አገር የሚባለውን ልማትና ሕዳሴ መጨበጥ የምትችለው፡፡

አባቶች ያስፈልጓታል፡፡ ምህረትን የሚሰብኩ፣ ለይቅርታ የተሰጡ፡፡ እጃቸው በደልን ለመጠቆም ሳይሆን ትውልዱን ለማቀፍ የተዘረጉ አስተዋይ ሰዎች ይሹናል፡፡ መዘናጠል፣መነታረክ መካሰስ ውጤቱን አይተናልና፡፡

በአለም ላይ ቀላሉና ርካሹ ነገር ጥፋትን አምኖ ይቅርታ ያለ መጠየቅ ሲሆን አሮጌው ስርዓት ደግሞ ማመካኘት ነው፡፡ አዳምና ሔዋና ያደረጉት ከተፈጠረው ጥፋት መሸሸንና ማሳበብን ነው፡፡ ከባዱ ነገር ደግሞ የበደለንን ሰው ይቅር ብለን ማፍቀር ነው፡፡ ክርስቲያኖች የተጠራነው ለዚህ ነው፡፡ ከየትኛውም ሰው ይልቅ ኢትዮጵያን ለዚህ ጊዜ የምህረት ልብ ያላቸው ሰዎች ያስፈልጓታል፡፡ ከታጎርንበት አዳራሽ እንውጣ የምህረት ልባችንን እናፍስስ፡፡ ሁሉም የራሱን የይቅርታ ምንጭ ይክፈት፣ እነዚህ ፍሳሾች ገባር ሆነው ከክርስቶስ ጎን ፈልቀው አለም ላይ ከሚዞሩት ታላቁ የምህረት ወንዝ ጋር ያብሩ፡፡ ወንዙም ወደ መላው የአለም አገራት ይፍሰስ ኢትዮጵያ ልጆች ከተበታተኑበት ታንኳቸው ላይ ወጥተው እየቀዘፉ ይምጡልን፡፡ በትዝታ ታፍነው በቂም ከሚቆዝሙበት፣ የስጋን ሞት ሸሽተው ነፍሳቸውን ከሚቀራመቱ አውሬ ጋር እየተጋፈጡ ካሉበት ይቀላቀሉን፡፡ በመሬት ላይ ሳይሆን በአዕምሮ ላይ የታጠረውን አደገኛ አጥር ማፍረስ ከባድ ሥራ ነው፡፡

## 6.4. እንደ ማህበረሰብ ማድረግ የሚገባን

*"ከክፉ እንድትጠብቃቸው እንጂ ከዓለም እንድታወጣቸው አልለምንም።"* ዮሐ 17፡15

አሁን የምናነሳው እንደ ቤተክርስቲያን ከወንድሞቻችን ጋር ሊኖረን ስለሚገባ ህብረት ሳይሆን በምንኖረበት ህብረተሰብ ውስጥ ካላመኑት ጋር ስንኖር የሚጠበቅብን ኃላፊነቶችን ነው። ለአማኞች ብቻ ሳይሆን ማንኛውም ዜጋ ቢከተለው ለአገራችን የሚበጁ ነጥቦችን እንደሚያገኙበት ተስፋ አደርጋለሁ።

**በቁጭት መነሳት!**

የፍቅር አርበኛ፣ የምህረት አባት፣ አስታራቂ ሽማግሌ እንደ አልማዝ የተወደዱብን ይመስላል። ሁሉንም ብሔሮች በአንድ አይን የሚያይ ታላቅ መሪ ያሻናል። አገራችን የሰላም አስከባሪ ኃይሎችን ወደ ሱማልያ አሰማርታ እየሰራች ነው፣ የደቡብ ሱዳንና የሱዳንን ጉዳይ ልሸምግል እያለች ነው፣ ጂቡቲን እኔን ጥማት ቅጥል ያርገኝ አንቺን ምን በወጣሽ በማለት በውሃ እያንበሸበሸች ነው። የታሪክ ድርሳናትን ስንፈትሽ ለደቡብ አፍሪካ የሰላምና እርቅ አርበኛ የሆነው ኒልሰን ማንዴላ የኢትዮጵያ ምሁራን አሻራ ያለበት ሰው ሆኖ እናያለን። የአፍሪካ ሕብረት ሲቋቋም አገራችን የተጫወተችው ሚና አስደናቂ ነበር።

ታድያ ለራሳችን እንዴት መሆን ተሳነን? ፍትህ እየመነመነ፣ እውነት የሞት ጣር እያሰማ፣ እኩልነት እየተሰደደ እንዴት ዝምታን መረጥን? ለሰው አገር ሲሳይ እየሆንን፣ የራሳችን ልጆች በብሔር ተከፋፍለው ሲባሉ አስታራቂ አባት እንዴት ጠፋ?

ኢትዮጵያን መታደግ የሚፈልግ ሰው መነሳት ያለበት ወሳኝ ጊዜ ቢኖር አሁን ነው። ለዘመናት እንደ ሰማይ ከዋክብት የራቀንን እውነተኛ አንድነት በመዳፋችን ላይ ለማስገባት ትንቅንቅ መግጠም ያለብን ወቅት ላይ ነን። ሁሉ ነገር ለፖለቲካ ፍጆታ ከዋለ ለአገር የሚተርፍ ነገር ይጠፋል። ገዢው ፓርቲ የአንድነት ምንጩ እኔ ነኝ ካለ፣ ተቃዋሚዎች ደግሞ አይ!

አሁን ላለው ብሔር ተኮር ጦርነቶች ችግሩ መንግስት ነው ብለው ያሳብባሉ። የራሳቸውን ጽንፍ ይዘው የሚዘላለፉ ከሆነ ሚዛናዊ ሆኖ ማዕከላዊ ቦታ ላይ ቆሞ የሚናገር አስተዋይ ሰው እየመነመነ ይመጣል።

አንድነት በመስማማት በውይይት የሚገኝ እንቁ ነገር እንጂ ጠመንጃ በመማዘዝ የሚመጣ ርካሽ ሸቀጥ አይደለም። ከተዋረደ ስራ የከበረ ውጤት አይጠበቅምና። በደም የምትገነባ አገር ሲያል ብቻ ነች። በዚህም ምድር ላይ ግን ፍቅርና ምህረት ብቻ ናቸው እውነተኛ ግንበኞች። ጥላቻና ነፍስ ማጥፋት ግን አፍራሽ ናቸው።

አገራችን ጥገና ያስፈልጋታል። አውራቂሱ ክፉኛ ጎድቷታል። የሰላም ግንበኞች ይታጠቁ፣ ጠቢባንም ይንቁ። የአገር ሽማግሌዎች የተበታተኑትን የኢትዮጵያ ልጆች በፍቅር ይሰብስቡ። ለጋራ ዓላማ አሰልፈው ታሪክ ይስሩ። ሁሉንም በእርቅ አስማምተው ለሚቀጥለው ትውልድ ፍቅርን አምርተን አንድነትን እናውርስ።

## በንስሃ እና በእርቅ እንጀምር

*“ሰዎችና እንስሶችም በማቅ ይከደኑ፥ ወደ እግዚአብሔርም በብርቱ ይጮኹ ሰዎችም ሁሉ ከክፉ መንገዳቸውና በእጃቸው ካለው ግፍ ይመለሱ።”* ዮና 3፡8

ኢትዮጵያ እንደሚወራልን በመልካም መንገድ የምትታይ አገር ብቻ አይደለችም። ብዙ ግፎች ተፈጽመውባታል። ንፁህ ደም ፈሶባታል። ስለዚህ ፍርስራሾችን ጠርገን ለአዲስ ግንባታ ማዘጋጀት አለብን። አገር የምትገነባው ጥፋቷን አምና በእግዚአብሔር ፊት ስትወድቅ ነው። እራሳችንን ማታለል የለብንም ኃጢአታችንንም ሳንሰውር በጌታ ፊት ተናዘን ምህረት እንለምን። ያን ጊዜ ፈውስ ይሆናል።

ያለፉት ነገስታት አንዱ ብሔር በሌላው ላይ የፈጸሙት ግፍ እና ግድያዎች በግልጽ ይታወቃሉ። እነዚህን ታሪኮች ለመሸፈን ለማጣመም ብሎም ለመድገም መሞከር በጉስቁልና ውስጥ ለመቆየት ሁኔታዎችን እንደማመቻቸት ነው። በግልጽ እንደሚታየዉ የሰይጣን መልዕክተኞች

በየብሔሩ ውስጥ ተሰግስገው ጥላቻ እና መለያየትን እየረጩ ይገኛሉ። እነዚህ ሰዎች ወደ ፊት ሳይሆን ወደኋላ እንድናስብ የሚያደርጉን ናቸው። ያለፈውን ነገር በይቅርታ አልፈነው እጅ ለእጅ ተያይዘን ወደ ፊት መሄድ አለብን።

ስለ እርቅ ስናስብ አንድ መሰረታዊ እውነት ማወቅ ያለብን ይመስለኛል። እርቅ እውነትን ከመፈለግ የሚጀመር ሂደት ነው። ይህ ይቅርታ ለይስሙላ ሳይሆን በእውነት ላይ የተመሰረተ፣ ከልብ የሆነ እና ዘላቂነት ያለው መሆን አለበት። እርቅ በአየር ላይ የምንፈጽመው ሳይሆን ተጨባጭ ሁኔታ ውስጥ የሚከናወን የፈውስ መንገድ ነው።

በቀል ለየትኛውም አካል አዋጪ መንገድ አይደለም። ያለፈውን ታሪክ ቆፍረን እራሳችንን ለጦርነት ከማዘጋጀት ይልቅ በፍቅር እና በይቅርታ አልፈን በጋራ ጉዳይ ላይ በማትኮር አብረን መኖር የሚያዋጣ ነው። ማርቲን ሉተር እንዲህ ይላሉ "ጥላቻ ጥላቻን ማስወገድ አይችልም ፍቅር ብቻ ነው ያንን ማድረግ የሚችለው"

## ቫይረሱን ለመግታት በጀት ይመደብ

ዘረኝነት አውዳሚ በሽታ ነው። ከጆሮ ደግፍ በሽታ ጋር ይመሳሰላል። ወደ ፊት ሳይሆን ወደ ጎን ወይንም ወደ ኋላ የሚያጣምም ነው። ዘረኛ የሆነ ሰው የፊቱን ቀና ብሎ ማየት አይችልም። የትላንትናውን መቆፈር ደስ ይለዋል። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ምርምሮች መደረግ አለባቸው። ዘረኝነት ላይ የጥናት ጽሑፎች ቢዘጋጁ መልካም ነው። በዚያ መሠረት የግንዛቤ ማስጨበጫ ፕሮግራሞች ቢቀረፁ ጥሩ ነው። የንስሃ፣ የትምህርት እና የውይይት ፕሮግራሞች ቢነደፉ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው።

ፍፁም የሆነ መፍትሄ በመጽሐፍ ቅዱሳችን ቁልጭ ብሎ በማያሻማ ሁኔታ ተጽፏል ያም የህግ ሁሉ ማሰሪያ ነው።

*"እንግዲህ ሰዎች ሊያደርጉላችሁ የምትወዱትን ሁሉ እናንተ ደግሞ እንዲሁ አድርጉላቸው፤ ሕግም ነቢያትም ይህ ነውና።"* ማቴ 7፡12

ይህንን መፍትሄ ይበልጥ ለመጠቀም ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ከዘረኝነት አንጻር ለማሳየት ያክል እነዚህን ደረጃዎች ብንከተል አዋጪ ነው፡፡

ሀ. ዘረኝነት ችግር መሆኑን እናረጋግጥ፡- ዘረኝነት የብዙ ሰዎች ህይወት የጠፋበት፣ ንብረት የወደመበት፣ ቤተክርስቲያን የተከፋፈለችበት ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ ከጥላቻ ምንም ስለማናተርፍ ዘረኝነት ችግር መሆኑን ልንተማመን ግድ ነው፡፡

ለ. የችግሩን ምንነት መረዳት፡- የክፋት ሁሉ ምንጭ ሰይጣን የመልካም ነገር ሁሉ መገኛ ደግሞ እግዚአብሔር ነው፡፡ አሮጌውን ማንነት በመጠቀም ሰይጣን የሰውን ልጅ በጥላቻ ይነድፈዋል፡፡ ዘረኝነት በእርግጥ አጸያፊ ተግባር ነው፡፡

ሐ. የችግሩን መንስዔዎች ማጥናት፡- ዘረኝነት በዋናነት ከእኔነት፣ ከትዕቢት፣ ከጥላቻ የሚመነጭ ነው፡፡ ዘረኛ የሆነ ሰው መጠኑ ይለያያል እንጂ እነዚህ ባህሪያት ይነበቡበታል፡፡

መ. የመፍትሄ አቅጣጫን ማስቀመጥ፡- ሙሉ መፍትሄው በእግዚአብሄር ቃል ውስጥ ተቀምጦአል፡፡ ያለፈውን መርሳት፣ ታሪክን በአግባቡ መያዝ እና መጠቀም በደልን በምህረት ማለፍ አስፈላጊ ነዉ፡፡

ሠ. እራሳችንን በየጊዜው መፈተሽ፡- በቆሸሸ ዓለም ውስጥ እስካለን አንዳንዴ በድንገት ልንስት እንችላለን ስለዚህ ቶሎ መታረም ከስህተት መማር ተገቢ ነው፡፡

## ታሪክን በአግባቡ መያዝ

*“አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ ከቀድሞ ጀምሮ፥ ያለውንም ተምሳሊት እናገራለሁ:: የሰማነውንና ያወቅነውን፥ አባቶቻችንም የነገሩንን፥ ለሚመጣ ትውልድ ከልጆቻቸው አልሰወሩም:: የእግዚአብሔርን ምስጋናና ኃይሉን ያደረገውንም ተኣምራት ተናገሩ::” መዝ 78፡2-4*

ታሪክ ያለፈ ነገር ቢሆንም ከዛሬ ኑሮአችን ጋር ቀጥተኛ የሆነ ግንኙነት አለው፡፡ ታሪክ የሰውን አእምሮ በተቆጣጠረ መጠን የመደገም ሰፊ እድል

አለው፡፡ በአግባቡ ካልያዝነው የትላንት ስህተት አሁን ባለው ትውልድ ሊደገም ይችላል፡፡ በተለይ እኛ ኢትዮጵያውያን የዘር ሐረጋችንን ቆጥረን ማቅራራት የትላንትናን እያወሳን መታበይ ደስ ይለናል፡፡

ትላንት ጥሩ እንኳን ቢሆን መረሳት አለበት፡፡ በቃ ያለፈ ነገር ጌታን ካላሳየን የማንማርበት ከሆነ መረሳት አለበት፡፡ እንኳንስ አውዳሚ ነገር ይቅርና ጠቃሚ ነገር እንኳን ይረሳል፡፡ በትውልድ መሃል መተማመን እና የወንድማማችነት ስሜት እንዲጎለብት ከመጥፎ ጠባሳ ተላቀን የጋራ የሆነ የልማት ስራ ላይ መሳተፍ አለብን፡፡

## ቋንቋን ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መጠቀም

*“ምድርም ሁሉ በአንድ ቋንቋና በአንድ ንግግር ነበረች፡፡”* ዘፍ 11፡1

ቋንቋ መግባቢያ ነው፡፡ ነገር ግን ቋንቋ የእውቀት ማሳያ፣ የብሔር መታወቂያ፣ የተሻልን ሰዎች እንደሆንን ለመግለጽ የምንጠቀምበት ከሆነ አደጋ ነው፡፡ በዓለም ላይ ያሉ ቋንቋዎች በቅንነት ከተጠቀምንባቸው ጌታን ለማምለክ፣ ወንጌልን ለመስራት እና ከሰዎች ጋር በስፋት ለመግባባት እድል ይሰጠናል፡፡ በፍቅር የማናደርገው ከሆነ ግን የሰው ቋንቋ ይቅርና የመላዕክትም ልሳንም ቢሆን አይጠቅምም፡፡

የቻይና እና የኢትዮጵያ ሰራተኞች አንድ ቋንቋ ባይናገሩም በአንድነት የግንባታ ስራዎችን እየሰሩ ይገኛሉ፡፡ እኛ ኢትዮጵያውያን ግን አብረን እየኖርን አንዱ ብሔር የሌላውን ብሔር ቋንቋ ለምዶ መግባባት አይፈልግም፡፡ ይህ ደግሞ መርገም እና እብሪት ነው፡፡ ቤተክርስቲያን ውስጥም አንድ አላማ ግልጽ መመሪያ ባለበት አንድ የሚያደርግ መንፈስ በፈሰሰበት አንድ መሆን ያለመቻል ትልቅ ኪሳራ እና ውርደት ነው፡፡

## ኩሬውን ማድረቅ ይሻላል

*የክርስቶስ ኢየሱስም የሆኑቱ ሥጋን ከክፉመሻቱና ከምኞቱ ጋር ሰቀሉ፡፡* ገላ 5፡24

ከላይ ያለው ክፍል አሮጌ የሆነውን ማንነት ታቅፈን ከኃጢአት ጋር እየተሻሸን ከምንኖር አመጽ የሚበቅልበትን ማንነት መግደሉ ወሳኝ ነው። የወባ ትንኝን አሳዶ ከመግደል አጎበር እና የወባ መድኃኒት ከመግዛት የወባ ትንኝ የምትራባበትን ኩሬ ማድረቅ ዘላቂ መፍትሄ ነው። አጎበር በአልጋ ላይ እንጂ በመስክ ላይ አይጠቅምም። ህብረተሰቡን እለት እለት ከማስታረቅ የሚጣሉበትን ምክንያት ማስወገድ ተገቢው ነው።

## ከንግድ መርህ እንማር

*"ገንዘብን እንጀራ ላይደለ፥ የድካማችሁንም ዋጋ ለማያጠግብ ነገር ለምን ትመዝናላችሁ? አድምጡኝ፥ በረከትንም ብሉ፥ ሰውነታችሁም በጮማ ደስ ይበለው።"* ኢሳ 55፡2

አንድ ነጋዴ  እቃ የሚገዛ ሰው ሲመጣ የቀበሌ መታወቂያ ጠይቆ ብሔሩን ከለየ በኋላ አይደለም የሚሸጥለት። የሰውየው ማንነት ከግምት አይገባም ለእርሱ ዋና ነገር ከእቃው የሚገኝ ትርፍ ነው። ዝንጀሮ እንኳን ቢመጣ የእቃውን ዋጋ ይክፈል እንጂ ችግር የለበትም ይሸጥለታል። አሁን ግን ቤተክርስቲያን የተሰጣትን ተልዕኮ ያለ ማዳላት መፈጸም ስትችል  በነጻ የተሰጣትን መዳን ለማስተዋወቅ ሰውን መምረጥ ጀመረች።እንንቃ! ለፍቅር እራሳችንን እናዘጋጅ።

## ሙዙን እንብላው

ዳኒ አልቬስ ይባላል በዜግነቱ ብራዚላዊ ሲሆን የባርሴሎና ክለብ የክንፍ ተጫዋች ነው። ሚያዚያ 2014 እ.አ.አ የቪላርያል ሜዳ በሆነው ኤል ማድሪጋል ስታድየም ላይ ባርሴሎና ከቪላርያል ጋር ሲጫወቱ ኃላፊነት እና አእምሮ የጎደላቸው ደጋፊዎች የመአዘን ምት ለመምታት እየተዘጋጀ ባለውብብራዚላዊውተጫዋች ላይ የስድብ ናዳ ማውረድ ጀመሩ። አንዱ የባሰበት ደጋፊ ግን ዘለፋው በቂ መስሎ ሳላላገኘው አንድ መላ ዘየደ የያዘዉን ሙዝ በመወርወር የአልቬስን ጭንቅላት እና ስነ-ልቦና ማናጋት። ተሳካለት ሙዙን ወረወረበት። ልበ ሰፊው እና አርቆ አሳቢው ጀግና መልሶ ከመወርወር ይልቅ ሙዙን ልጦ በእስታድየሙ ውስጥ ባሉት ተመልከቾች እና በቴሌቪዥን በሚከታተለውብዙ ህዝብ ፊት ካጣጣመው

በኋላ "ብርታት ሰጠኝ!" አለ፡፡ በአጸፋው ስድብ እና ንዴትን የጠበቁ የቪላርያል ደጋፊዎች እፍረትን ተከናነቡ፡፡ አልቭስም አለምን አጀብ ያሰኘ ቅንነት አሳየ፡፡ ውሎ ሳያድር ከፊፋ ፕሬዝዳንት ጀምሮ እስከ ተራ ደጋፊዎች አድናቆት እና ምስጋና ጎረፈለት፡፡ ብልህ ሰው ከስድብ ምክርን ያወጣል እንደሚባል ለክፋት የተሰራበትን ለመልካም አደረገው፡፡ የባርሳው ጀግና አሁንም በተግባሩ አለምን ትልቅ እውነት አስተምሯታል፡፡[43] እኔም የባርሴሎና ክለብ ደጋፊ እና አድናቂ እንደ መሆነ መጠን በዳኒ አልቭስ ተደስቻለሁ! ጀግና ማለት ኳስን በመጠለዝ የተካነ ብቻ ሳይሆን በፍቅር እና ማህበራዊ ጉዳይ ምሳሌ መሆን የቻለ ነው፡፡

## መልካም ባህሎቻችንን ብንጋራስ?

እኛ ኢትዮጵያዊያን ወደ ማንም ማማተር እስከማያስፈልግ ድረስ ጌታ በመልካም ባህልና አኗኗር ባርኮናል፡፡ አንዱ ብሔር ከሌላው በትህትና መማር ከቻለ እንቁ የሆኑ ባህላትን መጋራት ይቻላል፡፡ ማጥላላት ከተቻለ መሞጋገስም ይቻላል ማለት ነው፡፡ በሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች ውስጥ ገንቢና አልሚ ባህላት እንዳሉን አልጠራጠርም፡፡ እነዚህ ውብ የባህላችን ቀለማት ቢዋሃዱ በአፍሪካ ቀንድ ለአለማችን አንድ ጌጥ የሆነች አገር ማበርከት እንችላለን፡፡ በፍቅርና በመደናነቅ ብንቀባበል፣ ስድብና ውንጀላን የምናስተናግድበት ልብ ስለማይኖረን በፍቅር ሐይቅ ውስጥ በአንድነት ስንዋኝ በሽበት ተወረን በደስታ ወደ መቃብራችን እንገባለን፡፡

ለምሳሌ ጉራጌ የሥራ ህዝብ ነው፡፡ ቻይናና ኮርያ ድረስ ተጉዘው በብዙ ሺዎች የሚቆጠሩ መዋዕለ ንዋይ አፍስሰው የሥራ ታታሪነታቸውን የሚተርኩልን ሚዲያዎችና ሰዎች አሉ፡፡ እዚያ ድረስ ከመሄዳቸው በፊት የጉራጌ ወንድሞቻችን ትጋትና ቆራጥነት ቢያስቃኙን በቀላሉ መማማር ይቻላል፡፡ የስራ ተነሳሽነታቸው አንዱ ሌላውን ለማሳደግ ያላቸው ፍላጎት ከእነርሱ ብንማር ስራ አጥ በአገራችን ባልተገኘ ብዬ ባልልም በእውነቱ የተሻለ ነገር ይኖር ነበር ማለት ግን እችላለሁ፡፡

---

43 Http//WWW.CNN Worldsportnews

የኦሮሞው ሕዝብ ለአንድ ልጅ የልጅነትን መብት ለማጎናጸፍ ከሚጠቀምባቸው አምስት ስልቶች አንዱና በብዛት የሚታወቀው ጉዲፈቻ ነው። ይህንን ባህል በትክክለኛው ስራ ላይ ቢውል የጎዳና ልጆች ቁጥር በተመናመነ ነበር። ሞጋሳ ከሌላ ብሔሮች ወደ ኦሮሞዎች የሚመጣን ሰው ባይተዋርነት እንዳይሰማው የሚደረግበት ባህል ነው። ለዚያ ሰው አዲስ ስም ተሰቶት እንደማንኛውም የማህበረሰቡ አባል ሙሉ መብት ተጎናጽፎ በሰላም ይኖራል። ብንጋራቸው ለሁሉም ብሔሮች የሚጠቅም የወንድማማችነትን ስሜት የሚያመጣ ነው።

የኮንሶ ህዝብ ለተፈጥሮ ሃብት ያላቸው እንክብካቤ የሚደንቅ ነው። አፈራቸውን ጎርፍ ያለ አንዳች ከልካይ መንትፎ እንዳይነጉድ የሚሟገቱ ጀግኖች ናቸው። እነርሱ ጋር አፈር አፈር ብቻ አይደለም። ከፈጣሪ የተቸሩት ልዩ ጥበቃ የሚደረግለት ውድ ስጦታቸው ነው እንጂ። ይህንንም አለም ያደነቀው፣ ለእኛ ደግሞ ኩራት የሆነን እንቁ ባህል ነው። ኮንሶ የተፈጥሮ አጠባበቅን የምንማርበት ዩኒቨርሲቲ ህዝቦቿም ደግሞ ምርጥ አስተማሪዎ ናቸው።

ተደናንቀን መተውና ደካማ ጎንን እየቆፈርን ከመናቆር ይልቅ ብናለማቸው ብናስተካክላቸው፣ ለሌሎች ብሔሮች ሊተገበር በሚችል ሁኔታ ስራ ላይ ብናውላቸው ትልቅ የአገር ሃብት ናቸው። ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾላቸው ብንጋራቸው እውነተኛ እድገት ማለት ይህ ነው። በምንም መንገድ ከአገራችን ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር የሚፋለሱ አስተሳሰቦችን እንደ ሸቀጥ ዝም ብለን ከምናግበሰብስ የራሳችንን መጀመርያ ተቀብለን አጎልብተን ብንጠቀም ውጤቱ የላቀ ነው።

የኢትዮጵያ ባህል የሚባሉት በአንድ አፀድ ስር የሆኑት በጣም ጥቂት ናቸው። ለምሳሌ እንግዳን መቀበል የኢትዮጵያ ባህል ተብሎ ሁሉም ይጋራዋል። ብዙ ባሕሎች ግን ከብሔር አልፈው የአገር ሃብት ሳይሆኑ ይኮላሻሉ። የሥራን ባህል የኢትዮጵያ ማድረግ እየተቻለ ለምን የጉራጌ ብቻ ይሆናል? ጉዲፈቻን ለምን የኦሮሞ ብቻ የኢትዮጵያ የምናደርግበትን መንገድ ለምን አንፈልግም?

## የአባ ዶዮ ወርቃማ ምክር

ወቅቱ ኢጣልያውያን ፋሽስቶች ኢትዮጵያን የወረሩበት ጊዜ ነበር፡፡ አባ ዶዮ በኢትዮጵያ ታሪክ የመጀመርያ በነበረው ፓርላማ አባል ነበሩ፡፡ እኚህን አባት የሜጫ ኦሮሞ ህዝብ "የሰላም አባት" እንዲላቸው ያደረገው ተግባር ጣሊያኖች "በከፋፍለህ ግዛ" መርህ የህዝብን አንድነት ለመበታተን እና እርስ በእርስ ለማፋጀት ያቀዱትን የዘር ልዩነት እሳት ማጥፋታቸው ነው፡፡

ይህም የኢጣሊያ ዕቅድ በእልፈታ እና ጀልዱ በመጠኑ ተፈጽሟል፡፡ በሜጫ ግን እርምጃው ከመወሰዱ የአገር ሽማግሌዎች "ከባላባቱ ከአባ ዶዮ ጋር እንማከርበት" ይሉና አባ ዶዮ ቤት ለመገናኘት ይወስናሉ፡፡ አባ ዶዮም ስለ እቅዱ የሰሙ ቢሆንም በቀጠሮው ይስማማሉ፡፡ ሽማግሌዎቹ ደግሞ የብልሁን እና የተከበሩትን የአባ ዶዮን ምክር እና ድጋፍ ማግኘት እንዳለባቸው ተማምነዋል፡፡

የቀጠሮው እለት ሽማግሌዎች ወደ አባ ዶዮ ቤት ሲገቡ በሩ ላይ ቆመው የሚቀበሏቸዉ አባ ዶዮ ሽማግሌዎች በስልቻ ከተቀመጠ ሰርገኛ ጤፍ እየዘገኑ እንዲገቡ አደረጉ፡፡ እንግዶች በሙሉ መግባታቸው ሲያረጋግጡ አባ ዶዮም ገቡ፡፡ እንደገቡ ሁሉም ሰርገኛ ጤፉን እንደያዙ አዩ…

"አባ ዶዮ! ምን አርጉት ብለው ነው ሰርገኛ ጤፍ ያሳፈስኸን" አሉ ሽማግሌዎቹ፡፡ "በሉ ስብሰባችን ከመጀመሩ በፊት ነጩንና ጥቁሩን ለዩልኝ" አሉ አባ ዶዮ ኮስተር ብለው፡፡

"አይ አባ ዶዮ! ትቀልዳለህ? እንዴት ተደርጎ ነው ነጭ እና ጥቁር የሚለየው? የማይቻለውን ምነው ቀለድህብን!" አሉ በአንድነት፡፡ " በሉ ይቅር በሉኝ! ካስቸገራችሁ ተዉት" አሉ አባ ዶዮ፡፡ ከዚያ ሚስታቸው ያዘጋጁት ምሳ ቀረበ፡፡ አባ ዶዮ እና ባለቤታቸው በማስተናገድ ተፍ ተፍ ብለው ጨዋታው ደርቶ ተበላ ተጠጣ፤ በመጨረሻም መሰቡ ተነሳ፡፡

"በሉ ወደ ጉዳያችን እንግባ ስብሰባችን ስለ ምን ነው?" አሉ አባ ዶዮ፡፡ "አይ! ‹ጣልያን ከአማራ ነጻ የምትወጣው አሁን ነው› ብሎናል፡፡ እልፈታ እና ጀልዱ አማራን እያባረሩ የሚያንገራግሩትንም እየገደሉ ነው፡፡ እኛ ግን

ከእርምጃችን በፊት ለአንተ እንነገር ካንተ ጋርም እንምከር ብለን ይኸው እንገናኝ አልን" አሏቸዉ።

"ማለፍያ ሃሳብ ነው አሉ" አባ ዶዮ። "ጣልያን ከባህር ማዶ መጥቶ ነጻ ሊያወጣን ነዋ! ጥሩ ነው።በሉ መጣሁ" ብለው ወጡና "ልጆች! አሰፋ እና ካሣን በአስቸኳይ ጥሩልኝ" ብለው ተመለሱ። አሰፋ እና ካሣ የአባታቸውን እግር ተከትለው ከተፍ አሉ።

"አማራን እንግደል ብላችሁ አይደል የመጣችሁ!"። "አዎ" ሽማግሌዎቹ ትንሽ ተያዩ። "በሉ ወደ ውጪ ሳንወጣ በፊት እነዚህን ልጆቼን ቀጥለን ደግሞ እናታቸውን እንግደላቸው" አሉ አባ ዶዮ-ጎራዴያቸውን እየወዘወዙ። "ምነው ጌታዬ! ለምን የአንተን ልጆች እንገድላለን?" ብለው ጠየቁ ሽማግሌዎቹ ተደናግጠው።

"እህ! አሁን ምሳ አብልታችሁ የወጣችው እናታቸው እኮ የመንዝ አማራ ናት። ልጆቹም በአባታቸው ኦሮሞ ቢሆኑም በእናታቸው አማራ ናቸው።አማራን መግደል ማባረር ካላብን ከዚህ እንጀምራ" አሉ አባ ዶዮ።

"ይህማ እንዴት ይሆናል? አናደርገውም። አንተስ እማናደርገውን ለምን ትጠይቀናለህ?" አሉ-እየተሰቃጠጡ።

"እህ! ምን ላድርግ ቅድም ‹ሰርገኛ ጤፍ ለዩ› ያልኳችሁ እኮ ለዚህ ነው። አማራ እና ኦሮሞ እንደ ሰርገኛ ጤፍ ተቀላቅሏል ወንድሞቼ…እስኪ ከእናንተ ውስጥ በአማራ ያልተጋባ ካለ ይንገረኝ በተለይ ከሸዋ አማራ ጋር ተቀላቅለናል እኛ ኦሮሞዎች ጣልያን የማያውቀው የማይገምተው የሚያኮራ የ‹የጉዲፈቻ› እና የ‹ሐርማ ሆዳ› (ጡት ማጥባት) ባህል አለን። በዚህ ባህላችን ከተለያዩ ጎሳዎች ጋራ አንድ ሆነናል። ይህ ባህላችን ከአባቶቻችን ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ የአንድነት እና የአብሮ መኖር መሰረት ነው። ስለዚህ ጣልያኖች ተለያዩ ቢሉን እኛ እንዴት መለያየት እንችላለን?" አሉ አባ ዶዮ - ግራ ቀኙን በዐይናቸው እየቃኙ። ሽማግሌዎች አባ ዶዮ ስላሳመናቸው በፋሽስቶች የተቀነባበረው የመተላለቅ

ድግስ ተበላሸ፡፡የአባ ዶዮ ምሳሌም በህዝቡ ህሊና የማይረሳ የሰላም መላ ተደርጎ እስካሁን ይታወሳል፡፡[44]

ይህ ተራ የአንድ ሽማግሌ ምክር ሳይሆን እውቅና ስልጡን የተባሉት ዲፕሎማቶች የተሰወረባቸውን መላ በመዘየድ ሁሉም አፍሪካውያን የተታለሉበት የአውሮፓውያንን ሴራ ያከሸፈ የወቅቱ የአህጉራችን ምርጡ ምክር ነዉ፡፡ ይህ ምክር በሩዋንዳ እና ቡሩንዲ ተግባራዊ ቢደረግ ኖሮ አንድ ሚልየን ህዝብ ባላለቀ፤ ሁቱ እና ቱትሲ የገዢዎቻቸውን ሰይጣናዊ የተንኮል ደባ ባልተቀበሉት ነበር፡፡

## 6.5. የፍቅር አብዮት ይቀጣጠል!

*"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል፡፡"* 1ዮሐ 3፡16

በቃ! ዓለም አሰልቺ እና ለመኖር የማትመች ስፍራ እየሆነች ነው፡፡ የሚሰሙ ወሬዎች መልካም ተስፋ የሚሰጡ ሳይሆን ልብን የሚያወርዱ ናቸው፡፡ እስኪ አስቡ! በመጨረሻ ዘመን ላይ ከሚገኙ ሰዎች ጋር በፍቅር እንደ መኖር ከባድ ነገር አለ?

*“ነገር ግን በመጨረሻው ቀን የሚያስጨንቅ ዘመን እንዲመጣ ይህን እወቅ፡፡ሰዎች ራሳቸውን የሚወዱ ይሆናሉና፥ ገንዘብን የሚወዱ፥ ትምክህተኞች፥ ትዕቢተኞች፥ ተሳዳቢዎች፥ ለወላጆቻቸው የማይታዘዙ፥ የማያመሰግኑ፥ ቅድስና የሌላቸው፥ ፍቅር የሌላቸው፥ ዕርቅን የማይሰሙ፥ ሐሜተኞች፥ ራሳቸውን የማይገዙ፥ ጨካኞች፥ መልካም የሆነውን የማይወዱ፥ከዳተኞች፥ ችኩሎች፥ በትዕቢት የተነፉ፥ ከእግዚአብሔር ይልቅ ተድላን የሚወዱ ይሆናሉ፤የአምልኮት መልክ አላቸው ኃይሉን ግን ክደዋል፤ ከእነዚህ ደግሞ ራቅ፡፡”* 2ጢሞ 3፡1-5፡፡

---

[44] ፍቅረ ማርቆስ ደስታ (2001) ጃገማ ኬሎ - የበጋዉ መብረቅ፡ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ ገጽ 15-18

ሁሉም ነገር ወደ ፍጻሜ እየገሰገሰ ነው፡፡ የዓለምን እድሜ ለመቋጨት አንድ ነገር ብቻ ቀረን እርሱም *ማቴ 24፡14 "ለአሕዛብም ሁሉ ምስክር እንዲሆን ይህ የመንግሥት ወንጌል በዓለም ሁሉ ይሰበካል፥ በዚያን ጊዜም መጨረሻው ይመጣል።"* ይህን እውን ለማድረግ አንድ ትልቅ ስልት መቀየስ አቅማችንን ማስተባበር አለብን፡፡ ቤተክርስቲያን ያለ የሌለ ኃይሏን ማሰባሰብ ይጠበቅባታል፡፡ እርሱም ፍቅር ነው! የፍቅር አብዮት መቀጣጠል አለበት፡፡ የፍቅር እንቅስቃሴ መጀመር አለበት፡፡

ዓለምን ጥላቻ እና ጦርነት አድቅቋታል፡፡ ይንከባከቡኛል ያለቻቸው መሪዎቿ አሽቀንጥረው ጣሏት፡፡ እሽሽግባቸዋለው በማለት ተስፋ ያደረገቻቸው ምሽጎች ተደርምሰው እርቃኗን አስቀሯት፡፡ ደስታና እርካታን ለማግኘት የፈበረከቻቸው ረቂቅ የስልጣኔ ምርቶች ሌላ ስጋት ፈጠሩባት፡፡ የምታደርገው ሁሉ እያታከታት ነው፡፡ ሲኦል አፏን ከፍታ ልትውጣቸው በጭካኔ ልታሰጥማቸው ተዘጋጅታለች፡፡ በክርስቶስ የቤዛነት ሥራ ካላመኑ መትረፍ እንደማይችሉ ግልጽ ነው፡፡

እኛ ክርስቲያኖች እለት እለት ስለ እግዚአብሔር ፍቅር እና ምህረት የምንዘምር ምን ያክል እንደተረዳነው ግራ ይገባኛል፡፡ የእግዚአብሔርን ፍቅር የምንገልጥባቸው መንገዶች የጠፉብን መሠለኝ፡፡ ምክንያቱም የፍቅር ማሽናችን ብዙ ፍቅርን ሳያመርት ተበላሽቶ ዝጎ የተቀመጠ ይመስለኛል፡፡ እንኳንስ በውጪ ያሉትን በፍቅር ስበን ወደ ቅዱሳን ጉባዔ በማምጣት የራሳችን ማድረግ ይቅርና ወንድሞቻችንን ለመቀበል መስፈርቶቻችን ብዙ ናቸው፡፡ ነፍሳችን በጥላቻ ተወጥራ በብሔር ተሰነጣጥቀን ተቀምጠናልና፡፡ ከራሳቸው ብሔር፣ ቋንቋ እና ባህል ወጥተው የምስራቹን ቃል እያጠፉ ላሉ ወገኖች ለማድረስ የደፈሩ የወንጌል አርበኞች እየመነመኑ ነው፡፡ ክርስቶስን ባለ ማግኘቱ ከእግዚአብሔር ቁጣ የሚሸሸበትን መጠለያ አጥቶ የሚንከራተተውን መጠበቅ እየተሳነን ነው፡፡ እኛ በቤት ሆነን የእግዚአብሔርን ፍቅር እያጣጣምን፤ በውጭ ላሉት የወንጌልን እውነት ያለ ማብሰር የእግዚአብሔር ቁጣ ይፍጃቸው ከማለት አይተናነስም፡፡

በዓለማችን ላይ እየተከናወኑ ያሉትን አሰቃቂ እና ተስፋ አስቆራጭ የጥላቻ እና የዘረኝነት ውጤቶችን መቀልበስ የምትችል ቤተክርስቲያን ብቻ ነች። የተመረጠ፣ ከፍቅር የመነጨ፣ ትልቅ ኃይል ያነገበ አንድ ህብረት ያሻናል። ልክ በክሩሴድ ጊዜ እ.እ.ኤ 1055 ጊዜ እንደ ተፈጸመው ስህተት በፍቅር መስዋዕት ለመሆን የመጣውን ጌታ በጦርነት ለመርዳት የመጣር አይነት ያለ ማስተዋል ችግሮች ይታያሉ። ጌታችን ያስታጠቀንን የጦር መሣሪያ እርሱም ፍቅርን ካልያዝን ማንንም ለጌታ መማረክ አንችልም።

## ከልብ የሆነ መልዕክት ለውድ ወዳጄ!

ውድ ወዳጄ ያልኩት አንተን/አንቺን ነው። ይህንን መጽሐፍ አንብበህ ስለ ጨረስክ ደስ ብሎኛል። በሁሉም ሀሳብ ላይ ተስማምተናል ለማለት አልደፍርም ያንንም ማድረግ አይጠበቅብህም። ብቻ በአንድ ነገር ላይ እንስማማ እርሱም ዘረኝነት እና መከፋፈል ለአገራችን እንደማይበጅ እና በቤተክርስቲያን ውስጥም ይህ ገዳይ መርዝ መገኘት እንደሌለበት። በቃ ከቁጭት እና ከሀሜት ተላቀን ወደ ተግባር እንሻገር። ማንንም ከመተቸትህ በፊት ልብህን ፈትሸው። በቃሉ ብርሃን የውስጥ ማንነትህን በርብረው። በመንፈስ ቅዱስ ምሪት ጥላቻ፣ በቀል፣ ዘረኝነት፣ ቂመኝነት መኖራቸውን እና አለመኖራቸውን አረጋግጥ። እነዚህ አጸያፊ ተግባራት እና ሀሳቦች በውስጥህ ከተገኘ አትሸማቀቅ ለመደበቅም አትሞክር። ምክንያቶችን በመደርደር እራስህን ነጻ ለማውጣት አትጣጣር ነገር ግን ጥፋትህን አምነህ ተናዘህ ንስሃ ግባ ላለመድገም ወስን በደሙ ታጠብ። ያው ሃጢአተኛ መሆንህን ያመለከተህ መንፈስ ይቀድስሃል። ከጌታ ጋር እርቅ ፍጠር። አሁን እንኳን ደስ አለህ! የለውጥ ፋና ወጊ ሆነህ የክርስቶስን የፍቅር አርማ አንግበህ መፍትሄ ለመሆን ተዘጋጅ። ዳግመኛ በዘረኝነት ቀንበር ሥር ላለመውደቅ ልብህን በቃሉ አውነት ሙላው። ይህንን ካደረክ የዓለምን የጥላቻ በረሃ የሚያለመልም የፍቅር ምንጭ ከውስጥህ መፍለቅ ይጀምራል። ሰውን ሁለት ቦታ ብቻ ከፍለህ የምይታበት አዲስ እይታ ይሰጥሃል። ያለ ክርስቶስ ወደ ዘላለም ጥፋት እየነጎዱ ያሉ፤ የኢየሱስን የድነት ታላቅ ሥራ ባለመቀበል ወይንም ባለማወቅ የሰይጣን ምርኮኛ ሆነው ያሉት እና በክርስቶስ በማመን የዘላለም ደስታ እና ፍስሃ ለመቀዳጀት የሚሄዱት። ነገሮችን እንደዚህ ከተረዳህ ዓላማህ እና ተልዕኮህ አንድ ነገር ብቻ ይሆናል። የልብህ ግለት በአንድ ጉዳይ ላይ ያተኩራል እርሱም ወደ ሞት የሚሄዱትን መታደግ። ውስጥህ በዚህ ሲሞላ ለዘረኝነት እና ለጥላቻ ስፍራ ታጣለህ ኢምንት ጉዳዮች ስለሚሆኑ አይታዩህም። በአንድ ወቅት እንደዝሆን ግዙፍ የነበሩ አሁን ግን እንደ ትንኝ ይሆናሉ።

የምነግርህ ማንም ያልሞከረውን አይደለም። አባትህ ኢየሱስ ይህንን ፈጽሞታል። በሥጋ ከአብርሃም ዘር ቢወለድም ለዓለም ህዝብ ሁሉ

ሞተ፡፡ ፍቅር ማለት ይሄ ነው፡፡ ሐዋሪያት እና የእምነት አባቶች ይህንን ደግመውታል፡፡ ብዙ የወንጌል አርበኞች ከወገናቸው ተሰደው ለሌሎች ብሔሮች መስዋዕት ሆነዋል፡፡ የማያውቁትን ህዝብ ቋንቋ እና ባህል ተቀብለው የክርስቶስን ፍቅር አንጸባርቀዋል፡፡

አንተም በቃ ወስን! አሁኑኑ ጀምረው ሌላ ሰውን አትጠብቅ፡፡ ከጌታ የተቀበልከውን ምህረት የበደሉህን እና የጠሉህን በማፍቀር ተለማመደው፡፡ የሚገፉህን በትህትና ቅረባቸው፡፡ ነፍስህን በጭፍን ጥላቻ ለማጥፋት ለሚመጡ ስለ ወንጌል ብለህ የፍቅር መስዋዕት አድርገህ እራስህን ለማቅረብ ተዘጋጅ፡፡ ይህ ድል የምንነሳበት ብቸኛው የጌታ ልጆች ስልት ነውና፡፡

እባህክ ወዳጄ! ለዘመናት የናፈቅነው ተሃድሶ ባንተ እንዲቀጣጠል የራስህን ችቦ ለኩሰው፡፡ ህብረት እና አንድ ልብ መሆን የመንፈሳዊ መነቃቃት ነዳጅ ከሆኑ ቤትህን የነዳጅ ማደያ ጣብያ አድርገው፡፡ የሚቀጥሉ ዘመናት ፍቅር እና ህብረት የሚታጨዱበት የመኸር ጊዜ እንዲሆንልን ምህረት እና ይቅር ማለትን በትጋት ዝራ! ጌታ ቅርብ ነው፡፡

ወንድምህ ባይሣ ገመቹ

# ዋቢ መጽሐፍት


1. ንጉሴ ቡልቻ (2002) መስተአየት፣ በሊቪንግ ትሩዝ አገልግሎት የታተመ፤ አዲስ አበባ፡፡
2. የአዲስ ኪዳን ማብራሪያ (2004) ራዕይ አሳታሚ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፡፡
3. ፍቅረ ማርቆስ ደስታ (2001) ጃገማ ኬሎ - የበጋው መብረቅ፡ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ፡፡
4. መጽሐፍ ቅዱስ አዲሱ መደበኛ ትርጉም ከማጥኛ ጽሁፍ ጋር በ1993 ዓ.ም በኢንተርናሽናል መጽሐፍ ቅዱስ ማህበር፡፡
5. ዳንኤል ተፈራ (2006)፣ ከፓርላማው በስተጀርባ፡ የተከበሩ አቶ ተመስገን ዘውዴ ሕይወት እና የፖለቲካ ቁጭት፤ አዲስ አበባ፡፡
6. ህብረ ብሔር፣ ህዳር 29 ቀን 2002፡፡
7. አዶኒስ (2006)፣ የአና ማስታወሻ፡፡
8. ብርሃን መጽሔት 64/2006፡፡
9. አባዱላ ገመዳ (1996). የኦሮሞ ህዝብ ትግል ከየት ወዴት? ሜጋ ማተሚያ ድርጅት፣ ፊንፊኔ ኢትዮጵያ፡፡
10. ዳንኤል ተፈራ (2003). ዳንዲ የነጋሶ መንገድ፣ንግድ ማተሚያ ድርጅት፣ አዲስ አበባ፡፡
11. ዶ/ር መለሴ ወጉ (2011) ባንስማማ፣ላለመስማማት እንስማማ፡፡
12. ፀጋአብ በቀለ (2005) ባለራዕይነት ክፍል 2፣ ሐዋሳ፡፡
13. መስፍን ወልደማርያም (2005) ፣ መክሸፍ እንደ ኢትዮጵያ ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ፡፡
14. ኤሊ ዊዝል (2006) ሌሊት ፣ ጳውሎስ ፈቃዱ (ትርጉም)፡፡
15. ሎሚ መጽሔት ቅጽ 2 ቁጥር 62 ሐምሌ 2005፡፡
16. ሮማን ፕሮቻዝካ (1935) ኢትዮጵያ የባሩድ በርሜል፡ ፀሐይ አታሚና አከፋፋይ ድርጅት
17. በፊሊፕ ሞሐቢር (1996) እንታረቅ፡አዲስ አበባ
18. በልሁ ደለለኝ (2002) ጽንፋዊነት፡ አዲስ አበባ
19. ፈቃዱ ሲሳይ (2007) ምጽአተ ዓም-ሓራ በአዲሱ አምሓሮች፡ አዲስ አዲስ አባባ

20. ሰለሞን ሲዩም (2007) የኦሮሞ ጉዳይ እና ኢትዮጵያ ብያኔ ከማሻሻያ እስከ አብዮቱ
21. Max Weber (1968) Guenther Roth, and Claus Wittich, eds.), *Economy and Society: An Outline of Interpretive Sociology,* Vol. 1 Berkeley, Calif.:University of California Press.
22. Anthony D. Smith (1991) *National Identity* Reno: University of Nevada Press.

23. Gorden Kerr (2009). Leaders Who Changed the World. Brown Book Group. London.
24. Http// WWW. CNN- World Sportsnews.
25. Dr. Aquiline Tarimo. (Sept 25, 2000). Ethinicity, Common Good and the Church in Contemporary Africa.
26. Samuel Waje Kunhiyop (2008). Africa Christian Ethics. Zondervan, Hippo Books. Nairobi.
27. Rojer and Jorge Mejia (Nov 3, 1988). Liturgical Memorial of St. martin of Porres.
28. Micheal M. Lombard and Robert W.Elchinger (2006). For Your Improvent. Lominger International. Akorn Comp. USA.
29. Watchman Nee, (1972). Sprtitual Authority. Christain Felloowship Puplishers. INC. New York.
30. Eric W.Gritsch and Robert W. Jenson (1976). Lutheranism: The theological Movenet and Its Confessional Writing. Fortress Press. Philadelphial. USA
31. Scott Marshall, Polical Affairs- USA July 2013, Monthly Juornal of the communist party. USA Tired of a system that just doesn’t work.
32. Microsoft ® Encarta ® 2009. © 1993-2008 Microsoft Corporation. All rights reserved.

33. Prophessor Asano Alegamu (2000) Federalism and Africa.
34. The Biblical Illustrator Copyright © 2002, 2003, 2006 Ages Software, Inc. and Biblesoft, Inc.).
35. Ralph Winter and Steven C. Hawthorne (2009). Perspectives on World Christian Movement.